በድጋሚ የታተመ

ሬይሞን ክኖ

# ዛዚ

ስብሐት ለአብ ገብረ እግዚአብሔር

ረይሞን ከኖ

# ዛዚ

የነፃ ነፃ ትርጉም - ስብሐት ገብረእግዚአብሔር

2002ዓ.ም.

© የተርጓሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው

All Rights Reserved

የመጀመሪያ ዕትም - 2002ዓ.ም. ስንዱ አበበ አሳታሚ

ሁለተኛ እትም - ነሐሴ 2002ዓ.ም. ቃልኪዳን ታደሠ

አሳታሚ ቃልኪዳን ታደሠ

# ማስተዋወቂያ

ይህ መፅሀፍ ትርጉም እንደመሆኑ፣ ተርጓሚና አንባቢ ከመነሻው ስለ ቃሉ አጠቃቀም ብንግባባ ይበጃል። እንበል፣ ሁለት አይነት ትርጉም አለ።

## አንደኛ - ትርጉም ለእንጀራ

እቺን የአበሳ ኑሮ ለመግፋት ያህል "በለስ ይቅናኝ!" እያልኩ የምሰራው ትርጉም። ማንነታቸው ይሁን ስንትነታቸውን ከማላውቀው፣ እንደኔው እንጀራቸውን ከሚያሳድዱ ተወዳዳሪዎች ጋር ተሽቀዳድሜ የማደርሰው

## ሁለተኛ - ትርጉም ለፍቅር

ፈረንሳይ አገር እየተማርኩ፣ የዩኒቨርሲቲው ቤተ መፃህፍት ውስጥ "Zazie dans le meэtro" የምትል ትንሽዬ መጽሀፍ አየሁ። ስሟ "ዛዚ" ስለከየፈኝ ብቻ አነበብኩት። በህይወታችን ከጥቂት ሴቶች ጋር ብቻ ፍቅር እንደሚይዘን፣ በንባባችንም ከጥቂት መጻህፍት ጋር ብቻ ፍቅር ይይዘናል። ይሄ ማለት፣ በድብርት ወይም በብስጭት ሰአት ላይ ስንሆን፣ ይህንኑ ደጋግመን ያነበብነውን መጽሀፍ የሆነ ገፅ ላይ ከፍተን ማንበብ እንጀምራለን... ንባባችን ሲቀጥል ቀስ በቀስ ሳይታወቀን ድብርታችን እየለቀቀን ይሄድና፣ ንባባችን የሙጥኝ መሆኑ አልፎ የመዝናናት የመደሰት ይሆናል።

እና ከዛዚ ጋር ፍቅር ስለያዘኝ ልተረጉማት ተነሳሁ። ሰላሳ ገጽ ከሄድኩ በኋላ ተመልሼ ሳነበው ታድያ፣ በአማርኛ ቃላት የተጻፈ ፈረንሳይኛ መሰለብኝ። ለአማርኛ አንባቢ አይሆንም።

ሳስብ ሳሰላስል ሰነበትኩና የፈረንሳዮቹንም፣ የኛንም ቋንቋ፣ ታሪክና ባህል በቂ ስለማውቅ፣ ነጻ ትርጉም ላደርገው መረጥኩ። ምናልባት "የነጻ ነጻ

ትርጉም" ማለት ይቻላል። ምክንያቱም ለራሴ እንዲህ አልኩ፦ ደራሲው ደፍሮ ነጻ ሆኖ የጻፋትን ያህል፣ ለምን እኔም አርአያውን ተከትዬ ደፍሬ ነጻ ሆኜ አልተረጉማትም? እሷ ራሷስ የመጨረሻ ደፋር አይደለችም?

ለኔ ዛዚ ናሙና የስነ-ጽሁፍ ፈጠራ ገጸ-ባህሪ ናት። መጽሀፉን ሳነብ ገና ምዕራፍ አንድ ውስጥ እያለሁ ከሷ ጋር ፍቅር ያዘኝ (የገዛ ራሴ ተንኮለኛ ልጅ መሰለችኝ - አቤት ተንኮሉጃ ሲከይፉኝ!)

አዋቂዎቹ "እንዲህ ብታደርጊ (ባታደርጊ) ይሻላል፣ ስታድጊ ይጠቅምሻል" ሲሏት "ይጠቅምሻል የቂጤን አበሳ ይስጠው!" ትላቸውና፣ ወደ ጉዳይዋ! (ትርጉም፡- እኔ ያሰኘኝን ነው የማደርገው)

ዛዚ እንደ ፈጣሪዋ ረይሞን ክኖ በተለያየ አጋጣሚና ሁኔታ የተለያየ ሰው ትሆናለች። "Zazie dans le meэtro" ውስጥ ያሉት ገጸ-ባህሪያት ሁሉ አዋቂዎች ናቸው። እሷ ብቻ ናት ልጅ። እና ይህን የእኛን የአዋቂዎች አለም፣ አራዳ - ነቄ - ቆቅ ዛዚ እያየችው ስትኖርበት፣ ስትጫወትበት፣ ስትማርበት እንዴት ነው?!

እሷን ሆኜ ባየሁትና በኖርኩት ያሰኛል፡- የራሴን ኑሮ ጉድለትና ጭንቀት እሷን ሆኜ ተጋፍጨው፣ በድል አድራጊነት አልፌዋለሁ። አልፌው ወድያው እረሳዋለሁ። ወደሚቀጥለው "የቂጤን አበሳ ይስጠው" ፍጥጫ ወይም መመዛዘን ወይም....

... ልተርጉማት ብዬ ከተነሳሁ በኋላ ደጋግሜ ደጋግሜ ሳነባት "ማናት ዛዚ፣ ማነው ደራሲው?" የሚል ሀሳብ ይመላለስብኝ ጀመር "እሱ እሷ ነው፣ እሷ እሱ ነች" እያለ እየተሽከረከረ ቀጠለ።

ይህን "ማስተዋወቂያ" ስወጥን ያሰብኩት ለአንባቢያን ስለ ደራሲው የህይወት ታሪክ ለመናገር ነበር፤ ያውም የዛዚን ገድል የሚያስረሳ ባለቅኔ፣ የልቦለድ ደራሲ፣ የነጻነት ታጋይ፣ እሱ ፈረንሳይ ሆኖ አየርላንድ ከእንግሊዝ ነጻ ለመውጣት የምታካሂደው የትጥቅ ትግል አድናቂ በመሆኑ ድጋፉን እንዴት በኮሚክ ልቦለድ መልክ እንደሚገልጸው (ዛዚን በገለጸበት ጥበብ!) ይህን ይህን ልተርክላችሁ ነበር።

ለካ የማያስፈልግ የመረጃ (information) ትርፍ ሸክም ሊሆንባችሁ ነበር፣ እግዜር አወጣችሁ! ሰውዬው ያበረከተልን ዛዚ ለኛ ከበቂ በላይ ናት - እሷ ፍሬ፣ ሌላው መረጃ ገለባ!

ዛዚን ስናነብ ደራሲው ለወላጆችም ለአሳዳጊዎችም ብዙ የሚነግረን ወርቅዬ ቁም ነገር አለ፣ በሳቅ ስም የተለበጠ። እሱ አማርኛ ሲያውቅና

ይቿን አረፍተ ነገር ቢያነባት ግን "ሳቁ ነው ወርቅ ኃባክህ፣ ቁም ነገሩ ሰም" ይለን ነበር እላችኋለሁ።

Zazie dans le meətro የተጻፈው ለልጆች ቢሆን፦፣ እኛ አዋቂዎች ስናነበው ለኛ ለራሳችን የተጻፈ እየመሰለን ትሄዳል። ልጆች ሲያነቡት ዛዚን ሆነው ይኖሩታል፣ አዋቂዎች ስናነበው ወላጆቿን ሆነን እንኖረዋለን። በዚህ መንፈስ ሳስበው የኛ ትርጉም ርዕስ "ዛዚ ፓሪስን ስትቀውጣት" መሆን ነበረበት። የመጽሀፉ ርዕስ ግን "ዛዚ በሜትሮ ስትሄድ" ነው። ምን አስባ እንደምትነሳ፣ ሀሳቧ ወደ አላማ ተሰውጦ፣ አላማዋን ለማሳካት አዋቂዎችን እንዴት ወደ መሳሪያዋ እንደምትለውጣቸው እንደምታሽከረክራቸው (ለምሳሌ መጀመሪያ የምናገኛት ተላላኪ እንዴት እንደምትሸወድ) የተቀረውን ለአንባቢያን ልተውላችሁ። ስለተረጎምኩላችሁ ትመርቁኛላችሁ።

እስከዚያው ድረስ፣ የዋናዎቹ ገጸ-ባህሪያት ስም ድምጹ ከኛ አገር ስሞች ጋር በጣም ስለሚራራቅ ግር እንዳያሰኛችሁ የሚከተሉት ናቸው፦

1. ጋብሪዬል - የገደል ቅራፊ የሚያክለው የዛዚ አጎት። ተደባዳቢም አርቲስት - ዳንሰርም።

2. ሻርል - ባለታክሲ። የጋብሪዬል ጓደኛ ስለሆነ ዛዚን ከስድነትዋ ሊገታት በመጣር ዘወትር ይጨቀጭቃታል፣ እንደ ወላጅ (የቂጤን አበሳ ይስጦት ትለዋለች) ውስጡን ግን ይፋቀራሉ።

3. ቱራንዶ - የሞን - ደ ፒዬቴ (Mont — de - pieəte) ካፌ - ሬስቶራንት ባለቤት። የማዶ ፕቲ-ፒዬ (Mado pits - pieds) አለቃ (እሷ የሻርል ፍቅረኛ ናት)

4. ግሪዱ - ጫማ ሰሪ። ብቻውን ይውላል። መጽሀፉ ውስጥ ያሉትን ገጸ-ባህሪያት እያንዳንዱን አበጥሮ ያውቃቸዋል - እነሱን ራሳቸውን፣ ሌሎች ሰዎችንም ጥቃቅን ጥያቄ ሳይቀር እየጠያየቀ። ማዶ ፕቲ-ፒዬ ምሳውን ከሞን - ደ - ፒዬቴ ስለምታመጣለት፣ ብዙውን መረጃ የሚሰበስበው ከሷ ነው። ያልታወቀበት ሳይኮሎጂስት!

5. ባልቴትዋ ሙዋክ - ሀብታም። የቀራቸው ከወንድ ጋር ለመፋቀር እድሜ አጭር ቢሆንባቸውም፣ ተስፋ ባለመቁረጥ ፍቅረኛ አደን የተሰማሩ።

6. ትሩስካዮን - ትራፊክ ፖሊስ(?) ባልቴትዋ ሙዋክ "በለስ ቀንቷቸው" ያጋጠማቸው ፍቅረኛ(?)። ከዚያ በፊት ስራ የፈታ ሀብታም ሆኖ ህፃናት የሚያሳድድ ኮርማ የስሪያ ፍየል(?) ዛዚን ሲያሳድዳት፣ አንድ ሰአት ያህል ያሳለፈ። ጂንስ ሱሪ እገዛልሻለሁ በሚል ማታለያ ተስፋ

እንቁልልጭ ሲጫወትባት ግማሽ ሰአት ያህል ከለፋ በኋላ ዛዚ በተንኮል ቀድማው ፍዳውን የምታሳየው፡፡

7. **ማርሰሊን** - የጋብሪዬል ሚስት፡፡ ዛዚን እንደ እናት ተቀብላ እንደ ታላቅ እህት የምትንከባከባት፡፡ እንደ ቄጠማ ልስልስ ውበት የታደለች፡፡

## ልዩ ማመላከቻ

ሬይሞን ክኖ ዋና ፍቅሩ ስነ-ግጥም ስለሆነ እና ዛዚን የጻፋት ለልጆች ስለሆነ፣ ልባችን እንደ እምዬ ማርያም የሚወዳትን ማርሰሊንን ሲገልጻት ደስ በሚሉ እንደ ረጅም ግጥም አዝማች የሚመላለሱ ቃላት ነው፡፡

ሌሎቹን ገጸ-ባህርያትም ቢሆኑ የዛዚ እኩያ የሆነው አንባቢ አንዱን ከሌላው ለመለየት እንዲችል ያህል ብቻ ትረካው ውስጥ ብቅ ባሉ ቁጥር "ግዙፍ" "ዝምተኛ" "ፓሪስ የምትደብረው" ምናምን እያለ ባጭሩ ይደጋግምለታል እንጂ የልብስም ሆነ የቁመና ወይም የፊት መልክ ገለጻ የለም - የገጸ-ባህሪዩን መስተዋት እያየ ካልሆነ በስተቀር

እንዲህ የሚያስጋልብ የሚያንሳፍፍ፣ የሚያበር ልቦለድ የጻፈልን ምርጥ ባለቅኔ እና እንቁ የልጆች ነብስ አዋቂ ለሬይሞን ክኖ የሳቅ ብርሀን ሆነን መንፈሳዊ ሻማ እንለኩስለታለን፡፡

እኔ ሳነባትም ስተረጉማትም የሳቅኩትን ያህል፣ እናንተም ስታነቡዋት እንድትስቁ እመኝላችኋለሁ፡፡

## ሌላ ልዩ ማመላከቻ

ፈረንሳይኛ የምታውቁ አንባብያን ምናልባት ለአንዳንዳችሁ የዛዚ የሳቅ ዛር ቢሰፍርባችሁና "ተርጉም ተብለሀል" ቢላችሁ፣ እና "በነጻ ነጻ" ሳይሆን "ነጻ ትርጉም" ስሩ ቢላችሁ - ይቅናችሁ

ይህ ተርጓሚ ልምዱን ቢያጋራን ጥሩ ነበር ካላችሁ ደሞ ደስታውን አልችለውም፡፡

**ስብሐት ለአብ**

# አንድ

"ማን-ይህን-ያህል-ሊገማ-ቻለ?" ብሎ አሰበ ጋብሪዬል እየተበሳጨ "ማመኑ ያስቸግራል፣ ታጥበው አያውቁም፡፡ ጋዜጣ ላይ ሲነግሩን በፓሪስ ከተሰሩት አፓርትመንቶች ባኞ ቤት ያላቸው ከመቶ አስራ አንድ እንኳ አይሞሉም - ይሄ አያስገርመኝም፡፡ ግን ያለባኞ ቤት መታጠብ ይቻላል፡፡ እነዚህ የከበቡኝ ተሳፋሪዎች፣ ምንም ያህል የሞከሩ አይመስሉም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ከፓሪስ ህዝብ በሙሉ ከሁሉ የባሰ የቆሸሸውን ሰው መምረጥ የሚያስመኝ አይደለም፡፡ ምንም ምክንያት የለም፡፡ ባጋጣሚ ነው እነዚህ የተሰበሰቡት፡፡ በኦስተርሊትዝ ባቡር ጣቢያ ለመሳፈር የሚጠብቁ ሰዎች በሊዮን ጣብያ ከሚጠብቁት ሰዎች የባሰ ይቆንሳሉ ብሎ ማሰብ የማይሆን ነገር ነው፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ምንም ምክንያት የለም፡፡ ለማንኛውም ግን እንዴት ያለ ቁናስ ነው!"

ጋብሪዬል ከእጅጌው ውስጥ ወይን ጠጅ የመሰለች የሀር መሀረብ አውጥቶ አፍንጫውን አበሰ

"ይህን ያህል የሚገማው ማን ነው እሱ" አሉ አንዲት ወይዘሮ ከማጀ ጮክ ብለው

ይህን ያሉት ስለራሳቸው እያሰቡ አልነበረም (ራስ ወዳድ አልነበሩምና) የተናገሩት ከዚያ ከሰውዬ ስለመጣው ሽቶ ነው

ጋብሪዬል በቃላት ጨዋታ ተረብ ፈጣን በመሆኑ "ይሄማ እምዬ ሆይ፣ በልዩ ስሙ ባርቡዝ የሚባለው፣ በታላቁ የሽቶ አምራች በፊዮር ቤት የተመረተው ሽቶ ነው" አላቸው

"እሱም ቢሆን አገሩን እንደዚህ እንዲመርዝ ሊፈቀድለት አይገባም" ሲሉ ቀጠሉ ወይዘሮዋ፣ መብቱ የራሳቸው መሆኑን እርግጠኛ ስለነበሩ

"የምትይው በደምብ ገብቶኝ ከሆነ፣ እምዬዋ፣ ያንቺ የተፈጥሮ ጠረን ከፅጌረዳዎቹ ያስንቃል፡፡ እረ ተሳስተሻል፣ እምየዋ፣ ተሳስተሻል!"

"ሰማኸው?" አሉት ወይዘሮዋ፣ አጠገባቸው የቆመውን ትንሽ ሰውዬ፣ ሊፈናጠጣቸው ሊወጣባቸው ህጋዊ መብት ያለው ሳይሆን አይቀርም "እንዴት ክብሬን እንደነካ ትሰማለህ፣ ይሄ አሳማ?"

ሚጢጢው ሰውዬ ጋብሪዬልን ሲያየው የገደል ቅራፊ ያክላል "እንዲህ ያሉት ግዙፎች ሁልጊዜ ደግየ ናቸው" ሲል አሰበ፣ በጉልበታቸው አያጠቀሙም፣ እንደ ፈሪነት ሆኖ ስለሚታያቸው "ቡፋ ብቻ!" ናቸው

ጮክ ብሎም "አቶ ጎሪላ፣ ትገማለህ?"

ጋብሪዬል በመሰልቸት "ኡፍ!" አለ፡፡ እንደገና በጉልበት መጠቀም ሊኖርበት ሆነ፡፡ ይሄ ግዳጅ ያስጠላዋል፡፡ ሰው ሰው ከሆነበት ጊዜ የተጀመረ፣ እስከዛሬ እንደቀጠለ ነው፡፡ እንግዲህ መደረግ ያለበትን ማድረግ ነዋ! እቺን አለም እንደዚህ የሚያስቸግሯት ሁልጊዜ እነዚህ ደካማዎች መሆናቸው'ኮ የጋብሪዬል ጥፋት አይደለም፡፡ እንዲያም ሆኖ ግን ለዚህ የትንኝ እድል መስጠት ይቻላል

"ያልከውን ድገም'ስቲ" አለው ጋብሪዬል

ጉልቤው እንዲህ መመለሱ በመጠኑ እያስገረመው፣ ሚጢጢው ሰውዬ የሚከተለውን መልስ ለማዘጋጀት ጊዜ ወሰደ፡-

"ምን ያልኩትን ልድገምልህ?"

ሚጢጢው በአባባሉ እንደ መደሰት አለ፡፡ ምን ዋጋ አለው፣ ወይዘሮዋ ችክ አሉ፡፡ የሚከተሉትን ቃላት ለመናገር ወደ ሚጢጢው ጎምበስ አሉ፡-

"አሁን ያልከውን - በለው"

ትንሹ ሰውዬ መፍራት ጀመረ፡፡ የሚሸሸግበት የቃላት አጥር በፍጥነት መፍጠር እንዳለበት ገብቶታል፡፡ የሚከተለውን ስንኝ ሞከረ፡-

"በመጀመሪያ፣ አንተ እንዲሉኝ አልፈቅድሉትም"

"ቡፋ!" አለው ጋብሪዬል ባጭሩ

እና ቃሪያ ጥፊ ቃጣበት፡፡ ሚጢጢው ሳያንገራግር በገዛ ራሱ ተዘረረ እለዎቹ እግር መሀል፡፡ እንድያው እልቅስ እልቅስ አለው፡፡ ደግነቱ፣ የመጡበት ባቡር ጣቢያ ደረሱና ትእይንቱ ተለወጠ፡፡ ሰዎቹ ሁሉ ንትርኩን ትተው ወደሚገቡት ተሳፋሪዎች ተመለከቱ፡፡ ቀድመው በፈጣን እርምጃ የገቡት በእጃቸው የክላሰር እና የመዛግብት ቦርሳቸውን ብቻ የያዙ የቢዝነስ

ሰዎች ናቸው - ደሞ ጉዞ መንገዝን ከማንም የበለጠ እኛ እናውቃለን የሚሉ ይመስላሉ

ጋብሪዬል ወደ ሩቅ አማተረ - የሚጠብቋቸው ሴቶች ዘግይተዋል ማለት ነው፤ ሴቶች ሲባሉ ሁልጊዜ እንደዘገዩ ነው። አይደለም እረ! አንዲት ልትደርስ ትንሽ የቀራት ልጅ ካጠገቡ ብቅ ብላ

"ዛዚ ነኝ" አለችው "አንቱ ጋብሪዬል ነህ እርግጠኛ ነኝ"

"ልክ ነሽ፤ እኔው ነኝ" አለ ጋብሪዬል፤ ድምፁን የመኳንንት እያስመሰለ "እኔ አጎትሽ ነኝ"

ልጅቷ ሳቋን ለቀቀችው። ጋብሪዬል በአክብሮት ፈገግ እያለ አቅፎ አነሳት፤ ወደሱ አስጠጋት፤ ሳማት፤ ሳመችው፤ መልሶ አስቀመጣት

"ሽታህ ደስ ሲል!" አለችው ልጅቱ

ግዙፉ ሰውዬ "ባርቡዝ የሚባለው በፊዮር ቤት የተመረተው ሽቶ ነው" አላት

"ከጀርባዬ ኋላ ትንሽ ትቀባኛለህ?"

"የወንድ ሽቶ ነዋ"

"ጉዳዩን አገኘሽው አይደል?" አለች ዣን ሳሎሼር፤ ገና አሁን እየደረሰች "እኔ እወስድልሻለሁ ብለሽኛል - እቻትልህ ውሰዳት"

"አሁኑኑ!" አለ ጋብሪዬል

"ላምንህ እችላለሁ ግን? ልባርግ፤ ቤተሰቡ በሙሉ እንዲደፍራት አልፈልግም"

"ምነው እማዬ? እያወቅሽው?! ባለፈው እንደዚያ ሲሆን ልክ በጊዜ ደረስሽኮ"

"የሆነ ሆኖ" አለች ዣን ሳሎሼር "እንደገና እንዲደገም አልፈልግም"

"አታስቢ" አለ ጋብሪዬል

"ጥሩ። እንግዲያው ተነገወዲያ በአስራ ሁለት ከስድሳ በሚነሳው ባቡር እንድንሄድ እዚሁ እንገናኝ"

"የሚወስዳችሁ ባቡር በሚቆምበት በኩል"

"እንከት!" አለች ዣን ላሎሼር በጀርመንኛ፣ ጀርመኖቹ ሲገዙዋት በተማረችው "በነገራችን ላይ፣ ሚስትህ ደህና ናት?"

"ደህና ናት። መጥተሽ አታይንም'ንዴ?"

"ጊዜ አላገኝም"

"ውሸማ ሲኖራት ሁልጊዜ እንደዚህ ናት" አለች ዛዚ "ቤተሰብ የሚባል ነገር ለሷ የለም"

"ደህና ሁኚ፣ የኔ ፍቅር። ደህና ሁን ጋቢ" ይህን ብላ ሄደች

ዛዚ ሁኔታዎችን ትዘግባለች፦

"ተይዛለች"

ጋብሪዬል ትከሻውን ከፍ ዝቅ አደረገ። ምንም አላለም። የዛዚን ሻንጣ አነሳ።

"እንሂድ" አለ። እና ወደፊት የመሮጥ ያህል ሲራመድ መንገዱ ላይ ያገኘውን ሁሉ ወደቀኝና ወደ ግራ እየገፋ ነበር። ዛዚ ከኋላ ኋላው ጋለበች

"አጎቴ" አለች። "በሜትሮ ነው 'ምንሄደው?"

"አይደለም"

"ምን ማለት ነው፣ አይደለም?"

ቆመች። ጋብሪዬልም ቆመ፣ ዞረ፣ ሻንጣውን አስቀመጠና ማስረዳት ጀመረ፦

"ማለቴ፣ አሁን የለም! ዛሬ አይቻልም። የስራ ማቆም አድማ አለ። ይህ ሜትሮ የሚባለው ዋነኛ የፓሪስ ማመላለሻ ከምድር ስር ተኝቷል ምክንያቱም እነዛ ትኬታችንን የሚበሱልን ሰራተኞች ስራ አቁመዋል።"

"እነዚህ አስጠሊታዎች!" አለች ዛዚ "እነዚህ ላሞች! እኔን እንዲህ ያደርጉኛል"

"አንቺን ብቻ አይደለም'ኮ እንዲህ ያደረጉሽ" አለ ጋብሪዬል ሁኔታዎችን በሚያመዛዝን እርጋታ!።

"ለሉ ግዴለኝም! ነገሩ እኔ ላይ ነው የደረሰው። እንዴት ደስ ብሎኝ ነበር መሰለህ! ስፈነጥዝ ነበር ሜትሮ ውስጥ በባቡር እንሸራሸራለሁ እያልኩ። እዝጌር ይውረድባቸው! አራም ሁሉ!"

"ለራስሽ ምክንያት መፍጠር አለብሽ" አለ ጋብሪዬል - ሃሳቦቹ አንዳንዴ ከታላላቆቹ ፈላስፋዎች ከቅዱስ ቶማስና ከካንት ተመጥነው የተቀላቀሉ ናቸው።

ከዚያም ወደ አስተዋዋቂነቱ እየመጣ፣ እንግዲህ ሲል ቀጠለላት፦

"እንደምንም ብለን ወጥተን መሄድ አለብን። ሻርል እየጠበቀን ነው"

"እሱንማ አውቀዋለሁ!" አለች ዛዚ በንዴት ቦግ እያለች "በጄኔራል ቬርሞንት የተፃፈው ‹ማስታወሻ› ውስጥ አንብቤዋለሁ"

"አይደለም ኧረ'ባክሽ!" አለ ጋብሪዬል "ሻርል ባለታክሲ ጓደኛዬ ነው። በዚሁ በስራ ማቆም አድማው ምክንያት አስቀድሜ በታክሲው እንዲወስደን ቀጥሬዋለሁ፣ ገባሽ? ወደፊት!"

ሻንጣውን ባንድ እጁ አነሳና በሌላው ዛዚን እየጐተተ ወጣ።

እንዳለውም፣ ሻርል አንድ ሳምንታዊ ጋዜጣ ውስጥ "የተሰበረ ልብ" የሚለውን ቋሚ አምድ እያነበበ ይጠብቃቸዋል። (ይሄ በፈረንሳይኛው ‹የተሰበረ ልብ - የሚደማ ልብ› የሚለው አምድ፣ ከዚህ በፊት ከልብ ካፈቀሩ በኋላ እምቢ ተብለው ወይም ተከደው በሀዘን የሚኖሩ ወንዶችና ሴቶች፣ የደረሰባቸውን አሳዛኝ ታሪክ ከተናገሩ በኋላ፣ ስምና አድራሻ የሚለዋወጡበት ነው - ምናልባት እድል ቢቀናቸው ለመገናኘት ፍቅርን እንደ አዲስ ለመመስረት። ሻርል ለአመታት ሲፈልግ የቆየው፣ አንዷን አግኝቶ፣ የአርባ አምስት ወርቃማ አመታቱን ገፀበረከት ሊያቀርብላት ነው። እዚህ ጋዜጣ ውስጥ እንደዚሁ ለራሳቸው ሲያዝኑ የሚያጋጥሙት ግን ወይ ሲበዛ ደሮ ራስ ናቸው ወይ ደሞ ሽሌ ናቸው።

"ሰላም፣ ሚጡ" አላት ዛዚን፣ ዞር ብሎ ሳያያት፣ ጋዜጣውን በጥንቃቄ አጣጥፎ ቂጡ ስር እያስቀመጠ "እንዴት አስቂ መሰለችህ መኪናዋ" አለች ዛዚ

"ግቢ" አለ ጋብርዬል "ማዳም አትሁኚብኝ"

"ለማዳም የቂጤን አበሳ ይስጣቸው" አለች ዛዚ

"ትስይፋለች፣ እቺ ሚጢጢ የእህትህ ልጅ" አለ ሻርል፣ ሞተሩን ከመቀስቀሻ መዘውሩ ጋር እያያያዘ።

ጋብሪዬል በማይከብድ ግን ጠንካራ በሆነ እጁ ዛዚን አንስቶ ታክሲው ውስጥ ወረወራትና ገብቶ ከጐኗ ተቀመጠ

"ጨፈለቅሽኝ!" ብላ ጮኸች ንዴቱ እያስቀወጣት

"ሊነሳብን ይመስላል" አለ ሻርል ባጭሩ፣ በለሳማዊ ድምፅ

መኪናውን አስነሳ

ትንሽ ከሄዱ በኋላ ጋብሪዬል አካባቢውን ግርማ በተሞላ የእጅ እንቅስቃሴ አመላከተ።

"አይ ፓሪስ!" ሲል ድምፁን አሳመረ "እንዴት ያለች ውብ ከተማ! እዩልኝማ ስታምር!"

"እሱ ስሜት አይሰጠኝም" አለች ዛዚ "እኔ 'ምፈልገው በሜትሮ መሄድ ነበር"

"ሜትሮ!" ጮኸ ጋብሪዬል "ሜትሮ!! ያውልሽ!!!"

እና በጣቱ አየሩ ውስጥ የሆነ ነገር አመለከተ

ዛዚ ግንባሯን ቋጠረች። ተጠራጠረች።

"ሜትሮ?" ደገመች "ሜትሮ" ብላ በንቀት ጨመረች "ሜትሮ። ከመሬት በታች ነው ሜትሮ። ይሄ ግን"

"ይሄኛው የአየር ነው" አለ ጋብሪዬል

"እንግድያው ሜትሮ አይደለማ"

"ላስረዳሽ" አለ ጋብሪዬል "አንዳንዴ ከመሬት ይወጣና፣ ከዚያ ቀጥሎ ተመልሶ ይገባል"

"ተረት ምናምን!" አለችው።

ጋብሪዬል የሚሆነው ጠፋው፣ እጁን አወራጨ። ከዚያ የጭውውቱን ርዕስ ለመለወጥ እየፈለገ፣ እንደገና እመንገዳቸው ላይ አንድ ነገር አመለከተ

"ይሄሳ!" ጮኸ "እዩ!! ፓንቴዮን!!!"

"ዛሬስ የማንሰማው የለም" አለ ሻርል፣ ፊቱን ሳያዞር

ቀስ እያለ ነበር የሚነዳው፣ ሚጢጢዋ አዲስ ትርኢቶች እንዲታዩዋት በዚያውም ትምህርት እንድትቀስም።

"ምናልባት ፓንቴዮን አይደለም ''ንዴ?" ጠየቀ ጋብሪዬል

ጥያቄው ውስጥ የሆነ ሽሙጥ ነገር አለ

"አይደለም" አለ ሻርል በማስረገጥ "አይደለም፣ አይደለም፣ አሁንም አይደለም፡፡ ፓንቴዮን አይደለም"

"እንግዲህ ባንተ አስተያየት ምን ይሆን?"

የሽሙጥ የነበረው ድምፅ ስድብ ሊሆን ምንም አልቀረውም፡፡ ለነገሩ አድማጩ መረታቱን ሊያምን እየተጣደፈ ነው፡፡

"እኔ አላውቅም" አለ ሻርል

"ይኸዋ! አየኸው"

"ግን እኮ ፓንቴዮን ላይሆንም ይችላል" አለ ሻርል ግትር ስለሆነ

"ዞር ዞር አንዱን መንገደኛ እንጠይቅ" ሀሳብ አቀረበ ጋብሪዬል

"መንገደኞቹ ሁሉም ጅል ናቸው" አለ ሻርል

"በጣም እውነት ነው" አለች ዛዚ በሰላማዊ ድምፅ

ጋብሪዬል መለስ አለ በጋለ ስሜት፡፡ የሚናገርበት አዲስ ርዕስ አገኘ

"ይሄሳ?" ጮኸ "ይሄማ..."

ብሎ ሳይቀጥል ሻርል ተአምራዊ ሀቅ በተገለፀለት ድምፅ አቋረጠው፡-

"አወቅኩት!" ጮኸ "አሁን ያየነው ቦታ ፓንቴዮን አይደለም፣ ጋር ደ ሊዮን ባቡር ጣቢያ ነው፡፡

"ምናለበት" አለ ጋብሪዬል ስሜት ሳይሰጠው "አሁን እሱ አልፏል እንርሳው፡፡ ይሄ ግን፣ ሚጡዬ እይልኝ፡፡ ድንቅ አርኪቴክቸር አይደለም? ሌዜንቫሊድ ነው..."

"ዞሮብሀል" አለ ሻርል "ይሄ ከሌዜንቫሊድ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፡፡"

"እሺ" አለ ጋብሪዬል "ሌዜንቫሊድ ካልሆነ ምን እንደሆነ አስተምረና"

"ያን ያህልም እርግጠኛ አይደለሁም" አለ ሻርል "ግን ቢሆን ቢሆን የረይ የወታደር ካምፕ ነው"

"እናንተ" አለች ዛዚ ስትፎግራቸው "ሁለታችሁም የምትከይፉኝ ልጆች ናችሁ"

"ዛዚ" አለ ጋብሪዬል፣ ከሚጫወታቸው ቲያትሮች የአንዱን ባለግርማ ሞገስ ገፀ ባህሪይ እየመሰለ "ሴዜንቫሊድን እና እውነተኛውን የናፖሊዮን መቃብር ለማየት የምትፈልጊ ከሆነ እኔ እወስድሻለሁ"

"ናፖሊዮን የቂጤን አበሳ ይስጠው!" አለች ዛዚ "በፍፁም ስሜት አይሰጠኝም ያ ቡፋ ከነ ደደብ ኮፍያው"

"እንግዲያው ምን ያስኝሻል?"

ዛዚ መልስ አትሰጥም

"አዎን" አለ ሻርል ባልተጠበቀ ደግነት "ምንድነው ስሜት የሚሰጥሽ?"

"ሜትሮ"

ጋብሪዬል ‹አህ!› ብሎ ዝም አለ፡፡ ሻርል ምንም አላለም፡፡ ከዚያ ጋብሪዬል ዲስኩሩን ይቀጥልና መልሶ ‹አህ!› ይላል፡፡

"እና መቼ ነው ይሄ አድማ የሚቆመው?" ጠየቀች ዛዚ ቃላቷ ውስጥ ንዴት እያመቀች፡፡

"እኔ አላውቅም" አለ ጋብሪዬል "እኔ ፖለቲካ ውስጥ የለሁበት!"

"ፖለቲካ አይደለም" አለ ሻርል "የእንጀራ ጉዳይ ነው"

"እርሶስ መስዬ" ጠየቀች ዛዚ "አንዳንዴ አድማ ይመታሉ?"

"እምዬዋ! ዋጋ ለማስጨመር በግድ እንደዛ ማድረግ አለብን"

"የናንተንስ ዋጋ ማስቀነስ ነበር! እቺ የእርሶ ጋሪ እንዴት ደባሪ ናት! ምናልባት ማርን ባህር ዳር ይሆን እንዴ ያገኙዋት!"

"እየደረስን ነው" አለ ጋብሪዬል እያስታረቃቸው "ያውና ማዞሪያው ጋ ያለው ሲጋራ መሸጫ ሱቅ"

"የትኛው ማዞሪያ?" አለ ሻርል በምፀት

"ቤቴጋ ያለው ማዞሪያ ነዋ" አለ ጋብሪዬል በየዋህነት

"እንግዲያው እሱ አይደለም" አለ ሻርል

"እንዴት!" አለ ጋብሪዬል "ያ እሱ አይደለም እያልከ ነው?"

"ኤዲያ" አለች ዛዚ "እንደገና ልትጀምሩ እንዳይሆን"

"እሱ አይደለም" አለው ሻርል ጋብሪዬልን

"ግን እውነቱን ነው 'ክ" አለ ጋብሪዬል በሱቁ አጠገብ ሲያልፉ "እዚህኛው ውስጥ ገብቼ አላውቅም"

"እኔ 'ምልህ አጐቴ" አለች ዛዚ "እንደዚህ የምትጃጃለው አውቀህ ነው ወይስ ሳትፈልግ ነው"

"አንቺን ለማሳቅ ብዬ ነው ልጇዋ" አለ ጋብሪዬል

"አታስቢ" አላት ሻርል "ሆን ብሎ አይደለም የሚያረገው"

"ብልጠት አይደለም" አለች ዛዚ።

"እውነቱን ልንገርሽ" አለ ሻርል "አንዳንዴ ሆን ብሎ ያረገዋል፣ አንዳንዴ ሳያውቅ ነው"

"እውነቱን!" ጮኸ ጋብሪዬል ሰውነቱን እያወራጨ "ልክ አንተ የምታውቀው ይመስል፣ እዚህ አለም ላይ ግን ማንኛውም ሰው የማያውቀው ይመስል። ይሄ ሁሉ ቅጥፈት ነው! ፓንቴዮን፣ ሌዚንቫሊድ፣ የረይ ወታደር ነምገ፣ ማዞሪያው ጋ ያለው የትንባሆ ሱቅ፣ ሁሉ። አዎ ሁሉም ውሸት"

ከብዶት ተሸንፎ አከለበት፣

"አህ ላላ! አይ መከራ!"

"ቆም እንበልና አፔሪቲቭ እንጠጣ'ንዴ" አለ ሻርል

"አይከፋም"

"ላ ካቭ መጠጥ ቤት?"

"ወደ ሴን - ዤርሜይን - ዴ-ፕሬ?" አለች ዛዚ እየተቁነጠነጠች

"አይደለም፣ ሚጡ" አለ ጋብሪዬል "ምን እያሰብሽ ነው? እንደሱም ጊዜው ያለፈበት የለም"

"ዘበናይ አይደለሽም ለማለት ዳርዳሩን እያልክ ከሆነ" አለች ዛዚ "አንተ ደግሞ ጅል ሽማግሌ ነህ ብዬ ልመልስልህ እችላለሁ"

"ሰማህልኝ?" አለ ጋብሪዬል

"ምን ታረገዋለህ?" አለ ሻርል "አዲሱ ትውልድ ነው"

"አዲሱ ትውልድ" አለች ዛዚ "አንተን..."

"ይሁን ይሁን" አለ ጋብሪዬል "ገብቶናል፡፡ መታጠፊያው ላይ ወደ አለው የሲጋራ ሱቅ ብንሄድስ?"

"ትክክለኛው መታጠፊያ" አለ ሻርል

"አዎ" አለ ጋብሪዬል "በኋላ ደሞ አብረኸን እራት ትበላለህ"

"ተባብለን አልነበረም 'ንዴ?"

"አዎን"

"ታዲያ ምን?"

"ታዲያ ማረጋገጤ ነዋ"

"ማረጋገጥ አያስፈልግም፣ ተግባብተን ስለነበረ"

"እንዲያው ምናልባት ኧረስተኸው እንዳይሆን ብዬ ላስታውስህ ነው እንበል"

"አልረሳሁም ነበር"

"እንግዲያው አብረኸን እራት ትበላለህ?"

"እኮ ምንድነው? ሜርድ" አለች ዛዚ "የተባለውን መጠጥ አንጠጣውም 'ንዴ?"

ጋብሪዬል ከታክሲው በብልሀትና በቅልጥፍና ወጣ፡፡ ሰው ሁሉ በሚመላለስበት መንገድ ላይ በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ተገናኙ፡፡ አሳላፊዋ በቸልተኝነት መጣች፡፡

ዛዚ "አንድ ካኮ ካሎ" ብላ አዘዘች

"የለንም" ተባለች

"ኤዲያ!" ጮኸች ዛዚ "ምን አይነት ነገር ነው?!" ተናዳለች

"ለኔ" አለ ሻርል "ቦዥሌ ወይን አሁን"

"ለኔ ደሞ" አለ ጋብሪዬል "አንድ ወተት-ግሬናዲን። አንቺስ?" ጠየቃት ዛዚን።

"ተናግሬያለሁ። አንድ ካኮ ካሉ"

"የለም አለች 'ኮ"

"እኔ'ምፈልገው ካኮ ካሉ ነው"

"ምንም ያህል ብትፈልጊው" አለ ጋብሪዬል በአባታዊ ትዕግስት "እንደሌለ አይተሻል 'ኮ"

"ለምን የላችሁም?" ጠየቀች ዛዚ አስተናጋጇን

"እንዲሁ" በቸልተኝነት መለሰ

"ግማሽ ቅልቅል አይስከሬምላ፣ ዛዚ?" ሲል ሀሳብ አቀረበ ጋብሪዬል "እሱስ አላማረሽም"

"አንድ ካኮ ካሉ ነው 'ምፈልገው፣ ሌላ አይደለም"

ሁሉም ሀሳብ ዋጣቸው። አሳላፊዋ አንድ ጭኗን አከከች።

"እዛኛው ቤት'ኮ ይገኛል" አለች በመጨረሻ "ጣልያኑ ቤት"

"እንዴት ነው" አለ ሻርል "በዦሌው አይመጣም 'ንዴ?"

ልታመጣ ሄደች። ጋብሪዬል ተነሳ ምንም ሳይናገር። በፍጥነት ጠፋ። ሁለት መምጠጫ ሳር በአፉ ወጥቶ የሚታይበት ጠርሙስ ይዞ መጣ። ይህንኑ ዛዚ ፊት አስቀመጠው።

"ይኸውልሽ ሚጡዬ" አለ በለጋስ ድምፅ

ምንም ሳትናገር ዛዚ ጠርሙሱን አነሳች

"ይኸውና አየኸው" አለ ጋብሪዬል ለጓደኛው "አስቸጋሪ አልነበረም። ልጆች'ኮ ከተረዳናቸው ይበቃቸዋል"

# ሁለት

"እዚህ ነው" አለ ጋብሪዬል

ዛዚ ቤቱን አስተዋለችው፣ የተሰማትን ግን አትገልፅም።

"ታዲያስ" ጠየቀ ጋብሪዬል "ይስማማል?"

ዛዚ ሀሳቧን ከመናገር እንደተቆጠበች የሚገልፅ የሚመስል ምልክት ታሳያለች።

"በበኩሌ" አለ ሻርል "ቱንራዶ ጋር እየሄድኩ ነው። የምነግረው አለኝ።"

"ገባኝ" አለ ጋብሪዬል

"እዚህ ውስጥ ምን የሚገባ ነገር አለ?" ጠየቀች ዛዚ

ሻርል ከእግረኛ መንገዱ ወደ ላ ካቭ ካፌ-ሬስቶራንት የሚወስዱትን አምስት ደረጃዎች ወርዶ በሩን ገፍቶ ገባና ከጠላት ወረራ ወዲህ በእንጨት ወደተሰራው ባንኮኒ አመራ።

"ሰላም፣ መሴ ሻርል" አለች ማዶ ፕቲፒዬ ለአንዱ ደንበኛ መጠጥ እየቀዳች።

"ሰላም፣ ማዶ" አለ ሻርል ወደሷ ሳይዞር

"እሷ ናት?" ጠየቀ ቱራንዶ

"ትክክል" መለሰ ሻርል

"እንደዚህ ትልቅ አልመሰለችኝም ነበር"

"እና?"

"ደስ አላለኝም። ለ,ጋቢ ነግሬዋለሁ፣ ቤቴ ውስጥ ጭቅጭቅ አልፈልግም" አለ ቱራንዶ

"ንሳ፣ አንድ ቦገሌ ስጠኝ"

ቱራንዶ ሀሳብ ይዞት በዝምታ ቀዳለት። ሻርል ቦኘሌውን ተጐነጨ፣ በመዳፉ ጀርባ ሙስታሹን አበሰ። ከዚያ በግማሽ ልብ ወደ ውጪ ተመለከተ። ለዚህ ሲባል ራሱን ቀና ማድረግ ነበረበት፣ እና የሚታየው እግሮች፣ ቁርጭምጭሚቶች፣ የሱሪ እጥፋቶች፣ አንዳንዴም እድል ሲገኝ አንድ ሙሉ ውሻ። ጣራ የሚደርሰው መስኮት አጠገብ አንዲት ሀዘንተኛ በቀቀን ተጠልላለች። ቱራንዶ የሻርልን ብርጭቆ እንደገና ሞላና ለራሱ አንድ ቀዳ። ማዶ ፐቲፒዬ መጥታ ከባንኮኒው እኋላ ከአለቃዋ ጐን ቆመችና ዝምታውን ሰበረች

"መሴ ሻርል" አለች "እርሶ ሁል ጊዜ እንደተከዙ ነው"

"ትካዜ የቂጤን አበሳ ይስጠው" አለ ሻርል

"እውነቴን ነው!" ጮኸች "ማዶ ፐቲፒዬ ዛሬ ጨዋ አይደሉም"

"ይከይፈኛል" አለ ሻርል ክፉ ገፅታ እየታየበት "ያቺ ትንሽየዋ ልጅ እንደዚህ ነው 'ምታወራው"

"አልገባኝም" አለ ቱራንዶ፣ ምንም ዘና ሳይል

"ቀላል ነው" አለ ሻርል "እቺ ልጅ ምንም ቃል መናገር አትችልም ቂጤ ብላ ካልጨመረችበት።"

"እና ቃላቱን በድርጊት ትተረጉመዋለች?" ጠየቀ ቱራንዶ

"ገና ናት" መለሰ ሻርል የምር "ግን ማድረጓ አይቀርም"

"አታረገውም" አቃሰተ ቱራንዶ "ያስ አይሆንም?"

በሁለት እጁ ራሱን ያዘና ፀጉሩን በመነጨት ከንቱ ማስመሰል ካሳየ በኋላ፣ ንግግሩን በሚከተሉት ቃላት ቀጠለ

"የሜርድ ሜርድ! ቤቴ ውስጥ እንዲህ አይነት ብልግና የምትናገር ወራዳ ልጅ አልፈልግም። ካሁን ይታየኛል፣ ሰፈሩን በሙሉ ነው 'ምትበክለው። ከአንድ ስምንት ቀን በኋላ..."

"ሁለት ሶስት ቀን ብቻ ነው 'ምትቆየው" አለ ሻርል

"እሱም በዛ!" ጮኸ ቱራንዶ "በሁለት ሶስት ቀን ውስጥ በደንበኝነታቸው የሚያከብሩኝ የጃጁ ሽማግሌዎች ሱሪ ውስጥ እጄን ለመስደድ በቂ ጊዜ ይኖራታል። ጭቅጭቅ አልፈልግም። ሰማኸኝ? ጭቅጭቅ አልፈልግም።"

አንድ ጥፍሯን ስታኝክ የነበረችው በቀቀን ጉንበስ አለችና መፀዳዷጏን እያቋረጠች ውይይቱ ውስጥ ገባችበት፦

"ታወራለህ" አለች በቀቀኗ ላቬርዲዩር "ታወራለህ፤ ይሄን ብቻ ነው ማድረግ የምታውቀው"

"እውነቷን ነው" አለ ሻርል "ዞር ዞር፤ ታሪኮችህን የምትነግረው'ኮ ለኔ መሆን የለበትም።"

"እደብረዋለሁ" አለ ጋብሪዬል በመውደድ "ግን የትንሽዬዋን ባለጌ ቃላት ለምን እንደደገምኩለት ራሴን እየጠየቅኩ ነው"

"እኔ እውነት ነው 'ምናገረው" አለ ሻርል "ደሞ የእህትህ ልጅ ከአስተዳደግ ጉድለት ምን ያህል ባለጌ እንደሆነች ልትደብቅላት አትችልም። እስቲ ልጠይቅህ፣ አንተ በልጅነትህ እንደዛ ነበር 'ምትናገረው?"

"አልነበረም" አለ ጋብሪዬል "ግን እኔ ትንሽ ሴት ልጅ አልነበርኩም"

"እንቀመጥ" አለች ማርሴሊን በለስላሳ ድምፅ፣ ሾርባውን እያቀረበች "ዛዚ፣ ነይ ቁጭ በይ"

ከሾርባው በዝግታ በየስሀኑ መጨለፍ ጀመረች።

"አሀ!" አለ ጋብሪዬል በደስታ "ቀጭን ሾርባ"

"እናብዛው'ንጂ" አለች ማርሰሊን በዝግታ

በመጨረሻም ዛዚ መጥታ፣ አይኗ ወደ ባዶ እያፈጠጠ ተቀመጠች። እንደራባት በቁጭት ተጎነዘበች

ከሾርባው በኋላ ቋሊማ ከሳቮያርድ ድንች ጋር፤ ከዛ በኋላ ጉበት (ጋብሪዬል ከመጠጥ ቤቱ ያመጣው - ላያመጣው አላስቻለውም፣ በግራም በቀኝም በጉበት ተከቦ ስለነበረ) ከዛ በኋላ ስኳር የበዛባቸው ጣፋጮች እና ቡና በስኒ

ሻርልና ጋብሪዬል ወደ ሌሊት ሽቀላቸው የሚሰማሩበት ሰአት ደረሰ።

የተለመደ፣ ዛሬ ግን ያልተጠበቀውን ግረናዲል በኪ.ርሽ ከጠጡ በኋላ ሻርል ወጥቶ ሄደ፡፡

የጋብሪዬል ስራ ግን ከአምስት ሰአት በፊት አይጀምርም፡፡ እግሮቹን ከጠረጴዛው ስር፣ (ኧረ ከዛም ን.ላፎ) ዘረጋ፡፡ እና ቀጥ ብላ ወንበሯ ላይ የተሰየመችውን ዛዚን አይቶ ፈገግ አለ፡፡

"ታዲያስ ሚጡ" አለ ከወምበሩ እየተነሳ "እንግዲህ እንተኛ"

"ማነው እኛ?" ጠየቀች

"እህ! አንቺ ነሻ" አለ ጋብሪዬል፣ ወጥመዷ ውስጥ እየገባላት "እዚያ ሳለሽ በስንት ሰዓት ነበር 'ምትተኚው?"

"እዚህ እና እዚያ ሁለት ናቸው፣ ተስፋ አለኝ"

"አዎን" አለ ጋብሪዬል እየገባው

"ለዚህ ነው እዚህ የተውኝ፡፡ እዚያ እንደሚሆነው እንዳይሆን አይደለም?"

"አዎ"

"እንዲያው ነው አዎ 'ምትለኝ ወይስ እውነትህን ነው"

ጋብሪዬል ወደ ማርሰሊን ሲዞር ፈገግ ብላለች፡-

"እቺ ትንሽዬ ልጅ የማሰብ ችሎታዋ ምን ያህል እንዳደገ ይታይሻል? ምን ይጨምርላቸዋል ብለን ትምህርት ቤት ልንልካቸው እንደምንቸገር ነው የማይገባኝ"

"እኔ ግን" አወጀች ዛዚ "ስልሳ አምስት አመት እስከሚሆነኝ ድረስ ትምህርት ቤት መሄዴ አይቀርም"

"እስከ ስልሳ አምስት አመት!?" ደገመ ጋብሪዬል እየገረመው

"አዎን" አለች ዛዚ "አስተማሪ መሆን ነው 'ምፈልገው"

"እንደመ·ያ አይከፋም" አለች ማርሰሊን በለዘብታ "ጡረታ አለው"

ይሄን ያለችው በልማድ ነው፣ ፈረንሳይኛ ቋንቋን በሚገባ በማወቋ

"ጡረታ የቂጤን አበሳ ይስጠው" አለች ዛዚ "እኔ ለጡረታው አይደለም አስተማሪ መሆን 'ምፈልገው"

"አይደለምና" አለ ጋብሪዬል "እኛም አልመሰለንም"

"እንግዲያው ለምንድነው?" ጠየቀች ዛዚ

"እሱን አንቺ ነሽ የምታስረጅን"

"በራስህ ልትደርስበት አልቻልክም፣ እ?"

"እንዴት ጠንካራ ነው የዛሬው ትውልድ" አለ ጋብሪዬል ለማርሰሊን፡፡

እና ለዛዚ፡-

"እሺ ለምንድነው አስተማሪ መሆን 'ምትፈልጊው?"

"ልጆቹን ለማስቀዘን" መለሰች ዛዚ "የዛሬ አስር አመት የኔ እድሜ የሚሆኑትን፣ የዛሬ ሀምሳ አመት፣ የዛሬ መቶ አመት፣ የዛሬ ሺ አመት፣ ሁልጊዜ ልጆቹን ማበሳጨት"

"ደሞስ?" አለ ጋብሪዬል

"የምር አስቃያቸዋለሁ፡፡ የእንጨት ወለሉን አስልሳቸዋለሁ፡፡ የጥቁር ሰሌዳውን ማጥፊያ ስፖንጅ አስበላቸዋለሁ፡፡ በኮምፓስ ቂጣቸውን እወጋቸዋለሁ፡፡ ደሞ ቂጣቸውን በካልቾ! ምክንያቱም ቦት አድርጌ ነው 'ምሄደው፡፡ በክረምት ከፍታው ይህን ሚያክል፡፡" ቁመቱን በባቷ እየለካች "ቁርጭምጭሚቱ ጋ እሾህም መኮርኮሪያ ያለው፣ ቂጣቸውን የምቸከችክ በት፡፡"

"ታውቂያለሽ" አለ ጋብሪዬል በእርጋታ "ጋዜጦቹ ሲነግሩን ዘመናዊ ትምህርት በእንዲህ አይነት አቅጣጫ አይሄድም፡፡ እንድያውም በተቃራኒው ወደ መለሳለስ፣ ወደ መግባባት፣ ወደ ደግነት ነው፡፡ ጋዜጣው እንዲህ አይደለም 'ንዴ 'ሚለው፣ ማርሰሊን?"

"አዎን" አለች ማርሰሊን በለዘብታ "ዛዚ፣ አንቺን ትምህርት ቤት አሰቃይተውሻል 'ንዴ?"

"ያስብላል እሱንስ አያሳየን!" አለች ዛዚ

"ከዚያም ሌላ" አለ ጋብሪዬል "ከሃያ አመት በኋላ አስተማሪዎች አይኖሩም፡፡ ሲኒማ፣ ቲቪ፣ ኤሌክትሮኒክስ፣ እና የመሳሰሉት ነገሮች ይተኩዋቸዋል፡፡ ይሄም ባለፈው ቀን ጋዜጣ ላይ ተፅፎ ነበር፡፡ አይደለም'ንዴ፣ ማርሰሊን?"

"አዎን" አለች ማርሰሊን በለዘብታ

ዛዚ ይህን የወደፊት ኑሮ ላንዳፍታ አሰበችበት

"እንግዲያው አስትሮኖት ነው'ምሆነው" ብላ ወሰነች

"እንዲያ ነው" አለ ጋብሪዬል ሀሳቧን በመደገፍ "ከጊዜው ጋ መራመድ ይገባል"

"አዎን" አለች ዛዚ "አስትሮኖት እሆንና የማርስን ሰዎች አስቀዝናቸ ዋለሁ"

ጋብሪዬል በጋለ ስሜት ጭኑን በመዳፉ ፀፋ፡-

"እቺ ልጅ 'ምታመጣቸው ሀሳቦች'ኮ!" እጅጉን ተደሰተ

"እንድያም ሆኖ፣ ሄዳ መተኛት ይኖርባታል" አለች ማርሰሊን በለስላሳ "አልደከመሽም?"

"አይ!" አለች ዛዚ እያዛጋች

"ደክሟታል እቺ ልጅ" አለች ማርሰሊን ለጋብሪዬል እየተናገረች "ሄዳ መተኛት አለባት"

"እውነትሽን ነው" አለ ጋብሪዬል፣ የትእዛዝ እንቀፅ ያለበት አረፍተ ነገር፣ እና ቢቻል ወድያውም ለተናገረችው ምላሽ የሚሆን አረፍተ ነገር ሊቀምም እየሞከረ፡፡

ይህን አረፍተ ነገር ለመቀመም በቂ ጊዜ ሳይወስድ ዛዚ ቲቪ እንዳለው ጠየቀችው፡፡

"የለኝም" አለ ጋብሪዬል ውሸቱን "ሲኒማ ቤት ነው ሄጄ 'ማየው"

"እንግድያው ሲኒማ ቤት ልትጋብዘኝ ትችላለህ?"

"ሰአቱ አለፈ" አለ ጋብሪዬል "እኔ ራሴ ደሞ ጊዜ የለኝም፡፡ በአምስት ሰአት ስራ ገቢ ነኝ"

"አንተ አታስፈልገንም" አለች ዛዚ "እኔና አክስቴ ብቻችንን እንሄዳለን"

"እሱማ በጭራሽ ደስ አይለኝም" አለ ጋብሪዬል በዝግታ፤ መልኩ ያስፈራል፡፡ የዛዚን አይን አይኗን እያየ፣ በጨካኝ ድምፅ "ማርሰሊን ከኔ ጋር ካልሆነ በፍፁም አትወጣም" አለና ቀጠለ፡-

"ይህን አላስረዳሽም፣ ሚጢ፣ በጣም ይረዝምብናል"

ዛዚ ወደ ሌላ እያየች አፋሸገች

"ደክሞኛል" አለች "ሄደ ልተኛ ነው"

ተነሳች። ጋብሪዬል ጉንጩን አቀረበላት። ሳመችው

"ቆዳህ ይለሰልሳል" አለችው።

ማርሰሊን አብራት ወደ መኝታዋ ሄደች። ጋብሪዬል ከአሳማ ቆዳ የተሰራ ቦርጆ የእርሳስ ኩል መያዣ አወጣ፣ ከነአባቱ ስም የመጀመሪያዎቹ ሁለት ፊደላት ታትመውበታል። ተቀመጠ፣ በትልቅ ብርጭቆ ግረናዲን ቀድቶ በትንሽ ውሃ በረዘውና በጣም የሚወደው የመድረክ ስራ እንዲያምርበት መኳኳል ጀመረ። ደም በሚገባ ይችልበታል፣ ከማንም ጥፍር አስተካካይ ጥበብ የገዛ ራሱን ይመርጣል። አንድ የብልግና ዘፈን በዜማ ብቻ ማንጐራጐር ጀመረ። ቀጥሎ፣ የሰስቱን የተረት ወርቅ ሰሪዎች ጀብዱ ካንጐራጐረ በኋላ፣ ልጅቱን እንዳይቀሰቅስ እየተጠነቀቀ የድሮ መዝሙሮችን ያፏጭ ጀመረ - "የማታ እሳት ሲጠፋ" "ለባንዲራዋ ሰላምታ" "አስር አለቃ ቂላቂሎ" ወዘተ

ማርሰሊን ተመለሰች

"ወድያውኑ ተኛች" አለች በለዘብታ

ተቀመጠችና ለሷ አንድ ብርጭቆ ኪርሽ ቀዳች

"ትንሽዬ መልአክ" አለ ጋብሪዬል በገለልተኛ ድምፅ

ቆርጦ የጨረሳትን የትንሿን ጣቱን ጥፍር በአድናቆት ሠመልከት ጀመረ። አደነቀና የቀለበት ጣቱን ጥፍር መቁረጥ ጀመረ።

"ቀኑን ሙሉ ምን ስናረጋት እንውላለን?" ጠየቀችው ማርሰሊን

"ይሄን ያህል ችግር አይኖርም" አለ ጋብርዬል "መጀመሪያ ወደ ቱር ኤፌር (አይፈል ታወር) ወስጄያት ጫፍ ላይ እንወጣለን። ነገ ከሰአት በኋላ"

"ነገ ጠዋትሳ?" ጠየቀች ማርሰሊን በለዘብታ

ጋብሪዬል በስጋት ፊቱ እየገረጣ

"ምንም ቢመጣ" አለ "ዛዚ እንዳትቀሰቅሰኝ"

"ይኸውልህ" አለች ማርሰሊን በለዘብታ "አንድ ፕሮብሌም" ጋብሪዬል ስጋቱ እየባሰበት ሄደ።

"ልጆች በጠዋት ነው 'ሚነሱት። አላስተኛ ትለኛለች... በደንብም እንዳላርፍበት... ታውቂኛለሽ'ኮ። ማረፍ አለብኝ፣ ጉልበቴን ማደስ አለብኝ የአስር ሰዓት እንቅልፍ የግድ ያስፈልገኛል። ለጤናዬ።"

ማርሰሊንን አየት

"ይሄ በሀሳብሽ አልመጣም?"

ማርሰሊን አይኗን ሰበረች

"ከስራህ ላስተጓጉልህ ብዬ አይደለም" አለችው በ ማታ።

"አመሰግናለሁ" አለ ጋብሪዬል በእርጋታ "ጠዋተ ድምፇን እንዳልሰማ ምን ማድረግ እንችል ይሆን?"

ሁለቱም ማሰብ ጀመሩ።

"የእንቅልፍ መድሃኒት ብናስውጣትስ" አለ ጋብሪዬል "እስከ እኩለ ቀን እንድያስተኛት፣ እንዲያውም እስከ አስር ሰአት። በፊንጢጣ የሚገባ መድሃኒት አለ አሉ ይህን ውጤት የሚያስገኝልን።"

ኳ.ኳ.ኳ. አለ በሩ በቀስታ። ቱራንዶ ነው

"ግቡ" አለ ጋብሪዬል

ቱራንዶ ከላቨርድዩር ጋር ገባ፣ ማንም "ኖር" ሳይለው ተቀመጠና ግረናዲኑን ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠ። ላቨርዲዩር የግረናዲን ጠርሙሱን በማይረሳ መጉምጀት ተመለከተች። ማርሰሊን ወደመጠጫዋ ትንሽ ቀዳችላት። ጋብሪዬል የመሀል ጣቱን ጥፍር ጨርሶ የአመልካች ጣቱን ጀመረ። ይሄ ሁሉ ሲሆን ማንም አልተናገረም።

ላቨርዲዩር ግረናዲዋን በአንድ አፍታ መጠጣችው። ማንቆሪያዋን መቆሚያዋ እንጨት ላይ አበሰች፣ ከዚያ በሚከተለው ስልት ተናገረች፦

"ታወራለህ፣ ታጣራለህ፣ ይሄን ብቻ ነው ማድረግ 'ምታውቀው"

"ማውራት የቂጤን አበሳ ይስጠው" ብሎ መለሰ ቱራንዶ በንዴት። ጋብሪዬል ስራውን እያቋረጠ በመጥፎ አይን አየው

"አሁን ያልከውን እስኪ ድገመው" አለ

"እኔ ያልኩት" አለ ቱራንዶ "ማውራት የቂጤን አበሳ ይስጠው ነው"

"ደፍሬ ልጠይቅህና፣ አሁን የተናገርከው አሽሙር ምን ለማለት ነው?"

"በአሽሙር ያልኩትማ፣ ያቺ ልጅ እዚህ መሆኗ ደስ አይለኝም"

"ሰማኸኝ? ደስ አለህ አላለህ ስሜት አይሰጠኝም"

"ይቅርታ፡፡ ልጅ ሳይኖር ነበር ያከራየሁህ፣ እና አሁን እኔ ሳልፈቅድ ልጅ አምጥተህብኛል"

"ያንተን ፈቃድ የት እንደማረገው ልንገርህ?"

"አውቃለሁ፣ አውቃለሁ፣ እንደ እህትህ ልጅ ተናግረህ እስከምታሳፍረኝ ድረስ ሩቅ አይሆንም"

"ካንተ እኩል ብልህ መሆን አያስፈልግም፡፡ ለመሆኑ ‹ብልህ› ማለት ምን እንደሆነ ታውቃለህ፣ አንተ ደደብ?"

"ይኸዋ!" አለ ቱራንዶ "ጀመረ 'ንግዲህ"

"ታወራለህ" አለች ላቨርዲዩር "ታወራለህ፡፡ ይሄን ብቻ ነው ማድረግ 'ምታውቀው"

"ይሄዋ ምን?" ጠየቀ ጋብሪዬል ቁልጭ ባለ ማስፈራራት

"ስትናገር በፀያፍ ቃላት መሆን ጀመረ" አለች ማርሰሊን

"ሊያበሳጩኝ ስለጀመረ'ኮ ነው" አለ ጋብሪዬል

"አትብሸቅ" አለች ማርሰሊን በለስላሳ ድምፅ

"እንዲህ ያለች ወራዳ ልጅ እቤቴ ውስጥ አልፈልግም" አለ ቱራንዶ በሚያሳዝን ቅላጼ

"ደበርኩህ?" ጮኸ ጋብሪዬል "ሰማኸኝ? ደበርኩህ ወይ?"

እጁን ጨብጦ ጠረጴዛውን ሲደቁሰው እተለመደው ቦታ ተሰነጠቀ፡፡ የላቨርዲዩር ጉጆ ምንጣፍ ላይ ሲወድቅ የተከተሉት የግረናዲን ጠርሙስ የኪርሽ ፉሽኮ፣ ትናንሽ ብርጭቆዎች፣ የጥፍር መቁረጫ ሰገባ፣ ላቨርዲዩር ቅሬታዋን በቁጣ አሰማች፣ ሽሮፑ የተዋበው የቆዳ ቦርሳ ላይ ፈሰሰ

ጋብሪዬል በተስፋ ቢስ ጩኸት የወደቀውን እቃ ለማንሳት ሲወረወር ወንበሩን መሬት ላይ ጣለው

በር ተከፈተ፡፡

"ምንድነው? ሜርድ! መተኛት አንችልም 'ንዴ?"

ዛዚ በፒጃማ ናት፡፡ አዛጋችና፣ ላቨርዲዩርን በጥላቻ እያየቻት

"ይሄስ የእንስሳት መሰብሰቢያ ነው!" አለች

"ታወራለህ፣ ታወራለህ" አለች ላቨርድዩር "ይሄን ብቻ ነው ማድረግ 'ምታውቀው"

ትንሽ እየገረማት በቀቀኗን ችላ ብላ ወደ ቱራንዶ ዞረችና አጎቷን ጠየቀች፡-

"ያ ደሞ ማነው?"

ጋብዬል እርሳስ መያዣውን በገበታ ልብሱ ጫፍ እየጠረገ ነበር፡፡

"ሜርድ" አጉረመረመ "አለቀለት ይሄ ቦርሳ"

"እኔ ሌላ እሰጥሀለሁ" አለች ማርሰሊን በዝግታ

"ጉሽ! እንዴት ጥሩ ነው!" አለ ጋብሪዬል "ከሆነ አልቀረ ግን የአሳማ ቆዳ ባይሆን የበለጠ ደስ ይለኛል"

"የቱ አይነት ይሁንልህ? የጥጃ ቆዳ?"

ጋብሪዬል ፊቱን ቅጭም አደረገ

"ጋሎሻ የሚባለው አሪፍ ቆዳ ቢሆንልህስ?"

ቅጭም

"የራሺያ ቆዳ?"

ቅጭም

"የአዞ?"

"ውድ ይሆናል" አለ፣ ፊቱ እየፈካ "ግን ጥሩ እቃ ነው፣ እና ዘናጭ!"

"እሱ ይሁን፡፡ ራሴ ሄጄ እገዛዋለሁ" አለች ማርሰሊን

ጋብሪዬል በጣም ፈገግ እያለ ወደ ዛዚ ዞረ፡-

"አየሽ? አክስትሽ'ኮ እንዷለች ደግ ናት"

"አልነገርከኝም'ኮ:: ያ ማነው?"

"ባለቤትየው ነው" አለ ጋብሪዬል "ልዩ አይነት ባለቤት! ታች ያለው መጠጥ ቤት ባለቤት"

"የላ ካብ?"

"ትክክል" አለ ቱራንዶ

"የእርሶ ካብ ውስጥ ይደነሳል?"

"በጭራሽ!" አለ ቱራንዶ

"ውዳቂ!" አለች ዛዚ

"ለሱ አታስቢ" አለ ጋብሪዬል "ደህና ገቢ አለው"

"እሱ ግን እዚያ ሳን-ዤርሜን-ዴ- ሰፈር ውስጥ ምን እያደረገ ሲደሰት ይውላል? ጋዜጦች ሁሉ ስለሱ ነው 'ሚያወሩት"

"ስለኔ ጉዳይ ማሰብሽ በጣም ደግ ነው" ነው ቱራንዶ በኩራት

"ደግነት የቂጤን አበሳ ይስጠው!" አለች ዛዚ ቁርጥ ባለ ድምፅ ቱራንዶ የድመት የሚመስል ድል አድራጊነት አሰማ

"አይ!" አለው ጋብሪዬልን "ከንግዲህ ልትከደኝ አትችልም፣ የሷን 'የቂጤ አበሳ ይስጠው ሰምቼዋለሁ"

"ምነው ቆሻሻ ምናምን ባትናገር?" አለ ጋብሪዬል

"እኔ አይደለሁም'ኮ" አለ ቱራንዶ "እሷ ናት"

"ያሳብቃል" አለች ዛዚ "ብሽቅ ነው"

"አሁን 'ንግዲህ ይብቃን" አለ ጋብሪዬል "መሄጃዬ ደረሰ"

"ደስ 'ሚል አይመስልም የሌሊት ዘበኛ መሆን" አለች ዛዚ

"ማንኛውም ሙያ በጣም ደስ አይልም:: አሁን ሂጂና ተኚ" ቱራንዶ የወፍ ጎጆውን እያነሳ እንዲህ አለ:-

"በዚህ ርዕስ ውይይታችንን እንቀጥላለን"

እና የብልህ ሰው ገፅታ እያሳየ፡-

"ውይይት የቂጤን አበሳ ይስጠው!"

"እንዴት ያለው ጅል ነው?" አለች ማርሰሊን እሱ ሳይሰማት

"ከሱ የተሻለ ለማግኘት አንችልም" አለ ጋብሪዬል

"እሺ ደህና እደሩ" አለ ቱራንዶ እንደ ቅድሙ በደግነት "ደስ 'ሚል ምሽት አሳለፍኩ፣ ጊዜዬን አላጠፋሁም"

"ታወራለህ፣ ታወራለህ" አለች ላቨርዲዬር "ይሄን ማድረግ ብቻ ነው 'ምታውቀው"

"ደስ ስትል!" አለች ዛዚ ወፏን እየተመለከተች

"ሂጂ 'ንጂ ተኚ" አለ ጋብሪዬል

ዛዚ በአንድ በር ወጣች፣ የማታው ጉብኚዎች በሌላ በር ወጡ

ጋብሪዬል ሁሉ ነገር ሰላም እስኪሆን ቆይቶ በተራው ወጣ። ደረጃውን ድምፅ ሳያሰማ ወረደ፣ እንደ ጨዋ ተከራይ

ማርሰሊን ግን ኮመዲኖ ላይ አንድ ነገር አየችና እንስታ በሩን ለመክፈት ሮጠች፣ እና በደረጃው ጉምበስ ብላ በለስላሳ ድምፅ ተጣራች

"ጋብሪዬል፣ ጋብሪዬል"

"ምነው ምን መጣ?"

"የከንፈር ቀለምህን ረሳህ"

# ሶስት

በመኝታ ቤቱ በአንዱ ማእዘን ማርሰሊን አንድ መፀዳጃ ቤት ብጤ ሰርታለች - አንድ ጠረጴዛ፣ መታጠብያ ሰሀን፣ ማንቆርቆርያ - ጭልጥ ያለ ገጠር ውስጥ ያለች እስኪመስል። እንዲህ ቢሆን ዛዚ ቤቷ አይናፍቃትም በማለት። ዛዚ ግን ግራ ተጋብታለች። ወለሉ ላይ በሚስማር የተጣበቀውን ሽንት ቤት ተጠቀመችበት፣ ሌላውንም ድንቅ ፅዳት መጠበቅያ ቁሳቁስ አስተዋለች።

ይሄ ፋራነት አስጠላት። ፊቷን ውሀ አስነካች፣ ማበጠርያውን በፀጉሯ ላይ አንድ ጊዜ ብቻ አስኬደች።

ወደ አጥር ግቢው አየች፣ ጭር ብሏል ያው ነው፣ ምንም ነገር ያለ አይመስልም። ጆሮዋን ወደ በሩ ብታቀርበውም ምንም ድምፅ አልተሰማት። በፀጥታ ከመኝታ ክፍሉ ወጣች። እንግዳና-ምግብ-ቤቱ ጨልሞ ፀጥ ብሏል። በዝግታ፣ እግሮቿ ባንድ መስመር ሲራመዱ እየተነካኩ፣ ግድግዳውንም እቃዎቹንም በጥንቃቄ እየነካካች፣ ለበለጠ ደስታ ደሞ አይኗን ጨፍና ነው፣ ሌላኛው በር ጋ ደረሰች። እና በስንትና ስንት ጥንቃቄ ከፈተችው።

ይሄኛው ክፍልም ጭለማና ፀጥታ ውጦታል - የሆነ ሰው ተኝቶ በሰላም ይተነፍሳል። ዛዚ በሩን መልሳ ዘጋች፣ በመጣችበት አኳኋን የጎሲት መሄድ ጀመረች (ሁሌ ደስ 'ሚል አካሄድ ነው መቸስ) እና በጣም ረዥም ጊዜ ካለፈ በኋላ፣ ሌላ እና ሶስተኛ በር ጋ ደርሳ፣ ከቅድሙ ባላነሰ ጥንቃቄ ከፈተችው።

የደረሰችበት መግቢያ በቀይና በሰማያዊ መስተዋት ባጌጠ መስኮት የገባ ጭላንጭል ያበራዋል። እንደ መጨረሻ በር ከፈተችና የጉዞዋን አላማ ደረሰችበት - ሽንት ቤት።

ዘመናዊ በመሆኑ ስለተስማማት ሩብ ሰአት ሙሉ እዚያው አሳለፈች። ቦታው ጠቃሚ ብቻ ሳይሆን የደስ ደስ አለው። ንፁህ ነው፣

ይበራል፡፡ ሀር አይነት! ወረቀቱ እጅ ውስጥ ሲንኮሻኮሽ ደስ ይላል፡፡ በዚህ ሰዓት የፀሀይ ጮራም ገብቷል፡፡ ጣራ ከሚነካው መስኮት የሚያንፀባርቅ ውሀ በዝግተኛ ጠብታ ይወርዳል፡፡

ዛዚ በረዥሙ አሰበች፡፡ ውሀ ማፍሰሻውን ልሳበው ወይስ አልሳበው? ቤቱን ይረብሻል መቼስ፡፡ እያመነታች ገመዱን ጎተተች፣ ፏፏቴው ወረደ፣ ዛዚ አድፍጣ ጠበቀች፣ ምንም ነገር ሲንቀሳቀስ አይሰማትም፡፡ በምትሀት ያንቀላፉ ይመስላል፡፡ ዛዚ በሲኒማ የምታውቃቸው ተዋናዮችን እየጨመረችበት አንድ የምትሀት ተረት ለራሷ ነገረች፡፡ የተረቱ ሂደት ትንሽ ግር አላት፣ በመጨሻ ላይ ግን የሁልጊዜው ንቁ ተመልካች አዕምሮዋ ስለተመለሰ፣ የምትሀት ተረቶች የመጨረሻ ጅል ናቸው ብላ ደምድማ ለመውጣት ወሰነች፡፡

እንደገና መግቢያው ጋ ስትደርስ አንድ ሌላ በር አየች፣ ወደ መውጫው የሚወስድ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ዛዚ እንጠንቀቃለን ብለው የተውትን ቁልፍ አዞረችው፡፡ ልክ ነው፣ መውጫው ጋ ደረሰች፡፡ በጣም ቀስ ብላ በሩን ዘጋችውና በጣም ቀስ ብላ ወረደች፡፡ ማረፊያው ጋ ትንሽ ቆመች፣ ምንም አይንቀሳቀስም፡፡ ወደ ምድር ቤት ወረደች፡፡ ኮሪደሩ ያውና፣ መውጫው በር ክፍቱን ነው፡፡ አራት ማዕዘን ብርሀን ገብቷል፡፡ ዛዚ ሄደች፣ ወጣች፡፡

ፀጥ ያለች መንገድ ናት፡፡ የሚያልፉት መኪናዎች ጥቂት ከመሆናቸው የተነሳ እግረ መንገዱ ላይ መጫወት ይቻላል፡፡

ሰዎች በዝግታ እየተዘዋወሩ ነው፡፡ ሲሻገሩ መጀመሪያ ወደ ግራ ቀጥሎ ወደ ቀኝ በመመልከት ከተሜነቱን ከጥንቁቅነት ጋር ያቀናጁታል፡፡

ዛዚ ያን ያህልም ቅር አላላትም፣ በእርግጥ ፓሪስ ውስጥ መሆኗን አውቃለችና፡፡ ከዚህም ጋር ፓሪስ አንድ ሰፊ መንደር መሆኑ ገብቷታል፡፡ እና ሌሎቹ ጉዳናዎችም ይሄን እንደማይመስሉ ታውቃለች፡፡ እንድያም ሆኖ በዓይኗ ለማየትና እርግጠኛ ለመሆን ራቅ ብሎ መሄድ ያስፈልጋል፡፡ መሄዱን ጀመረችው፣ ዘና ባለ ሙድ

ዳሩ ምን ይሆናል፣ ቱራንዶ ድንገት ከመጠጥ ቤቱ ወጣና ከደረጃው ስር ጮኸ፡-

"ማጡ፣ ወዴት እየሄድሽ ነው?"

ዛዚ አትመልስለትም፡፡ እርምጃዋን ማስረዘም ይበቃታል፡፡ ቱራንዶ የመጠጥ ቤቱን ደረጃዎች ወጣ፡-

"አንቺ ሚጡ" ችክ አለና መጮሁን ቀጠለ

ዛዚ ወዲያው አካሔዷን ወደ ጅምናስቲክ እርምጃዋን ለወጠች፣ ማዞሪያው ጋ ታጠፈች። ሌላው መንገድ ይበልጥ ህይወት ዘርቶበታል። አሁን ዛዚ በፍጥነት እየሮጠች ነው፣ ሰው ሊያያት ጊዜም ሀሳብም የለውም። ታዲያ ቱራንዶ ደሞ በበኩሉ እየጋለበ ነው። እንዲያውም ተወረወረ፣ ያዛት፣ ክንዷን ጨበጣት፣ ምንም ሳይናገር በሀይል! እና ቀኝ ኋላ አዞራት። ዛዚ ሳታመነታ መጮህ ጀመረች

"ኡ ኡ! ኡ ኡ!"

ይህ ጩኸት እዚያ ያሉትን የቤት እመቤቶችና የወንዶችን ትኩረት ሳይስብ አልቀረም። የግላቸውን ስራ ወይም ስራፈትነት እየተዉ ወደ ኡኡታው አተኮሩ።

እዚህ አስደሳች ውጤት ላይ ዛዚ ጨመረችበት፡-

"ከዚህ ሰውዬ ጋር መሄድ አልፈልግም! ይሄን ሰውዬ አላውቀውም! ከሱ ጋር መሄድ አልፈልግም"

ቱራንዶ ድርጊቱ ተገቢ መሆኑን ያውቃል፣ ይህን የማስፈራራት ጩኸት ከምንም አልቆጠረው። ደግነቱ ወዲያውኑ ስህተቱ ታየው ወግ አጥባቂ የሆኑ የግብረ ገብ ጠባቂዎች ከበውታል

በነዚህ ምርጥ ተመልካቾች ፊት ዛዚ ከአጠቃላይ ክስ ወደ ዝርዝር ተሻገረች፡-

"ይሄ ሰውዬ" አለች ከመሬት ተነስታ "ባለጌ ነገሮች ተናገረኝ"

"ምን አለሽ?" ጠየቀች አንዲት ሴትዮ ለወሬው እየጉመዥች

"ማዳም!" ጮኸ ቱራንዶ "እቺ ትንሽ ልጅ ከቤቶቿ ሸሽት ነው። ወደ ወላጆቿ መውሰዴ ነበር"

ከበባው ስር የሰደደ ጥርጣሬውን በመሳቅ ገለፀ።

ሴትየዋ ወደ ዛዚ ጐንበስ አለችና ቀጠለች

"በይ ሚጡዬ፣ አትፍሪ፣ ንገሪኝ ይሄ ቆሻሻ ሰውዬ ያለሽን"

"በጣም ባለጌ ነው" አንሾካሸከች ዛዚ

"የሆነ ምናምን ነገር እንድታረጊለት ጠየቀሽ'ንዴ?"

"አዎን፣ ማዳም"

ዛዚ በሹክሹክታ አንዳንድ ዝርዝሮችን በጆሮዋ ነገረቻት። ሴትየዋ ቀና አለችና ቁራንዶ ፊት ላይ ተፋች

"ብስብስ!" አለችውና በተጨማሪ እንደምርቃት እንደገና ድጋሚ ፊቱ ላይ ተፋችበት

አንድ ሰውዬ ጠየቀ:-

"ምን አድርጊልኝ ነው ያላት?"

ሴት ወይዘሮዋ ስብከተ ዛዚን ለሰውዬው በጆሮው ነገረችው

"እዬ! ድጋሚ?" አለ ሰውየው "ከተፈጠርኩ እንዲህ አይነት ሀሳብ መጥቶልኝ አያውቅም"

ቁራንዶ ሀሳብ ገብቶት እንደገና

"ኧረ በፍፁም! ሁሉም የሷ ፈጠራ ነው"

"እንዴ! ኧረ ስሙልኝ! የማይታመን'ኮ ነው" አለ አንዱ ሌላ

"እሉ አንዳንድ ጨርሰው ወራዳ የሆኑ ባለጌዎች" አለ ሌላኛው

እስከ አሁን የዛዚ ዝርዝሮች ህዝቡ መሀል ተሰራጭተዋል። አንዲት ሴትዮ "አልገባኝም" አለች

አንድ ሰውዬ ሊያስረዳት ከኪሱ ወረቀት አውጥቶ በስክሪቢቶ ስዕል ሰራ

"እንዲህ ነው ለካ" አለች፣ እንደሰመመን እየወሰዳት።

"በተጨባጭ ይሻላል?" አለች ስለስክሪብቶው ነበር የተናገረችው።

ሁለት አማተር ሳይኮሉጂስቶች ይወያያሉ:-

"በበኩሌ" አለ አንዱ "ሲያወሩ እንደሰማሁት የሆኑ (ዝርዝሮች ይናገራል)

"ይሄም አይደንቀኝም" አለ ሌላው "እርግጥ ነው፣ እንደነገሩኝ ከሆነ..." (ዝርዝሮች ይናገራል

"ይሄም አይደንቀኝም" መለሰ ሌላው "እርግጥ ነው፣ ብለው እንደነገሩኝ ከሆነ..." (ዝርዝሮች ይናገራል)

ወሬው ስቧት ከሱቋ የወጣች አንዲት ነጋዴ አንዳንድ ምስጢሮቿን ተናገረች

"እኔ ልንገራችሁ:: ባሌ ምን እንደነካው እንጃ፣ አንድ ቀን፣ ይሄን ያህል የጠለቀ ስሜት ከየት እንዳመጣ ለእናንተ ልተውና..."

"ምናልባት መጥፎ መፅሐፍ አንብቦ ይሆናል" ሀሳብ አቀረበ አንዱ

"ምናልባት ይሆናል:: ለማንኛውም፣ ካሰኘህ ወደምትሄድበት ሄደህ አድርግ እንጂ በአሳፋሪ ብልግናዎችህ አትነዝንዘኝ:: እንዲህ ነው ያልኩት ባሌን:: እሱ እንድናረግ የፈለገው..." (ዝርዝሮች)

ሁሉም ልክ ነሽ እሱ

ቱራንዶ አላዳመጠም፣ ራሱን አላታለለም:: የዛዚ ክስ በህዝቡ መሀል የቀሰቀሰው የቴክኒካዊ ዕውቀት ዝርዝር ከለላ በማድረግ ሹልክ ብሎ ጠፋ:: ግድግዳውን ተጠግቶ እየተራመደ መጠምዘዣውን አለፈና በፍጥነት ወደ መጠጥ ቤቱ ገብቶ፣ ከጠላት ግዛት ወዲህ በእንጨት ከተሰራው ባንኮኒ በስተኋላ ቆሞ አንድ ትልቅ ብርጭቆ ቦገሌ ወይን ቀድቶ በአንድ ትንፋሽ ከጨለጠ በኋላ ደግሞ፣ እንደመሀረብ በሚጠቀምባት ጨርቅ ግንባሩን አበሰ::

ማዶ ፐቲ-ፒዩ ድንች እየላጠች ጠየቀችው:-

"ደህና አይደሉም እንዴ?"

"አታንሺብኝ! ከተፈጠርኩ እንደዚህ ቦክቼ አላውቅም:: እነዚህ ጅሎች በሙሉ ቅንዝራም ወጠጤ መስያቸዋለሁ:: እዚያው ቆይቼ ቢሆን ይከታትፉኝ ነበር"

"ይህ እንግዲህ ለወደፊቱ የማታውቁት ነገር ውስጥ ጥልቅ አለማለትን ያስተምርታል" አለች ማዶ ፐቲ-ፒዩ::

ቱራንዶ አልመለሰም:: ጭንቅላቱ ውስጥ ያለውን ትንሽ ቲቪ ከፍቶ በሀሳቡ የገዛ ራሱን ዜና ማየት ጀመረ:: ቅድም የደረሰበትን ሁሉ ታሪክ መፅሐፍ ውስጥ ሊጨምረው ሲል፣ ለትንሽ ያመለጠውን፣ እና ቢያንስ ለዕለቱ የወሬ አጣጣሚዎች ዜና ሊያበቃው የነበረውን - በጊዜ ነቅቶ ያመለጠውን ጉድ ሲያስብ እንቀጠቀጠው፣ እንደገና ላቡ ፊቱ ላይ ችፍ ችፍ አለ::

"ኧረ ያንተ ያለህ!"

"ታወራለህ" አለች ላቨርዲዩር "ታወራለህ፣ ይሄን ብቻ ነው ማድረግ 'ምታውቀው"

ቱራንዶ ፊቱን ጠራረገ። እና ሶስተኛ ብርጭቆ በዣሌ ወይን ቀዳ

"ያንተ ያለህ!" ብሎ ደገመ

ይሄ ፊሊፕ ነበር አሁን የሚያስጨንቀውን ስሜት የሚያወጣለት የመሰለው

" እና ምንድነው?" አለች ማዶ ፐቲ-ፒዩ "አልሞቱም'ኮ"

"ምነው እዛ ባየሁሽ?!"

"ምነው እዛ ባየሁሽ?! ምንም ማለት አይደለም። እርሶና እኔ ሁለት ነን እንጂ አንድ አይደለንም"

"አይ! እንግዲህ ወሬ አታብዢ። አያስፈልገኝም!"

"እና ሌሎቹን ማስጠንቀቅ አስፈላጊ አይመስሎትም?"

እውነቷን'ኮ ነው። ሜርድ! አላሰበበትም ነበር። የተቀዳለትን ሶስተኛ ብርጭቆ ትቶት ተወረወረ

"እዩልኝ!" አለች በዝግታ ማርሰሊን

"ሚጡ" አለ ቱራንዶ፣ ትንፋሽ እያጠረው "ሚጡ፣ እኔ'ምለው፣ እ፣ ጠፋች"

ማርሰሊን አልመለሰችለትም፣ በቀጥታ ወደ ክፍሏ ሄደች። እውነቱን ነው።

"አየኋት" አለ ቱራንዶ "ልይዛት ሞከርኩ። እልም አለች"

ማርሰሊን ወደ ጋብሪዬል ክፍል ገባች፣ ነቀነቀችው፣ ይካብዳል፣ መጐተቱ ያስቸግራል፣ መንቃት ከየት መጥቶ? መተኛት ይወዳላ ሰውየው! እየተነፈሰ ተንቀሳቀሰ። ከተኛ ጥኝ ነው በቃ፣ እንዲህ በቀላሉ አይነቃም።

በመጨረሻ "ምን ምን?" ብሎ ጮኸ።

"ዛዚ ጠፍታ ሄደች" አለች ማርሰሊን በለስላሳ። አያት። ቃል አልተናገረም። ጋብሪዬል ባንዳፍታ ነው 'ሚገባው - ጅል አይደለም። ተነሳ፣ የዛዚን ክፍል በአይኑ ፈተሸ። ጋብሪዬል ነገሮችን ራሱ ማረጋገጥ ያስፈልገዋል።

"ምናልባት ሽንት ቤት ውስጥ ተዘግቶባት ይሆናል" አለ በተስፋ

"አይ!" አለች ማርሰሊን በዝግታ "ቱራንዶ አይቷት ነበር"

"በትክክል ያየኸውን ንገረኝ እስቲ" አለው ቱራንዶን

"ስትሸሽ አየኋት። ሮጬ ያዝኳት፣ ወዳንተ ላመጣት ፈልጌ"

"መልካም" አለ ጋብሪዬል

"እሺ ይሁን። ልጅቱ ግን ሰዎቹን ለጠብ ቀስቅሳቸዋለች። እየጮኸች ምናምን ነገር ሊያደርገኝ ይፈልጋል አለቻቸው"

"እና እውነቷን አልተናገረችም?" አለ ጋብሪዬል

"ኧረ በጭራሽ!" አለ ቱራንዶ ትግስቱ እያለቀ

"አይታወቅም ብዬ ነው"

"እሺ ይሁን፣ አይታወቅም"

"ይኸውልህ!"

"ተወው'ንጂ ይቀጥል" አለች ማርሰሊን በለዘብታ

"እና ሰዎቹ ሁሉ ከበቡኝ፣ ጥርሴን ሊያራግፉ እየተዘጋጁ። ያተኮሰው ወጠጤ መስያቸው'ኮ ነው። ጅላጅል ሁላ!"

ጋብሪዬልና ማርሰሊን በሳቅ ፈነዱ

"ጊዜዬን ስጠብቅ፣ ወሬ እያወሩ ረሱኝና እግሬ አውጪኝ አልኩ"

"ፍርሀት ለቀቀብህ?"

"እንዲህ አይምሰልህ! ከተፈጠርኩ እንዲህ ቦክቼ አላውቅም፣ በጦርነቱ ጊዜ ቦምቡ በሚወርድብን ሰአት'ንኳ"

"እኔ በበኩሌ" አለ ጋብሪዬል "ቦምቡ በሚወርድበት ሰአት አልፈራሁትም። ኤሮፕላኖቹ የእንግሊዝ ከሆኑ፣ ቦምቦቹ የሚወድቁት እኔ ላይ ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም፣ ያነጣጠሩት ጀርመኖች ላይ ነው። እኔማ እንግሊዞቹ ከመጡ እጄን ዘርግቼ እንደማቅፋቸው ነው።"

"ሞኝ አስተሳሰብ ነው" አለ ቱራንዶ

"እንድያም ሆኖ ግን ፈርቼ አላውቅም፣ ደሞ ንክች አርገውኝ አያውቁም፣ እንዳየኸው ነው - ከሁሉ በከፋው ሰአት'ንኳ ቢሆን።"

"የሂትለር ወታደሮች የተጠለልንባቸውን ቦታዎች እየጣሱ የሚገቡበት አይተነው የማናውቅ መሳሪያ ነበራቸው።"

"እኔ ለራሴ ደንታም አልሰጠኝ፣ ውጭ ቆሜ ርችቱን አያለሁ። ዷ! ይላል የጦር መሳርያ። መጋዘኑ ሲፈነዳ፣ ጣቢያው እንደ አፈር ድቅቅ ሲል፣ ፋብሪካው ብትንትኑ ሲወጣ፣ ከተማዋ ስትንበለበል - - ወደር የማይገኝለት ትርኢት!"

ጋብሪዬል ሲጨርስ "ኡፍ!" ብሎ ተነፈሰ፡- "እውነት'ኮ ነው፣ ኑሮዋችን አይከፋም ነበር"

"እኔ ግን በበኩሌ" አለ ቱራንዶ "በጦርነቱ ምንም የተደሰትኩበት ነገር አላጋጠመኝም። ጥቁር ገበያ ብሞካክር ከሞኝ አልተሻልኩም። እንዴት እንደማደርግ አላውቅም መሰለኝ፣ ሁል ጊዜ መቀጮዬን እንደቀመስኩ ነበር። ዕቃዎቼን ይመነትፉኛል፣ መንግስት፣ የቀረጥ ቢሮ፣ ተቆጣጣሪዎቹ ሱቄን ይዘጉብኛል። በጁን ወር በአርባ አራት አመተ ምህረት እንኳንም ዘጉት። ምክንያቱም በኋላ አንድ ቀን ድንገት አንድ ቦምብ ወረደ፣ ሱቁ ቡን አለ ቦነነ! ገደ ቢስነት። ደግነቱ ይሄን ቤት መውረሴ ነበር። ባይሆን ኖሮ ግን..."

"ዞሮ ዞሮ ማዘን አያስፈልግህም" አለ ጋብሪዬል "ይኸው፣ እየተንፈላሰስክ ነው 'ምትኖረው። የያዝከው ሙያ 'ንኳ የስራ ፈት ነው"

"ምነው በኔ ቦታ ሆነህ ባየሁህ! አቤት ሲያደክም የኔ ሙያ! አሰልቺ! እና ከዚያ በላይ የጤና ጠንቅ"

"እንደ'ኔ ሌሊት መሽቀል ቢኖርብህ ኖሮ ምን ትል ነበር ይሆን? እና ቀን መተኛት። ቀን መተኛት በጣም አድካሚ ነው፣ ሲያዩት ባይመስልም። እንደ ዛሬ በማይታመን ሰአት ሲቀሰቅሱህማ ባይነገር ይሻላል... ሁልጊዜ ጠዋት ጠዋት እንዲህ እንዳይሆን እንደፀለይኩ ነው"

"እቺን ልጅ ቤት ውስጥ መቆለፍ ይገባል" አለ ቱራንዶ

ጋብሪዬል በሀሳብ ተውጦ "ለምን ሸሽታ ሄደች ይሆን?" ሲል አጉተመተመ

"ድምፅ ማሰማት አልፈለገችም" አለች ማርሰሊን ለስለስ ባለ ድምፅ "እና እንዳትቀሰቅስህ ብላ ልትንሸራሸር ወጣች"

"ብቻዋን እንድትንሸራሸር አልፈቅድም" አለ ጋብሪዬል "ባቡር መንገድ የብልግና ትምህርት ቤት ነው። ይሄን ሰው ሁሉ ያውቃል"

"ምናልባት ጋዜጦቹ እንደሚሉት ኮብልላ ይሆናል" አለ ቱራንዶ

"ቀልድ እንዳይመስልህ" አለ ጋብሪዬል

"መጠንቀቅ ያስፈልጋል። እኔስ ብሆን ለሚያዩኝ ምን እመስላለሁ?"

"ሄደህ ብትፈልጋት የሚሻል አይመስልህም?" አለች ማርሰሊን በቀስታ

"እኔ በቀጥታ ልተኛ መሄዴ ነው" አለና ጋብሪዬል ወደ አልጋው አቅጣጫ አመራ

"ፈልገህ ብታመጣት'ኮ ተግባርህን ፈፀምክ፣ እንጂ ከዛ በላይ አይደለም"

ጋብሪዬል አስካካ። እና እየተቅለሰለሰ በዛዚ ድምፅ "ተግባር የቂጤን አበሳ ይስጠው" ብሎ አምባረቀ።

እና ጨመረበት፡-

"በገዛ ራሷ ራሷን ታገኛለች እባክሽ"

"እንዲያው ለምናልባቱ" አለች ማርሰሊን በዝግታ "፡ንድ የሆነ ወጠጤ ቢያጋጥማትስ?"

"እንደ ቱራንዶ?" አለ ጋብሪዬል በሳቂታ ድምፅ

"ይሄ ምኑም አያስቅ" አለ ቱራንዶ

"ጋብሪዬል" አለች ማርሰሊን በቀስታ "ሄደህ ልታመጣት ትንሽ ጥረት ማድረግ ይኖርብሀል"

"አንቺ ሂጂ"

"የሚታጠብ ልብስ ጥጃለሁ'ንጂ..."

"የሚታጠቡ ልብሶችን አውቶማቲክ ለሆኑት የአሜሪካ ማሽኖች መስጠት ይሻልዎታል" አላት ቱራንዶ "ስራ ይቀንስሎታል። እኔ 'ማረገው እንደዛ ነው"

"እና" አለ ጋብሪዬል በኩራት "ልብሶቿን ራሷ ስታጥብ ደስ የሚላት ቢሆንስ? እ? እዚህ ውስጥ ምን ያገባሀል? ታወራለህ ታወራለህ ይህን ብቻ ነው ማድረግ የምታውቀው። የአሜሪካን ማሽኖች እዚህ ውስጥ አሉኝ"

ቂጡን እየመታ ያሳየዋል

"እንዲህ ነው?" አለ ቱራንዶ በምፀት "እኔ ደሞ አሜሪካን ወዳድ መስለኸኝ"

"አሜሪካን ወዳድ?!" ብሎ ጮኸ ጋብሪዬል "ትርጉማቸውን የማታውቀውን ቃላት ነው 'ምትናገረው። አሜሪካን ወዳድነት ልብሳችንን ቤታችን ውስጥ ማጠብ የሚከለክል ይመስል። ማርሰሊንና እኔ አሜሪካን ወዳድ ብቻ አይደለንም። ከዚያም ጋር፣ ትሰማለህ አንት ቅል ራስ፣ አጠባ ወዳድ ነን፣ እ? ዝም አልክ አይደል አንት ዶሮ ራስ?!"

ቱራንዶ የሚመልሰውን አጣ። ወደ ተጨባጩ የአሁን ፕሮብሌም ተመለሰ።

"ወደ ልጅቱ መሮጥ ይገባሀል" ብሎ መከረው ጋብሪዬልን

"ባንተ የደረሰው በእኔም እንዲደርስ? በተራው ህዝብ ያለ ፍርድ እንድጨፈጨፍ?"

ቱራንዶ ትከሻውን ከፍ ዝቅ አደረገ "አንተም ራስህ" አለ በንቀት ድምፅ "ታወራለህ ታወራለህ፣ ይሄን ብቻ ነው ማድረግ የምታውቀው።"

"እንግዲያው ሂዳ" አለች ማርሰሊን በዝግታ ለጋብሪዬል

"ሁለታችሁም ደበራችሁኝ" አጉተመተመ ጋብሪዬል

ወደ ክፍሉ ገባ፣ በስልት ለበሰ፣ ለመላጨት ጊዜ ያላገኘለትን አገጩን በሀዘን ደባበሰ፣ በረኸርሙ ተነፈሰ፣ ተመልሶ ብቅ አለ።

ቱራንዶና ማርሰሊን ስለልብስ ማጠብያ ማሺኖች ጠንካራና ደካማ ጉን እየተወያዩ ናቸው። ጋብሪዬል ጉምበስ ብሎ የማርሰሊንን ግምባር ሳመ።

"ደህና ሁኚ" አላት በቁም ነገር "ተግባሬን ልፈፅም እየመረሸኩ ነው"

የቱራንዶን እጅ ጠበቅ አርጎ ጨበጠው፣ ሲለያቸው የሚሰማቸው ሀዘን ልቡን እየጨመቀው "ተግባሬን ልፈፅም እየወጣሁ ነው" ከሚሉት የተለዩ ታሪካዊ ቃላት ለመናገር አላስቻለውም። አስተያየቱ ግን የሚሄዱበትን ስፍራ ታላቅ ተግባር በሚጠብቃቸው ግለሰቦች ሀዘን አይነት ተጋርዶ ነበር።

ሲሎቱ ሀሳባቸውን ሰበሰበ

እየወጣ ነው። ወጣ።

ሲወጣ አየሩን ሳበው። የሚሸተው የተለመዱ ጠረኖች ነበሩ፣ በተለይ ላ ካቲ የሚወጡት። ወደ ሰሜን ወይስ ወደ ደቡብ መሄድ

እንደሚኖርበት ማወቅ አልቻለም፣ ምክንያቱም የመንገዱ አቅጣጫ እንደዛ በመሆኑ። ደግነቱ፣ አንድ ጥሪ ማመንታቱን ቆረጠለት። ግሪዱ ጫማ ሰፊው ነው ከተለጣፊ ሱቁ የሚጠራው። ጋብሪዬል ወደሱ ሄደ።

"እርግጠኛ ነኝ ትንሿን ልጅ ነው የሚፈልጉት"

"አዎን" አለ ጋብሪዬል ቅዝቅዝ ባለ ስሜት

"የት እንደሄደች አውቃለሁ"

"እርሶ ሁልጊዜ ሁሉን ነገር ያውቃሉ" አለ ጋብሪዬል እየበሸቀ

("ይሄ ደሞ" አለ ለራሱ፣ በሚጢጢዋ የውስጥ ድምፁ "ከሱ ጋር ባወራሁ ቁጥር የበታችነት ስሜቴን ያባርርልኛል")

"አይመለከቶትም'ንዴ" ጠየቀ ግሪዱ

"እሱማ በግድ ይመለከተኛል"

"እንግዲያው ልናገር?"

"ጫማ ሰሪዎችኮ ያስቃሉ" አለ ጋብሪዬል "አንድ ጊዜም ስራቸውን አያቋርጡም፣ ይወዱታል ያሰኛል፣ እና በፍፁም እንደማያቋርጡ ለማሳየት መስታወት ጉጆ ውስጥ ይቀመጣሉ፣ ሰው እንዲያደንቃቸው። የተቀደደ የሀር እግር ሹራብ እንደሚሰፉ ሴቶች"

"እርሶስ" መለሰ ግሪዱ "ሰው እንዲያደንቆት ምን ውስጥ ነው የሚቀመጡት"

ጋብሪዬል ጭንቅላቱን አከከ

"ምንም" አለ በልፍስፍስ ድምፅ "እኔ አርቲስት ነኝ። ምንም ቀሽም ነገር አልሰራም። አሁን ይሄን የምናወራበት ሰዓት አይደለም፣ የልጅቷ ጉዳይ ያስቸኩላል"

"ስለሷ ማውራት ደስ ስለሚለኝ ነው" መለሰ ግሪዱ በእርጋታ

ከስራው ቀና አለ

"ታዲያስ? ስለሆነ ጉዳይ ማወቅ ይፈልጋሉ ወይስ አይፈልጉም?"

"አስቸኳይ ነው እያልኮት'ኮ ነው"

ግሪዱ ፈገግ አለ

"ቴራንዶ ከአጀማመሩ ነግሮዎታል"

"ሊናገር የፈለገውን ተናግሯል"

"ለማንኛውም፣ እርሶ ማወቅ የሚፈልጉት ከዚያ በኋላ የደረሰውን ነው"

"አዎን" አለ ጋብሪዬል "ከዚያ በኋላ ምን ተደረገ?"

"ከዚያ በኋላስ ይሉኛል? አጀማመሩ አያበቃዎትም'ንዴ? እቺ ልጅ ከቤተሰቦቿ ጠፍታ መሸሿ ነው!"

"ደስ ማለቱ!" አለ ጋብሪዬል

"ለፖሊስ ማስታወቅ ብቻ ነው 'ሚኖርቦት"

"ለኔ ምንም ማለት አይደለም" አለ ጋብሪዬል በጣም በደከመ ድምፅ

"ብቻዋን ቤት አትመለስም"

"ማን ያውቃል?"

ግሪዱ ትከሻውን ከፍ ዝቅ አደረገ

"ዞሮ ዞሮ ስለጉዳዩ የተናገርኩት ሁሉ ለኔ ስሜት አይሰጠኝም"

"ለኔስ ቢሆን?" አለ ጋብሪዬል ከልብ

"ለመሆኑ እርሶ ልብ አሎት'ንዴ"

ጋብሪዬል በተራው ትከሻውን ከፍ ዝቅ አደረገ፡፡ "ደግሞ ደግሞ ጭራሽ ስድብ ይጨምርልኛል 'ንዴ?!"

ምንም ሳይናገር ወደቤቱ ተመልሶ ተኛ፡፡

# አራት

የከተማው ነዋሪዎች እና ወሬኞቹ ወይዛዝርት ስለ ጉዳዩ ውይይታቸውን እየቀጠሉ እያለ ዛዚ ሹልክ ብላ ጠፋች። በመጀመሪያ በቀኝ በኩል ባለው መንገድ ሄደች፣ ቀጥሎ በግራ፣ እንዲህ እያለች የከተማው መግቢያ በር ደረሰች። አስገራሚ ባለ አራት እና አምስት ፎቅ ሰማይ ጠቀስ ህንፃዎች በተንበሸበሸ ጉዳና ዳርና ዳር ይታያሉ። እግረኛ መንገዱ ላይ ቀናቸው ያለፈ የጉልት መደቦች ተጣበዋል። የተጨናነቀ ህዝብ በየአቅጣጫው እየተንጠባጠበ ይመጣል። ፊኛ ሻጭ ሴትዮ፣ የልጆች ተሽከርካሪ ፈረስ፣ ሙዚቃ፣ እነዚህ በሚተራመሰው ህዝብ ትርኢት ላይ ይህንን ጨዋ ስልት ጨመሩበት። ይሄ ሁሉ ሲያስደንቃት የቆየችው ዛዚ ከሷ ምንም ያህል ሳይርቅ እግረኛ መንገድ ላይ የተተከለ በቄንጠኛ ፊደላት METRO የሚል የተፃፈበት የብረት ሰሌዳ እስኪታያት ጊዜ ወሰደ። ወዲያውኑ የጉዳናውን ትርኢት ረሳች፣ ወደ መግቢያው ተጠጋች — እፎ በድንገተኛ መገረም ደርቋል። አጠገቧ ያለው የሰው መደገፊያ በአጫጭር እርምጃ ስትዞረው መግቢያውን አገኘች። ግን የብረት በሩ ተዘግቷል። አድማው እንደቀጠለ ነው። ብረት የተቀላቀለበት ደረቅ ሀገር ከተከለከለው መቀመቅ ቀስ እያለ ሲወጣ ሸተታት። ዛዚ ብስጭትጭት ብላ ማልቀስ ጀመረች።

ለቅሶዋ በጣም ስላስደሰታት፣ በምቾት ለመንሰቅሰቅ አግዳሚው ወንበር ላይ ሄዳ ተቀመጠች። ትንሽ ካለቀሰች በኋላ ታድያ፣ አጠገቧ ሰው እንዳለ ተሰማት። ሀዘኗን ረስታ ምን እንደሚቀጥል ለማየት ዝም ብላ ቆየች። የቀጠሉት በቀጭን የወንድ ድምፅ የሚከተለውን የጥያቄ ሀረግ ያዘሉ ቃላት ነበሩ፡-

"ምነው የኔ ልጅ፣ ትልቅ ሀዘን ደርሶብናል'ንዴ?" ይሄንን ግብዝነት የተሞላ ጅል ጥያቄ ስትሰማ ለቅሶዋ በእጥፍ ጨመረ ልቧ ውስጥ መንሰቅሰቅ ከማብዛቷ የተነሳ ትንፋሿን ለመቁረጥ ጊዜ አላገኘችም።

"ይሄን ያህል ጨንቆናል?" ተጠየቀች

"አዎን መስየ"

ይሄ ወጠጤ ምን እንደሚመስል ለማየት ጊዜው ደረሰ:: እጇን ፊቷ ላይ ስታረግ የእንባዋ ምንጭ እየደረቀ ወደ ሰውየው ዞረች:: አይኗን ማመን አቃታት:: ሰው እንዳያውቀው በትልቅ ጥቁር ሙስታሽ እና ክብ በሆነ ባርኔጣ፣ በዣንጥላ እና በትልልቅ ጫማ ተደብቋል:: "ሊሆን አይችልም!" አለች ዛዚ ለራሷ በትንሽየዋ ውስጣዊ ድምፅ "ሊሆን አይችልም! የድሮ የህብረ ትርኢት ተዋናይ መሆን አለበት"

ሰውየው ፊቱን እንደማጨማደድ አያለ፣ የሚያስደንቅ ንፅህና ያለው መሀረብ የያዘ እጁን ዘረጋላት:: ዛዚ ተቀበለችውና ፊቷ ላይ የረጋውን ቆሻሻ ካበሰች በኋላ ገፀበረከቱ ላይ ብዙ ንፍጥ ሰጠፈችበት::

"ታድያስ፣ ንገሪኛ" አለ ሰውየው በሚያደፋፍር ድምፅ "ምን ሆነሽ ነው? ወላጆችሽ ሙቱሽ? የሆነ ዕቃ ጠፍቶብሽ እንዳይቆጡሽ ፈርተሽ ነው?"

ገመትኳት ብሏል በሱ ቤት:: ዛዚ በጣም የረጠበ መሀረቡን መለሰችለት:: ይሄን ቆሻሻ ወደ ኪሱ ሲመልስ ምንም አይነት መፀየፍ ሳያሳይ ቀጠለ:-

"ሁሉንም ንገሪኝ:: አትፍሪ:: ልታምኚኝ ትችያለሽ"

"ለምን?" አለች ዛዚ፣ ሽር አስባ እየተኮላተፈች

"ለምን?" ጠየቀ ሰውየው ግር እያለው

አስፋልቱን በዣንጥላው መጫር ጀመረ

"አዎን" አለች ዛዚ "ለምን ኦምኖታለሁ?"

"እንዴ!" አለ ሰውየው መሬት መጫሩን እየተወ "እኔ ልጆች ስለምወድ:: ትንንሽ ሴት ልጆች:: እና ትንንሽ ወንድ ልጆች"

"ባለጌ ሽማግሌ ኖታ?!"

"ኧረ በፍፁም!" ጮኸ ሰውየው፣ ዛዚን እስኪገርማት እያመረረ

ሰውየው በመገረሟ ቅር እየተሰኘ ካኮ ካሎ ጋበዛት:: መጀመሪያ ወዳጋጠማቸው ቡና ቤት ገቡ (በውስጠ ታዋቂ በቀን ብርሀን፣ ሰው ሁሉ እያየ፣ ደግ ሀሳብ አይደለም?)

ካኮ ካሎ የመጠጣቱ ሀሳብ ምን ያህል እንዳስደሰታት ላለማሳየት ስትል ዛዚ ከመንገዱ ማዶ ያለው ህዝብ በሁለት የጉልት መደቦች ተርታ መሀል ሲተላለፉ ትክ ብላ ታስተውል ጀመር

"እነዚህ ሰዎች ምንድነው 'ሚያደርጉት?" ጠየቀች

"የሰልቫጅ እቃ አይነት ሁሉ የሚሸጥበት ገበያ እየሄዱ ነው፣ ማለቴ ገበያው ወደነሱ እየመጣ ነው።"

"ሳልቫጅ ገበያ" አለች ዛዚ፣ ያልደነቃት እየመሰለች "እዚያ ነው የራምብራንትን ስዕሎች በርካሽ ገዝተው በኋላ ለአንዱ አሜሪካን 'ሚሸጡት። ቀናቸውን አላባከኑም።"

"የራምብራንት ስዕሎች ብቻ አይደለም እዛ 'ሚገኘው" አለ ሰውየው "ጤና ለመጠበቅ የተሰሩ ጫማዎች፣ ልብስ ማጠቢያ፣ ሚስማሮች፣ ተሰብሶ የሚያውቅ ኮት ሳይቀር።"

"አሜሪካኖቹ ጥለውት የሄዱት?" አለች ዛዚ

"ታዲያስ! ድንች ጥብስ ሻጮችም አሉ። ያውም ጠዋት የተጠበሰ አሪፍ ድንች"

"እንኳን አሜሪካኖቹ ጥለውልን ሄዱ በሉኛ!"

"ከፈለግን። አነስ ያለ ጥሩ አይስተርም ይገኛል። መርዝ የሌለበት"

"አሜሪካኖቹ ሰማያዊ ጅንስስ ጥለውልን አልሄዱም?"

"አይጠረጠርም። እና በጨለማ የሚበራ ኮምፓስም"

"ኮምፓስ'ንኳ ስሜት አይሰጠኝም" አለች ዛዚ "ጅንስ ሱሪ ግን..."

"ሄደን ልናይ እንችላለን" አለ ሰውየው

"ከዚያ በኋላስ?" አለች ዛዚ "ምገዛበት ፍራንክ የለኝም፣ አንዱን ሱሪ ልሰርቅ ካልሆነ"

"ለማንኛውም ሄደን እንይ" አለ ሰውየው

ዛዚ ካኮ ካሎዋን ጨርሳለች። ሰውየውን አየችውና እንዲህ አለች "እርሶ የአሜሪካኖቹን ጫማ አርገው ሲወጡ ይታየኛል እንሂድ"

ሰውየው ከፈለና ህዝቡ መሀል ገቡ። ዛዚ የብስክሌት ታርጋ የሚቀርፁትን፣ በረጅም መቃ መሳይ የቀሰጠ መስታወት እየነፉ ቅርፅ የሚሰጡትን፣ ክራቫት አስተሳሰር የሚያሳዩትን፣ ለአት የሚሸጡትን አረቦች፣ ማንኛውንም ነገር የሚሸጡትን አዟሪዎች፣ ይህን ሁሉ ችላ ብላ እየተሽሎከሎከች ሄደች። ሰውየው በቅርብ ይከተላታል፣ ከዛዚ እኩል አራዳ

ነው። ለጊዜው ልትጠፋበት አልፈለገችም፣ ግን ማምለጡ ቀላል አይሆንም ብላ ተጠነቀቀች። ጥርጥር የለውም ጮሌ ነው።

የተለያዩ ሸቀጦች ከተደረደሩበት ፊት ለፊት ቀጥ ብላ ቆመች። ቆማ ቀረች። እንዳው እንደቆመች ቀረች። ሰውየው ሲደርስባት ቀጥ ብሎ ቆመ። ነጋዴውም ንግግሩን ጀመረ።

"ኮምፓስ ነው 'ምትፈልጊው?" ጠየቀ ረጋ ብሎ "የእጅ ባትሪ? የላስቲክ ጀልባ?"

ዛዚ በጉጉትና በስጋት ተንቀጠቀጠች፣ ምክንያቱም ሰውየው ሊያታልላት መፈለጉን መቶ በመቶ እርግጠኛ አይደለችም። የፈለገችውን የሚናገርላትን አጭር የእንግሊዝኛ ቃል ለመናገር አልደፈረችም፣ ሰውየው ነው የተናገረው።

"ለዚች ልጅ የሚሆን ጅንስ ሱሪ አይኖራችሁም?" ጠየቀ ሰልባጅ ሻጩን "እሱን ነው 'ምትፈልጊው፣ አይደለም?"

"አዎን" አለች ዛዚ

"ጅንስ ሱሪ አለኝ ወይ?" አለ ሻጩ "ከፈለኩ አለኝ። ከፈለግሽም ዝንታለሙን የማያረጅ አለኝ"

"ይሁን" አለ ሰውየው "ግን ልጅቱ ማደግ እንደምትቀጥል ግልፅ ነው። ካንድ አመት በኋላ ልትለብሰው አትችልም ይኖውን። ያን ጊዜ ምን እናረገዋለን?"

"ለታናሽ ወንድሟ ወይ ለታናሽ እህቷ ይሆናል"

"የላትማ"

"ለከርሞ ሊወለድ ይችላል (ሳቅ)"

"በዚህስ አትቀልድ" አለው ሰውየው በቁም ነገር "ምስኪን እናቷ ሞታለች።"

"እእ! ይቅርታ"

ዛዚ ወጠጤውን ላንዳፍታ አየችው፣ ልትገምተው ያህል። እንድያውም ልትመረምረው ፈለገች። ይሄ ጉዳይ ግን ሊቆይላት ይችላል። አሁን ትእግስቷ አልቋል በቁጣ እየተቁነጠነጠች ነው።

"በኔ ልክ አላችሁ?" ጠየቀች

"በሚገባ ነዋ፣ ማድሟዜል"

"እና ዋጋው ስንት ነው?"

አሁንም ዛዚ ናት ጠያቂዋ። በዘልማድ። ቆንቋናነት ሳይሆን፣ ቆጣቢ በመሆንዋ።

ዋጋው ተነገራት ሰውየው ራሱን በአምንታ ነቀነቀ። ውድ የሆነበት አይመስልም። አኳኋኑን ስታይ ነው እንዲህ የመሰላት።

"ለብሼ ልለካው እችላለሁ?" ጠየቀች

ባለሱቁ ግራ ገባው። ‹እቺ ሞኝ ውጫጭ፣ ታላቁ የፊዮር መደብር ውስጥ ያለች መስሏታል!? በቆንጆ ፈገግታ ጥርሶቹን ሁሉ እያሳየ፦›

"አትቸገሪ" አላት "ይህኛውን ላሳይሽ"

ልብሱን ዘርግቶ እፊትዋ ሰቀለው። ዛዚ ለምቦጯን ጣለች። ልትለካው ፈልጋለች

"አይተልቅብኝም?" ጠየቀች በድጋሚ

"ይመልከቱ ማድሟዜል። ከባትዎ በታች አይወርድም። እዩልኝ ይሀን ደሞ፣ እንዴት ጠባብ እንደሆነ። ጥብቅ ማለቱ ሊጠብዎት ትንሽ ነው የቀረው። እርስዎ'ንኳ ቀጠን ያሉ ኖት እንጂ ውፍረት የለቦትም"

ዛዚ ጉሮሮዋ ደረቀ። ጂንስ ሱሪ። ሳይታሰብ። ለመጀመሪያ ጊዜ በፓሪስ ስትዘዋወር የምትለብሰው። አቤት እንዴት አሪፍ ይሆን ነበር!

ሰውየው ድንገት እንደ መፍዘዝ አለ። በዙሪያው የሚደረገውን እያስተዋለ ይመስላል።

ነጋዴው "ይደሰቱበታል፣ በኔ ይሁንቦት። አያልቅም። ዝንታለሙን አያልቅም!" አከረረ

"ነገርኮት'ኮ" አለ ሰውየው በግማሽ ልበና "የማያልቅ መሆኑ ስሜት አይሰጠኝም"

"የማያልቅ መሆኑ'ኮ ቀላል ነገር አይደለም" ቸክ አለ ነጋዴው

"ግን" አለ ሰውየው በድንገት "በእውነቱ፣ ጉዳዩ ገብቶኝ ከሆነ፣ እነዚህ ጂንስ ሱሪዎች የሚመጡት ከአሜሪካኖቹ ነው"

"አዎና!" አቋረጠው የመደብ ሱቅ ነጋዴው

"እንግድያው ምናልባት ሊያስረዱኝ ይችላሉ? አሜሪካኖቹ ሰራዊታቸው ውስጥ ያልደረሱ ውጫዊ ልጃገረዶች ነበሩዋቸው'ንዴ?"

"ሁሉ ነገር ነበራቸው" አለ ሻጩ ቅር ሳይለው

ሰውየው ያመነው አይመስልም

"እሺ ምን?" አለ ሳልሻጅ ሻጩ፣ በአለም ታሪክ ሂደት ምክንያት ጦርነት ለመዋጋት ሁሉም ነገር ያስፈልጋል በሚል ስብከት ሽያጩን ለማከናወን ቆርጦ የተነሳ በመሆኑ።

"ይሄሳ?" ጠየቀ ሰውየው "ስንት ነው ዋጋው?"

ጥቁር መነፅር ነው። ሰውየው ሞከረው።

"ጂንሱን ሱሪ ለሚገዛ ምርቃት ነው" አለ መደብ ነጋዴው፣ ሽያጩ እንደተጠናቀቀ ቆጥሮት።

ዛዚ የሱን ያህል እርግጠኛ አልሆነችም። ‹ምንድነው 'ንግዲህ? ሀሳቡን አይቆርጥም'ንዴ? ምን እየጠበቀ ነው? ምን መስሎታል? ምንድነው 'ሚፈልገው? ባለጌ ሰው መሆን አለበት - ያውም ደካማ አስቀያሚ አይነቱ ሳይሆን፣ እውነተኛው ባለጌ ሰው። መጠንቀቅ፣ መጠንቀቅ፣ መጠንቀቅ ያሻል። እና ምን? ጂንስ ሱሪውን...›

እፎይ! አበቃ። ከፈሉ። ሸቀጡ ተጠቀለለና ፓኬቱን በክንዱ አቅፎ ያዘው — የሰውየው የራሱ ክንድ። ዛዚ ውስጡን መነጫነጭ ጀመረች። አሁንም ገና አላለቀም?

"አሁን" አለ ሰውየው "ሂደን የሚበላ ቢጤ እንፈልግ"

ወደፊት ተራመደ፣ በርግጠኝነት። ዛዚ ተከተለችው፣ ወደ ፓኬቱ እያማተረች። እንደዚህ አስከትሏት አንድ ቡና ቤት ደረሱ። ተቀመጡ። ፓኬቱ ወምበር ላይ ተቀመጠ — ዛዚ ልትደርስበት በማትችል ርቀት "ምን ትፈልጊያለሽ?" ጠየቀ ሰውየው "ትንንሽ ኦይስተር አሳዎች ወይስ ድንች ጥብስ?"

"ሁሉንም" አለች ዛዚ፣ በንዴት ልትቀውስ እየደረሰች

"ለሚጡ አሳዎቹ ይምጡላት" አለ ሰውየው ረጋ ብሎ ለአስተናጋጁ "ለኔ ሙስካዴ ወይን ከሁለት እንኳር ስኳር ጋር።"

ምግቡ እስኪመጣ አልተነጋገሩም። ሰውየው በሰላም ያጨሳል። አሳዎቹ እንደቀረቡላት ዛዚ ጉብ አለችባቸው፣ ስጎው ውስጥ ጠለቀች፣

ጭማቂው ውስጥ ተዘፈቀች፣ ተጨመላለቀች። የኢሊ አይነት ድንጋይ የለበሱት ትንንሾቹ አሳዎች በሀያላን ጠረኖች ጥርሶችዋ ጉልበት ተፈለቀቁ። ልጅቱ ሁሉንም ልትቆረጣጥም ምንም አልቀራትም።

ይሄ ሁሉ ከተጠናቀቀ በኋላ "አሁን ድንች ጥብሱ ቢመጣልኝ አይከፋኝም" አለች። ይሁን አለ ሰውየው። እሱ መጠጡን በትንሹ እየተጉነጨ ያጣጥማል፣ ጉሽ ቫርትረዝ ወይን የሚጠጣ ይመስላል። ድንች ጥብሱ መጣ፣ በሀይል ያቃጥላል። ዛዚ ስትስገበገብ እጇን አቃጠላት፣ አፏን ሳይሆን!

ሁሉ ነገር ሲያልቅ ቢራና ወይን ጭማቂዋን ባንዴ ጨለጠች፣ ሶስቴ በትንሹ አገሳች፣ እና ወንበሯ ላይ ፈልሰስ አለች። ድካም ጨርሷት ገፅታዋ ላይ ጭራቅ ሲመስሉ የሚችሉ ጥላዎች ካለፉ በኋላ ፊትዋ በራ። ‹ቢያንስ ይሄ ተገኝቷል› ስትል በእርካታ አሰበች። ከዚያ፣ ለሰውየው ወዳጅነት የሚገልፅ የሆነ ነገር የመናገር ጊዜው ደርሶ እንደሆነ አሰበች። ግን ምን ትበለው? ብዙ ጥረት የሚከተለውን አስገኘላት፡-

"ብርጭቆዎትን ለመጨረስ ጊዜ ወሰደቦት። አባዬ ቢሆን ይሄን ጊዜ አስሯን ይጨልጣት ነበር።"

"ብዙ ይጠጣሉ 'ንዴ አባትሽ?"

"ይጠጣ ነበር ነው'ሚባለው። ሞቷል"

"ሲሞት በጣም አዘንሽ?"

እጇን እያወራጨች "እንዲህ አይምሰሎት። ያ ሁሉ ምናምን ሲደረግ ለማዘን ጊዜ አላገኘሁም" አለች

"ምን ሲደረግ ኖሯል?"

"አሁን አንድ ግማሽ ብደግም እወዳለሁ፣ ግን ሎሚ ጭማቂ የሌለው፣ የእውነት ቢራ በእውነተኛ ብርጭቆ"

ሰውየው አዘዘላትና የሻይ ማንኪያ ይምጣልኝ አለ። ብርጭቆው ከተጨለጠ በኋላ የቀረውን ስኳር ሊልስ ፈልጎ ነው። ይሄ ስነስርአት በሚፈፀም ጊዜ ዛዚ ከብርጭቆዋ አረፋውን መጠጠች፣ ከዚያ ጥያቄውን መሰሰች፡-

"ጋዜጣ ያነባሉ?"

"አንዳንድ ጊዜ"

"የሳን-ሞንትሮን ሰፈር ልብስ ሰፊዋን ያስታውሳሉ? የባሏን ጭንቅላት'ንኳ በመጥረቢያ የፈለጠችው? ይኸውሎት፣ እማዬ ነበረች:: ባልየው ደም፣ የታወቀ ነው፣ አባዬ ነበረ"

"እ!" አለ ሰውየው

"አያስታውሱም?"

እርግጠኛ የሆነ አይመስልም:: ዛዚ አመረረች::

"ሜርድ! ወሬው ግን በበቂ ተናፍሶ ነበር:: ለዚህ ብላ እማዬ ከፓሪስ አንድ ዝነኛ ጠበቃ አስመጣች፣ እንደኔና እንደርሶ የሚናገር አይነት! አንድ ጆል ነው:: እንዲያም ሆኖ ግን እማዬን ነፃ አወጣት:: ሆነ በቃ! ያውም ተዝናንቶ:: ሰዎቹ ደሞ ለማዬ እንዴት አጨበጨቡላት! በድል አድራጊነት ስሜት ተሸከመዋት ሲሄዱ ምንም አልቀራቸው:: አቤት ያን ቀን የጨፈርነው እማዬን ያሳዘናት አንድ ነገር ብቻ ነበር:: የፓሪሱ ሰውዬ ጠበቃው፣ ቋሊማ ቢሰጡት ክፍያ ነው ብሎ አልቀበልም አለ:: ደግነቱ ዦርዥ ደረሰላት"

"ዦርዥ ማን ነው?"

"አንድ አስቂ ባለ ሉካንዳ ነው፣ የ'ማዬ ውሽማ:: እሱ ነው መጥረቢያውን የሰጣት (ዝምታ) እንጨቷን እንድትቆርጥበ፦:"

ከቢራዋ በትንሹ ፉት አለች፣ በቁንጥ፣ ትንሽ ጣቷን ልትዘረጋ ምንም አልቀራት::

"ይሄ ብቻም አይደል" ቀጠለች "እኔ አሁን ፊቶ የሚያዩኝ ልጇ ችሎቱ ላይ መሰከርኩ፣ ያውም በዝግ ችሎት"

ሰውየው ምንም ምልክት አልሰጠም

"አላመኑኝም 'ንዴ?"

"ኧረ በፍፁም! ልጅ ወላጆቹ ላይ እንዲመሰክር ህግ አይፈቅድም"

"በመጀመሪያ አንዲት ወላጅ ብቻ ነበረች የቀረችኝ:: ከዛ ደግሞ እርሶ ምንም አያውቁም:: ሳን-ሞንትሮ ቢመጡ አንድ ደብተር አሳዮታለሁ፣ ስለኔ የተፃፈውን ሁሉ ከጋዜጣዎቹ ቀድጄ ለጥፌያለሁ:: እንዲያውም፣ እማዬ እስርቤት እያለች፣ ዦርዥ ለክሪስማስ ስጦታዬ "l'Argus de la Press" (የጋዜጣ ፅሁፎች ስብስብ) አንድ አመት ሙሉ እንዲልኩልኝ ገንዘቡን በቅድምያ ከፍሎልኛል:: ይህን ስብስብ ያውቁታል?"

"አላውቀውም" አለ ሰውየው

("ፋራ! ደሞ'ኮ ከኔ ጋር ማውራት ይፈልጋል" አለች ለራሷ)

"ለምን በዝግ ችሎት መሰከርሽ ግን?"

"ለማወቅ ጓጉተዋል፣ እ?"

"ያን ያህልም አይደለም"

"እቤት ከፋቶ!" አለችና ከቢራዋ በትንሹ ተጎነጨች፣ በዝነጣ፣ እንደያው ትንሽ ጣቷን ልትቀስር ምንም አልቀራት። ሰውየው ቅር አላለውም (ዝምታ)

"አይዞት!" አለች ዛዚ በመጨረሻ "እንደዚህ ማኩረፍ አያስፈልግም። ልነግርት ነው'ኮ ታሪኬን"

"እያዳመጥኩ ነው"

"ይኸውሎት፣ እማዬ አባዬን ለአይኗ ማየት አስጠላት። እና አባዬ በሀዘን ብዛት መጠጣት ጀመረ። እቤት ስንት ጠርሙስ ነበር 'ሚጠጣው! እንዲህ በሚሆንበት ሰአት ድመት ራሷ'ንኳ ብትሆን አጠገቡ ባትደርስ ይሻላታል። መዝሙር ውስጥ እንዳለው። ያውቁታል?"

"ገባኝ" አለ ሰውየው

"ጥሩ። እንግድያው ልቀጥል፦ አንድ ቀን፣ እሁድ፣ ኳስ ጨዋታ አይቼ እየተመለስኩ ነው፣ ሳን-ሞንትሮን ስታድየም ከነፍሊዝ ቀይ ኮከብ ጋር ተጋጥመው። በዲቪዝዮን ሲመዘን ቀላል አልነበረም። ስፖርት ስሜት ይሰጦታል እርሶ?"

"እም። ካች ፉትቦል ሲሆን" (ጉልቤዎች እየተገፈታተሩ የሚጫወቱት)

ዛዚ የሰውየውን አነስተኛ ቁመና እያየች አስካካች

"በተመልካችነት ደረጃ?" አለች

"ማንም የሚያውቀው ብልሀት ነው እሱ" መለሰ ሰውየው በእርጋታ ዛዚ እየበገነች ቢራዋን ጨለጠች። ከዚያ ዝም!

"አይዞሽ!" አለ ሰውየው "እንዲህ ማኩረፍ አያስፈልግም። በይ፣ ይልቅስ ታሪክሽን ቀጥይልኝ"

"ታሪኬን መስማት ያሰኞታል?"

"አዎን"

"እንግድያው ቅድም ውሸትዎን ነበር?"

"ይልቅ ቀጥይልኝ"

"ረጋ ይበሉ። ታሪኬን በደምብ እንዲደሰቱበት"

# አምስት

ዛዚ. ለሰውየው ታሪኳን በሚከተለው ስልት ቀጠለች፡-

"አባዬ 'ንግዲህ ቤት ውስጥ ብቻውን ነበረ፣ ብቻውን ሲጠብቅ። 'ሚጠብቀው ልዩ ነገር አልነበረውም፣ እንዲያም ሆኖ ይጠብቅ ነበር። እና ብቻውን ነበር፣ ማለቴ ብቻውን የሆነ ይመስለው ነበር። ይቆዩኝ፣ ስቀጥል ይገባዎታል። ወደቤት ተመለስኩ። ጥምብዝ ብሎ ሰክሮ ነበር ማለት እችላለሁ፣ እና ሲስመኝ ጀመረ አባቴ በመሆኑ። ከዛ ግን ደፋር ማሻሸት አመጣ። ያኔ እኔ አይ አይሆንም አልኩ፣ ምክንያቱም የት እየሄደ እንደሆነ ገብቶኛል፣ ይሄ ወራዳ! ይሄ በፍፁም አይሆንም ስለው፣ ዘለለና በሩን ቆለፈ። ቁልፉን አውጥቶ ኪሱ ከተተና አይኖቹን አንከባለለ፣ አ-አ-አ እያለ። ልክ እንደ ሲኒማ ውስጥ የሚያስገርም ነበር። ‹አበሳሽን ታያለሽ!› ብሎ ጮኸብኝ ‹አበሳሽን ታያለሽ!› እንደውም እነዚህን ቆሻሻ ዛቻዎች ሲወረውርብኝ ትንሽ ትንሽ ለሀጭ ይወርደው ነበር። እና በመጨረሻ እላዬ ላይ ዘለለ። በቀላሉ አመለጥኩት። ሰክሮ ስለነበረ በአፍጢሙ ተደፋ። ተነሳ፣ እንደገና ሊያሳድደኝ ጀመረ። የለየለት ረብሻ ነበር። እና በመጨረሻ ያዘኝ! ባለጌ ዛቻዎቹን እንደገና ጀመረ።

ግን በዚህ ደቂቃ በሩ ቀስ ብሎ ተከፈተ። ምክንያቱን ልንገሮትና፣ እማዬ መውጣቴ ነው፣ ስፓጌቲና የአሳማ ስጋ እገዛለሁ፣ ብላው ነበር። ግን አውነቷን አልነበረም፣ ልብስ ማጠቢያ ክፍል ተደብቃ ነበር። እዛ ነበር እንግዲህ መጥረቢያውን ያስቀመጠችው። እና ቀስ ብላ ተመለሰች። የታወቀ ነው፣ የቁልፍ መያዣዋንም ይዛ ነበር። ቀላል አልነበረችም ነቄዋ ሴትዮ፣ እ?"

"አዎና!" አለ ሰውየው

"እንግዲህ በሩን በቀስታ ከፈተች። እና በእርጋታ ገባች። አባዬ ሳራሱ ስለ ሌላ ነገር እያሰበ ነው፣ ምስኪን ሰውዬ፣ ጨርሶ ምንም አላስተዋለም። እና በንዲህ አይነት ነበር ጭንቅላቱን የተፈለጠው።

ማስተዋል ነበረበታ! እማዬ በደምብ ነበር ያነጣጠረችው። ሲያዩት ደስ የሚል አፊነበረም፣ እንዲያውም ይዘገንናል። የስነ-ልቦና ቀውስ እስኪደርስብኝ'ኮ! ድረስ እና በዚህ አኳኋን ነው ነፃ የተለቀቀችው። እኔም ዦርዥ ነው መጥረቢያውን የሰጣት ብዬ ነበር። ልዩነት አላመጣም። እነሱ 'ንዳሉት ይሄን ያህል ባለጌ የሆነ ባል ሲኖረን አንድ ነገር ብቻ ነው ማድረግ የሚኖርብን፣ እንፈልጠዋለን። ነግሬዎታለሁ"

"‹እንኳን! ደግ አረግሽ!› አሏት። ጉድ ፈላ፣ አይመስሎትም?"

"ሰዎች..." አለ ሰውየው፣ ሰውነቱን እያንቀሳቀሰ

"በኋላ እኔ ላይ ጮኸችብኝ ‹የተረገምሽ ጅል!› ስለ መጥረብያው መናገር ለም'ናባሽ አስፈለገ?" አለችኝ ‹ምን ማለትሽ ነው?› ብዬ መለስኩላት ‹እውነቱን አይደለም 'ንዴ?› ‹የተረገምሽ ጅል!› ብላ ደገመች፣ እና በደስታው መሀል ልትደበድበኝ ፈለገች። ግን ዦርዥ አሳረፋት። ከዛ ደሞ የማታውቃቸው ሰዎች እያጨበጨቡላት በመሆኑ ስለሌላ ነገር ማሰብ አልቻለችም - ለትንሽ ጊዜ ያህል"

"በኋላስ?" ጠየቀ ሰውየው

"በኋላማ ዦርዥ ሆነ በዙርያዬ 'ሚያንዣብበው። ‹ተው'ንጂ› አለችው ‹ሁለታችሁን በተራ ብገድላችሁ ሰው አይስቅም?› ከዛ በኋላ አባረረችው። ለኔ ስትል ውሽማዋን ተወችው። ጥሩ እናት አይደለችም?"

"በጣም!" አለ ሰውየው በተግባቢነት

"ታድያ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሌላ አግኝታለች፣ ለሱ ብላ ነው ፓሪስ የመጣችው። በሄደበት ትከተለዋለች። እኔን ግን ለወጠጤዎቹ ብቻዬን ጥላኝ እንዳትሄድ ብላ (እሱ ደሞ፣ በብዛት አሉ) ለአጎቴ ጋብሪዬል አደራ ትታለት ሄደች። እሱ ካለ ምንም መፍራት አይኖርብሽም" አለችኝ

"ምክንያቱስ?"

"እሱን እኔ አላቅም። ገና ትላንትና ነው የመጣሁት። ነገሮችን ለማገናዘብ ጊዜ አላገኘሁም"

"እና አጎትሽ ጋብሪዬል ስራው ምንድነው?"

"የሌሊት ዘበኛ ነው። ጧት ከስድስት ሰባት ሰዓት በፊት ተነስቶ አያውቅም"

"እና ገና እንቅልፍ ላይ እያለ ነው የወጣሽው?"

"እም"

"እና ቤቱ የት ነው?"

"ብዛ በኩል" (ትጠቁማለች)

"እና ቅድም አግድም ወንበሩ ላይ ያስቀስሽው ለዚህ ነበር?"

ዛዚ አልመሰለችም፡፡ ችክ ማለት ጀምሯል ሰውየው

"የት እንዳለሽ ጠፍቶሽ ነው፣ እ?"

ዛዚ ትከሻዋን ከፍ ዝቅ አደረገች፡፡ እንዴት ያለ ብሽቅ ሰውዬ ነው?!

"ያጉትሽ ጋብሪዬልን አድራሻ ልትነግሪኝ ትችያለሽ?"

ዛዚ ከሚጢጢዋ የውስጥ ድምጿ ጋር በቁም ነገር ተወያየች፡-

‹እንዴ! እኔ ምን ጥልቅ አረገኝ? ምን መስሎታል? የሚገባውን አሁን እንሰጠዋለን፡፡›"

ድንገት ብድግ አለች፣ ፓኬቱን አነሳች፣ ተፈተለከች፡፡ ህዝቡ መሀል ገባች፣ በሰዎቹና በሱቅ መደቦቹ መሀል ተሸሎከሎከች፣ በዝግታ ተራመደች፣ ከዛ ፈጠን አለች፣ ከዛ ቀስ፣ ከዛ ሩጫ፣ ዙሪያ ጥምጥም ሮጠች፣ ከዛ በሌላው አቅጣጫ ሌላ ዙሪያ ጥምጥም፡፡

ይሄ የዋህ ሰውዬ የተሰራውን ጉድ አይቶ ገፅታው ምን እንደሚመስል ታይቷት ለመሳቅ ልትጀምር ስትል፣ ያላገኘችውን ድል መጉናፀፏ ገባት፡፡ ከጉኗ አንድ ሰው ይራመዳል፡፡ ሰውየው መሆኑን ለማወቅ ቀና ማለት አላስፈለጋትም፡፡ ቢሆንም ቀና ብላ አየች፡፡ ማን ያውቃል፣ ምናልባት ሌላ ሰው ሊሆን ይችላል፡፡ አሄሄ! እሱ ራሱ ነው፡፡ ምንም ያልተለመደ ነገር የደረሰበት አይመስልም፣ ዝም ብሎ በሰላም ይራመዳል፡፡

ዛዚ ምንም አላለችም፣ በጭንቅላቷ ዘምበል አለች አካባቢውን ተመለከተች፡፡ ከትርምሱ ወጥተዋል፡፡ አሁን የሚገኙት መካከለኛ ስፋት ያለው ጉዳና ላይ ነው፣ የጅል መልክ ያላቸው ደጋግ ሰዎች፣ አባወራዎች፣ ጡረተኞች፣ ልጆቻቸውን የሚያንሸራሽሩ እናቶች፣ እንዲያው ባጭሩ፣ ልዩ ልዩ ስብጥር ያለው የሰው አይነት

(‹ያለቀለት ጉዳይ ነው› አለች ዛዚ በትንሿ ውስጣዊ ድምፇ፡፡ ወደ ውስጥ ተነፈሰችና ‹ወጠጤ መጣብኝ!› ብላ እየጮኸች ለጦርነት ልትፎክር አፏን ከፈተች፡፡) ሰውየው ግን ምኑም ሞኝ አልነበረ፣ ፓኬቱን በሀይል ነጠቃትና፣ በሁለት እጁ ትከሻዋን ይዞ እየነቀነቃት፣ በሚከተሉት ቃላት ጮኸባት፡-

"አታፍሪም፣ አንቺ ሌባ?! ጆርባዬን አሹሬ እየሸኘና ብድግ አርገሽ ውስድ!"

ቀጥሎ እየከበባቸው ለሄደው ህዝብ አመለከተ፡-

"አቤት! እነዚህ ገና ቤት 'ንኳ ያልሆኑ ልጃገረዶች! እዩልኝ፣ ልትሰርቀኝ! ሞከረች"

እና ፓኬቱን ወደ ላይ አንስቶ አነቃነቀው

"አንድ ጅንስ ሱሪ" ብሎ ጮኸ "ጅንስ ሱሪ! እቺ ውርጋጥ ልትሰርቀኝ ነበር"

"ታዲያ ይሄ አያሳዝንም?" ሲሉ አስተያየት ሰጡ አንዷ ወይዘሮ

"መጥፎ ዘር!" አለች ሌላዋ

"ወራዳነት!" አለች ሶስተኛዋ "እቺን ልጅ የሰው ንብረት የተቀደሰ መሆኑን አላስተማሯትም ማለት ነው?"

ሰውየው ልጅቱ ላይ መጮሁን ቀጠለ

"እህ? ወደ ፖሊስ ጣቢያ ብወስድሽስ? ወደ ፖሊስ ጣቢያ! እስር ቤት ትገቢያለሽ፡፡ ከዛ ወደ ልጆች ፍርድ ቤት ትወሰጂያለሽ፡፡ መደምደሚያው ማረሚያ ቤት ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ይፈረድብሻል፣ የመጨረሻው ትልቅ ቅጣት ይበየንብሻል!"

የተከበረው ከፍተኛ ማህበረ-ሰብ አባል የሆኑ አንዲት ሴት ወይዘሮ ትናንሽ እቃ በውድ ዋጋ ወደሚሸጥበት እቅጣጫ ሲሄዱ ይህንን ጫጫታ ለማስተዋል ስለተገደዱ ቆም አሉ፡፡ የጭቅጭቁን ምክንያት ከከበበው ህዝብ ለማወቅ አጠያየቁና፣ ነገሩ በመከራም ቢሆን ገባቸው፡፡ ይህ የነዝናዛ ልዩ ሰው ጥቁር መነፅሩ፣ ጥቁር ሙስታሹ፣ ክብ ባርኔጣው፣ ለተመልካቾቹ እንግዳ ነገር ባይመስላቸውም፣ ምናልባት እዚህ ልዩ ሰውዬ ውስጥ ሊኖር የሚችለውን ሰው የመሆን ስሜት ሊያገባቡ ሞከሩ፡፡

"መስየ" አሉት "ለዚች ልጅ ይዘኑላት፡፡ ምናልባት መጥፎ ትምህርት ተሰጥቷት ቢሆን፣ የሷ ጥፋት አይሆንም፡፡ ይሄን መጥፎ ድርጊት ለመፈፀም የገፋፋት ራብ ሊሆን ይችላል፡፡ ግራም ነፈሰ ቀኝ፣ አክብደን — እደግመዋለው አክብደን-ልንፈርድባት አይገባም፡፡ እርሶ በፍፁም ተርበው አያውቁም፣ መስዬ?"

"እኔ፣ ማዳም" ሲል መለሰ ሰውየው በምሬት ድምፅ (ዛዚ ለራሷ ‹ሲኒማ ላይ 'ንኳ ከዚህ አብልጠው አይጫወቱትም› አለች) ርቦኝ ያውቃል'ንጂ! እኔ'ኮ የማደጎ ቤት ልጅ ነኝ፣ ማዳም"

ህዝቡ በማጉረምረም ልባዊ ሀዘኔታውን ገለፀ። ሰውየው በዚህ ውጤት በመጠቀም ይህንኑ ህዝብ እየሰነጠቀ ተራመደ ዛዚን እየጐተተ፣ በተውኔት ትራጀዲ ዜማ "ወላጆችሽ ምን እንደሚሉ እናያለና!" እያለ እያዜመ

ከዚያ እልፍ እንዳለ ዝም አለ። በፀጥታ ትንሽ ከተራመዱ በኋላ "እረ! ጃንጥላዬን እዛ ቡና ቤት ረሳሁት" አለ

ለራሱ ነበር የሚያወራው፣ በትንሽ ድምፅ። ዛዚ ግን ከተናገረው ቃላት አንድ ነገር ለማወቅ ጊዜ አልወሰደባትም። ሰውየው የውሸት ፖሊስ የሚመስል ወጠጤ አይደለም፣ እውነ፤ኛ ፖሊስ የሚመስል ወጠጤ ለመምሰል የሚሞክር ፖሊስ ነው። ምክንያቱም ጃንጥላውን ረሳ። ይህ የሀሳቦቿ ቅደም ተከተል ምንም እንከን የሌለው መስሎ ተሰማት። ዛዚ አጎቷን ከእውነተኛ ፖሊስ ጋር ግምባር ለግምባር ማገናኘት ደስ 'ሚል ረቂቅ ብልሀት ሳይሆን አይቀርም የሚል ሀሳብ መጣባት።

ይህን ጉዳይ ከተወያዩበት በኋላ ሰውየው ይሄን ሁሉ አይደለሁም አላትና የት እንደምትኖር ጠየቃት። ሳታምታታ አድራሻዋን ነገረችው።

እንዳለችውም ብልሀቷ ደስ 'ሚል ሆነ። ጋብሪዬል በሩን ከፍቶ "ዛዚ!" ብሎ ሲጮህ፣ ዛዚ ደስ በተሰኘ ድምፅ "አጐቴ፣ ይኸውልህ ሊያናግርህ የሚፈልግ ፖሊስ" ስትለው፣ ግድግዳውን እየተደገፈ ፊቱ በድንጋጤ አረንጓዴ መሰለ። እውነት ነው፣ በመብራቱ ሊሆን ይችላል እዚህ መግቢያ ላይ ጨለማ በመሆኑ። ይሄ ሲሆን ሳለ ሰውየው ምንም ያላስተዋለ መሰለ። ጋብሪዬል "ይግቡ'ንጂ" አለው፣ ስልቱን በሳተ ድምፅ

እና ወደ ምግብ ቤት ሲገቡ ማርሰሊን በደስታ ዘላ ዛዚን አቀፈቻት። ጋብሪዬል "ለመስየ 'ሚጠጣ ቅጅላቸው" አላት። ሰውየው ምንም እንደማይጠጣ ምልክት አሳየ። ጋብሪዬል ግን ሙሉ ሊትሮ ግረናዲን እንዲያመጡለት አዘዘ።

ሰውየው ሳይጋበዝ በገዛ ራሱ ፈቃድ ተቀመጠ። ጋብሪዬል ወይኑን በርከት አርጎ ቀድቶ ትንሽ ቀዝቃዛ ውሀ ጨመረበት

"ሃ ነም መጠጣት አይፈልጉም?"

ጭንቅላቱን እየነቀነቀ እምቢ አለ

ጋብሪዬል ጠጥቶ ብርጭቆውን ጠረጴዛ ላይ አስቀመጠና ሰውየውን እያየ ቆየ። ሰውየው ግን ማውራት ያሰኘው አይመስልም። ዛዚና ማርሰሊን ቆመው በአይነ ቁራኛ ይጠብቋቸዋል።

ረጅም ጊዜ ወስዶ ሊሆን ይችላል።

በመጨረሻ ጋብሪዬል ንግግሩን ለመክፈት እንዲህ አለ፦

"እሺ፣ እንግዲህ እርሶ ፖሊስ ኖት?"

"አረ በፍፁም!" አለ ሰውየው ከልቡ "እኔ ለራሴ አንድ ምስኪን የሳልቫጅ ነጋዴ"

"እንዳታምነው" አለች ዛዚ "አንድ ምስኪን ፖሊስ ነው"

"መግባባት ያስፈልጋል" አለ ጋብሪዬል በለስላሳ ድምፅ

"ሚጡ እየቀለደች ነው" አለ ሰውየው አሁንም በወዳጅነት

"ፔድሮ - ሰርፕለስ በመባል እታወቃለሁ፣ እና ሳልቫጅ ተራ ቅዳሜ፣ እሁድ እና ሰኞ ቢመጡ፣ አገራችን ነፃ ስትወጣ የአሜሪካን ጦር ትቷቸው የሄደውን ልዩ ልዩ ዕቃዎች ለህዝቡ ሳድል ያገኙኛል።"

"እና በነፃ ነው 'ምታድሏቸው?" ጠየቀ ጋብሪዬል ትንሽ ትንሽ ማወቅ እየፈለገ

"ይቀልዳሉ?" አለ ሰውየው "ባጥሬ ገንዘብ ነው 'ንጂ (ዝም አለና) ከአሁኑ ጉዳይ በስተቀር"

"ምን ማለትዎ ነው?" ጠየቀ ጋብሪዬል

"ልጅቱ አንድ ጅንስ ሱሪ ሰርቃኛለች ማለቴ ነው ባጭሩ"

"ይሄ ብቻ ከሆነ" አለ ጋብሪዬል "ትመልስሎታለች"

"ይሄ ቆሻሻ" አለች ዛዚ "መልሶ ነጥቆኛል"

"እንግዲያው" አለ ጋብሪዬል "የርስዎ ቅሬታ ምንድነው?"

"ቅሬታዬ፣ ይኸው ነው"

"ጅንስ ሱሪው የኔ ነው" አለች ዛዚ "እሱ ነው ሰርቆ የወሰደብኝ። አምን። ደሞ ከዚያም በላይ ፖሊስ ነው። ተጠንቀቅ፣ አጎቴ ጋብሪዬል"

ጋብሪዬል አልተረጋጋም፣ ሌላ ብርጭቆ ግረናዲን ቀዳና፦

"ግልፅ አይደለም ይሄ ሁሉ" አለ "ፖሊስ ከሆኑ ለምን እንደሚጮሁብኝ አይገባኝም፣ ካልሆኑ ደሞ ጥያቄዎች ሊያቀርቡልኝ አይችሉም"

"ይቅርታ" አለ ሰውየው "እኔ አይደለሁም የጠየቅኩት፣ እርሶ ነዎት"

"እሱ እውነት ነው" አመነ ጋብሪዬል በአመዛዛኝነት

"ይኸዋ!" አለች ዛዚ "እያወቀ ሲታለልለት ነው"

"አሁን መጠየቅ ምናልባት የኔ ተራ ይሆናል" አለ ሰውየው

"ጠበቃ ሳትይዝ መልስ እንዳትሰጠው" አለች ዛዚ

"ሰላም ስጪኝ" አለ ጋብሪዬል "ማድረግ ያለብኝን እኔ አውቃለሁ"

"እንድትነግረው የሚፈልገውን ሁሉ ያውጣጣሀል"

"ሞኝ እመስላታለሁ" አለ ጋብሪዬል፣ ሰውየውን በወዳጅነት እያናገረው "የዛሬ ልጆች እንዲህ ናቸው"

"ድሮ ቀረ ለጥንታውያኑ ከበሬታ" አለ ሰውየው

"እንዲህ ያለውን ጅልነት መስማት ቂል ያስብላል" አለች የራሷ አስተሳሰብ ያላት ዛዚ "ከዚህ መሄድ ይሻላል"

"እንዲያ ነው!" አለ ሰውየው "የእንስታይ ፆታ አባላት ላጭር ጊዜ ቢወጡልን?"

"እንዴታ!" አለች ዛዚ እያስካካች።

ስትወጣ ሰውየው ወምበር ላይ የረሳውን ፓኬት ቀስ ብላ ወሰደች

"እንግዲህ ሄድን" አለች ማርሰሊን በዝግታ፣ በተራዋ ስትወጣ በሩን በቀስታ ዘጋች

"ታድያስ" አለ ሰውየው (አጭር ዝምታ) "እንደዚህ ነው ትንንሽ ልጆችን በሽርሙጥና እያስተማሩ የሚኖሩት?"

ጋብሪዬል በተውኔታዊ እንቅስቃሴ ቅሬታውን ሊያሰማ አስመሰለ፣ ግን ወድያውኑ መለስ አለ

"እኔ ነኝ፣ መስየ?" አጉተመተመ

"አዎን" መለሰ ሰውየው "እርስዎ ራስዎ! አይደለሁም ሲሉኝ እንዳይሆን"

"አይደለሁም፣ መስየ"

"ደፋር ነዎት። እጅ ከፍንጅ! እቺ ልጅ ሳልቫጅ ገበያ ስትሽረሙጥ ነበር። ሌላው ቢቀር ሰአረቦች እንደማይሸጧት ተስፋ አለኝ"

"ፈፅሞ አላረገውም፣ መስየ"

"ለፖላንድ ሰምችስ?"

"ኧረ የለም፣ መስዩ"

"ለፈረንሳዮችና ለእድለኛ ቱሪስቶች ብቻ ነው?"

"ኧረ ለማንም"

ግረናዲኗ መስራት ጀምራለች። ጋብሪዬል እየነቃ ሄደ።

"እየካዱ ነው ለካ?" ጠየቀ ሰውየው

"እንዴታ!"

ሰውየው ሰይጣናዊ ፈገግታ አሳየ፣ እንደ ሲኒማ ውስጥ

"እሺ ይንገሩኝ፣ የኔ ግድንግድ" አለ እየተንቀባረረ "ህገ ወጥ ስራዎችን የሚያከናውኑት በየትኛው ሙያ ስር እየተደበቁ ነው?"

"ልድገምልዎ፣ ህገ ወጥ ስራ የለኝም"

"ነገር አያብዙ። ሙያ?"

"አርቲስት"

"እርሶ? አርቲስት? ልጅቱ'ኮ የሌሊት ዘበኛ መሆንዎንትን ነግራኛለች"

"እሷ ምንም አታውቅም። ደሞ ለልጆች'ኮ ሁልጊዜ እውነቱን አንነግራቸውም። አይደለም?"

"ለኔ ግን ይነገረኛል?"

"እርስዎ ልጅ አይደሉማ (የወዳጅነት ፈገግታ እያሳየ) ልቅዳልዎት?"

(በእንቅስቃሴ አልጠጣም ይለዋል)

ጋብሪዬል ለራሱ ሌላ ግረናዲን ቀዳ

"እሺ" ቀጠለ ሰውየው "ምን አይነት አርቲስት?"

ጋብሪዬል እንደ ማፈር ብሎ አይኑን ሰበረና፡-

"እንደ ሴት ለብሶ ድንቅ ዳንስ ማሳየት" ሲል መለሰ

# ስድስት

"ምን እየተባባሉ ነው?" ጠየቀች ዛዚ ጅንስ ሱሪውን ለብሳ እያበቃች

"በጣም ቀስ ብለው ነው 'ሚያወሩት" አለች ማርሰሊን ጆሮዋን በሩ ላይ ለጥፋ "ሊገባኝ አልቻለም"

በለስላሳው እየዋሸች ነበር ማርሰሊኗ፣ ሰውየው እንዲህ ሲል ይሰማታል "‹ምክንያቱ ይኸው ነዋ! እርስዎ ቡሽቲ ስለሆኑ ነው እናቷ እቺን ልጅ አደራ የሰጠችዎት›"

ጋብሪዬል መለሰ "እንዴ! አይደለሁም እያልኩዎት አይደለም'ንዴ? እርግጥ ነው፣ የምደንሰው በቡሽቲዎች ናይት ክለብ የሴት ልብስ ለብሼ ነው፣ ይሄ ግን ምንም ማለት አይደለም። ሰውን ለማሳቅ ብቻ ነው። ገባዎት? በግዙፍነቴ ምክንያት በሳቅ ይፈርሳሉ። እኔ ግን ለራሴ ቡሽቲ አይደለሁም፣ ማስረጃውም እቻት ሚስት አለችኝ"

ዛዚ በአድናቆት ምራቋን ዋጠች። ለማማሩ ጂንስ ሱሪዋ በጣም ያምርባታል። ሚጢጢ ቂጧን እየነካካች የመጨረሻ እንደተዋበች ሲታያት በረጅሙ ተነፈሰች፣ በደስታ ተዋጠች

"ምንም አይሰማሽም?" ጠየቀች "እንዲያው ምንም ምንም?"

"ምንም" መለሰች ማርሰሊን በዝግታ፤ አሁንም እየዋሸች፣ ምክንያቱም ሰውየው እየተናገረ ነው "ምንም ማለት አይደለም። ለማንኛውም እናቷ አደራ የሰጠችዎት እንደ ቡሽቲ ስለምትቆጥርዎት መሆኑን ሊክዱ እንዳይሆን"

ጋብሪዬል ማመን ነበረበት "‹እሱም አለበት፣ እሱም አለበት›" ብሎ ነበር ያመነው።

"ስታይኝ እንዴት ነኝ?" አለች ዛዚ "አልዘነጥኩም?"

ማርሰሊን ማዳመጧን ትታ ተመለከተቻት

"ዛሬ ልጃገረዶቹ የሚለብሱት እንደዚህ ነው" አለቻት በለስላሳ ድምፅ

"አልወደድሽውም"

"አዎን እንጂ! ንገሪኝ 'ስቲ፣ ያ ሰውዬ ፓኬቱን ስለወሰድሽበት ምንም እንደማይል እርግጠኛ ነሽ?"

"የራሴ ነው እያልኩሽ አይደለም'ንዴ?! ለብሼው ሲያየኝ ይደነግጣል መቼስ!"

"ወጥቶ ሳይሄድ እንዲያይሽ አስበሻል ማለት ነው?"

"አሁኑኑ መሄዴ ነው" አለች ዛዚ "እዚህ ቁጭ ብዬ አልበሰብስም"

ተሻገረችና በሩ ላይ ጆሮዋን ለጠፈች። ሰውየው ሲናገር ሰማችው "‹እንዴ! ፓኬቱን የት አረኩት?›"

"ስሚ'ንጂ፣ አክስቴ ማርሰሊን" አለች ዛዚ "እየቀለድሽብኝ ነው ወይስ እውነት ደንቁረሻል? የሚባባሉት በደምብ ይሰማል"

"እና ምን እየተባባሉ ነው?"

ዛዚ የአክስቷን የወደፊት ድንቁርና ጉዳይ በጥልቀት መመርመሩን ለጊዜው እየተወች እንደገና ጆሮዋን በሩ እንጨት ላይ ለጠፈች። ሰውየው ይናገራል "‹አሀ! መፈለግ ያሻል፣ ፓኬቱን ያቺ ልጅ እንዳልሰረቀችኝ ተስፋ አለኝ›"

ጋብሪዬል ሀሳብ አቀረበ "ምናልባት ይዘውት አልመጡ 'ንደሆነ?"

"ኧረ ይዤው ነው የመጣሁት" አለ ሰውየው "‹ያቺ ውርጋጥ ሰርቃኝ ይሆንና ጉድ ይፈላል!›"

"አቤት እንዴት ነው 'ሚጮኸው" አለች ዛዚ

"አይሄድም 'ንዴ?" ጠየቀች ማርሰሊን

"አይሄድም" አለች ዛዚ "ይኸውልሽ፣ አሁን ደሞ ስላንቺ ጉዳይ እንዲህ ይለዋል፦ "‹ሳስብበት ምናልባት የርሶ ሚስት ትሆናለች ፓኬቱን የሰረቀችኝ። ምናልባትም ሚስቶትም በበኩሏ ጂንስ ሱሪ መልበስ አምሯት ይሆናል›"

"ኧረ በፍፁም!" አለ ጋብሪዬል

"‹እንዴት ያውቃሉ?›" መለሰ ሰውየው "‹የቡሽቲ ጠባይ ካለው ባል ጋር ስትኖር ሀሳቡ መጥቶላት ሊሆን ይችላል›"

"ቡሽቲ ማለት ምንድነው?" ጠየቀች ዛዚ

"ጂንስ ሱሪ የሚለብስ ወንድ ነው" አለች ማርሰሊን

"እየቀለድሽብኝ ነው" አለች ዛዚ

"ጋብሪዬል ሊያስወጣው ይገባል" አለች ማርሰሊን

"አሪፍ ሀሳብ!" አለች ዛዚ

ከዚያ፣ እየተጠራጠረች

"እስቲ! በዖ እንዲያስወጣው እንንገረው"

"እንግዲህ ታያለሽ"

"ቆይ፣ እኔ መጀመሪያ ልግባ"

በሩን ከፈተችና በጠራ ከፍ ባለ ድምፅ የሚከተሉትን ቃላት ተናገረች፡-

"ታዲያስ አጎቴ ጋብሪዬል፣ ጂንስ ሱሪዬ 'ንዴት ነው?"

"እረ ባክሽ ቶሎ ወደዛ ሂውልቂ!" ጮኸ ጋብሪዬል እየተረበሸ "እሁኑኑ ለሰውየው መልሺላቸው"

"መመለስ የቂጤን አበሳ ይስጠው!" ጮኸች ዛዚ "ምንም ምክንያት አይኖርም፡፡ የራሴ ነው"

"እኔ እርግጠኛ አይደለሁም" አለ ጋብሪዬል በመሰላቸት

"እምን" አለ ሰውየው "በፍጥነት እውልቂ"

"አስወጣው 'ንጂ" አለች ዛዚ ለጋብሪዬል

"ፖሊስ ነው ብለሽ ታስጠነቅቂኝና ከዚያ ደሞ ደብድበው ትይኛለሽ?"

"ፖሊስ በመሆኑ'ኮ ልንፈራው አይገባም" አለች ዛዚ በማጋነን "ባለጌ ነገሮች እንስራ ያለኝ ወራዳ ነው፡፡ ስለዚህ ምንም ፖሊስ ቢሆን ዳኛ ፊት ይቀርባል፡፡ ዳኞቹን ደሞ እኔ አውቃቸዋለሁ፤ ትንንሽ ሴት ልጆች ይወዳሉ፡፡ እና ይሄ ብስብስ ፖሊስ ሞት ይፈረድበትና አንገቱ በጊሎቲን ይቆረጣል - እኔ ደሞ ደሙ ከሚፈስበት ፍሩሽክ የሞላው ቅርጫት ላይ ጭንቅላቱን አነሳና ፊቱ ላይ እተፋበታለሁ፡፡ በል ምን ትሆን?"

ጋብሪዬል ይሄ ሁሉ ጭካኔ እየታየው አይኑን ጨፍኖ ተንቀጠቀጠ፡፡ ወደ ሰውየው ዞረ፡-

"ይሰማሉ" አለው "በሚገባ አስበውበታል? የሚያውቁት ነው፣ ልጆች ሽብርተኛ ናቸው"

"አንቴ ጋብሪዬል" አንጓራች ዛዚ "እምልልሀለሁ፣ ጂንስ ሱሪው የኔ ነው። ልታግዝልኝ ይገባሀል! እንዲህ አይነቱ ብሽቅ፣ ደደብ እና ምናልባትም በትርፉ ሰአት ሌባ የሆነ ምናምንቴ ሲሰድበኝ ዝም ካልከው እማዬ ታዝንብሃለች"

"ሜርድ!" ብላ ጨመረች ለራሷ፣ በትንሿ ውስጣዊ ድምፅ "La Dame aux Came'lias" ፊልም ውስጥ ሚሼል ሞርጋን ከምትጫወተው እኩል ተጫወትኩ'ኮ!

በዚህ አሳዛኝ መማፀን ከልቡ የተነካው ጋብሪዬል መቸገሩን በነዚህ ምጥን ሀረጎች፣ በግማሽ ድምፅ፣ እና ግማሽ ራሱ ተናገረ፡-

"እንዲያም ሆኖ፣ አንድን ፖሊስ ደብድቦ ወደዛ መወርወር ይከብዳል"

ሰውየው አስካካ።

"አቤት እንዴት ያለ ጠማማ አስተሳሰብ ነው ያለዎት!" አለ ጋብሪዬል ፊቱ እየቀላ

"አፍንጫዎ ስር ያለው አይታዎትም'ንዴ?" አለ ሰውየው፣ ሰይጣኑን ሜፊስቶፊሊስን መምሰሉ እየባሰበት "ሽርሙጥና፣ ግብረ-ሰዶም፣ ሌላ ፆታ መስሎ መታየት፣ ይሄ ሁሉ የአስር አመት ፅኑ እስራት ያስከትላል"

ከዚያ ወደ ማርሰሊን ዞረ፡-

"ማዳምሳ? ስለርስዎ አንዳንድ መረጃዎች ብናገኝ እንወዳለን"

"የትኛዎቹን?" ጠየቀች ማርሰሊን በዝግታ

"ጠበቃሽ እያለ ብቻ ነው መናገር" አለች ዛዚ "አንቴ አልሰማኝ አለ፣ አሁን እንዴት እንደተቸገረ ይታይሻል"

"ዝም አትይም?" አለ ሰውየው ዛዚን "አዎን" ቀጠለ "ማዳም በምን ሙያ እንደሚተዳደሩ ሊነግሩኝ ይችላሉ?"

"የቤት እመቤት" መለሰ ጋብሪዬል በአስፈሪ ድምፅ

"ምን ምን ይሰራሉ ማለት ነው?" ጠየቀ ሰውየው በምፀት

ጋብሪዬል ወደ ዛዚ ዞሮ ጠቀሳት፣ የሚከተለውን ለማጣጣም እንድትዘጋጅ

"ምን ምን ይሰራሉ?" አለና ደገመ ጋብሪዬል "ቆሻሻ ይደፋሉ፣ እንዲህ አድርገው"

ሰውየውን በሰደርያው አንቆ አነሳው፣ በወለሉ ላይ እየጐተተ ወስዶ ወደ ታችኛው ደረጃ አሽቀንጠረው፡፡

ድምፅ አሰማ፣ የሚቃትት ድምፅ፡፡ የወረወሩለት ባርኔጣው ተከተለው፣ ከበፊቱ ባነሰ ድምፅ አቃሰተ፡፡

"ወንዳታ!" ጮኸች ዛዚ በደስታ እየዘለለች፡፡ ይህ ሲሆን ሳለ፣ ሰውየው ተነስቶ ሙስታሹንና ጥቁር መነፅሩን ወደ ቦታቸው መለሰና ወደቡና ቤት ገባ

"ምን ይወስዳሉ?" ሲል ጠየቀው ቱራንዶ

"አንድ ማነቃቂያ" አለ ሰውየው

"ብዙ አይነት ማነቃቂያ ነው ያለን"

"ለኔ ሁሉም ያው ነው"

ጥግ ሄዶ ተቀመጠ

"ምን ልሰጠው እችላለሁ?" ብሎ አሰበ ቱራንዶ "አንድ ፌርኒጥ ብራንካ?"

"እሱማ 'ሚጠጣ አይደለም" አለ ሻርል

"ምናልባት ቀምሰኸው አታውቅ ይሆናል፡፡ ያን ያህልም አይከፋም፣ ለሆድ በጣም ጥሩ ነው፡፡ ትንሽ ሞክር"

"እሺ በብርጭቆ ትንሽ ጠብ አርግልኝ" አለ ሻርል በተግባቢነት

ቱራንዶ አብዝቶ ቀዳለት

ሻርል ከንፈሮቹን እየመጠጠ በተመስጦ ቀመሰው፣ ዋጠው፣ ሌላ ተጐነጨ፡፡

"ታዲያስ?" ጠየቀ ቱራንዶ

"ለክፉ አይሰጥም"

"ትንሽ ልጨምርልህ"

ቱራንዶ ብርጭቆውን እንደገና ሞላና ጠርሙሱን ወደ መደርደሪያው መለሰ። አሁንም ሲፈላልግ ቆይቶ ሌላ ነገር አገኘ።

"አርከቡዝ የሚባል መጠጥም አለ" አለ

"እሱ ዘመን አልፎበታል። በኛ ጊዜ የሚያስፈልገን አቶሚክ መጠጥ ነው"

ይህ አባባል የአለምን ታሪክ ስላስታወሳቸው ሁሉም ሳቁ

"እናንተማ" ጮኸ ጋብሪዬል ወደ መጠጥ ቤቱ ጥልቅ እንዳለ "እናንተማ እዚህ ቤት ውስጥ ሳይፋችሁን እየቀጫችሁ ነው። እኔ አለሁ'ንጂ። ወይ ታሪክ! አንድ ወፍራም ግሬናዲን ስጠኝ ውሃ ሳታበዛ። መነቃቃት ያስፈልገኛል። አቤት የሆንኩትን ብታውቁ!"

"እሱን በኋላ ታወራልናለህ" አለ ቱራንዶ እንደማፌር እያለ

"አረ! አንተ ነህ 'ንዴ? እንዴት ዋልክ?" አለው ሻርል ጋብሪዬልን "ምሳ ከኛ ጋር ነህ?"

"ተባብለን አልነበረም'ንዴ?"

"እንዲሁ ላስታውስህ ብዬ ነው"

"ምንም ማስታወስ አያስፈልገኝም"

"እሺ፣ መጋበዜን እያረጋገጥኩልህ ነው እንበል" አለ ሻርል

"ማረጋገጥ አያስፈልግም፣ ምክንያቱም አስቀድመን ተስማምተንበ ታል"

"እንግዲያው እዚሁ ቆይተህ ከኛ ጋር እራት ትበላለህ" ብሎ ደመደመ ሻርል፣ ንግግራቸውን እሱ ሊቋጭ በመፈለጉ።

"ታወራለህ ታወራለህ" አለች ላቨርድዬር "ይህን ብቻ ነው ማድረግ 'ምትችለው"

"ጠጣ 'ንጂ" አለው ቱራንዶ ጋብሪዬልን

ጋብሪዬል ምክሩን ተቀበለ

(በረዥሙ እየተነፈሰ) "ወይ ታሪክ! ዛዚ ከአንድ ሰውዬ ጋር ስትመለስ አይታችኋታል?"

"አዎን" አሉ ቱራንዶዋ ማዶ-ፐቲ-ፒዩ በቁጥብነት

"እኔ ከዚያ በኋላ ነው የመጣሁት" አለ ሻርል

"እና" አለ ጋብሪዬል "ሰውየውን ተመልሶ ሲያልፍ አላያችሁትማ"

"አየውልህ" አለ ቱራንዶ "ሲያልፍ በሚገባ ለማስተዋል ጊዜ አልነበረኝም። ስለዚህ ባየው እንደማውቀው እርግጠኛ አይደለሁም። ግን ምናልባት ከኋላህ እዛ ጥግ የተቀመጠው ሰውዬ ሊሆን ይችላል"

ጋብሪዬል ዞረ። ሰውየው ወንበር ላይ ተቀምጦ ያዘዘውን የሚያነቃ መጠጥ በትዕግስት እየጠበቀ ነው።

"ኧረ በዝጌር ያለህ!" አለ ቱራንዶ "ይቅርታ! የረሳሁዎት መሰለኝ"

"ግድ የለም" አለ ሰውየው በጨዋነት

"ፌርኒፕ-ብራንካ ባመጣልዎት እንዴት ነው?"

"ጥሩ ነው ካሉኝ፣ እሺ".

ይህን ጊዜ ጋብሪዬል ፊቱ እየተለዋወጠ ልፍስፍስ ብሎ ወለሉ ላይ ተጋደመ

"ፌርኒፕ-ብራንካውን ሁለት አርገው" አለ ሻርል ጓደኛውን እያነሳ።

"ሁለት ፌርኒፕ-ብራንካ፣ ሁለት" አለ ቱራንዶ ሳያስብ

ሁኔታዎች ጭንቀት ስለቀሰቀሰበት ብርጭቆዎቹን መሙላት አቅቶት እጁ ይንቀጠቀጣል፣ ቡኒው መጠጥ እየፈሰሰበት፣ ፊሳሹ አጫጭር ቅርንጫፎች እየበቀለ፣ በጠላት ወረራ ጊዜ ከእንጨት የተሰራውን ባንኮኒ ያጎድፈዋል

"እሱን ወዲህ በሉ" አለች ማዶ ፐቲ-ፒዩ፣ ጠርሙሱን ለሜት ካፈዘዘው አለቃዋ እጅ እየነጠቀች።

ቱራንዶ ግምባሩን አበሰ። ሰውየው ዘግይቶ የመጣለትን የሚያነቃቃ መጠጥ በሰላም ፉት ይላል። ሻርል የጋብሪዬልን አፍንጫ አፍኖ መጠጡን ወደ አፉ ሲያንቆረቁርለት በከንፈሩ መጋጠሚያ ትንሽ ትንሽ ተንጠባጠበ።

ጋብሪዬልን ጭንቅላቱን በሀይል ነቀነቀ።

"የሞትክ ጅል" አለው ሻርል በጓደኛ ፍቅር

"ደካማ ሰው!" አለ ሰውየው እየተነቃቃ

"ይሄን ማለት አይገባም" አለ ቱራንዶ "ጠንካራነቱንማ አስመስክ ሯል። በጦርነቱ ጊዜ"

"ምን ሰራና ነው?" ጠየቀ ሰውየው በቸልተኝነት

"የታወጀውን የስራ ግዳጅ ፈፅሟል" ሲል መለሰ ባለመጠጥ ቤቱ፣ ለሁለቱም ፈርኒጥ እየቀዳ።

"አሀ!" አለ ሰውየው ስሜት ሳይሰጠው

"ምናልባት አያስታውሱም ይሆናል" አለ ቱራንዶ "አቤት ሰው እንዴት ቶሎ ይረሳል! በስራ ግዳጅ ወደ ጀርመን አገር መወሰዱን አያስታውሱም?"

"ታዲያ ይሄ'ኮ ጠንካራ ሰው መሆኑን ያሳያል ማለት አይደለም" አለ ሰውየው

"ሲወርድብን የነበረው የቦምብ መአትስ? ረስተውታል'ንዴ" አለ ቱራንዶ

"እና ቦምቦቹን ምን ያረጋቸው ነበረ? ይሄ ፊናንተ ጉልቤ በእጁ ቀልቦ እንዳይፈነዱ ያመክናቸው ነበር?"

"የርሶ ብልጥ ነኝ ባይነት አያስቀንም" አለ ሻርል፣ ንቀቱ ሊመጣበት እየጀመረ

"አትጨቃጨቁ" ሲል አጉረመረመ ጋብሪዬል፣ ያለበት ሁኔታ እየታወቀው

ሆን ብሎ፣ መንገዳገዱ በሚያስታውቅ አካሄድ አንድ ጠረጴዛ አጠገብ እንደመውደቅ አለ — የሰውየው ጠረጴዛ። ጋብሪዬል ከኪሱ ትንሽ ወይን ጠጅ መሀረብ እያወጣ ፊቱን ነካ ነካ ሲያደርግ መጠጥ ቤቱን ጨረቃዊ፣ ቢጫ እና ብርማ መአዛ አወዱት

"እፍ!" አለ ሰውየው "የርሶ ውድ ጨርቅ አገማን"

"እንደገና ሲያስጠሉኝ ሲጀምሩ 'ንዳይሆን ብቻ!" አለ ጋብሪዬል፣ ብስጭት እየታየበት "ይሄ ሽቶ ከታላቁ ከፌዮር መደብር የመጣ ነው'ኮ"

"ሰዎችን ልንረዳቸው ይገባል" አለው ሻርል ጋብሪዬልን "አንዳንድ ባሳገር አለ፣ የረቀቀ ነገር የማይወድለት"

"የረቀቀ? አሁንስ አሳቀኝ!" አለ ሰውየው "ይሄማ እር ማርቀቂያ ፋብሪካ ውስጥ የረቀቀ መሆን አለበት"

"እንዴት ያለ እውነት እንደተናገሩ አልገባዎትም!" ሙሽ ጋብሪዬል በደስታ "ዋነኛ በሆኑት ፋብሪካዎች የሚመረተው ሽቶ ስሙን ከጠሩት ነገር ተለክቶ አነስ ያሉ ጠብታዎች ይጨምሩበታል"

"ኮሎኛስ አይጨምሩበት ይሆን?" ጠየቀ ቁራንደ፣ ወደነዚህ ምርጥ ሰዎች በአይናፋር አድናቆት እየተጠጋ

"አንተ ደሞ አንዳንዴ ደደብ ትሆናለህ" አለ ሻርል "ጋብሪዬል ምንም አይነት ሞኝነት ቢሰማ ምንም ሳይገባው እንደሚደጋገመው ታውቅ የለም 'ንዴ? አንዴ ከሰማው በቂ ነው"

"የምንደግመው'ኮ ብንሰማው ነው" መለሰ ጋብሪዬል "አንተስ ብትሆን፣ በገዛ ራስህ ሞኝ ነገር ፈጥረህ ታውቃለህ?"

"ይሄን ያህል ማብዛትም አያስፈልግም" አለ ሰውየው

"ምኑን ማብዛት?" ጠየቀ ሻርል

ሰውየው በበኩሉ ምንም ሳይመስለው፣ እና በሸር ተነሳስቶ

"እርሶ ሞኝ ነገር ተናግረው አያውቁም?" ሲል ጠየቀ

"ሞኝነቶቹን ለራሱ ለብቻው ይይዛቸዋል" አላቸው ሻርል ለሁለቱ "ማስመሰሉን ይችልበታል"

"ይሄ ሁሉ ለኔ ግልፅ አይደለም" አለ ቁራንዶ

"በምን ነበር የጀመርነው?" ጠየቀ ጋብሪዬል

"ልትናገረው የምትችለውን ሞኝ ነገር ሁሉ አንተ ራስህ እየፈጠርከው አይደለም እያልኩ ነው" አለ ሻርል

"ምን ሞኝ ነገሮች ተናገርኩት?"

"ምን አውቃለሁ? አንተ ምትናገረው ተቆጥሮ አያልቅ!"

"እንደዛ ከሆነ ዘንዳ፣ ብዙ ሳትጨነቅ አንዷን ብትጠቅስልኝ ትችላለህ!"

"እንግዲህ ዲስኩራችሁን እንድትቀጥሉ ልተዋችሁ ነው" አለ ቁራንደ፣ ስለ ጉዳዩ ምንም ስላልገባው

ደምበኞች እየመጡ ነው፣ አንዳንዶቹ የራሳቸውን መብያ ሳህን ይዘዋል

ሳቨርዲዩር የሁልጊዜውን ‹ታውራለህ ታወራለህ፣ ይህን ብቻ ነው ማድረግ የምታውቀው› ስትል ትሰማለች

"እሺ" አለ ጋብሪዬል በሀሳብ እየሄደ "ስለምን ነበር 'ምናወራው?

"ስለምንም" አለ ሰውየው "ምንም"

ጋብሪዬል በተፀየፈ ገፅታ ንቆት ተወውና፡-

"እንግዲያው እዚህ ለምንድነው የመጣሁት?" አለ

"እኔን ፍለጋ ነው የመጣኸው" አለው ሻርል "ታስታውሳለህ? እዥ ቤት ምሳ እንበላና፣ ከዛ ሚጡን ወደ ቱር-ኤፊል እንወስዳታለን"

"እንሂዳ"

ጋብሪዬል ተነስቶ ሰውየውን ቻው ሳይል ሻርልን አስከትሉ ወጣ

ሰውየው ማዶ-ፐቲ-ፒዩን ተጣራ

"እዚሁ እንደጀመርኩ ለምሳ ልቆያ" አለ

ደረጃውን ላይ ጋብሪዬል ቆም ብሉ ሻርልን ጠየቀው፡-

"ምሳ ብንጋብዘው ጨዋነት ነበር፣ አይመስልህም?"

# ሰባት

ግሪዱ ስራ ቦታው ነው ምሳውን 'ሚበላው፣ ደምበኛ ቢመጣ እንዳያጣው በዚህ ሰአት ማንም ደምበኛ እንደማይመጣ ቢያውቅም እስራው ቦታ መብላት ሁለት ጥቅም አለው፡፡ አንደኛ፣ በዚህ ሰአት ማንም አብሮት ስለሌለ ምሳውን በሰላም መብላት ይችላል፡፡ ይህን ምሳ አብዛኛውን ጊዜ ማዶ-ፕቲ-ፒዬ ወደ ሰባት ሰአት ላይ፣ የተመጋቢው ግርግር ካለፈ በኋላ ነው ምታመጣለት፡፡

"ዛሬ ትሪፓ 'ሚሆን መስሎኝ ነበር" አለ ግሪዱ፣ አንድ ማዕዘን ጋ የደበቀውን ሊትሮ ቀይ ወይን ለመሳብ ጉምበስ እያለ

ማዶ-ፕቲ-ፒዬ ትከሻዋን ከፍ ዝቅ እያደረገች "ትሪፓ? የሌለ ተረት ነው!" አለችው፡፡

እሱም አሳምሮ ያውቀዋል'ኮ

"ሰውየውስ?" ጠየቀ ግሪዱ

"በመጨረሻ ምሳውን በላ፡፡ አያወራም" አለች ማዶ-ፕቲ-ፒዬ

"ጥያቄዎች አይጠይቅም?"

"ምንም"

"ቱራንዶሳ፣ አያዋራውም?"

"አይደፍርም"

"ለማወቅ አይፈልግም?"

"ለማወቅ ስለማይፈልግ አይደለም፡፡ መጠየቅ ስለማይደፍር ነው"

"ይሁን"

ግሪዱ በቲ መቀዝቀዝ የጀመረውን የተፋጨ ድንች መጉረስ ጀመረ

"ከዚህ ቀጥሎስ?" ጠየቀች ማዶ-ፕቲ-ፒዩ "ምን ይምጣ? ብሬ ፎርማጆ? ካምቤር ፎርማጆ?"

"ብሬው ጥሩ ነው?" ጠየቃት

"ያን ያህልም አይፈለግም"

"እንግዲያው ከሌላው አምጪልኝ"

ማዶ-ፕቲ-ፒዩ ልትሔድ ስትል ግሪዱ ጥያቄ ወረወረባት፡-

"እሱስ? ምን ተመገበ?"

"ልክ እንደ ርሶ"

ከሱቁ እስከ ላ ካቭ መጠጥ ቤት ያለውን አስር ሜትር በሩጫ አስኮከችው፡፡ መልሱን በዝርዝር ለማምጣት እንደሆን ቆይታ ትደርስበታለች፡፡

እውነትም ደግሞ፣ ግሪዱ የተሰጠውን መረጃ ዝርዝር የጉደለው ሆኖ አግኝቶታል፡፡ ቢሆንም፤ የተላከችውን ፎርማጆ ይዛለት እስክምትመለስ ሀሳቦቹን ለማሰላሰል ያግዘዋል፡፡

"ታዲያስ" ጠየቀ ግሪዱ እንደመጣችለት "ሰውየውስ?"

"ቡና ጠጥቶ እያበቃ ነው"

"እና ምን ያወራል?"

"አሁንም ምንም"

"በደምብ በላ? ወስፋቱ ተከፍቶ በላ?"

"አዎና! በምግብ የመጣ'ክ አይለግምም"

"በመጀመሪያ ምን ወሰደ? ጣፋጩን ሰርዲን ወይስ የቲማቲም ሰላጣ?"

"እንዷርሶ እያልኩት? ልክ እንደርሶ ከዛ በፊት ምንም አልቀመሰም"

"ምን ምን ጠጣ?"

"ቀይ ወይን"

"ሩብ? ግማሽ?"

"ግማሽ፡፡ ጭልጥ አደረገው"

"አሀ!" አለ ግሪዱ የማወቅ ፍላጉቱ በግልጽ እየጨመረ

ፎርማጆውን ከመግመጡ በፊት ጥርሶቹ መሀል የተቀረቀሩትን የስጋ ብጥስጣሾች እያወጣ ጥያቄውን ቀጠለ

"የሸንት ቤት ጉዳይስ? ወደ ሸንት ቤት አልሄደም?"

"አይ!"

"ለውሀ ሸንት 'ንኳ?"

"አልሄደም"

"አሁን ስታይው ፊቱ ምን ይመስላል?"

"ምንም"

ግሪዱ በዘዴ ያዘጋጀውን ስፊ ፎርማጆ በስልት መረሸበት - ማለት ቅራፊውን ወደ ሰሀኑ ዳር ገፋው - ከሁሉ የሚጣፍጠውን በመጨረሻ ለመጉረስ

ማዶ ፑቲ-ፒዩ የሚያረገውን በግማሽ ልብ ትከታተላለች፣ ምንም ሳትቸኩል። ነገር ግን እዚያ ስራው ይጠብቃታል፣ ሂሳብ ስንት ነው የሚሉ ደምበኞች ይኖራሉ፣ ለምሳሌ ያሰውዬ። ሱቁን ተደግፋ ቆየች። እና፣ ግሪዱ እየበላ ማውራት ያለመቻሉን ተገንዝባ የራሷን የግል ችግር መናገር ጀመረች

"ቁም ነገረኛ ሰው ነው" አለች ስለሻርል "ሙያ ያለው ያውም ጥሩ ሙያ። ሆነሉ፣ ታ..ሊ ጥሩ ስራ ነው፣ አይደለም?"

ግሪዱ ሰውነቱን አንቀሳቀሰ

"ያን ያህልም አላረጀ፣ ያን ያህልም ወጣት አይደለም። ሙሉ ጤና። ጉበዝ። ያስቀመጠው ገንዘብም ይኖራል። ሻርል ሁሉ ነገር አለው። አንድ ጉድለት ብቻ አለበት፣ ይኸውም፣ ለፍቅር ከመጠን በላይ ዋጋ ይሰጣል።"

"እዎን" ሲል አመነ ግሪዱ፣ በሁለት ጉርሻ መሀል

"እንዴት ያስቀኛል መሰሉት! የፍቅር ታሪክ ያለበት ጋዜጣ ፈልፍሎ ሲያወጣ፣ ወይም በፍቅር የተሰቃዩ ሴቶች የሚፅፉትን መፅሔቱ ውስጥ ሲያነብ ‹ይህን እንዴት ማመን ይችላሉ?› እለዋለሁ በሀሳብዎ የሚስሏትን ሴት እንዴት እዚያ ጋዜጣ ውስጥ አገኛታለሁ ብለው ማመን ይችላሉ? የዛች አይነት ሴት ከሆነችኮ በነዚህ ጋዜጣዎች መገልገል አያስፈልጋትም። ገዞም ብትል መጥተው ያገኟታል። አይደለም'ንዴ?"

ግሪዱ የመጨረሻውን ጉርሻ እየዋጠ ነው፡፡ ፎርማጆውን ጨረሰ፣ በእርጋታ ብርጭቆ ወይን ቀዳ፣ ጠርሙሱን ቦታው መለሰ፡፡

"እሱስ ለዚህ ጥያቄ ምን መልስ ይሰጣል?" አለ ግሪዱ

"ቁም ነገር የሌለው ምናምን ይናገራል ‹እንቺስ በሀሳብሽ የምትስይውን ወንድ አዘውትረሽ ታገኚዋለሽ?› ይለኛል፡፡ ቀልድ'ኮ አይገባውም"

"ፍቅርሽን መግለፅ ያሻል" አለ ግሪዱ

"እኔም አስቤ ነበር፣ ግን የሚመች አልሆነም፡፡ ለምሳሌ በአንዳንድ አጋጣሚ ደረጃው ላይ አገኘዋለሁ፡፡ ያን ጊዜ እንዴ እንሳሳማለን፣ ዘፈኑ ውስጥ ጫማ ሰፊው እና ፍቅረኛው ሲገናኙ እንደሚሳሳሙት ግን ያን ያህል እንደሚያስፈልግ ልናገረው አልችልም፡፡ ለዚህ የሚሆን ዕውቀት የለኝም (ዝም ብላ ቆይታ) እንደሚገባ እንዳናግረው አንድ ቀን እራት ብጋብዘው ጥሩ ነበር፣ እሺ 'ሚለኝ ይመስሉታል?"

"ለማንኛውም፣ እምቢ ለማለት ጨዋነቱ አይፈቅድለትም"

"ይኸውሎታ! ሻርል'ኮ ሁልጊዜ'ኮ ጨዋ አይደለም"

ግሪዱ ጭንቅላቱን በመነቅነቅ አለመስማማቱን ገለፀ፡፡

አለቃዋ ደጃፉ ላይ ቆሞ ጮኸ፡- "ማዶ!"

እሷም "መጣሁ!" ብላ ጮኸች፣ ቃላቷ አየሩን በተፈለገው ፍጥነትና ሀይል እንዲሰነጥቁት፡፡

"ለማንኛውም" ስትል ቀጠለች ለግሪዱ፣ ረጋ ባለ ድምፅ "እኔ ማወቅ 'ምፈልገው፣ እዛ ጋዜጣ ውስጥ የሚያገኙት ፍቅረኛ በሱ ሀሳብ ከኔ በምን እንደምትሻል ነው፣ ቂጧ የወርቅ ይሆን ወይስ የሀር?"

የቱራንዶ ድጋሚ የጉጉት ወፍ መሳይ ጩኸት ሌላ መላምት ለመሰንዘር አላስቻላትም፡፡

የምሳ ዕቃዎቹን ይዛ ስትሄድ ግሪዱ እንደገና ከጫማዎቹና ከጉዳናው ጋር ብቻውን ቀረ፡፡ ስራውን ወዲያውኑ አልጀመረም፡፡ ለቀኑ ከመደባቸው አምስት ሲጋራዎች አንዷን ጠቀለለ፡፡ በእርጋታ ማጨስ ጀመረ፡፡ ለሚያየው ሰው ስለሆነ ጉዳይ የሚያስብ ሲመስል ሲችል ምንም ያህል አልቀረውም ማለት ይቻላል፡፡ ሲጋራዋ ልታልቅ ትንሽ ሲቀራት አጠፋትና፣ ቁሩዋን "ባልዳስ" እሚባለው በወረራው ዘመን የለመደው መደበቅያ ሳጥን ውስጥ በጥንቃቄ ከሌሎች ቁሩዎች ጋር አኖራት፡፡

ትንሽ ቆይቶ የሆነ ሰው መጣና "ምናልባት የጫማ ማሰሪያ ሲባጎ አይኖርትም ይሆን?" ብሎ ጠየቀው "የኔ ማሰርያ ተበጠሰብኝ"

ግሪዱ ቀና አለ፡፡ በእርግጥ ያ ሰውዬ ነው፣ እና ንግግሩን ቀጠለ

"ከዚህ የባሰ 'ሚያበሽቅ ነገር የለም፣ አይደል?"

"እኔ'ንጃ" አለ ግሪዱ፡፡

"ቢጫ ነው 'ምፈልገው፡፡ ከፈለጉም ቡኒ ይሁን፣ ብቻ ጥቁር አይሁን"

"ምን እንዳለኝ ልፈልግ 'ስቲ" አለ ግረዱ "የጠየቁኝ የከለር አይነት ሁሉ መኖሩን ግን ላረጋግጥሎት አልችልም"

አልተንቀሳቀሰም፣ ሰውየውን መመልከት ለሱ በቂው ሆነ፡፡ ሰውየው ይህን ያላስተዋለ ይመስላል

"ቀስተደመናዊ ህብረቀለም የፈለግኩ ያህል አይርቅም መቸስ" አለ ሰውየው

"ምናዊ ከለር?"

"የቀስተ-ደመና ህብረቀለማት"

"እነሱ ለጊዜው የሉኝም፡፡ ሌሎች ቀለማት ቢሆኑም አይኖሩኝም"

"ጊዜያ ሳጥን ውስጥ ያለውስ፣ የጫማ ማሰርያ አይደለም?"

ግሪዱ ጉርምርምታ እያሰማ፡-

"ይስሙኝ አንቱ፣ ሰው ቤቴ መጥቶ እንደዚህ ሲያነፈንፍ አልወድም"

"እንዲያም ሆኖ ግን እርስዎ የጫማ ማሰርያ መግዛት ለሚያስፈልገው ሰው እምቢ አይሉትም፡፡ ለተራብ ሰው ዳቦ እንደመከልከል ይሆናል"

"ወደዛ! እንዳዝንሎት ለማድረግ አይሞክሩ"

"ጫማ ቢሆንስ? አንድ ጥንድ ጫማ ለመሸጥ እምቢ ይላሉ?"

"አሁን ገና ተሸወዱ" አምባረቀ ግሪዱ

"እንዴት ማለት?"

"ጫማ ሰሪ ነኝ 'ንጂ ጫማ ነጋዴ አይደለሁም። Ne sutor ultra crepidam ጥንታውያኑ 'ንደሚሉት። ላቲን ይገባዎታል ምናልባት? Usque non ascendam እኔም ሰአሊ ነኝ።" Adios amigos et toc.

"ግን በርግጥ ሊገባዎት አይችልም — ካህን አይደሉም፣ ዛፓ ኖት"

"ይህን ደሞ ከየት አመጡት እባኮትን?"

"ዛፓ ወይም አሳዳጅ ወጠጤ"

ሰውየው በሰላማዊ ሁኔታ ትከሻውን ከፍ ዝቅ አደረገና ያን ያህልም ሳያምንበት፣ ያን ያህልም ምሬት ሳያሰማ፦

"ስድብ! ይሄ ሆነ የጠፋችውን ልጅ አግኝቼ ለወላጆቿ ስለመለስኩላቸው የማገኘው ምስጋና። ስድብ"

በረዥሙ ከተነፈሰ በኋላ ጨመረ፦

"ግን እንዴት ያሉ ወላጆች ናቸው!"

ግሬዱ ቂጡን ከወንበሩ እያላቀቀ፣ በሚያስፈራ ድምፅ ጠየቀ፦

"እኮ ወላጆች ምን ጥፋት ተገኘባቸው? በምን ሊወቅሱዋቸው ፈለጉ?"

"አይ! ምንም" (ፈገግ አለ)

"በሏ! ተናገሩ"

"አጎትየው አክስት ነው"

"እውነት አይደለም!" ጮኸ ግሬዱ "እውነት አይደለም' እንዲህ እንዳይሉ ከልክያለሁ"

"ምንም የሚከለክሉኝ ነገር የሉትም፣ ወዳጄ። ከርሶ ትዕዛዝ እምቀበል አይደለሁም"

"ጋብሪዬል ሀቀኛ ነው" አለ ግሬዱ በስነ-ስርአታዊ ድምፅ "ሀቀኛና የተከበረ ዜጋ። ደሞም የሰፈር ሰው ሁሉ ይወደዋል"

"ሁሉ ወደዱሽ!"

"አሁንስ ደበሩኝ ‹እኛ የበላይ ነን› የሚል አስተያየት ልድገምሎት - ጋብሪዬል አይደለም። ይገባዎታል ወይስ አይገባዎትም?"

"ማስረጃ ይስጡኝ"

"እስቸጋሪ አይደለም" አለ ግሪዱ "ባለ ትዳር ነው"

"ይሄ ምንም ማስረጃ አይሆንም" አለ ሰውየው "ለምሳሌ ንጉስ ሄንሪ ሶስተኛን ብንወስድ፣ አግብቶ ነበር"

"እኮ ማንን?" ፈገግ አለ

"ንግስት ሉዊዝ ደ ቮዴሞን"

ግሪዱ አስካካ

"ይቺ ደግዬ ሴት የፍራንስ ንግስት ብትሆንኮ ይታወቅ ነበር"

"ይታወቃል"

"ይህን የሰሙት በቲቪ ነው (የቀፈፈው ገፅታ እያሳየ) "እነሱ የሚናገሩትን ሁሉ እርሶ ያምኑት ይሆን'ንዴ ምናልባት?"

"በመፃህፍት ሁሉ ተፅፎ መገኘቱ አልቀረም"

"በስልክ ማውጫው ጭምር?"

ሰውየው 'ሚመልሰው ጠፋው

"ይኸውሎት" አለ ግሪዱ በየዋህነት

እነዚህንም ባለ ክንፍ ቃላት ቀጠለበት፡-

"ይመኑኝ፣ ተሸቀዳድሞ በሰው መፍረድ አይገባም። ጋብሪዬል ቡሽቲዎች ናይት-ክለብ ውስጥ ሴት መስሎ ይደንሳል፣ እውነት ነው። ግን ያ ምንን ያረጋግጣል፣ እ? ምን ይረጋገጥበታል? ይበሉ ጫማዎን ይስጡኝ፣ ከሩን ሳስገባሎት"

ሰውየው ጫማውን አወለቀና የክር መለወጡ ስነስርአት እስኪፈፀም እንካሳ ሆኖ ቆየ።

"ምንም አያረጋግጥም" አለ ግሪዱ "ገራገሮችን ማስደሰት ካልሆነ በስተቀር። ያን የሚያክል የገደል ቅራፊ ሰውዬ ጥብቅ ያለ አንፀባራቂ ቱታ ለብሶ ማየት ፈገግ ያስብላል፣ ያን የሚያክል ጉልቤ ጠብዚራ በጣም አጭር ሀብረቀለማዊ ሚኒ-ስከርት ለብሶ ሲታይ - ያ ነው ሰዎችን የሚያስቃቸው። ይሄ ብቻም አይደለ። ኦፔራ ላይ እንደሚታየው አይነት ባሌ ዳንሱን ልክ እንደ ሽንቅጠቹ አሳምሮ ሲደንሰው፣ ያኔ ሰዎቹ በሳቅ ይሞታሉ። ሰዎቹ ሞኝ ስለሆኑ ነው ማለት ከፈለጉ፣ እውነት ነው። ግን'ኮ ዞሮ ዞሮ እንደ ማንኛውም ሙያ ነው፣ አይደለም?"

"የትኛው ሙያ?" ብሎ በዚያው ተወው ሰውየው

"የትኛው ሙያ? የትኛው ሙያ?" አለ ግሪዱ፣ የሰውየውን ቅላፄ በምፀት እየደገመ "እርስዎስ? በሙያም ይኮሩበታል?"

ሰውየው አልመለሰም

ሁለቱም ዝም አሉ

"ይኸው" አለ ግሪዱ "ይኸውና ጫማዎ ከነአዲስ ማሰርያው፡፡"

"ስንት ነው 'ምከፍሎት?"

"ምንም" አለ ግሪዱ

ሲቀጥልም

"ለነገሩ፣ እርሶ ብዙም አይናገሩ"

"እንዲህማ ሊሉኝ አይገባም፡፡ እኔ ነኝ እርሶን ፍለጋ የመጣሁት"

"እዎን፣ ግን ጥያቄ ሲጠየቁ መልስ አይሰጡም"

"ለምሳሌ የትኛውን?"

"ጉመን ይወዳሉ ወይ?"

"ከዳቦ ጫፍ ጋር ልበላው እችላለሁ፣ ግን ልቤ እስኪጠፋ አልወደውም"

ግሪዱ ሲያስብ ትንሽ ቆየ፣ ከዚያ በዝቅተኛ ድምፅ "እረ የዝጌር ያለህ!" እያለ ማለ

"ምን ተፈጠረ?" ጠየቀ ሰውየው

"ምን ሲያረጉ ወደዚህ ሰፈር እንደመጡ ለማወቅ ብዙ በከፈልኩ"

"የጠፉች ልጅ ወደ ወላጆቿ ለመመለስ ነው የመጣሁት"

"በመጨረሻኮ ሊያሳምኑኝ ሆነ"

"እና ብዙ ችግር አስከተለብኝ"

"አይ!" አለ ግሪዱ "ያን ያህል ከባድ አይደለም"

"የሳልባድ አገር ንጉስና የሰማያዊ ጂንስ ልእልት ተረት ማለቴ አይደለም፡፡ አለ የባሰ"

ሰውየው ጫማውን መልሶ ማድረግ ጨርሷል

"የባሰ አለ" ሲል ደገመ

"ምን?" ጠየቀ ግሪዱ ለማወቅ ጓጉቶ

"ሚጢጢዋን ወደ ወላጆቿ አደረስኳት። እኔ ራሴ ግን ጠፋሁ"

"እሱ'ንኳ ምንም አይደለም" አለ ግሪዱ ተመልሶ እየተረጋጋ "በግራ በኩል እንደተጠመዘዙ፣ ትንሽ እልፍ ብለው ወደ ሜትሮ መግቢያውን ያገኛሉ። እንደሚያዩት ነው፣ አስቸጋሪ አይደለም"

"እዚያ ላይ አይደለም ነገሩ። እኔ ራሴ ነኝ የጠፋሁብኝ"

"አልገባኝም" አለ ግሪዱ፣ እንደገና በትንሹ እየሰጋ

"ጥያቄዎች ይጠይቁኝ፣ ጥያቄዎች ይጠይቁኝ፣ ያን ጊዜ ይገባዎታል"

"እርሶ ሲጠየቁ አይመልሱማ"

"አቤት ፍርደ ገምድልነት! ልክ ስለ ጉመኑ መልስ ያልሰጠሁ ይመስል"

ግሪዱ ጭንቅላቱን አከከ

"እሺ ለምሳሌ..."

ግን ሲቀጥል አልቻለም፣ አፍሯል

"ይበሉዋ!" አለ ሰውየው እያረረ "ይናገሩ'ንጂ"

ግሪዱ ራሱን ደፍቶ ዝም አለ

ሰውየው አገዘው

"ምናልባት ስሜን ማወቅ ይፈልጋሉ ለምሳሌ"

"አዎ! ስምዎ ማን ነው?"

"ይኸውሉት 'ንግዲህ፣ አላውቀውም"

ግሪዱ ቀና አለ፡-

"እቺ ብልጠት ናት" አለ

"አይደለችም፣ እኔ አላውቀውም"

"እንዴት ሆኖ?"

"እንዴት ሆኖ? እንደዚሁ። በቃሌ አልያዝኩትም" ዝም አለ

"እየቀለዱብኝ ነው" አለ ግሪዱ

"በምን ምክንያት?"

"ሰው የገዛ ስሙን በቃል ማጥናት ያስፈልገዋል 'ንዴ?"

"እርሶ" አለ ሰውየው "ስምዎ ማን ይባላል?"

"ግሪዱ" አለ ግሪዱ፣ ምንም ሳይጠረጥር

"ይኸዋ! ግሪዱ የሚባል ስምዎን በቃል ያውቁታል"

"እውነትም" አጉረመረመ ግሪዱ

"እኔጋ የባሰ ሆኖ ሚገኘው ግን ምንድነው?" ቀጠለ ሰውየው "ከበፊቱን ስም ይኑረኝ አይኑረኝ አለማወቁ ነው"

"ስም?"

"ስም"

"ሊሆን አይችልም" አለ ግሪዱ ድክም እያለው

"ሊሆን ይችላል፣ ይችላል። ምን ማለቴ ነው ሊሆን ይችላል?! እየሆነ ነው እኮ!

"ስም ኖሮት አያውቅማ?"

"እንደዚያ ይመስላል"

"እና ችግር አድርሶቦት አያውቅም?"

"ያን ያህልም አልደረሰብኝም" (ዝም አለ)

ሰውየው ደገመ

"ያን ያህልም አልደረሰብኝም" (ከዛም ዝም)

"እድሜዎስ?" ጠየቀ ግሪዱ በድንገት "ምናልባት እድሜዎትንም አያውቁም ይሆን'ንዴ?"

"የለም" መለሰ ሰውየው "ላውቀው አልችልም"

ግሪዱ የሰውየውን ጭንቅላት በጥንቃቄ አስተዋለ

"እንትን ውስጥ ይኖርዎት ይሆ..."

አቋረጠ

"መናገሩ ያስቸግራል" አጉረመረመ

"አደል? እንግዲህ፣ ስለሙያዬ ሲጠይቁኝ፣ መልሱን የማልሰጥት ምክንያት እምቢ ለማለት በመፈለጌ አይደለም"

"እዎን'ንጂ" ሲል አመነ ግሪዱ እየተጨነቀ

ፍዝዝ ያለ የሞተር ድምፅ ሰምቶ ሰውየው ተገላመጠ፡፡ አንድ አሮጌ ታክሲ ጋብሪዬልና ዛዚን ይዞ አለፈ

"ሽርሽር መሄዳቸው ነው" አለ ሰውየው

ግሪዱ ምንም አልተናገረም፡፡ ሰውየው ራሱ ሽርሽር ቢሄድለት ተመኘ፡፡

"የቀረኝ እርስዎን ማመስገን ብቻ ነው" ሲል ቀጠለ ሰውየው

"ምንም አይደል" አለ ግሪዱ

"ሜትሮውሳ፣ በዚህ በኩል ነው 'ሚገኘው?" (ያመለክታል)

"አዎን፡፡ በዚያ ነው"

"ጠቃሚ መረጃ ነው" አለ ሰውየው "በተለይ ሜትሮው ውስጥ የስራ ማቆም አድማ በመኖሩ."

"ካርታውን ሲመለከቱ ይችላሉ" አለና ግሪዱ የአንዱን ጫማ ሶል በሀይል መቀጥቀጥ ጀመረ

ሰውየውም ሄደ፡፡

# ስምንት

"አቤት ፓሪስ!" ጮኸ ጋብሪዬል፣ በስግብግብ የስሜት ምቅታ። "እይልኝ'ማ ዛዚ" ብሎ በድንገት ጨመረ፣ የሆነ ነገር በርቀት እያመለከተ ኹሬ!! ሜትሮ!!!"

"ሜትሮ?" አለች ግንባሯን ቋጥራ

"የእየሩ ማለቴ ነው" አለ ጋብሪዬል በበጎ መንፈስ

ዛዚ ልታምባርቅበት ስትል እየቀደማት እንደገና ጮኸ

"ያ ደሞ! እዛ ወድያ!! ተመልከቺ!!! ፓንቴዮን!!!!

"ፓንቴዮን አይደለም" አለ ሻርል "ሌዜንቫሊድ ነው"

"እንደገና ልትጀምሩ 'ንዳይሆን ብቻ!" አለች ዛዚ

"አይደለም'ንጂ" አለ ጋብሪዬል "ምናልባት ፓንቴዮን እንዳይሆን?"

"አይደለም" መለሰ ሻርል "ሌዜንቫሊድ ነው"

ጋብሪዬል ወደሱ ዞረና አይን አይኑን እያየ፡-

"እርግጠኛ ነህ?" ብሎ ጠየቀው "ይህን ያህል እርግጠኛ ነህ?"

ሻርል አልመለሰም

"ለመሆኑ ግን፣ ስለምን ነገር እስከ መጨረሻ እርግጠኛ ሆነህ ታውቃለህ?" አበክሮ ጠየቀ ጋብሪዬል

ይህን ጊዜ "አገኘሁት!" ብሎ ጮኸ ሻርል "ይሄ እንትንየው ሌዜንቫሊድ አይደለም፣ ሳከሬ-ከር ነው"

"አንተ ደሞ" አለ ጋብሪዬል እየተደሰተ "ምናልባት ባጋጣሚ ሳከሬ ደደብ ሳትሆን ትቀራለህ?"

"በናንተ እድሜ ኮሚክ ህፃናት መሆናችሁ ድብርት ይለቅብኛል" አለች ዛዚ

ይህን ጊዜ ዙርያውን የተንጣለለውን ከተማ በዝምታ ተመለከቱ ከዚያ ዛዚ ሶስት መቶ ሜትር ከበታቻቸው ያለውን ሁኔታ አስተዋለችና

"ያን ያህልም ከፍታ የለውም" አለች

"ቢሆንም" አለ ሻርል "ሰዎችን ለይቶ ማወቅ ሊያስቸግር ምንም አይቀረው"

"አዎን" አለ ጋብሪዬል አየሩን እያሸተተ "ምንም ያህል አይታዩም፣ ግን ይሸታሉ"

"ሜትሮ ውስጥ ከሚሸተው ግን ያንሳል" አለ ሻርል

"አንተ በሜትሮ አትሄድም'ኮ፡፡ እኔም"

ይህን አሰቃቂ ርእስ ለመሸሽ ፈልጋ ዛዚ አጎቷን፡-

"አታይም'ንዴ" አለችው "ጎምበስ ብለህ እይ'ስቲ፣ ደስ ይላል'ኮ"

ጋብሪዬል ቁልቁል ወደ ጥልቀቶቹ አይኑን ጣል ሊያረግ ሞከረ፡፡

"ሜርድ!" አለ እያፈገፈገ "እንዴት ያዞረኛል መሰላችሁ!"

ግንባሩን አበሰ፣ እናም ሽቶ ታጠነ

"እኔ መውረዴ ነው" ቀጠለ "አልበቃችሁ ከሆነ ታች ምድር ቤት እጠብቃችኋለሁ"

ዛዚና ሻርል ሊያስቀሩት ሳይችሉ ሄደባቸው

"ሀያ አመት ሆነኝ ከዚያ ላይ ሳልወጣ" አለ ሻርል "የሚወጡ ሰዎችን ግን ብዙ ጊዜ በታክሲ አምጥቻለሁ"

ዛዚ ይሄ ጉዳይ ስሜትም አይሰጣት

"እርሶ ብዙ አይስቁም" አለችው "እድሜዎ ስንት ይሆናል?"

"ስንት አመቴ ይመስልሻል?"

"እስቲ፣ ወጣት አይደሉም - ሰላሳ አመት"

"አስራ አምስት ጨምሪበት"

"እንግድያው በጣም ያረጁ አይመስሉም፡፡ አጎቴ ጋብሪዬልሳ?"

"ሰላሳ ሁለት"

"እሱ ግን ከዛ 'ሚበልጥ ይመስላል"

"ለሱ 'ንዳትነግሪው አደራ። ያስለቅሰዋል"

"በምን ምክንያት ያስለቅሰዋል? ሰዶማዊ ነገር ስለሚሰራ?"

"ይህን ደሞ ከየት አመጣሽው?"

"ሰውየው ነው ለአጎቴ ጋብሪዬል ያለው — ያ መልሶ ያመጣኝ ሰውዬ። ሰውየው እንደዚሁ ሲያወራ በዚህ በሰዶማዊነት የተነሳ እስራት ሊከተል ይችላል ሲል ነበረ። ምንድነው 'ሱ?"

"እውነት አይደለም"

"እውነት ነው'ንጂ፣ ሰውየው 'ንደዚህ ብሏል" አለች ዛዚ፣ ከንግግሯ አንዷን 'ንኳ ሊጠራጠሩ በመብቃታቸው እየተማረረች።

"እንደሱ ማለቴ አይደለም። ሰውየው ስለጋብሪዬል የተናገረው እውነት አይደለም ማለቴ ነው"

"ሰዶማዊ መሆኑ? ምን ማለት ነው ግን? ሽቶ ይቀባል ማለት ነው?"

"በቃ! ገብቶሻል"

"የሚያሳስር ነገር የለበትማ"

"በጭራሽ የለበትም"

ለደቂቃ ያህል ሳክሬ - ከር ቤተ ክርስትያንን እያዩ ህልም ውስጥ ገቡ

"እርሶስ" ጠየቀች ዛዚ "ሶዶማዊ ኖት?"

"ሲያዩኝ የቢስኪሌት ፔዳል እመስላለሁ'ንዴ?" (በፈረንሳይኛ "ፔዳል" ቡሽቲ ነው)

"አይ፣ እርሶማ ሹፌር ኖት"

"ይኸዋ! ገብቶሻል"

"ምንም አልገባኝም"

"እንግዲህ ስእል አልሰራልሽ"

"ጥሩ ስዕል ይሰራሉ?"

ሻርል ወደ ሌላ በኩል ዞሮ Gau እና Ballu የተባሉት አርኪቴክቶች ያነፁትን የሴንት - ክሎቲልድ ቤተ ክርስቲያን የደወል ቤቶች በተመስጦ ሲመለከት ቆየ። ከዚያ ሀሳብ አቀረበ

"ብንወርድስ?"

"ንገሩኝ 'ስቲ" አለች ዛዚ ሳትንቀሳቀስ "ለምንድነው ሚስት ያላገቡት?"

"ኑሮ እንዲህ ሆነ"

"ለምን አያገቡም?"

"የምትሆነኝን ሴት አላገኘሁም"

ዛዚ በአድናቆት አፏጨች

"እንደኔ ማንም የለ ባይ ኖታ!" አለች

"እንደዚህ ነው። ንገሪኝ 'ንጂ፣ አንቺ ስታድጊ ልታገቢያቸው 'ምትፈልጊ ሰዎች ብዙ 'ሚኖሩ ይመስልሻል?"

"አንድ ደቂቃ" አለች ዛዚ "ስለምንድነው 'ምናወራው? ስለ ወንዶች ወይስ ስለ ሴቶች?"

"ለኔ ስለሴቶች፣ ላንቺ —"

"የሚያነፃፅሩት አይደለም"

"አልተሳሳትሽም"

"አሪፍ ሰው ኖት እርሶ" አለች ዛዚ "ስለምን እያሰቡ 'ንደሆነ በፍፁም አያውቁም። አድካሚ መሆን አለበት። ለዚህ ነው ብዙውን ጊዜ ያመረሩ 'ሚመስሉት?"

ሻርል ፈገግ ለማለት ተገደደ

"እኔ ብሆንስ፣ ደስ እሉታለሁ?"

"አንቺማ ገና ልጅ ነሽ"

"በአስራ አምስት፣ እንድያውም በአስራ አራት አመታቸው 'ሚያገቡ አሉ። ይህን 'ሚወዱ ወንዶችም አሉ።"

"እንግድያው እኔ ብሆን ደስ አልሽ ነበር?"

"እሱማ አይሆንም" አለች ዛዚ ባጭሩ

እቺን ቀዳማዊት ሀቅ ካጣጣመ በኋላ፣ ሻርል ንግግሩን በነዚህ ቃላት አስኬደ፡-

"ታውቂያለሽ? ላንቺ አድሜ በጣም 'ሚገርሙ ሀሳቦች አሉሽ"

"እሱስ እውነት ነው፣ እንድያውም ከየት እንደማመጣቸው ይገርመኛል"

"እሱንማ እኔ አይደለሁም ልነግርሽ 'ምችለው"

"አንዳንድ ነገር ለምን ይነገራል፣ ሌላ ለምን አይነገርም?"

"መናገር ያለብንን ካልተናገርን ልንግባባ አንችልማ"

"እና እርሶ ለሰው እንዲገቡት መናገር ያለቦትን ሁልጊዜ ይናገሩታል?"

"ሰው ያሰበውን ሁሉ ለመናገር አይገደድም መቸስ፣ ሌላ ነገር መናገር ይችላል"

(ሰውነቱን እያንቀሳቀሰ ዝም ይላል)

"እንዴ! መልስ ይስጡኝ 'ንጂ!"

ይሄ ሁሉ 'ኮ ጥያቄ አይደለም

"በሀሳብ ታ፡ጨንቂኛለሽ፡፡ "ጥያቄ ነው'ንጂ፡፡ ብቻ መልሱን እርሶ 'ማታውቁት ጥያቄ ነው"

"ለመጋባት ገና አልተዘጋጀሁም ይመስለኛል" አለ ሻርል፣ በሀሳብ ተውጦ

"ያውቃሉ?" አለች ዛዚ "ሴቶች ሁሉ እንደኔ ጥያቄ አይጠይቁም'ኮ"

"ሴቶች ሁሉ!? እዩልኝማ፣ ሴቶች ሁሉ! አንቺ'ኮ ገና ውጫጭ ነሽ"

"ይቅርታዎትን! እኔ የሴት ቅርፅ ይዣለሁ"

"ይሁን 'ንግዲህ፡፡ ብልግና ይቅር"

"እዚህ ውስጥ ምንም ብልግና የለውም፡፡ ህይወት ነው"

"ጨዋ ናት ይቺ ህይወት"

ሙስታሹን እየሳበ፣ እንደገና ሳክሬ - ክር ቤተ ክርስትያንን በትኩዜ ተመለከተ

"ህይወትን እናንተ እንደምታውቋት ነው:: በሙያችሁ ብዙ ኮሚክ ነገር 'ሚታይ ይመስላል"

"ይህን ከየት አመጣሽው?"

"Sanctimontronais du dimanche ውስጥ አነበብኩት፣ ዝነኛ የሆኑ የፍቅር ታሪኮች፣ ስነ-ከዋክብት፣ እና ብዙ ሌላ:: እዛ እንደሚሉት ታክሲ ነጂዎች ግብረ-ስጋን በየመልኩና በያይነቱ ያዩታል:: በመጀመሪያ ክፍያውን በገንዘብ ሳይሆን በአይነት ሊፈፅሙ የሚፈልጉ ሴት ተሳፋሪዎች አሉ:: ይሄ ብዙ ጊዜ ይገጥሞታል?"

"እም! ይሁን፣ ይሁን"

"ይህን ብቻ ማለት ነው 'ሚያውቁት? ‹ይሁን፣ ይሁን› ስሜትዎ ሳይታመቅቦት አልቀረም"

"እረ 'ንዴት ያለችው ችኮ ናት!"

"አይዞት አይጨነሁ:: ይልቅስ ኮምፕሌክሶትን ይንገሩኝ"

"ምን የማንሰማው አለ?!"

"ሴቶች ፍርሀት ይለቁበታል እ?"

"እኔ መውረጃ ነው:: ምክንያቱም እያዞረኝ ነው:: ይህን በማየት አይደለም (ያመለክታል) እንዳንቺ አይነቷን ውርጋጥ በማየት ነው"

ይርቃታል:: ትንሽ ቆይቶ እንደገና ከባህር ወለል ጥቂት ሜትር በላይ መሆኑን አየ:: ጋብሪዬል አይኑ ፍዝዝ ብሎ ይጠብቃቸዋል፣ እጆቹ የተከፈቱት ጉልበቶቹ ላይ ናቸው:: ሻርልን ሲያየው የእህቱ ልጅ አብራው የለችም:: ዘለለ፣ ፊቱ በስጋት ተለዋወጠ

"አታረገውም!" ብሎ አምባረቀ

"ወድቃ ቢሆን ትሰማት ነበር" አለ ሻርል፣ በድካም ተሸንፎ እየተቀመጠ

"እሱ'ንኳ ምንም አልነበረም:: ብቻዋን መተው ግን!"

"መውጫው ጋ ታገኛታለህ:: ክንፍ አውጥታ አትበርም"

"እሱስ ነው፣ ግን እስከዚያው ድረስ ምን ያህል ጣጣ ታመጣብኝ ይሆን? (በረዥሙ ተነፈሰና) ምነው አውቄ በነበር!"

ሻርል ስሜት አልሰጠውም

ጋብሪዬል ቱር-ኤፌልን ተመለከተ፣ በጥንቃቄ! ከዚያ በረዥሙ፣ ተናገረ፡-

"የፓሪስን ከተማ ለምን በሴት እንደመሰሉዋት ግራ ይገባኛል። እንዲህ አይነቱ ምናምን ያለባት! ይሄ ሳይታነፅ በፊት ቢሆን'ንኳ ምናልባት። አሁን ግን እስፖርት በማብዛት ወንድ እንደሚሆኑት ሴቶች'ኮ ነው - ይሄ ጋዜጣ ውስጥ የምናነበው ነው (ዝምታ)

"ምነው ዱዳ ሆንክ? ስለዚህ ምን ታስባለህ?"

"እሂሂሂ!" ሻርል እንደ ፈረስ በህመም በረዥሙ አስካካ። እና ራሱን ደፍቶ በሁለት እጁ ይዞ ለቆቃ አሰማ፡-

"እሱም" አለ በሚያለቃቅስ ድምፅ "እሱም... ሁልጊዜ ያ ነገር... ሁሌ ግብረ-ስጋዊነት... የሁልጊዜ ጉዳይ... ሁሌ... ቀንም ይሁን ማታ...፡ አስጠሊታነት... ብስብስነት... እሚያስቡት ስለዚሁ ብቻ!"

ጋብሪዬል በደግነት ትከሻውን ያዘው

"ደስ ያለህ አትመስልም" አለው "እንደዚሁ ምን ተፈጠረ?"

"የእህትህ ልጅ ናታ!... ሸርሙጣ የእህትህ ልጅ..."

"አአ! ተጠንቀቅ" ጮኸ ጋብሪዬል፣ እጁን ወደሰማይ እየዘረጋ "የእህቴ ልጅ የእህቴ ልጅ ናት። ቋንቋህን ለዘብ አድርገው፣ አለዚያ ስለሴት አያትህ በረዥሙ ይነገርሃል"

ሻርል ተስፋ የመቁረጥ ምልክት አሳየ፣ ከዚያ ብድግ ብሎ፡-

"ስማ" አለ "ከዚህ ጉዳይ ወጥቻለሁ። ይቺን ውርጋጥ እንደገና ባላያት እመርጣለሁ። ደህና ሁን" ብሎት ወደታክሲው ተወረወረ

ጋብሪዬል በሩጫ ተከተለው፡-

"እኛስ በምናችን ቤት እንገባለን?"

"በሜትሮ ትሄዳለህ"

"አሪፍ ጅልነቶች አሉት" አጉረመረመ ጋብሪዬል፣ መከተሉን እየተወ ታክሲዋ ርቃ ሄደች

ጋብሪዬል ሲያስብ ከቆየ በኋላ ስለራሱ እነዚህን ሀምሌታዊ ቃላት አነበነበ፡-

"መሆን ወይም አለመሆን፣ ይሄ ነው ችግሩ፡፡ መውጣት መውረድ፣ መሄድ መምጣት፣ ይህን ሁሉ ሜትሮ ሲወስደው ቱር-ኤፌልም ሆነ ፓንቴዮን ቤተ መቅደስ ልብ አይሉትም፡፡ ፓሪስ ዓለም እንጂ ሴላም አይደለች፣ ጋብሪዬል ህልም እንጂ ሴላም አይደለ (ድንቅ!) ዛዚ የህልም ህልም (ወይም የቅዠት) ይሄ ታሪክ ራሱ ደሞ በሙሉ የህልም ህልም፣ የዚያ ህልምም ህልም፣ አንድ ጅል ደራሲ (አ! ይቅርታ!) ታይፕ-ራይተር ላይ የፃፈው"

"እዚያ ማዶ፣ ከሪፐብሊክ አደባባይ አልፎ - ትንሽ እልፍ ብሎ መቃብሮች ላይ በላይ ተከምረዋል፣ ያለፉ የፓሪስ ኗሪዎች፣ በደረጃዎች እየወጡ የወረዱ፣ በመንገዶች የሄዱና የመጡ፣ ሲሄዱ ሲቀጥሉ ሲቀጥሉ የጠፉ! የሀኪም መቆንጠጫ ከማህፀን አመጣቸው፣ የሬሳ መኪና ይወስዳቸዋል፡፡ ቱር ኤፌልም ይዝጋል፣ ፓንቴዮን ቤተመቅደስም ይሰነጣጠቃል፡፡ ጠቅላላ ሂደቱም ከመሬት በታች የሚኖሩትን ሙታን አጥንታቸውን ከዚች ጭንቀት ካጐናፀፋት ከተማ አፈር ጋር ለማዋሀድ ይፈጥናል፡፡

"እኔ ግን እየኖርኩ ነው፣ ማወቄም እዚህ ያቆማል፡፡ ምክንያቱም በኪራይ መኪናው የሸሸው ባለታክሲ፣ ወይም በሶስት መቶ ሜትር ከፍታ አየር ላይ ተንጠልጥላ የቀረችው የእህቴ ልጅ፣ ወይስ ቤት የቀረችው ለስላሳዋ ሚስቴ ማርሰሊን — ስለነሱ በዚች ባሁኗ ደቂቃ የማውቀው "አሌክሳንድሪን" በተባለው የቅኔ ስልት ቢነገር፣ ይህ ብቻ ነው ሙታን ሲሆኑ ምንም አልቀራቸው፣ እዚህ የሌሉ በመሆናቸው

"ይሄ ሁሉ እየሆነም ግን፣ ከነዚህ ከከበቡኝ ደጋግ መላጣ ቱሪስቶች ጭንቅላት በላይ "ይሄ ሁሉ አይሆንም የሚታየኝ ምንድነው?" ጎብኚዎቹ ከበውታል፡፡ ተጨማሪ አስጎብኚ መስሏቸው ወደሚያይበት አቅጣጫ እየተመለከቱ ናቸው፡-

"እና እርስዎ ምን ይታይዎታል?" ጠየቀ አንዳቸው፣ በፈረንሳይኛ ቋንቋ የተካነ፡፡

"አዎን" ድጋፉን ጨመረ ሌላኛው "የሚታይ ምን አለ?"

"በእርግጥ" ቀጠለ አንዱ ሶስተኛ "ምን ማየት ይገባናል?"

"ማን ማየት" ጠየቀ አንዱ አራተኛ "ምን ማየት ማን ማየት ማን ማየት?"

"ምን ማየት?" አስተጋባ ጋብሪዬል "እንዴ!" ሰውነቱን በለስላሳው እያንቀሳቀሰ "ዛዚን ማየት፣ ከትርምሱ ወጥታ ወደኛ ስትመጣ"

ካሜራዎቹ ብልጭ-ድርግም አሉ፣ ከዚያ ሰዉ ልጅቱን አሳለፏት። እያስካካች

"ታድያስ አንቴ፣ ሰዉ ሁሉ እኛን እየፈለገን ነው'ንዴ?"

"እንደምታይው ነው" አለ ጋብሪዬል በደስታ

ዛዚ ትከሻዋን ከፍ ዝቅ አደረገች፣ እና ህዝቡን ተመለከተች። ሻርልን አላየችውም፣ እና አለማየቷን ተናገረች

"ሄዷል" አለ ጋብሪዬል

"ለምን?"

"ለምንም"

"ለምንም። ይሄ መልስ አይደለም"

"እንዴ! ሄደ 'ንደዚሁ"

"ምክንያት ነበረው"

"እንደምታውቂው ነው" ሻርል

"ልትነግረኝ አትፈልግም?"

"ከኔ እኩል ታቂዋለሻ"

አንድ ተጓዥ ጣልቃ ገባና፤ በላቲን (ማለት ምሁራን ብቻ የሚያውቁት እንደ አገራችን ግእዝ በጥንት ዘመን የሞተ ቋንቋ) እየጐረረ "Male bonas horas collocamus si non dicis isti puellae ይሄ ቻርልስ የተባለው ሰው ለምን እንደሄደ" አለ

"አንተ ሚጢጢ ሽማግሌ" አለ ጋብሪዬል "በማያገባህ ጥልቅ አትበል" በእንግሊዝኛ እንዲህ ብሎ አከለበት "እሷ ምክንያቱን ታውቃለች፣ እና በጣም እያስቸገረችኝ ነው"

"እንዴ!" ጮኸች ዛዚ። "ዛሬ ደሞ የውጪዎቹን ቋንቋ መናገር ቻልክበት'ንዴ?"

"ሆን ብዬ ያደረግኩት አይደለም" አለ ጋብሪዬል፣ በትህትና አንገቱን እየደፋ

"በጣም የሚገርም ነው!" አለ አንዱ ጎብኚ

ዛዚ ወደ መነሻ ነጥብዋ ተመለሰች

"ይሄ ሁሉ'ኮ ሻርል ለምን እንደሸሸ አይነግረኝም"

ጋብሪዬል ተበሳጨ

"የሸሸው እሱ የማይገባውን ነገሮች ስለምትናገሪ፣ ለእድሜው የማይነገሩ ነገሮችን"

"እንተሳ አጎቴ ጋብሪዬል፣ ለእድሜህ የማይሆኑ የማይገባህ ነገሮች ብናገር፣ ያኔ ምን ታረጋለህ?"

"ሞክሪኝ" አለ ጋብሪዬል በፍርሀት ድምፅ

"ለምሳሌ" ቀጠለች ዛዚ ያለምህረት "ሶዶማዊ ነህ ወይስ አይደለህም፣ ብዬ ብጠይቅህ ይገባሀል? ለእድሜህ የሚሆን ነው?"

"በጣም የሚገርም ነው" አለ አንድ ተጓዥ (የቅድሙ ራሱ)

"ምስኪን ሻርል" ብሎ በረዥሙ ተነፈሰ ጋብሪዬል

"መልስ ትሰጠኛለህ ወይስ? ሜርድ?!" ጮኸች ዛዚ "ይህን ቃል ታቀዋለህ ወይ - ሶዶማዊ"

"አምና!" አጓራባት ጋብሪዬል "ስእል ልሰራልሽ ትፈልጊያለሽ?"

ህዝቡ ትኩረቱ ተስቦ ድጋፉን ሰጠ፡፡ አንዳንዶች አጨበጨቡ

"እስቲ!" አለች ዛዚ

ይህን ጊዜ ነበር ፌዶር ባላኖቪች ብቅ ያለው

"በሉ እንንቀሳቀስ!" ብሎ ማጓራት ጀመረ "ቶሎ ቶሎ በሉ ወደ መኪናው እንግባ — እኮ ፈጠን!"

"አሁን ወዴት እየሄድን ነው?"

"ወደ ሴንት-ሻፔል" መለሰ ፌዶር ባላኖቪች "የጎቲክ አርት እንቁ፡፡ በሉ 'ንግዲህ እንንቀሳቀስ! እኮ ቶሎ ቶሎ!"

ሰዎቹ ግን አልተንቀሳቀሱም፣ ጋብሪዬልና የእህቱ ልጅ ትኩረታቸውን በጣም ስለሳቡት

"ይኸዋ!" አለችው ዛዚ "ስእሉን እንዳልሰራኸው አየህ አደለም?"

"አቤት እቺ ልጅ ስታታክተኝ!" አለ ጋብሪዬል

ፌዶር ባላኖቪች በልበ ሙሉነት ወደ ቦታው እየተመለሰ ቢያስተውል፣ ተከትለውት የመጡት ሶስት ወይ አራት ቄንጋሮች ብቻ ናቸው።

"እኮ ምንድነው!" አምባረቀ "ዲሲፕሊን የለም'ንዴ? ኧረ ያንተ ያለህ! ምን እያረጉ ነው?"

ክላክሱን አንድ ሁለቴ ነፋ። የተንቀሳቀሰ ሰው የለም። አንድ ፀጥ ያሉ ጉዳናዎችን የሚወድ ፖሊስ ብቻ በክፉ አይን ያየዋል። ፌዶር ባላኖቪች ከእንዲህ አይነቱ የሰው ዘርያ ጋር የቃላት ውዝግብ ውስጥ መግባት ባለመፈለጉ፣ ከጋቢናው ወረደና ተሳፋሪዎቹን እንደዚህ ትእዛዝ ለመጣስ ምን እንደገፋፋቸው ለማወቅ ፈልጎ ተሰብስበው ወደ ቆሙበት ገና ከማየቱ፡-

"እንዴ! ጋብሪዬል ነው ለካ!" ጮኸ "እዚህ ምን እያደረግክ ነው"

ከበውት የቆዩት አድናቂዎች ይህን መገናኘት አይተው በገርነት ሲደነቁ፣ ጋብሪዬል "እሽ! እሽ!" አለው በሹክሹክታ

"ምናልባት" ቀጠለ ፌዶር ባላኖቪች ድምፁን ሳይቀንስ "‹የነጩ ሕሞራ እሚሚት› የሚባለውን ዝነኛ ዳንስህን፣ ብን ያለች አጭር ቀሚስህን ለብሰህ ልታሳያቸው እንዳይሆን?"

ጋብሪዬል ቃል አጥሮት "እሽ! እሽ" አለው እንደገና

"ደግሞስ እቺ ይዘሀት 'ምትንቀራፈፈው ልጅ ማን ናት? ከየት አፈሰካት?"

"የእህቴ ልጅ ናት። እና ቤተሰቤን እንድታከብርልኝ ለማስታወስ ሞክር በእድሜ ገና ልጅ ቢሆኑም"

"ይሄ ደሞ ማን ነው?" አለች ዛዚ

"ጓደኛዬ ነው፣ ፌዶር ባላኖቪች"

"ይኸውልህ - ጋብሪዬል፣ ናይት ክለቦቹን ማስጎብኘት ትቻለሁ። በማህበረሰባችን የማእረግ እርከን እድገት በማሳየቴ፣ አሁን እነዚህን ጆሎች ወደ ሴንት - ሻፔል እየወሰድኩ ነው"

"ምናልባት እኛን ቤታችን ልታደርሰን ትችል ይሆናል። ይሄ የማመላለሻ ምናምን እንትኖች የስራ ማቆም አድማ እያለ፣ የምንፈልገው ቦታ መሄድ አልቻልንም። አይን ቢዞር ታክሲ አይታይም"

"ቤት መግቢያችን'ኮ ገና ነው" አለች ዛዚ

"ለማንኛውም" አለ ፌዶር ባላኖቪች "ሴንት-ሻፔል ሳይዘጋ ቀድመን በዚያ ማለፍ አለብን። ከዚያ በኋላ" አለው ጋብሪዬልን "ቤትህ ላደርስህ እችላለሁ"

"እና ሴንት-ሻፔል ቀልብ ይስባል?" ጠየቀ ጋብሪዬል

"ሴንት-ሻፔል! ሴንት ሻፔል!" እያሉ ቱሪስቶቹ እየጮሁ ጋብሪዬልን በጥድፊያቸው ጠራርገው ወደ ኦቶቡሱ ወሰዱት

"ትኩረታቸውን ስቦታል" አላት ፌዶር ባላኖቪች አብራው ቆማ የቀረችውን ዛዚ

"እኔ በበኩሌ መቸስ" አለች ዛዚ "ከነዚህ ከብቶች ጋር እየተንቀራፈፍኩ እሔዳለሁ ማለት የማይታሰብ ነው።"

"እኔ በበኩሌ" አለ ፌዶር ባላኖቪች "ስሜት አይሰጠኝም"

እና እዚያው ትቷት ሄደ ገብቶ ከመሪው ፊት ተቀመጠና በቶሎ ማይክሮፎኑን አንስቶ

"እንግዲህ እንንቀሳቀስ!" ማይክሮ-ጮኸ፣ በደስታ እየፈነደቀ "እኮ ቶሎ ቶሎ!"

የጋብሪዬል አድናቂዎች እስካሁን አመቻችተውታል። ብቃት ያላቸው የፎቶ ማንሻ መሳሪያዎች እያነጣጠሩ የብርሀኑን መጠን በብቃት ይለካሉ። ይሄ ሁሉ ትኩረት ቢያኩራራውም፣ የእህቱ ልጅ ሁኔታ ግን አስግቶታል። ከፌዶር ባላኖቪች ጠይቆ ተጠቃሽዋ ከከብቶቹ ጋር መምጣት አልፈልግም ማለትዋን በማወቁ፣ የኢንተርናሽናሎቹን አድናቆታዊ ከበባ ጥሶ ወረደ። ወደ ዛዚ ተወረወረና ባንድ እጁ ይዞ ወደ መኪናው እየጐተተ ወሰዳት

ካሜራዎቹ ብልጭ ድርግም አሉ

"አሳመምከኝ!" ጮኸች ዛዚ፣ በንዴት እያበደች

ሆኖም ግን፣ እሷንም ሳይቀር ባለ ከባድ ጎማው ተሽከርካሪ ወደ ሴንት-ሻፔል ይዟቸው ተጓዘ።

# ዘጠኝ

"ክብ መስኮታችሁን በደንብ ክፈቱ" ይላል ፌዶር ባላኖቪች

"በቀኝ በኩል አርሰይ ባቡር ጣቢያ ይታያችኋል። እንደ አርኪቴክቸር በቀላሉ የሚገመት አይደለም፣ እና ስለ ሴንት-ሻፔል ቤተክርስትያን ሊክሳችሁ ይችላል በጊዜ ያልደረሰን እንደሆነ። ምናልባት መዘግየት አይቀርልንም ይሆናል፣ የሁለቱ ወገኖች የስራ ማቆም አድማ ባስከተለው መጨናነቅ የተነሳ"

ጭልም ባለ መደናገር የተሳሰሩት ተጓዦች ሁሉም ባንድነት "እረ!" አሉ።

አክራሪዎቹ ግን በበኩላቸው የድምፅ ማጉያውን ማጉረምረም ልብ ሳይሉት ቀርተው ኖሮ፣ ወምበሮቹ ላይ የኂሊት ተዝናንተው ታላቁን አስጎብኚ ጋብሪዬልን በተመስጦ ያስተውሉታል። ፈገግ አለላቸው፣ እነሱም ተስፋቸውን ጣሉበት!

"ሴንት-ሻፔል" ለማለት ሞከሩ "ሴንት-ሻፔል..."

"አዎን፣ አዎን" አላቸው በወዳጅነት "ሴንት-ሻፔል (ዝም አለ። ከዚያም ግዙፍ ቁመናውን በልስልስ እንቅስቃሴ እያስደነሰ) የጎቲክ ስነ-ጥበብ እንቁ!" ሊቀጥል ሲል

"መዘባረቅ አትጀምር 'ንግዲህ!" ጮኸችበት ዛዚ በምሬት

ተጓዦቹ "ይቀጥሉ! ይቀጥሉ!" ብለው እየጮሁ የሚጢጢዋን ድምፅ አጠፉት "መስማት እንፈልጋለን፣ መስማት እንፈልጋለን!" ሲሉ ጨመሩ፣ ከዝነኛው የቋንቋ መማርያ "ቤርሊትዝ" በታላቅ ጥረት በቃረሙት ፈረንሳይኛ

"እንዳሰኛቸው ሊነዱህ እንዳይሆን ብቻ!" አለች ዛዚ

እጇን ወደ ሱሪው ጨርቅ ላከችና ያለ ምህረት ቁንጥጥ አደረገችው። ከህመሙ የተነሳ በጋብሪዬል ጉንጭ ወፋፍራም እንባዎች ይወርዱ ጀመር። ተጓዦቹ የትላልቅ ከተማ ስሬ ልምድ ቢኖራቸውም፣

አስጎብኚያቸው ሲያለቅስ ማየት ስጋት ላይ ጣላቸው። ይህን እንግዳ ሁኔታ አንዳንዶቹ ከመነሻው እስከ ውጤቱ፣ ሌሎቹ ከውጤቱ እስከ መነሻው በአመክንዮ በመተንተን፣ ሰውየው ጉርሻ ወይም ቲፕ ይገባዋል ብለው ወሰኑ። መዋጮ ተሰበሰበ፣ ምስኪኑ ሰውዬ ጉልበት ላይ አስቀመጡለት። እነሆ፣ የሰውየው ፊትም የቀድሞ ፈገግታውን ለበሰ! (ህመሙ ስለቀረለት እንጂ ገንዘቡ 'ንኳ ያን ያህልም አልነበረም)

"ይሄ ሁሉ በጣም እንግዳ ነገር ሳይሆንባችሁ አይቀርም" አሳቸው ተጓዦቹን ባይን አፋርነት

ለየት ያሉ ሰው መሆናቸው የሚያስታውቅ አንዲት አፍቃሬ - ፈረንሳይ የታዳሚዎችን የጋራ ሀሳብ ገለፁ፦

"ሴንት-ሻፔልሳ?"

"አ!አ!" አለ ጋብሪዬል ሰውነቱን በጣም እያንቀሳቀሰ

"ሊናገር ነው" አሉ ቋንቋ አዋቂዋ ወይዘሮ ሳገራቸው ሰዎች

ይህን ሲሰሙ አንዳንዶቹ ተበረታትተው እየተነሱ ወምበሩ ላይ ቆሙ፣ ከንግግሩም ማይም ዳንስ ከሚመስለው የሰውነት እንቅስቃሴውም ምንም እንዳያመልጣቸው። ጋብሪዬል ራሱን ለማደፋፈር ያህል ጉሮሮውን ጠረገ። ታድያ ዛዚ ቁንጥጫዋን እንደገና ላከችበታ!

"እው-ይ!" አለ ጋብሪዬል በህመም

"ምስኪን ሰውዬ!" ጮሁ ወይዘሮዋ

"ብስብስ ጎደሎ!" አጉረመረመ ጋብሪዬል ጭኑን እያሻሸ

"እኔ'ንደሆንኩ" ጆሮው ውስጥ አንሾካሾከች "እሚቀጥለው ቀይ መብራት ጋ መውረዴ ነው። ያኔ 'ምታረገውን ታረጋለህ፣ አጎቴ"

"በኋላ ወደ ቤታችን እንዴት እንመለሳለን?" አለ ጋብሪዬል እያለቃቀሰ

"መመለስ አላስፈኝም እያልኩህ!"

"እነዚህ ይከተሉናላ!"

"ካልወረድን" አለች ዛዚ በጭካኔ "ሰዶማዊ መሆንክን እነግራቸዋለሁ"

"በመጀመሪያ" አለ ጋብሪዬል በሰላማዊነት "እውነት አይደለም። ከልሌቱ ደሞ፣ የምትናገሪው አይገባቸውም"

"እውነት ካልሆነ 'ንግድያው ለምንድነው ያ ሴት አሳዳጅ ወጠጤ እንደሉ ያለህ?"

"አ! ይቅርታ። አሳዳጅ ወጠጤ ለመሆኑ አንዳችም መረጃ አልተገኘም"

"እና ምን ትፈልጋለህ?"

"ምን እፈልጋለሁ? ተጨባጭ እውነት!" አላት፣ የሆነ ድንቅ ሀሳብ ብልጭ ያለበት እየመሰለ። ይህም ተንገዋቹን ትልቅ ስሜት አሳደረባቸው፣ የዚህ ውይይት ምስጢር እየሳባቸው፣ የቋንቋው ቃላት አስቸጋሪነት ሩቅ ከሆነው አገራቸው ሀሳቦች ጋር ተጣምሮባቸው

"ከዚህም ጋር" ቀጠለ ጋብሪዬል "ያመጣሽው ጊዜ ዛፓ ነው ብለሽን ነበር"

"አዎን። አሁን ግን ሴት አሳዳጅ ወጠጤ መሆኑን እየነገርኩህ ነው። ደሞ አንተ ስለዚህ ነገር ምንም አታቅም"

"አይ! ይቅርታ፣ አውቀዋለሁ" ጭንቅላቱን እየነቀነቀ

"ምን እንደሆነ ታቃለህ?"

"በሚገባ ነዋ!" መለሰ ጋብሪዬል በሽቆ "እንዲህ አይነት ሰዎች ሲጠጉኝ ሲመጡብኝ በተለያየ ጊዜ ወደዛ ገፍትሬያቸው አውቃለሁ። ገረመሽ?"

ዛዚ ሳቅዋን ለቀቀችው

"እኔ በጭራሽ አይገርመኝም" አሉ አፍቃሬ-ፈረንሳይዋ ወይዘሮ፣ ርእሰ-ጉዳዩ የኮምፕሌክስ ምዕራፍ በመሆኑ በግምት ገብቷቸዋል "ኧረ! በጭራሽ!! እንዲያው በጭራሽ!!!"

እና ግዙፉ ሰውዬ ላይ የማሰኑ ትኩረታቸውን ተከሉበት

ጋብሪዬል በእፍረት እየቀላ የከራባቱን ቋጠሮ አስተካከለ፣ ሳይታወቅበት በፈጣን ጣቱ የሱሪው ዚፕ ዝግ መሆኑን አረጋገጠ።

"እሺ" አለች ዛዚ መሳቁ እያበቃት "የውነት ወንድ አጎቴ ነህ። አሁንስ፣ እየሄድን ነው?"

እንደገና ልምዝግ አድርጋ ቆነጠጠችው። ጋብሪዬል "እውይ!" ብሎ እየጮኸ በትንሹ ነጠረ። የታወቀ ነው መቸስ፣ እቺን ጭንጋፍ ሁለት ወይ

ሶስት ጥርሷን በአንድ ቃሪያ ጥፊ ሊያራግፍላት ይችል ነበር። ግን አድናቂዎቹ ምን ይሉታል? በትውስታቸው ውስጥ እድፋም አሰቃቂ የህፃናት ጨፍላቂ ጭራቅ ሆኖ ከሚቀር፣ ዘወር ብሎ ከአይናቸው መጥፋትን መረጠ።

በቂ የተሳፋሪ መጨናነቅ ስላጋጠመው ጋብሪዬል ዛዚን አስከትሎ በዝግታ ሲወርድ፣ በሁኔታው ግራ የተጋቡትን ተጓዦች እሱም እነሱም እየተግባቡ የሚለያዩ የሚያስመስል ገፅታ አሳያቸው — እየሸወዳቸው መሆኑን ለመደበቅ የተሞከረች ግብዝነት፡፡ ነገሩም ተሳካለትና የተጠቀሱት ተጓዦች ሊያስቀሩት በቂ ጥንቃቄ ለመውሰድ ሳይቻላቸው መንገዳቸውን ቀጠሉ

ፌዶር ባላኖቪች እንደሆነ የጋብሪዬል መሄድና መምጣት ምንም ስሜት አይሰጠውም፡፡ እሱ የሚጠነቀቀው በጎቹን ወደ ተፈለገው ስፍራ እንዲያደርሳቸው ብቻ ነው፣ ይኸውም የቦታው ዘበኞች ወደየመጠጥ ቤቱ ሳይበተኑ መሆን አለበት — እንዲህ አይነቱ መዘግየት በፕሮግራማቸው ውስጥ የሚያመጣው ቀውስ ሊስተካከል የማይችል በመሆኑ፡፡ ምክንያቱም በነጋታው ተጓዦቹ ወደ ጂብራልታር ባለጥንታውያን ስገነቶች አምባ ይመርሻሉ፡፡ የጉዞዋቸው ቅደም ተከተል ይኸው ነው፡፡

እስኪርቁ በአይኗ ከተከተለቻቸው በኋላ ዛዚ ትንሽ ሳቀች፡፡ ከዚያ፣ በፍጥነት የአጎቷን ጭን በጨርቁ ዘልቃ በቁንጥጫ ምዝልግ አደረገችው

"ሜርድ! አሁንስ በዛ!" ጋብሪዬል አጓራ "እንዲህ አይነቱ ሜርድ ጨዋታ አያስትም - እስከዛሬ አታቂም?"

"አጎቴ ጋብሪዬል" አለች ዛዚ በሰላማዊ ሁኔታ "አንተ፣ ሰዶማዊ ነህ ወይስ አይደለህም? እስከዛሬ አላስረዳኸኝም፡፡ ሁለተኛ፣ እነዛን ሁሉ ቅድም በውጭ ቋንቋ የተናገርካቸውን ቆንጆዬ ነገሮች ከየት አመጣሀቸው? መልስልኝ"

ጋብሪዬል "ሀሳቦችሽ ከእድሜሽ በጣም ርቀው ነው 'ሚፈጥኑት" አለ በቀዘዝታ

"መልስልኛ ታድያ!" አለችና ቁርጭምጭሚቱ ላይ አንድ እርግጫ አቀመሰችው

ጋብሪዬል ባንድ እግሩ እያነከሰ፣ በስቃይ የሚዘል እያስመሰለ ፊቱ አኮማተረ "እውይ!" ብሎ ጮኸ "ኧረ እውይ!"

"መልሱን ተናገር!" አለች ዛዚ

ባንዱ ማእዘን በኩል ያንዣበቡ የነበሩት ባለፀጋ ወይዘሮ ወደ ልጅቱ እየተጠጉ እነዚህን ቃላት ተናግሯት፡-

"ምነዋ የኔ ቆንጆ፣ ጉዳቸው'ኮ እኚህን ምስኪን ሰውዬ:: ትልቅ ሰዎችን እንደዚህ ማንገላታት አይገባም"

"ትልቅ ሰዎች የቂጤን ጦስ ይስጣቸው!" አለች ዛዚ "ስጠይቀው አልመልስም ይላል"

"ይሄ በቂ ምክንያት አይደለም:: ግፍ መስራት፣ ውዲቱ ልጄ ሆይ፣ በሰዎች ግንኙነት ውስጥ ሁልጊዜ ሊወገድ ይገባዋል:: በአፅንኦት የሚኮነን ነው"

"ኩነኔ የቂጤን አበሳ ይስጠው!" መለሰችላቸው ዛዚ "ስንት ሰአት ነው ያልኮት ይመስል ጥልቅ?!"

"አስር ከሩብ" አሉ ወይዘሮዋ

"እቺን ልጅ አትተዋትም?" አለ ጋብሪዬል አግድም ወንበር ላይ ተቀምጦ

"እርስዎ ደሞ የምትገርሙ አይነት አስተማሪ ነዎት?" አሉ ወይዘሮዋ

"አስተማሪ የቂጤን አበሳ ይስጠው!" ይህ ነበር ዛዚ የሰጠችው አስተያየት

"ማስረጃ ቢፈልግ እሷ ስትናገር ማድመጥ በቂ ነው:: እንዲህ አይነት ስድ ብልግና!" አሉ ወይዘሮዋ፣ በጣም የመንገሽገሽ ምልክቶችን ሁሉ እያሳዩ

"እንግዲህ የገዛ ራስዎትን ቂጥ ይጠብቁ" አለ ጋብሪዬል "ስለማስተማር የገዛ ራሴ ሀሳቦች አሉኝ"

"የትኞቹ?" ጠየቁ ወይዘሮዋ፣ የገዛ ቂጣቸውን አግድም ወምበሩ ላይ ከጋብሪዬል ጐን እያኖሩ

"በመጀመሪያ፣ መግባባት"

ዛዚ በጋብሪዬል በወድያ በኩል ተቀመጠችና በትንሹ ቆንጠጥ አደረገችው

"የኔ ጥያቄሳ?" ውብ ገፅታ እያሳየች ጠየቀች "አይመለስልኝም?"

"ምንም ቢሆን መቸስ ሴን ወንዝ ውስጥ ልወረውራት አልችልም" አጉተመተመ ጋብሪዬል፣ ጭኑን እያሻሸ

"ተግባቢ ይሁኑ" አሉ ወይዘሮዋ፣ ለዛ በተጉናፀፈ ፈገግታ

ዛዚ ወደሳቸው ጎምበስ ብላ እንዲህ አለቻቸው፡-

"ካንቴ ጋር መዳራት አይበቃዎትም'ንዴ? ባለትዳር ነው ገባዎት!"

"ማድሟዜል፣ የእርስዎ አሽሙር ባሏ የሞተባት ሴት ላይ ሊሰነዘር የሚገባው አይደለም"

"ገለል ልበል መሰለኝ" አጉረመረመ ጋብሪዬል

"ከዛ በፊት መልስ ትሰጠኛለህ"

ጋብሪዬል ይሄ ሁሉ ምንም እንደማይመለከተው አይነት እያስመሰለ ሰማዩን ይመለከታል

"መልስ መስጠት የፈለጉ አይመስልም" ሲሉ አመለከቱ፣ ባል የሞተባቸው ወይዘሮ

"ግዴታ ይኖርበታል" አለችና ዛዚ ቁንጥጫ ቃጣችበት

አጎትየው ገና እጇ ሳይነካው ዘለለ፡፡ ሁለቱ እንስት ፆታ አባላት በሁኔታው ሲበዛ ተደሰቱ፡፡ በእድሜ ቀዳሚዋ የሳቃቸውን ከፍ-ዝቅ እየመጠኑ የሚከተለውን ጥያቄ ሰነዘሩ፡-

"እንዲነግሩኝ ምትፈልጊው ምንድነው?"

"ሰዶማዊ ነው ወይስ አይደለም?"

"እሳቸው?" ጠየቁ ወይዘሮዋ (ፀጥ አሉና) "ያለአንዳች ጥርጥር"

"ያለአንዳች ጥርጥር ምን?" ጠየቀ ጋብሪዬል፣ በቂ በሚያስፈራራ ድምፅ

"ሰዶማዊ ነዎት" ነገሩ በጣም ኮሚክ ስለሆነባቸው አስካኩ

"አረ አይሆንም! ይተው'ንጂ" አለና ጋብሪዬል፣ ጀርባቸውን በትንሹ መታ ቢያደርጋቸው ቦርሳቸው ወደቀባቸው

"ከርስዎ ጋር መወያየት አይቻልም" አሉ ባላቸው የሞተባቸው ወይዘሮ፣ አስፋልቱ ላይ የተበተኑትን የተለያዩ እቃዎቻቸውን እየሰበሰቡ

"ለወይዘሮዋ ጨዋነት አላሳየሀቸውም" አለች ዛዚ

"ደግሞ ጥያቄዎችዋን ከመመለስ በመሸሽ አይደለም ልጅቱን ማስተማር የሚቻለው" ሲሉ ጨመሩ ባላቸው የሞተባቸው ወይዘሮ፣ ተመልሰው ከጐኑ እየተቀመጡ

"ከዚህ የበለጠ ተግባቢ መሆን ተገቢ ነው" ብላ ጨመረች ዛዚ በግብዝነት። ጋብሪዬል ጥርሱን አፋጨ

"ይበሉዋ ይናገሩ! ነዎት ወይስ አይደሉም?"

"አይደለሁም! አይደለሁም! እንደገናም አይደለሁም!" አለ ጋብሪዬል በአፅንኦት

"ሁሏም ይህንኑ ነው ምትለው" አሉ ወይዘሮዋ፣ በጭራሽ ሳያምኑት

"በመሰረቱ" አለች ዛዚ "ምን ማለት እንደሆነ ማወቅ ነው የፈለግኩት"

"ምን? ሶዶማዊ ምን እንደሆነ አታውቂም?"

"በግምት አማውቀው ይመስለኛል፣ ግን እሱ እንዲነግረኝ እፈልጋለሁ"

"እና በግምት ምን ይመስልሻል?"

"አጎቴ፣ ትንሿን መሀረብህን አውጣና አሳየን 'ስቲ"

ጋብሪዬል በረዥሙ እየተነፈሰ ታዘዘ። መንገዱ ታወደ

"ገባዎት?" ጠየቀች ዛዚ እየተራቀቀች

እሳቸውም ዝቅ ባለ ድምፅ "በታላቁ የሽቶ አምራሽ በፊዮር ቤት የተመረተ"

"በትክክል!" አለ ጋብሪዬል፣ መሀረቡን ወደ ኪሱ እየመለሰ "የወንድ ሽቶ"

"ይሄ እውነት ነው" አሉ ባላቸው የሞተባቸው ወይዘሮ

ዛዚን ደሞ፦

"እንድያው በፍፁም አንቺ የገመትሽው አይደለም"

ዛዚ ክፉኛ በሽቃ ወደ ጋብሪዬል ዞረች

"እንግድያው ሰውየው ለምን በዚህ ጉዳይ ወነጀለህ?"

"የቱ ሰውዬ?" ጠየቁ ወይዘሮዋ

"አንቺንም ሽረሞጥሽ ብሎ ወነጀለ'ሽኮ" አላት ዛዚን

"የምን መሽርሞጥ?" ጠየቁ ወይዘሮዋ

"እውይ!" ጮኸ ጋብሪዬል

"አታብኸው'ንጂ፣ አንቺዬ" አሉ ወይዘሮዋ፣ ለይስሙላ እያቀማጠሉዋት

"የርሶ ምክር አልተፈለገም" ብላ ዛዚ ጋብሪዬልን እንደገና ቆነጠጠችው

"ልጆች'ኮ በእውነት ደስ የሚሉ ናቸው" አጉረመረመ ጋብሪዬል በግማሽ ልቡና፣ ሰማእትነቱን በፀጋ እየተቀበለ

"እርስዎ ግን ይኸውና እንዲህ እስክትረግጥዎት ድረስ እያስጨነቁዋት ነው። ልጆችን የማይወዱ ከሆነ" አሉ ባለፀጋዋ ወይዘሮ "የማስተማር ሀላፊነቱን ለምን እንደወሰዱ ግር ያሰኛል"

"እሱ" አለ ጋብሪዬል "ራሱን የቻለ ሌላ ታሪክ ነው"

"ይንገሩኝ እስቲ" አሉ ወይዘሮዋ

"አመሰግናለሁ" አለች ዛዚ "ታሪኩን አቀዋለሁ"

"እኔ አላውቀውማ" አሉ መበለትዋ

"እሱ ስሜት አይሰጠንም። ታድያስ አጎቴ፣ መልሱሳ?"

"አይደለሁም አልኩሽ'ኮ፣ አይደለሁም፣ እንደገናም አይደለሁም"

"አንድ ሀሳብ ከያዘች አትለቅም" ሲሉ ወይዘሮዋ፣ አዲስ ያመነጩት የመሰላቸውን አስተያየት ሰነዘሩ

"ሚጢጢዬ፣ የለየላት ቂብ በቅሎ" አለ ጋብሪዬል በርህራሄ

ቀጥለው ወይዘሮዋ ቅድም ከሰጡት አስተያየት ያላነሰ ብልህነት ያለው ቁም ነገር ተናገሩ፡-

"ይችን ልጅ በሚገባ የሚያውቁዋት አይመስሉም። የተለያዩ ተሰጥዎቿን ገና ቀስ በቀስ እያስተዋሉ ነው ያሰኛል"

"ተሰጥዎዎች" የሚለውን ቃል በድምፃቸው የጥቅስ ምልክት አኖሩበት

"ተሰጥዎ የቂጤን አበሳ ይስጠው" አጉተመተመች ዛዚ

"እርስዎስ ነቄ ኖት!" አለ ጋብሪዬል "ደርሰውበታል! ገና ትላንትና ነው የተረከብኩዋት"

"ገባኝ"

"ምኑ ነው የገባዎት?" ጠየቀች ዛዚ በምሬት

"እሳቸውስ ያውቁታል ብለሽ ነው?" አለ ጋብሪዬል፣ ትከሻውን ከፍ - ዝቅ እያደረገ

መበለትዋ ይህን የሚያንኳስስ አይነት ቅንፍ ችላ እያሉ ቀጠሉ፡-

"እና የእህትዎ ልጅ ናት?"

"ትክክል!" መለሰ ጋብሪዬል

"እሱ ደሞ አክስቴ ነው" ቀጠለችበት ዛዚ፣ ቀልዱ አዲስ ስለሆነባት (ይህም የልጅ እድሜዋ ታይቶ ታስፈላት)

"ሄሎ!" ብለው ተጣሩ ሰዎች ከታክሲ እየወረዱ

ከተጓዦቹ መሀል በፌዶር ባላኖቪች አስጎብኚነት እጅግ የተመሰጡት ቱሪስቶች አሉ። ፈረንሳይ - ወዳድዋ ወይዘሮ እየመሩዋቸው ከድንቅ ጉብኝታቸው እንደተመለሱ፣ ከጋይድ ሁሉ ሊቅ የሆነውን አስጎብኚያቸውን በሮማ ዘመን በተተለመችው በፓሪስ ጠመዝማዛ አደናጋሪ ጐዳናዎች ዋሻ አሳድደው ሊይዙት ተነሱ

የደረቀ እሳተ-ገሞራ መስሎ ተደንቅሮ ትራፊክ የሚያጣብበውን ብሽቅ ህንፃ ካለፉ በኋላ፣ በተአምራዊ እድል በእጃቸው አስገቡት። ትልቅ ደስታ እንደተሰማቸው አሳዩ፣ ምክንያቱም ቂም አያውቁም — የሚያስቀይማቸው ምክንያት ሊኖር መቻሉን እንኳ አይጠረጥሩም። በዚህ እንደ ጥንታውያን ፈረንሳውያን ፈረሰኛ ጦረኞች "ሞን ጂ ሴንት-ሻፔል!" የሚል መፈክር እያሰሙ ጋብሪዬልን አፈፍ አድርገው ወደ አቶቡሳቸው ጐተቱት፣ ፍጥነታቸው እያንሳፈፈው ደርሰው አስቀመጡት፣ እና ይህን ሀውልታቸውን ከበቡት፣ ከዚህ ቀጥሎ የሚያጋጥማቸውን የፓሪስ ገፅታ ልቅም አድርጎ በዝርዝሩ ሳያሳያቸው በርሮ እንዳይጠፋ

ዛዚና ሁለቱ ወይዘሮዎች መንገዱ ላይ ቆመው ቀሩ። አቶቡሱ ሲሄድ ፈረንሳይኛ ተናጋሪዋ ወይዘሮ ለዛዚ ላመሉ ያህል ምፀታዊ ተግባብተናል ማስመሰል ምልክት አሳዩዋት። ባላቸው የሞተባቸው ሌላዋ ወይዘሮ በበኩላቸው፣ ለመናገሩ የፈረንሳይኛ ችሎታቸው ባይተናነስም ጩኸታቸውን እያቀለጡት ጮቤ ረገጡ! በዚህ ሰአት እዚያ የነበሩት ዜጋዎች ወንዶቹም ሴቶቹም ከሁካታው ለመራቅ አፈገፈጉ

"እንዲህ መጮህዎትን ከቀጠሉ" አለች ዛዚ ስታስፈራራቸው "ያ ዛፓ ተመልሶ ይመጣቦታል። ዋ!"

"አንቺ የዋህ የሆንሽ ፍጡር" አሉ መበለትዋ "እንዲመጣ ብዬ'ኮ ነው 'ምጮኸው - ኡኡ! ተጠለፍን! ጠላፊዎች ያዙን! ኡኡኡ!"

በመጨረሻም የወፍራሟ ሴትዮ ጩኸት የጠራው ፖሊስ ደረሰ

"ምን ተፈጠረ?" ጠየቀ

"አልጠራኖትም" አለች ዛዚ

"ሆኖም ግን ጩኸት አሰምታችኋል" አለ ፖሊስየው

"አንድ ሰውዬ ተጠልፎ! ተወስዷል!" አሉ ወይዘሮዋ በስሜት እያለከለኩ "ያውም ቆንጆ ሰውዬ!"

"እረ የግዜር ያለህ" አጉረመረመ ፖሊስየው፣ ለአደን እየተነሳሳ

"አክስቴ ናት" አለች ዛዚ

"እሱስ?" ጠየቀ ፖሊስየው

"እሱ ነው አክስቴ አልኩህ'ኮ፣ አይገባህም'ንዴ"

ባላቸው ወደሞተባቸው አመለከተ

"እሳቸውስ ታድያ?"

"እሳቸው? ምንም አይደሉም"

ፖሊስየው የሁኔታዎችን ፍሬ-ነገር ለመገንዘብ ያህል ፀጥ አለ። ወይዘሮዋ ዛዚያዊ ወኔ ቢነሸጣቸው፣ ደፋር እቅድ ብልጭ አለባቸው

."ጠላፊዎቹን እናሳድዳቸው" አሉ "እና ሴንት-ሻፔል ስንደርስ እንታደገዋለን"

"ሩቅ ያስኬዳል" አለ ፖሊሱ በንኡስ ከበርቴነቱ ስልት "እኔ'ኮ ያገር አቋራጭ እሽቅድምድም ሻምፒዮን አይደለሁም"

"እኔ ወጪውን ችዬ በታክሲ ደርሰንበት እርስዎ የፖሊስ ጀብዱ ሲሰሩ አይታይዎትም?!"

"እውነታቸውን ነው" አለች ቆጣቢዋ "እኔ እንደመሰለኝ ፋራ አይደሉም'ለካ!"

"አመሰግናለሁ" አሉዋት ወይዘሮዋ ደስ እያላቸው

"ምንም አይደል" አለች ዛዚ

"ቢሆንም ያስደስታል" አበክረው ጨመሩ ወይዘሮዋ

"ይሁን እሺ." አለች ዛዚ በትህትና

"እነዚህን ሁሉ ሰላምታዎቻችሁን ከተለዋወጣችሁ በኋላ —" ሲል ፖሊሱ

ወይዘሮዋ እያቋረጡት "እርስዎ አልተጠየቁም" ሲሉት

"ይኸዋ የሴት ነገር!" ጮኸ ፖሊሱ "እንዴት ማለት እባኮትን? ምንም እንዳረግላችሁ · አልጠየቃችሁኝም? አምን ቀላል ነገር ነው የጠየቃችሁኝ፣ ይኸውም ሲያስኘው ድንገት ቅስፍ አረጎ የሚይዘኝን ኢምንት የጉን ውጋት ከምንም እንዳልቆጥረው! ይሄ ለናንተ ምንም ካልሆነ፣ እንግድያው እኔ ስለምኑም ምኑም አይገባኝም!"

ናፍቆት በሚታይበት ቅሬታ እንዲህ ጨመረ፡-

"የምናውቃቸው ቃላት ለካ ዛሬ የድሮ ትርጉማቸውን አጥተዋል!" ብሎ የጫማውን ሹል እየተመለከተ በረዥሙ ተነፈሰ

"ይሄ ሁሉ'ኮ አንቴን አይመልስልኝም" አለች ዛዚ "እንደገና ጠፍታ ሸሸች ይሉኛል። አይሆንም! በጭራሽ አይሆንም!"

"አትስጊ ልጄዋ" አሉ ባልቴትዋ "አብሬሽ ቆይቼ ቀና አስተሳሰብ የለሽና ጥፋት የሌለብሽ መሆንሽን እመሰክራለሁ"

"ምንም ጥፋት የሌለበት ሰው'ኮ" አለ ፖሊሱ "ማንም አያስፈልገውም"

"ይሄ ወራዳ!" አለች ዛዚ "በጣም አይዞሽ-አይዞሽ እያለ ሲመጣብኝ ይታየኛል። ሁሉም ያው ናቸው"

"አንቺ ምስኪን ልጅ፣ ይህን ያህል ታውቂያቸዋለሽ ማለት ነው?"

"እሱን አቃንሱብኝ፣ አንቱ ምስኪን እመቤት" መለሰች ዛዚ እየተቅለሰለሰች "ይታይዎት እንግዲህ፣ እማዬ የአባዬን ጭንቅላት በመጥረብያ ፈለጠችው። ታድያ ከዚያ ወድያ ፖሊሶች አይቼ እንደሆን ቀድሜ እሰራላቸዋለሁ"

"ወይ ጉድ!" አለ ፖሊሱ

"የፖሊሶቹ'ንኳ ምንም ያህል አይደለም" አለች ዛዚ "ዳኞቹ አሉ'ንጂ። እነሱማ..."

"ሁሉም ክብት ናቸው" አለ ፖሊሱ ያለ አንዳች ማዳላት

"ፖሊሶቹን እንደ ዳኞቹ — እንጃ! ስራሁላቸዋ! እንዲች! (ጣቶቿ መሀል ፉጨት እየፈጠረች)"

ባልቴትየዋ በአድናቆት ያስተውሏታል

"እኔንስ?" አለ ፖሊስየው "እንዴት አድርገሽ ነው 'ምትስሪልኝ?"

ዛዚ መረመረችው

"እርሶን" አለች "ከዚህ በፊት የሆነ ቦታ አይቾታለሁ"

"ከሆነ ያስገርመኛል" አለ ፖሊስየው

"ለምን ተብሎ? ለምን ከዚህ በፊት የሆነ ቦታ አይቾት ሊሆን አይችልም?"

"እውነት ነው'ኮ" አሉ ባላቸው የሞተባቸው ወይዘሮ "እቺ ልጅ ልክ ናት"

"አመሰግናለሁ፣ እመቤቴ" አለች ዛዚ

"ምንም አይደል"

"ኧረ ምስጋና ይገባዎታል"

"እኔ'ኮ ለነዚህ እንስት ስሜትም አልሰጣቸው" አጉረመረመ ፖሊሱ

"ታድያስ" አሉ ባልቴትዋ "ይህን ብቻ ነው ማድረግ 'ሚያውቁት? እኮ ትንሽ ይንቀሳቀሱ!"

"እርግጠኛ ነኝ'ኔ፣ የሆነ ቦታ አይቻቸዋለሁ"

ይሁን እንጂ ባላቸው የሞተባቸው ወይዘሮ አድናቆታቸውን እስካሁን በድንገት ወደ ፖሊስየው ቀልብሰውታል።

"ችሎታዎትን ያሳዩን 'ንጂ" አሉት፣ እነዚህን ቃሎች በቅንዝራዊ ትኩሳታም ጥቅሻ እያጀቡ "እርስዎን የመሰለ የፖሊስ ሰራዊት አባል መቸስ የማያውቀው ብልሀት አይኖርም። ህግ ሳይጥስ መሆኑ የታወቀ ነው መቸስ"

"ክብት ነው 'ባኮትን!" አለች ዛዚ

"ተይ'ንጂ" አሉ ወይዘሮዋ "ልናደፋፍራቸው ልናግባባቸው ይገባል።"

እና እንደገናም በረጠበና ትኩሳት በሚያስነሳ አይን አዩት

"ስታሂል!" አለ ፖሊስየው፣ በድንገት እየተንቀሳቀሰ "የምታዩትን ታያላችሁ። ትሩስካዩን ምን ማድረግ እንደሚችል አሳያችኋለሁ"

"ስማቸው ትሩስካዮን ነው!" ጮኸች ዛዚ በጋለ ስሜት

"እኔ ደሞ" አሉ ባላቸው የሞተባቸው ወይዘሮ፣ አፍረው ፊታቸው ትንሽ እንደ መቅላት እያለ "ስሜ ማዳም ሙዋክ ነው"

ቆየት ብለው "እንደ ማንኛውም ሰው" ሲሉ ጨመሩበት

# አስር

በሽቦ በሚሳበው የተራራ ቁርጎ ሰራተኞች እና በሜትሮዎቹ የስራ ማቆም አድማ የተነሳ፣ በጐዳናዎቹ የተለያዩ የመኪና አይነቶች ተበራክተው ነበር። በዚህ በኩል ደሞ አግረኞቹ (ወንዶችም ሆኑ ሴቶች) ትእግስታቸው ኀልቆ ወይም ደክሟቸው "ሊፍት" ይጠይቃሉ፤ የሊፍት ምኞታቸው እንደ ሚሟላ ያመኑትም፣ ባለመኪናዎቹ ባልተለመደ የሁኔታዎች አስቸጋሪነት ምክንያት የህብረት መንፈሳቸው ይቀሰቀሳል የሚል እምነት ነበራቸው።

ትሩስካዮንም በበኩሉ፣ ጐዳናው ዳር ቆመና ከኪሱ ፊሽካ አውጥቶ ሲነፋ፣ጆሮ የሚበሱ ጥቂት ድምፆች ተሰሙ

የማያልፉት መኪናዎች መንገዳቸውን ቀጠሉ። ብስክሌት የሚነዱት ምንም ሀሳብ ሳይኖርባቸው በደስታ እየጮሁ፣ እጣ ፈንታቸው ወደመራቻው ይሄዳሉ። ባለ ዶቅዶቁዎቹም የሞተራቸውን ጩኸት እየጨመሩበት ሄዱ'ንጂ አላቆሙም። ዳሩ ገ ሩስካዮን የሚነፋው ለነሱ አልነበረም

ሁሉ ነገር ቀጥ አለ። የትራፊኩ መጨናነቅ የሆነ ቦታ ሲደርስ ድንገት ተገድቦ መሆን አለበት። ከዚያ ቀጥሎ መሀል ለመሀል የምትሄድ ተራ (ግን ብቸኛ) መኪና ብቅ አለች። ትሩስካዮን በፊሽካው ፊር አደረገ! እቺኛዋ መኪናስ ቆመችለት።

ትሩስካዮን ወደሱ ሲመጣ "ምንድነው?" ጠየቀ ሾፌሩ በጠበኛ ድምፅ "ምንም ጥፋት አልሰራሁም። እኔ'ኮ የጐዳናውን ስርአት አውቀዋለሁ። ደሞ አስፈላጊው ወረቀት ሁሉ አለኝ። እና ምን ይሁን? ሰላማዊዎቹን ዜጋዎች እየመጡ ከማስቸገር ይልቅ ቢሄዱና ሜትሮው እንዲሰራ ቢያደርጉ ይሻል ነበር። ይሄ አይበቃዎትም? እንዴ! ምን እናድርግሎት?!" ብሎ መንገዱን ቀጠለ

"እንዲያ ነው ትሩስካዮን!" ጮኸች ዛዚ በምፀት ኩስተር እያለች

"እንደዚህ ልናቃልለው አይገባም" አሉ ባልቴትዋ ሙዋክ "ዋስራ ዘዴውን ያከሽፍበታል"

"ብፊትም በደምብ ገምቼዋለሁ - ክብት ነው"

"ስታይው መልክ መልካም አይመስልሽም?"

"ቅድም'ኮ" አለች ዛዚ በንቀፌታ "አንቱ ነበር ደስ ይለኛል ያሉት። ሁሉንም ነው'ንዴ ሚፈልጉዋቸው?"

ተደጋጋሚ ቀጭን የፊሽካ ፉጨቶች ትኩረታቸውን እንደገና ወደ ትሩስካዮን ጀብዱዎች ሳቡት። ጀብዱዎቹ ኢምንት ነበሩ። አሁን የትራፊክ መጨናነቁ አንድ የሆነ ቦታ ላይ ተፈትቷል፣ ተሽከርካሪዎች እየተግተለተሉ በፖሊስየው ፊት በዝግታ ያልፋሉ፣ ፉጨቱን ግን ማንም ከቁብ የቆጠረው አይመስልም። ከዚያ ቀጥሎ መግተልተሉ እንደገና ቀነሰ፣ የመጨናነቁ ብዛት ትራፊኩን በሆነ አንድ ቦታ ቀጥ አድርጎ አቁሞታል።

ከዚያ ቀጥሎ አንዲት መሀል ለመሀል የምትሄድ መኪና ብቅ አለች። ትሩስካዮን ፊሽካውን አፏጨ፣ መኪናዋ ቆመች።

"ምንድነው?!" ጠየቀ ሾፌሩ በጠበኛ ድምፅ፣ ትሩስካዮን ሲመጣበት "ምንም ጥፋት አልሰራሁም። እኔ'ኮ የመንጃ ፈቃድ አለኝ። ደሞ አስፈላጊው ወረቀት ሁሉ አለኝ፣ እና ምን ይሁን? ሰላማዊ ዜጋዎችን እየመጡ ከማስቸገር ቢሄዱና ሜትሮው እንዲሰራ ቢያረጉ ይሻል ነበር። ይሄ አይበቃዎትም? አለዚያ ይሂዱና የሞርኮ ጠንቋይ ያማክሩ"

"ሆ!" አለ ትሩስካዮን፣ ጨዋነቱ እየተቀየመ

ዱሩ ምን ያደርጋል፣ ሰውየው ሄዷል

"ብራቮ ትሩስካዮን!" ጮኸች ዛዚ ስሜት ፈንቅሏት ደስታ ውስጥ እየዋኘች

"ይበልጥ ደስ-ደስ እያለኝ ሄደ" አሉ ባላቸው የሞተባቸው፣ ድምፃቸውን ዝቅ አድርገው

"ወይዘሮዋ ጨርሰው ቀውሰዋል" አለች ዛዚ፣ እሷም ድምጿን ዝቅ አድርጋ

ትሩስካዮን ተበሳጭቶ የመለዮ ልብሱንም የፊሽካውንም ብቃት ይጠራጠር ጀመር። ተጠቃሹን እቃ ለማድረቅ ሲል፣ ሞልቶት የነበረውን ምራቅ ለማራገፍ እየነቀነቀው እያለ፣ አንዲት መሀል ለመሀል ስትሄድ

የነበረች ተራ መኪና በገዛ ራሷ መጣችና አጠገቡ ቆመች። አንድ ጭንቅላት በመስኮትዋ ብቅ ብሎ የሚከተሉትን የተስፋ ቃላት ተናገረ:-

"ይቅርታ አለቃዬ፣ የጎቲክ ስነጥበብ እንቁ የሆነው ሴንት-ሻፔል ቤተክርስትያን ለመድረስ አቋራጭ መንገድ ሊያመላክቱኝ ይችሉ ይሆን?"

"እንዴታ!" መለሰ ትሩስካዮን በዘልማድ እየቀጠለ "መጀመሪያ በግራ መሄድ ነው፣ ከዚያ ቀጥሎ በስተቀኝ፣ ከዚያ ቀጥሎ ጠበብ ያለ አደባባይ ሲደርሱ በቀኝ በኩል ሶስተኛውን መንገድ መያዝ፣ ቀጥሎ በግራ በኩል ሁለተኛውን፣ ከዚያ ትንሽ ወደ ቀኝ፣ ሶስት ጊዜ ግራውን፣ በመጨረሻም ሀምሳ አምስት ሜትር በቀጥታ ፊት ለፊትም። የታወቀ ነው መቸስ፣ እዚህ ሁሉ ውስጥ ማለፍ ክልክል የሆነባቸው መንገዶች ይኖራሉ፣ ይሄም ስራዉን የሚያቃልልልዎት አይሆንም"

"መቼም ቢሆን ላልደርስ ነው" አለ ነጂው "ደሞ'ኮ ከከተማ ዳር ሴንት-ሞንትሮን የመጣሁት ለዚሁ ብዬ ነበር"

"ተስፋ መቁረጥ አይገባም" አለ ትሩስካዮን "ለምሳሌ እንበል፣ እኔ ባደርስዎትስ?"

"ሌላ ጉዳይ ሳይኖርዎት ይቀራል?"

"አይምሰልዎት። ነፃ ነኝ እንደ አየሩ። አንድ ነገር ብቻ፣ ይኸውም እነዚህን ሁለት ሰዎች (በእጁ እያመለከተ) መልካም ፈቃድዎ ሆኖ በተሽከርካሪዎ ቢወስዱዋቸው?"

"ብወስዳቸው ግድ የለኝም። ብቻ ከመዘጋቱ በፊት ልድረስ"

ባላቸው የሞተባቸው "በኔ ይሁንብሽ" አሉ ክሩቅ "አሁንስ አንዲት መኪና ብጤ የወረሰ ይመስላል"

"ሊያስደንቀኝ ነው" አለች ዛዚ በሚዛናዊነት

ትሩስካዮን ፈጥኖ ወደነሱ ጋለበና ጨዋነት በጉደለው ቅላፄ እንዲህ አላቸው:-

"ኑ ቶሎ በሉ! ሰውየው ሊያሳፍረን ነው"

"እንሂድ" አሉ ባልቴትዋ ሙዋክ "ወደ ጠላፊዎቼ!"

"ውይ! እነሱን ረስቻቸው!" አለ ትሩስካዮን

"ምናልባት ለነጂው ወዳጅዎ ይህን ባይነግሩት ይሻላል" አሉ ባልቴትዋ በዲፕሎማት መንፈስ

"እንደዚህ ነው?" ጠየቀች ዛዚ "ወደተባለው ቤተክርስትያን ሊወስዱን ነው?"

"ፈጠን በሉ'ንጂ!"

ትሩስካዮንና ባልቴትዋ ሙዋከ ዛዚን በሁለት በኩል በክንድዋ አንስተው በጉዳናው መሀል ወደ መጣችው ተራ መኪና ውስጥ ወረወሩዋት

"እንዲህ ሲያደርጉኝ አልወድም እኔ!" አንጓራች ዛዚ በንዴት እየጦፈች

"ጠባፊዎች ትመስላላችሁሳ?" አለ የሳንኩቲ ሞንትሮን ሰፈሩ ሰውዬ በቀልድ

"ሳይሆኑ የመምሰል ነገር ቀላል ጉዳይ ነው" አለ ትሩስካዮን፣ ከጉኑ እየተቀመጠ "ከመዘጋቱ በፊት ለመድረስ ከፈለጉ አሁን መሄድ ነው"

አስነሱ። ሂደቱን ለማገዝ ትሩስካዮን ከትከሻው ወጣ ብሎ ፊሽካውን እንደ ጉድ መንፋት ጀመረ። ምንም ቢሆን ውጤት ማስከተሉ አልቀረም። የገጠሩ ሰውዬ በደስታ ፈነደቀ

"አሁን ወደ ግራ መዞር" አዘዘ ትሩስካዮን

ዛዚ አኩርፋለች

"ታድያስ" አሉዋት ባልቴትዋ ሙዋከ ሲ[illegible]ግደቁ "አጎትሽን ልታገኚው ስለሆነ ደስ አላለሽም?"

"አጎት የቂጤን አበሳ ይስጠው!" አለች ዛዚ

"እንዴ!" አለ ነጂው "እቺ የዣ'ን ሳሉቬር ልጅ ናት። በወንድ ልብሷ ምክንያት ተቀይራብኝ አላወቅኳትም'ንጂ"

"ያውቋታል?" ጠየቁ ባልቴትዋ ሙዋከ፣ ምንም ስሜት ሳይሰጣቸው

"መሰለኝ" አለ ሰውየው

እውነት አውቋት እንደሆነ ለማረጋገጥ ዞረ፣ እና ልክ ይህን ጊዜ ከፊቱ ይሄድ የነበረውን መኪና ገጨ

"ሜርድ!" አለ ትሩስካዮን

"እሷ ራሷ ናት" አለ የሳንክቲሞንትሮኑ ሰውዬ

"እኔ በበኩሌ አላቆትም" አለች ዛዚ

"ምን እየተፈጠረ ነው? መንዳት አያውቁም'ንዴ" አለ ተገጪው፣ ከገጪው ጋር አንዳንድ የሚያስገመግሙ ስድቦችን ለመለዋወጥ ከመኪናው ወርዶ እየመጣ "አአ! ይሄ'ንኳ አይገርመኝም... ገጠሬ... እየመጡ የፓሪስን ጉዳናዎች ከማጣበብ ይልቅ፣ ሄደው የሰፈር እንትን ምናምንዎትን ቢጠብቁ ይሻልዎታል"

"እንዴ! መስዬ" አሉ ባላቸው የሞተባቸው ወይዘሮ ሙዋክ "የማያስፈልግ ጉዳይ ሲያወሩ እያዘገዩን'ኮ ነው! እኛ ለራሳችን ግዳጅ ለመፈፀም እየመረሽን ነው። የተጠለፈ ሰው ልናስፈታ ነው"

"ምን? ምን?" አለ የሳንክቲሞንትሮን ሰውዬ "እኔ የለሁበትም። ፓሪስ የመጣሁት የሲኒማ ካው-ቦይ ለመጫወት አይደለም"

"እርስዎስ?" አለ ሌላው አሽከርካሪ፣ ትሩስካዮንን እያናገረ "መጥሪያ ፅፈው እስኪሰጡት ምን እየጠበቁ ነው?"

"እያስቡ" መለሰለት ትሩስካዮን "እንደ ተሰጠው ይቁጠሩት። ለኔ ይተዉልኝ"

እና ጠርዙ የተጨረማመተ አሮጌ የመጥሪያ ደብተር ላይ የሚፅፍ ፖሊስ እየመሰለ፡-

"ግራጫ ካርድዎትን ይዘዋል?"

ትሩስካዮን ካርዱን የሚመረምር አስመሰለ

"ዲፕሎማቲክ ፓስፖርት የሎትም?"

(የተንገሸገሸ አሉታ)

"እሺ ይበቃል" አለ ትሩስካዮንየው "ሊሄዱ ይችላሉ"

ተገጪው ሀሳብ ይዞት ወደ መኪናው ገባና መንዳቱን ቀጠለ። የሳንክቲሞንትሮን ሰውዬ ግን አልተንቀሳቀሰም

"እንዴ!" አሉ ባልቴትዋ ሙዋክ "ምን እየጠበቁ ነው እርስዎ?"

በስተኋላቸው ጥሩንባዎቹ ይጮሀሉ

"ካው-ቦይ መጫወት አልፈልግም እያልኩዎት! በራሪ ጥይት ቶሎ ብሎ ነው 'ሚቀልበው"

"እኛ ሰፈር ቢሆን ግን ማንም እንዲህ አያስቦነም" ዛዚ ጉረረች

"አንቺ!" አለ ሰውየው "አውቅሻለሁ'ኮ። ተራራዎችም ቢሆን ታጋጪያለሽ"

"ይሄማ ጅልነት ነው" አለች ዛዚ "እንደዚህ ስሜን ለማጥፋት ለምን ይሞክራሉ?"

የጥሩምባዎቹ ጩኸት እየጨመረ ሄዶ ነጒድጓድ አከለ

"ያስነሱ'ንጂ!" ጮኸ ትሩስካዮን

"ነብሴን እወዳታለሁ" እቅጯን ተናገረ የሳንክቲሞንትሮን ሰውዬ

"ሀሳብ አይግባዎት" አሉ ባልቴትዋ ሙዋክ አሁ'ንም በዲፕሎማት መንፈስ "ምንም አደጋ የለም። ቀልድ ጨዋታ ነው"

ሰውየው የዚችን ወይዘሮ መሳይ አሮጊት ሁኔታ አጣርቶ ለማየት ዞረ። ይህ ምርመራ ወደ እምነት እንዲያዘነብል አደረገው

"ቃል ይገቡልኛል?" ጠየቀ

"አልኩዎት'ኮ"

"አስቀያሚ ውጤቶችን የሚያስከትል የፖለቲካ ጉዳይ እንዳይሆን ብቻ"

"አይደለም ኧረ፣ ዝም ብሎ ቀልድ ነው፣ በኔ ይሁንብዎት"

"እንግድያው እንሂዳ" አለ ሰውየው፣ በሙሉ ልብ ያልተረጋጋ ቢሆ'ንም

"አውቅሻለሁ ቢሉኝ ጊዜ" አለች ዛዚ "ምናልባት ባጋጣሚ እማዬን አይተዋት ይሆን'ንዴ? እሷም ፓሪስ ውስጥ ነው ያለችው"

ገና ትንሽ መንገድ እንደሄዱ፣ አጠገባቸው ከነበረ አንድ ቤተ-ክርስትያን አስር ሰአት ተደወለ (የቤተ-ክርስትያኑ ስነ-ህንፃ ኒዮ-ክላሲክ ነው።)

"ነገርየው ገደል ገባ" አለ የሳንክቲሞንትሮን ሰውዬ

እንደገና ፍሬን ያዘ፣ ይህን ከበስተኋላ አዲስ የማስጠንቀቅያ ጥሩምባዎችን ድምፅ ቀሰቀሰ

"ከዚህ በኋላ ዋጋ የለውም" ሲል ቀጠለ "አሁን ይዘጋል"

ፍጥነት ለመጨመር ተጨማሪ ምክንያት ሆነልዎታ!" አሉ ባልቴትዋ ሙዋክ፣ ሚዛናዊነትና ስትራቴጂ እያመቻቹ "አለዚያማ የተጠለፈብንን ሰው ማግኘት ላንችል'ኮ ነው"

"ስሜት አይሰጠኝም 'ባኮትን!" አለ ሰውየው

እንድያም ሆኖ በኋላው የጥሩምባ ጨኸት ከማየሉ የተነሳ መንገዱን መቀጠል ግድ ሆነበት፣ በሱ ምክንያት የተገደቡት አሽከርካሪዎች ብስጭታቸው ተጠቃልሎ በአየሩ ሞገድ የገፈተረው መስሎ ተሰማው።

"ይበሉ "ንግዲህ" አለ ትሩስካዮን "እልህዎትን ይተዉት። ልንደርስ ምንም ያህል አልቀረን። በኋላ ለሰፈርዎ ሰዎች ሲናገሩ፣ ሴንት-ሻፔል ቤተ-ክርስትያንን ራሱን ባላየውም ተጠግቼው ነበር፣ ሊሉዋቸው ይችላሉ። እዚሁ ከቀሩ ግን—"

"በል ሲለው'ኮ ብዙ ይናገራል" ስትል ዛዚ ስለ ፖሊስየው ሚዛናዊ አስተያየትዋን ሰነዘረች

"በይበልጥ እየወደድኩት መጣሁ" አጉረመረሙ ወይዘሮዋ ለራሳቸው፣ ድምፃቸው ዝቅ ከማለቱ የተነሳ ማንም ሳይሰማቸው

"እማዬላ?" እንደገና ዛዚ ሰውየውን ጠየቀችው "አውቅሻለሁ ቢሉኝ ጊዜ፣ ምናልባት ባጋጣሚ አላዩዋትም ይሆን?"

"ወቼ ጉድ!" አለ የሳንክቲሞንትርው ሰውዬ "ምኑም ሊገባኝ አይችልም!" ይሄ ሁሉ መኪና እያለላችሁ፣ ስተት ብላችሁ ይችኑ የኔዋን መረጣችሁ"

"ሆን ብለን ያረግነው አይደለም" አለ ትሩስካዮን "ኢማላውቀው ከተማ ከሆነ እኔም ብሆን መንገድ እጠይቃለሁ"

"ነው፣ ግን" አለ የሳንክቲሞንትሮኑ ሰውዬ "ሴንት-ሻፔልላ?"

"እሱስ እውነቶን ነው። ወደዛው እንሂዳ"

"እሺ" አለ የሳንክቲሞንትሮኑ ሰውዬ "እየሄድኩ ነው"

"ወደ ጠላፊዎቹ!" ጮሁ ባልቴትዋ ሙዋክ

ትሩስካዮን ደሞ መንገድ የሚያጣብቡትን መኪናዎች ለማስወገድ ጭንቅላቱን አውጥቶ ፊሽካውን ይነፋ ጀመር፣ በመጠኑም ቢሆን ፈጠን አሉ።

"ይሄ ሁሉ ምስኪን ነገር ነው!" አለች ዛዚ "እኔ'ምወደው ሜትሮውን ብቻ ነው"

"እርሶስ ጉረኛ ኖት" አለች ዛዚ

"አቅሙ እስካለኝ ድረስ..."

"እንድያም ሆኖ ግን ቅድም ለታክሲ ዱዲ ታህል'ንኳ ለማውጣት ዝግጁ አልነበሩም"

"አያስፈልግም ነበራ፣ እንደምታይው"

"እየሄድን ነው" አለ ትሩስካዮን፣ ተሳፋሪዎቹ "ጉሽ!" እንዲሉት ዞሮ እያስተዋላቸው

"አዎና!" አሉት ባልቴትዋ፣ ስሜት እየፈነቀላቸው

"ማጋነን አያስፈልግም" አለች ዛዚ "እዛ 'ምንደርሰው አጎቴ ከተዘጋበትና ከሄደ በኋላ ይሆናል"

"የተቻለኝን ያህል እየሞከርኩ ነው" አለ የሳንክቲሞንትሮኑ ሰውዬ፣ ወደ መኪና ማቆምያው እየነዳ፡፡ "አቤት! ሴንት-ሞንትሮን ሜትሮ ቢኖረው ኖሮ! አይደለም፣ ሚጡ?" ብሎ ጮኸ

"ኤድያ!" አለች ዛዚ "እንደዚህ አይነቱ ማባበል ነው በተለይ የሚያንገሸግሸኝ፡፡ የእኛ ፋራ መንደር ውስጥ ሜትሮ ሊኖር 'ሚችል ይመስል!"

"አንድ ቀን ይመጣል ታያለሽ" አለ ሰውየው "ከእድገት ጋር ሁሉ ቦታ ሜትሮ ይኖራል፡፡ እንድያውም የአረፍ አረፍ ነው 'ሚሆነው፡፡ ሜትሮና ሄሊኮፕተር — የትልቅ ከተማ ማመላለሻ ይሄ ነው 'ሚሆነው፡፡ ማርሰይ ለመሄድ ሜትሮ እንሳፈርና በሄሊኮፕተር እንመለሳለን"

"ለምን በተገላቢጦሹ አይሆንም?" ጠየቁ ባልቴትዋ ሙዋክ፣ አዲሱ ፍቅራቸው እንደ ፈላስፋው ዴካርት የማሰብ ፍጥነታቸውን ገና አጥፍቶ ያልጨረሰባቸው በመሆኑ

"ለምን በተገላቢጦሹ አይሆንም?" አለ ሰውየው "... በንፋሱ ፍጥነት ምክንያት"

ይህ ረቂቅ ብልህነት ምን ስሜት እንዳሳደረባቸው ለመገመት ትንሽ ወደኋላ ዞረ፣ ይህም በሁለተኛው ረድፍ የቆመውን አቶቡስ አስገጨው፡፡

ደርሰዋል። እውነትም፣ ፌዶር ባላኖቪች ተከሰተና የተለመደውን ዲስኩር ጀመረ፦

"እኮ ምንድነው? መንዳትም አያውቁ? አሀ! ይሄስ አይገርመኝም... ባላገር... የፓሪስን ጉዳናዎች ከማጣበብ፣ ሄደው ምናምኖትን ቢጠብቁ ይሻሉ·ታል"

"እንዴ!" ጮኸች ዛዚ "ፌዶር ባላኖቪች ኖት ለካ። አንቴን አላዩትም?"

"ወደ አንትየው!" አሉ ባልቴትዋ ሙዋክ ከመኪናው እየወጡ

"አይ! ጉዳዩ በዚህ አይበቃማ" አለ ፌዶር ባላኖቪች "እያዩ ማየት ነበር። አዩት ይህንን-የስራ መሳሪያዬን አበላሽተውልኛል"

"እርስዎ በሁለተኛው ረድፍ ነቡራ ያቆሙት። እንደዚህ አይደረግምኮ"

"ክርክር አትጀምሩ" አለ ትሩስካዮን በተራው እየወረደ "እኔ አስተካክለዋለሁ"

"አይሆንም!" አለ ፌዶር ባላኖቪች "እሱ መኪና ውስጥ ስለነበሩ ወገናዊ ይሆኑብኛል"

"እንግድያው 'ምታረጉትን አርጉ" አለ ትሩስካዮን ባልቴትዋን ሙዋክ ለመፈለግ እየተፈተለከ፣ በዛዚዋ ተከልለው ጠፍተውበት ስለነበረ።

# እስራ አንድ

Café des Deux Palais በረንዳ ላይ ጋብሪዬል አምስተኛውን ጠርሙስ ግሪናዲን እየጨለጠ፣ ለተሰበሰቡት ሰዎች ይደሰኩራል፣ የአድማጮቹ ትኩረት በሙሉ ተስቧል፣ የፈረንሳይኛ እውቀት የተሰጣቸውን ጥቂቱ ብቻ ቢሆኑም

"ለምን?" እያላቸው ነበር። "ማንም ምንም ኢምንት ነገር ሲያሳጣችሁ እስከቻለ ድረስ ለምን እቺን ኑሮ አትችሉዋትም? ማንም ኢምንትን ነገር ያመጣታል፣ ማንም ኢምንትን ነገር ይወስዳታል። ይህ ባይሆንማ ኖሮ፣ እጣ-ፈንታ ሲኮረኩመንና የምንወደው ሙያ ውርደት ሲያመጣብን፣ የምግብ ሱቅ ሻጭ ሲሸፍጠን፣ የሉካንዳ ዋጋ ሲንርብን፣ ወተት ሻጮች በውሀ ሲበርዙብን፣ ወላጆች ሲያበሽቁን፣ መምህራን ቁጣ ሲያወርዱብን፣ ሻምበል ባሻዎች ሲጮሁብን፣ ሀብታሞች ሲማግጡብን፣ የተደመሰሱት ሰቆቃ ሲያሰቃየን፣ ማለቅያ የለሹ ህዋ በፀጥታው ሲውጠን፣ የአበባ ጉመኑ ሽታ ሲያፍነን፣ ወይም መጫወቻ የእንጨት ፈረሶቹ ደነዝ ሲሆኑብን - ይህን ሁሉ ማን ይችለው ነበር? የምናውቀው መጥፎና ከምንችለው በላይ የሚበዛብን የጥቂት ህዋሳት ባህሪ (ሰውነቱን ያንቀሳቅሳል) ወይም ህላፊነት የማይሰማው፣ ማንነቱ ያልታወቀ ሰው ሳያስብበት የተኰሰው በራሪ ጥይት ይህን ሁሉ ስጋታችንን ወደ ሰማያዊው ሰማይ ቢያበንነውስ?

"አሁን የማወራላችሁ እኔ፣ የዳንሰኛ ሚኒስክርት ለብሼ፣ በቂ ፀጉር የለበሱ የምኮራባቸው ጭኖቼን በሙያዬ ደምብ ላጭቼ ሳበቃ፣ እንደናንተ ያሉ ሰዎች በምሉት አዳራሽ ውስጥ በማሳይበት ጊዜ እነዚህን ፕሮብሌሞች አሰላስያቸዋለሁ። እዚህ ላይ ልጨምረው የሚገባኝ አለ፣ ይኸውም ፍላጎታችሁን ከገለፃችሁ፣ ከዛሬ ማታ ጀምሮ ይህን ትርኢት መመልከት ትችላላችሁ"

"እንዲያ ነው!" ጮሁ ተንገርቹ በመተማመን

"ኧንዴት ነው አጎቴ፣ ከመቸውም የበለጠ ተፈላጊ እየሆንክ ሄድክ'ኮ"

"ኧ! እዚህ ነሽ'ንዴ" አለ ጋብሪዬል በሰላማዊ ስሜት "ይኸው እንደምታይው፣ በህይወት እገኛለሁ፣ ያውም በሙሉ ብልፅግና ውስጥ"

"ሴንት-ሻፔልን አሳየሀቸው?"

"በለስ ቀናቸው፡፡ እየተዘጋ ነበር፣ በህብረ-ቀለም የሚያበሩትን መስኮቶች ከመቶ ሜትር ቅርበት (እየተራመደ ያሳያታል) ይህንን ያህል ለማየት የሚበቃ ነበራቸው፡፡ በጣም ነው የተደነቁት (እያመለከተ) እነሱ፡፡ አይደለም'ንዴ ውቢቷ እመቤት ሆይ?"

የተመረጠችው ቱሪስት አዎንታዋን በደስታ ገለፀች

"እንዲያ ነው!" ጮሁ ሌሎቹ

"ጠላፊዎቹ ተያዙ!" ጨመሩ ባልቴትዋ ሙዋክ፣ በትሩስካዮን የቅርብ ተከታይነት፡፡

ፖሊስየው ወደ ጋብሪዬል ቀረበና፣ በአክብሮት እጅ እየነሳው፣ የጤንነቱን ሁኔታ ጠየቀው፡፡ ጋብሪዬል ደህና መሆኑን ባጭሩ ነገረው፡፡ ያኛውም የነፃነትን ፕሮብሌም እያነሳ ምርመራውን ቀጠለ፡፡ ጋብሪዬል በበኩሉ የነፃነቱን ብዛት እያረጋገጠ፣ በተጨማሪም የሚመቸው መሆኑን ለጠያቂው አረጋገጠለት፡፡ እርግጥ ነው፣ በዚህ ረገድ ከመነሻው ጀምሮ፣ ማንም ሊደርስበት የማይገባ መብቱን ለመንካት አሌ በማይባል አኳኋን የተሞከረ መሆኑን አልካደም፣ ሆኖም ግን ሁኔታውን ሲለምደው በመጨረሻ መሰረታዊ ለውጥ ስላካሄደበት ጠላፊዎቹ ዞረው አገልጋዮቹ ሆነዋል፣ በቅርብ ጊዜ በህሊና ዳኝነታቸው እንዳፈቀደው ለማዘዝ እንደሚችልም ገልጿል፡፡

ለመደምደም ያህልም፣ ፖሊሶች የግል ጉዳዩ ውስጥ ጥልቅ እያሉ ማነፍነፋቸው እንዳስጠላው ጨምሮ ተናግሯል፡፡ እና ይህ አይነቱ ድርጊት እያንገሸገሸ እስኪያቅለሸልሸው ድረስ ከመሆን ስለማይርቅ፣ ከኪሱ ትንሽዬ፣ ክሬም ከለር አራት ማእዘን ሀር ጨርቅ አውጥቶ (የገናናው የፊዮር ሱቅ በሆነው ባርቡዝ ሽቶ የተነከረ) ግምባሩን ጠረገ፡፡

ትሩስካዮን ቀረናው፣ ይቅርታ ጠየቀ፣ ለጋብሪዬል በተጠንቀቅ ሰላምታ ሰጠ፣ በደምቡ መሰረት ቀኝ-ኋላ ዞረ፣ ርቆ ሄደ፣ ሰዎች መሀል ተሰወረ፣ እየገሰገሱ በሚያሳድዱት ባልቴት ሙዋክ ታጅቦ

"አቤት እንዴት አርገህ ዘለፍከው!" አለችው ዛዚ ጋብሪዬልን፣ አጠገቡ እየተቀመጠች "ለኔ እንጆሪ-ቸኮላት አይስ-ክሬም ይምጣልኝ"

"መልኩን ከዚህ በፊት የሆነ ቦታ ያየሁት ይመስለኛል" አለ ጋብሪዬል

"አሁን 'ንግዲህ ፖሊስየው ተባሯል" አለች ዛዚ "ምናልባት መልስ ትሰጠኝ ይሆናል። ሰዶማዊ ነህ ወይስ አይደለህም?"

"እምልልሻለሁ፣ አይደለሁም"

እና ጋብሪዬል መሬቱ ላይ እየተፋ ከንዱን ዘረጋ፣ ይህም ተጓዦቹን በመጠኑ አስገረማቸው። የዚህን የጥንታውያን ፈረንሳዮች የባህላዊ አፈ-ታሪክ ገፅታ ሊያስረዳቸው ሲል፣ ዛዚ የማስተማር አላማውን እየቀደመች "ካልሆንክ ታዲያ ሰውየው ነህ ለምን አለ?" ብላ ጠየቀችው።

"እንደገና ተጀመረ!" አለቃቀሰ ጋብሪዬል

ተጓዦቹ ትንሽ ትንሽ ገብቷቸው፣ ምንም የሚያስቅ እንዳልነበረ ሲያዩ፣ ዝቅ ባለ ድምፅ እና በናት ቋንቋቸው ተመካከሩ። አንዳንዶቹ ልጅቱን ሰይን ወንዝ ውስጥ እንጣላት ሲሉ፣ ሌሎቹ ደሞ ድምፅ አልባ እንድትሆን ጭብጥ ጥጥ ካጐረስናት በኋላ በብርድ ልብስ ጠቅልለን ስናበቃ፣ ማንኛውም ጣቢያ ስንደርስ በአደራ እንተዋት አሉ። ብርድልብስ መሰዋት የሚፈልግ ሰው ከጠፋ፣ ሻንጣ ሊያገለግል ይችላል፣ በሚገባ ካጨቁት።

ይኼ መመካከር ያሰጋው ጋብሪዬል አንዳንድ ነጥቦችን ሊሰቅላቸው ወሰነ

"እሺ 'ንግድያው" አለ "ሁሉንም ማታ አስረዳሻለሁ። እንድያውም የሚሻለው፣ ዛሬ በገዛ አይንሽ ታያለሽ"

"ምንድነው 'ማየው?"

"ታያለሽ አልኩሽ፣ ቃሌ ነው"

ዛዚ ትከሻዋን ከፍ ዝቅ አደረገች

"የተስፋ ነገር፣ እኔ..."

"እንደገና መሬት ላይ ልትፋልሽ'ንዴ?"

"ይበቃል። አይስ-ክሬሜ ውስጥ ትተፋብኛለህ"

"እንግድያው አሁን ሰላም ስጪኝ። ታያለሽ ብያለሁ"

"ሚጡዋ ምንድነው 'ምታየው?" ጠየቀ ፌዶር ባላኖቪች፣ ከሳንክቲሞንትሮን ሰውዬ ጋር የደረሰበትን ግጭት ጉዳይ እልባት ካስያዘ

በኋላ (ለነገሩ፣ ሰውየው ከአካባቢው ለመጥፋት ሀይለኛ ጉጉት ይታይበት ነበር)

በተራው ጋብሪዬል አጠገብ ሲቀመጥ ሲል ተጓዦቹም ለአስጐብኚ ያቸው በአክብሮት ቦታ ለቀቁለት።

"ዛሬ ማታ ወደ ሞን-ደ-ፒዬቴ ናይት ክለብ ልወስዳት ነው" አለ ጋብሪዬል (ወደ ቱሪስቶቹ እያመለከተ) "እና ሌሎቹንም"

"ቆይ" አለ ፌዶር ባላኖቪች "ይሄ ፕሮግራማችን ውስጥ የለበትም። እኔ ተጓዦቼን በጊዜ ማስተኛት አለብኝ፣ ምክንያቱም ነገ ጧት የካብ ግምብ መከላከያዋ ተጥሶ ወደማያውቀው ታሪካዊቷ ጅብራልታር መሄድ አለባቸው። የጉዞ መስመራቸው ነው"

"እንድያም ሆኖ ግን ደስ እየተሰኙ ናቸው"

"ምን እንደሚጠብቃቸው ስለማያውቁ ነዋ!"

"ለወደፊት በደስታ የሚያስታውሱት ይኖራቸዋል" አለ ጋብሪዬል

"ለኔም" አለች ዛዚ፣ ስለ እንጆሪና ስለቸኮላት የተለያየ ጣእም የነበሩ ልምዶችዋን እስታውሳ በስልት እያነፃፀረች

እሱስ ይሁን" አለ ፌዶር ባላኖቪች "ምን-ደ-ፒዬቴ መግቢያቸውን ማን ይከፍላል? ተጨማሪ ክፊሉ ቢባሉ እሺ አይሉም"

"ለኔ ተውልኝ። በእጄ ውስጥ ናቸው" አለ ጋብሪዬል

"በነገራችን ላይ" አለችው ዛዚ "ልጠይቅህ የፈለግኩት ጥያቄ ትዝ ሊለኝ እየጀመረ ነው መሰለኝ"

"ይሁን። በኋላ ትቀጥያለሽ" አለ ፌዶር ባላኖቪች "አሁን ወንዶቹ እንነጋገር ተይን"

ዛዚ ፀጥ አለች እየተገረመች

ባጋጣሚ አንድ ቦይ ሲያልፍ ፌዶር ባላኖቪች አዘዘ፡-

"ለኔ አንድ ድራፍት"

"በኩባያ ወይስ በጣሳ?" ጠየቀ ቦዩ

"በሬሳ ሳጥን ውስጥ" መለሰ ፌዶር ላኖቪች፣ ቦዩን በምልክት እያስናበተው

"ያሁንዋስ የመጨረሻ አረፍ ናት!" አለች ዛዚ ስትፈራ ስትቸር "ጄኔራል ቬርሞት ራሱ 'ንኳ ቢሆን ያለ ረዳት ሊፈጥራት አይችልም!"

ፌዶር ባላኖቪች ልጅቱ የምትለውን አንዱንም አልሰማ

"እሺ 'ንግዲህ" ጠየቀው ጋብሪዬልን "ተጨማሪ እንዲከፍሉ ልናስገድዳቸው እንችላለን ነው 'ምትለኝ?"

"በእጇ ውስጥ ናቸው እያልኩህ!? ልንጠቀምባቸው ይገባል:: ለምሳሌ ልጠይቅህ:: ለእራት የት ነው 'ምትወስዳቸው?"

"እንዴ ጥንቃቄ ይደረግላቸዋል'ኮ ‹ቡዊሶን ዳርዣን› ምግብ ቤት ናቸው ለእራት:: እሱን ግን የጉዞ ድርጅቱ ነው 'ሚከፍለው"

"ተመልከት 'ንግዲህ:: ቱርቢጎ ጉዳና እኔ 'ማውቀው ምግብ ቤት አለ አስር እጅ ያነሰ 'ሚከፈልበት:: አንተ ሄደህ የቅንጦት ምግብ ቤትህን አዛኙ የጉዞ ድርጅቱ ከሚከፍለው ላንተ ድርሻህን እንዲያስብልህ ታረጋለህ፣ ሁላችንም እናተርፋለን:: ከዚያም በላይ ደሞ፣ እኔ ምወስዳቸው ቦታ እንደ ሚንበሸበሹ የታወቀ ነው፣ ይህንም የምንከፍለው ሞን-ደ-ፒዬቴ ለመግባት ከምንጠይቃቸው ተጨማሪ ክፍያ ይሆናል:: ሌላኛው ምግብ ቤት የሚመልስልንን ደግሞ እንካፈለዋለን"

"እናንተ ሁለታችሁ ግን ጮካ ልጆች ናችሁ" አለች ዛዚ

"ይሄ 'ንኳ አይን ያወጣ ውሸት ነው!" አለ ፌዶር ባላኖቪች "እኔ ለራሴ የምሰራው ሁሉ ለነሱ (ያመለክታል) ደስታ ነው የምናስበው ይህንኑ ብቻ ነው:: የዚችን ፓሪስ የምትባለውን ዝነኛ ከተማ የማይረሱት ትዝታ ይዘው እንዲሄዱ፡፡ ተመልሰው ይመጡ ዘንድ"

"እሺ 'ንግዲህ፣ ሁሉም ነገር ድንቅ ነው" አለ ጋብሪዬል "የእራት ሰአት እስኪደርስ በፓሪስ ብቸኛውን፣ ከምድር በታች ሰፊ አዳራሽ ውስጥ የሚገኘውን አስራ አምስት የፑል ጠረጴዛና ሀያ የፒንግፖንግ ጠረጴዛ ይለማመዱበታል::"

"መልካም ትውስታ ይሆንላቸዋል"

"ለኔም ይሆንልኛል" አለች ዛዚ "በዚያች ሰአት ሽርሽር ስለምሄድ"

"አታስብ" አለ ፌዶር ባላኖቪች "ያሰበችበት መከላከያ ቢኖራት ነው"

"እንድያም ቢሆን፣ እናቷ አደራ የሰጠችኝ በሌ-አል እና ሻቶ-ዶ መካከል እንድትንቀዋለል አይደለም"

"ቀስ እያልኩ ባንተ ምግብ ቤት አጠገብ እመላለሳለሁ" አለች ዛዚ ስታግባባ

"እሱማ የባሰ የሽሌ ስራ 'ምትሰሪ ያስመስልሻል" ጮኸ ጋብሪዬል እየተሸበረ "በተለይ ጂንስ ሱሪሽን ለብሰሽ! የሰፈር ዱርዬዎች እሱ'ኮ"

"ባለጌዎች እሱ" አለ ፌዶር ባላኖቪች፣ ኑሮን በጥልቀት የሚያውቃት ትልቅ ሰው

"ይሄማ ለኔ ጥሩም አይደል" አለች ዛዚ እየተወራጨች

"አሁን ልታግባባህ የጀመረች 'ንደሆነ" አስጠነቀቀ ጋብሪዬል "ያቀድነው ሁሉ ገደል ገባ"

"ምነው?" ጠየቀች ዛዚ "ስዶማዊ ነው 'ንዴ?"

"ጤነኛ ሰው ማለትሽ ነው" አስተካከለ ፌዶር ባላኖቪች "ድንቅዬ ናት እቺ ሚጡስ! አይደለምንዴ፣ አንቴ?" እያለ ጭኑን መታ ሲያረገው ጋብሪዬል ተውረገረገ፡፡

ተጓዦቹ ለማወቅ በሚፈልግ አይን ይመለከቱዋቸዋል

"ሊሰላቹ ሳይጀምሩ አይቀሩም" አለ ፌዶር ባላኖቪች "ወደ ፑል መጫወቻው ወስደህ የምታዝናናቸው ጊዜው እየደረሰ ነው፡፡ ምስኪን የዋሀን፣ ፓሪስ ማለት ይሄ ነው ብለው ማመናቸው!"

"ሴንት-ሻፔልን ያሳየሁዋቸው እኔ መሆኔን እየረሳህ ነው" አለ ጋብሪዬል እየተኩራራ

"ጅሎ" አለ ፌዶር ባላኖቪች፣ ወላጆቹ ሩስኪ ቢሆኑም የቧ-ኮሎምብ ሰፈር ልጅ ነውና ፈረንሳይኛዋን ጠንቅቆ ስለሚያውቃት "አንተ'ኮ ያስጐበኘሀቸው የንግድ ፍርድ ቤትን ነው"

"እያታለልከኝ መሰለኝ" አለ ጋብሪዬል ማመን እያቃተው "እርግጠኛ ነህ ግን?"

"እረ 'ንኳን ሻርል እዚህ አልኖረ" አለች ዛዚ "ነገሮች የባሰውን ይወሳሰቡ ነበር"

"ሴንት እንትና??? ሴንት እንትን???" ከተጓዦቹ መሀል የበለጠ ፈረንሳይኛ ተናጋሪ የሆኑት በስጋት ጠየቁ

"ላ ሴንት-ሻርል" አላቸው ፌዶር ባላኖቪች "የጎቲክ ስነ-ጥበብ እንቁ!"

"እንደዚህ" ጨመረላቸው ጋብሪዬል ሰውነቱን እያንቀሳቀሰ

ተጓዦቹ ተረጋግተው ፈገግ አሉ

"ታድያስ?" አለ ጋብሪዬል "ትገልፅላቸዋለህ?"

ፌዶር ባላኖቪች ያስጐብኚ ገለፃውን በልዩ ልዩ ቋንቋ አሰማቸው

"እንዴ!" አደነቀች ዛዚ፣ ሊቅ እየመሰለች "ይችልበት የለም'ንዴ፣ ይሄ የሩስኪ ዘር!"

ችሎታው ይበልጥ የታየው ደሞ ተጓዦቹ መስማማታቸውን ለመግለፅ እየፈነጠዙ ገንዘባቸውን አውጥተው ሲከፍሉ ነበር። ይህም ለጋብሪዬል ያላቸውን አድናቆት እና ፌዶር ባላኖቪች የቋንቋዎች እውቀቱ ስፊ መሆኑን የሚያመለክት ነበር።

"አሁን መጣሁ ወደ ሁለተኛው ጥያቄዬ" አለች ዛዚ "ቱር-ኤፌል ስር ያገኘሁህ ጊዜ የውጪዎቹን ቋንቋ ከሱ እኩል ትናገር ነበር። ምን ነክቶህ ነበር? እና ለምን አሁን አትናገረውም?"

"ይህን ላስረዳሽ አይችልም" አለ ጋብሪዬል "እንዴት እንደሚመጡልን ከማይታወቁት ነገሮች አንዱ ነው። ማለት፣ የጂንየስ ብልጭታ"

የግረናዲን ብርጭቆውን ጨለጠ

"ምን ታረጊዋለሽ?! አርቲስት ስንባል እንደዚህ ነን"

# አስራ ሁለት

ትሩስካዮን እና ባልቴትዋ ሙዋከ ጥቂት መንገድ ሄደው ነበር። በቀስታ ጕን ለጕን፣ ግን በቀጥታ ወደ ፊት፣ እና ደሞ በዝምታ። ይህን ጊዜ ጕን ለጕን እየሄዱ መሆናቸው ታወቃቸው፣ ተያዩና ፈገግ አሉ፣ ልብ ለልብ ተነጋገሩ። እየተያዩ እንደቆሙ ቆዩ ምን እንደሚባባሉ፣ በምን ቋንቋስ እንደሚገላለፁ እያሰቡ። ይህን ጊዜ ባልቴትዋ መገናኘታቸውን ለማክበር አስበው ሴባስቶፖል ጕዳና ወደሚገኘው ካፌ-ድዩ-ቬሉሲፔድ ሄደው በቢራ እንዲቀዘቅዙ ሀሳብ አቀረቡ። ካፌው አንዳንድ ባለበረንዳ ነጋዴዎች አታክልታቸውን ከመደርደራቸው በፊት ጉሮሮዋቸውን የሚያረጥቡበት ነበር።

አንድ የእብነ በረድ ጠረጴዛና ከፋይ የለበሰ ወምበር ጋ ተቀመጡ። እና ሁለቱም ቢራቸውን በትእግስት እየተጕነጩ ቆዩ (ያቺ በርበሬ የመሰለ ቆዳ ያላት አስተናጋጅ ራቅ እስከትልላቸው) በመጨረሻም የፍቅር ቃላቱን በቢራቸው አረፋዎች እያሻገሩ ያዥጕደጕዱት ዘንድ!!

ሰዉ ባለደማቅ ቀለማት የፍራፍሬ ጭማቂ እና ባለግራጫ ቀለማት የአልኮል መጠጦች በሚጠጣበት ሰአት፣ እነሱ በተጠቀሰው የከፋይ አግድም ወምበር ላይ እንደተሰየሙ ይቆያሉ፣ በተገማመዱት ጣቶቻቸው ሽብር ውስጥ የሚከተውን የወሲብ ቅንዝር በስንትና ስንት ቃላት እየተለዋወጡ — በአካል እስኪተቃቀፉ ለማቆያ ያህል፡-

"ይቆዩኝማ" አለ ትሩስካዮን "ይህን ዩኒፎርም በቅፅበት አውልቄ ልጥለው አልችልም። የተራ ዜጋ ልብስ አለኝኮ" አለና ከፍ ብሎ በስተቀኝ በሚገኘው ስፈሮይድ ምግብ ቤት አፔራቲብ እንዲያዝዙ ገንዘብ ሰጣቸው። ምክንያቱም እሱ የሚኖረው ራቅ ብሎ ራምቡቶ መንገድ ዳር ነው።

ባላቸው የሞተባቸው ወይዘሮ ሙዋከ ወደብቸኝነታቸው ተመለሱና በረዥሙ ተነፈሱ። "እብደት ነገር ውስጥ እየገባሁ ነው" አሉ በለሆሳስ

እነዚህ ጥቂት ቃላት ሳይደመጡ መንገድ ላይ ወድቀው አልቀሩም፣ ከደንቆሮነት በምንም ከማትጉራበት እንስት ጆሮ ውስጥ ገቡ።

ለውስጣዊ ጉዳይ ታቅደው የነበረ ቢሆንም፣ የሚከተለውን መልስ ከውጭ አስከተሉ

"ምንድነው እሱ የማይደረገው?"

"እንዴ! አንቺዬ፣ እዚህ ነሽ ለካ" አሉ ባልቴትዋ ሙዋከ

"ቅድም ሳያችሁ ደስ ትሉ ነበር፣ እርስዎና ፖሊስየው"

"ላንቺ አይን" አሉ ባልቴትዋ ሙዋከ

"በኔ አይን? ምን በኔ አይን?"

"ደስ ማለታችን" አሉ ባልቴትዋ ሙዋከ "ለሌላ አይን ግን ደስ አንልም"

"ደስ የማይላቸውን" አለች ዛዚ "ሜርድ! እላቸዋለሁ"

"ብቻሽን ነሽ 'ንዴ"

"እዎና! እየተንሸራሸርኩ ነው"

"ለአቱም ቦታውም ልጃገረድ ብቻዋን የምትለቀቅበት አይደለም። አጎትሽ የት ደረሰ?"

"ተንገኖቹን ያንከራትታቸዋል። ወደ ፑል መጫወቻ ወስዷቸዋል። እስከዛው እኔ ንፋስ እየተቀበልኩ ነው። ምክንያቱም እኔ ፑል ይደብረኛል። ግን ለእራት ተመልሼ መሄድ አለብኝ። ከዛ በኋላ ሄደን ሲደንስ እናየዋለን"

"ሲደንስ? ማ?"

"አጎቴ"

"ይሄ ዝሆን ይደንሳል?"

"ያውም ከሚኒ-ስከርት ያጠረ ጉርድ ለብሶ ነዋ!" ዛዚ በኩራት መለሰች

ባልቴትዋ ሙዋከ ተገርመው ፀጥ አሉ

ምግብ በጅምላና በችርቻሮ የሚሸጥበት ሱቅ ደረሱ፣ መኪናዎች በአንድ አቅጣጫ ብቻ ከሚሄዱበት ከዚህ ጉዳና ተሻግሮ፣ አንድ መድሀኒት

ቤት አረንጓዴ ደማቅ ብርሃኑን ህዝቡ ላይ ይዘረግፈዋል:: ሰዉ ይስገበገባል በካምሲላ፣ ተፈጭቶ ለተቀመመ የገጠር ስጋ፣ ለቺዝ፣ ለኬክ፣ ወዘተ

ይሄ መርመስመስ እየቀጠለ እያለ፣ ህዝቡ ወደየማምሻው በሜትሮ ለመሳፈር ሲሄድ ብዛቱ እየቀነሰ ይሄዳል::

ባላቸው የሞተባቸው ወይዘሮ ሙዋክ በረዥሙ ተነፈሱ

"ካንቺ ጋር ትንሽ ብራመድ ቅር ይልሻል?"

"ምን እንደማደርግ ለመከታተል ፈልገው ነው?"

"አይደለም ኧረ! አብረሽኝ እንድትሆኚ ፈልጌ ነው"

"ስለሱ ስሜት አይሰጠኝም:: ብቻዬን መሆን ነው 'ምመርጠው"

ባለቤትዋ ሙዋክ አሁንም በረዥሙ ተነፈሱ

"እና እኔ ብቻዬን መሆኔ እየከፋኝ?!... ብቻዬን... ብቻዬን"

"ብቻዬን የቂጤን አበሳ ይስጠው!" አለች ልጃገረዲቱ፣ የተለመደ የቋንቋ እርማትዋን እያካሄደች

"ለትልልቅ ሰዎች አስቢልን 'ንጂ" አሉ ወይዘሮዋ፣ እንባ እየተናነቃቸው "አቤት ብታውቂ ኖሮ!..."

"ለፖሊስየው ነው እንዲህ 'ሚሆኑለት?"

"አይ ፍቅር!... አድገሽ ብታውቂው..."

"ዞረው ዞረው እንዲህ አይነቱን ፀያፍ ነገር ሊያወሩልኝ እንደሆነ ገብቶኛል:: በዚህ ከቀጠሉ ፖሊስ ነው ምጠራሎት - ሌላ ፖሊስ"

"ይሄስ ጭካኔ ነው!" አሉ ባልቴትዋ ምርር ብለው

ዛዚ ትከሻዋን ከፍ ዝቅ አደረገች

"ምስኪን አሮጊት... አይዞት፣ መጥፎ ሰው አይደለሁም:: እስኪሻሎት ድረስ አብሬዎት እቆያለሁ:: ልቤ ደግ ነው፣ እሺ?"

ሙዋክዋ መልስ ለመስጠት ጊዜ ሳያገኙ፣ ዛዚ ጨመረችላቸው:-

"እንድያም ሆኖ ግን... ዛፓ ብሆን እኔ..."

"እምትይው ይገባኛል:: ግን ምን ታረጊዋለሽ፣ ነገሮች እንደዚያ ሆኑ:: ምናልባት አጎትሽ ባይጠለፍ ኖሮ..."

"ባለትዳር ነው ብዮታለሁ'ኮ። አክስቴ ደሞ ከርሶ አስሬ ይበልጥ ታምራለች"

"ቤተሰቦችሽን ማሞጋገሱን ተይው። የኔው ትሩስካዮን ይበቃኛል ማለቴ በኋላ ሳገኘው ይበቃኛል"

ዛዚ ትከሻዋን ከፍ ዝቅ አደረገች

"ይሄ ሁሉ ሲኒማ ነው" አለች "ለጨዋታችን ሌላ ርእስ የሉትም?"

"የለኝም!" አሉ ባልቴትዋ ሙዋክ አጠንክረው

"እሺ 'ንግዲያው" አለች ዛዚ እሷም እያከረረች "የደግነት ሳምንት ያለቀ መሆኑን ልንገሮት። ቻው!"

"እንድያም ሆኖ አመሰግናለሁ፣ ልጄዋ" አሉ ባልቴትዋ ሙዋክ፣ በይቅር ባይነት።

መንገዱን አብረው ለየብቻ ተሻገሩና ስፌሮይድ ምግብ ቤት ሲደርሱ ተገናኙ

"እንዴ!" አለች ዛዚ "አሁንም እዚህ ኖት። እየተከተሉኝ ነው'ንዴ?"

"ሌላ ቦታ ባይሽ በመረጥኩ" አሉ ባልቴትዋ

"እኚህስ ሲበዛ ለየት ያሉ ልዩ ናቸው። ካምስት ደቂቃ በፊት ከርሶ መገላገል አቅቶን ነበር። አሁን ደሞ ርቀን መሸሽ አለብን። ፍቅር ነው 'ንዲህ 'ሚያረጎት?"

"ምን ይደረግ? እውነት ለመናገር፣ ከትሩስካዮኔ ጋር እዚሁ ቀጠሮ አለኝ"

ከምድር በታች ትልቅ ሁካታ ይሰማል

"እኔ ደሞ ከአጎቴ ጋር" አለች ዛዚ "ሁሉም እዛ ናቸው። እታች። ይሰሙዋቸዋል እንደ ቅድመ-ታሪክ ዘመን ሲተራመሱ? ከዚህ በፊት እንደነገርኩዎት፣ እኔ የሆንኩ 'ንደሆን የፑል ነገር..."

... ባልቴትዋ ሙዋክ ከምድር በታች ቤቱ ውስጥ ምን ምን እንዳለ ዘረዘሩ

"እዛ የለም የርሶ ዱርዩ" አለች ዛዚ

"ገና ነው" አሉ ወይዘሮዋ "ገና ነው"

"ነው'ንጂ ዛፓዎች መጠጥ ቤት አይገቡም፡፡ ከልክል ነው"

"እዚያ ላይ ተሸወድሽ" የሲቪል ልብስ ለማጥለቅ ነው የሄደው?"

"እና እንደዚያ ሆኖ ሲያዩት ያውቁታል?"

"አፈቅረዋለሁ!ኮ" አሉ ባልቴትዋ ሙዋከ

"እስከዛው ድረስ" አለች ዛዚ በቀላሉ "ይውረዱና ከኛ ጋር አንድ ቢራ ይጠጡ፡፡ ምናልባት'ኮ ከምድር በታች አዳራሹ ውስጥ ሊሆን ይችላል፡፡ አውቆ ያደረገው ሊሆንም ይችላል"

"ማጋነን አይገባም፡፡ ፖሊስ እንጂ ሰላይ አይደለም"

"እንዴት ያውቃሉ? ምስጢሩን ነግሮዎታል'ንዴ? ገና ከአሁኑ?"

"እምነቴን ጥዬበታለሁ" አሉ ሴት ወይዘሮዋ፣ ከመመሰጣቸው ባላነሰ ሚስጥራዊነት

ዛዚ አሁንም እንደገና ትከሻዋን ከፍ ዝቅ አደረገች

"ታድያስ... አንድ ቢራ ሀሳቦትን ያድስሎታል"

"ይሁና" አሉ ባልቴትዋ፣ ለአቱን ካዩ በኋላ ፖሊሱ ፍቅረኛቸው እስኪመጣ ገና አስር ደቂቃ መጠበቅ እንደሚኖርባቸው በማወቃቸው

ከደረጃው ከፍታ ሲመለከቱ፣ ትንንሽ ኳሶች አረንጓዴ ምንጣፍ ላይ በፍጥነት ሲንሸራተቱ፣ ሌሎች ከነሱ ቀለል ያሉ ደሞ ከቢራ ጠርሙሶቹና ከሰዎቹ እርጥብ ብብት በሚተንነው ጉም ሲዥጐረጐሩ ይታያል

ዛዚ እና ባልቴትዋ ሙዋከ ጋብሪዬል በተጓዦቹ በጠባቡ ተከብቦ በጣም አስቸጋሪ የሆነ የከረምቦላ ውርወራ ሲያጠና አዩት፡፡ ተሳካለትና በተለያዩ ቋንቋዎች አሞገሱት፡፡

"ተደሰቱ'ኮ፣ አደል?" አለች ዛዚ በአጎትዋ እየተኩራራች

ወይዘሮዋ "በጣም"

"አቤት እንዴት ጅል ናቸው!" ቀጠለች ዛዚ በሀዘኔታ "ደሞ'ኮ ገና ምንም አላዩም፡፡ ጋብሪዬል ከሚኒ-ስከርት ያጠረ ጉርድ ለብሶ ሲያዩት እንዴት እንደሚደነቁ!"

ሴት ወይዘሮዋ ፈገግ አሉ፡፡ "አክስት ማለት ግን ምንድነው?" ጠየቀቻቸው ዛዚ እንደ ቅርብ ጓደኛ "ቡሽቲ፣ ሰዶማዊ፣ ሆሞ - በነዚህ መካከል ምን ያህል ልዩነት ይኖራል?"

"አይ አንቺ ምስኪን ልጅ!" አሉ ባልቴትዋ በረዥሙ እየተነፈሱ፣ በፖሊስየው ማራኪነት ብትንትኑ ወጥቶ ከነበረው ከራሳቸው ግብረ-ገብ ርጋፊ አንዳንድ ጊዜ ለሌሎች ከሚተርፈው እያቀበሉዋት። ጋብሪዬል አንድ እሱ ራሱና ጥቂት አረፎች ብቻ የሚችሏትን የከረምቦላ ምት አልሞ እንደሳተ አያቸውና አጭር የእጅ ሰላምታ ላከላቸው። ከዚያ ረጋ ብሎ ጨዋታውን ቀጠለ፣ ቅድም የፎረሸውን ውርወራ ችላ በማለት።

"ተመልሼ መውጣቴ ነው" አሉ ባልቴትዋ በቆራጥነት

"መልካም ቀይ ፅጌረዳ!" ተመኝችላቸው ዛዚ፣ ከረምቦላውን ለመከታተል እየተጠጋች።

ጋብሪዬል የኳሶቹን አሰላለፍ ሲያነጣጥር፡- ተመቺዋ ኳስ F2 ላይ ሌላዋ ነጭ ኳስ G3 ላይ ቀይዋ F4 ላይ ናቸው። ጋብሪዬል ዘዴውን እያሰላሰለ የመምቻውን እጀታ ሰማያዊ ቾክ ቀባው

"ሰው ላይ ልጥፍ ትላለች ባልቴትዋ" አሳት ዛዚን

"ወደ መጠጥ ቤትህ ስንመለስ መጥቶ ያዋራህ ዛፓ ጋር በአደገኛ እየተበሳሰሉ ነው"

"ስለሱ ስሜት አይሰጠንም። አሁን ተይኝ ልጫወት። ቀልድ የለም። ሰላም። እርጋታ።"

በሰዉ ሁሉ አድናቆት እየተከበበ፣ ዘንጉን ወደ ላይ አነሳ፣ በመቀጠል በጫፉ አጫዋችዋን ኳስ በሾጣጣ ክብ እንድትሄድለት አሳናት። የተመታችው ኳስ የታቀደላትን መስመር ስታ፣ አረንጓዴው ምንጣፍ ላይ በሰያፍ መንከባለልዋ በቤቱ አዛዦች የተተመነ ዋጋ አስገኝችለት። በቅድምያ ሳይነገራቸው በአጐራባች ጠረጴዛዎች ላይ ተመሳሳይ ውጤት ለማምጣት ሲጥሩ የነበሩት ተጓዦች አድናቆታቸውን ገለፁ። ሄደው እራታቸውን የሚበሉበት ሰአት ደረሰ።

ተጨማሪ ወጪውን ከከፈለና የሂሳብ ካርኔውን በትክክል ካከፋፈለ በኋላ ጋብሪዬል ሰዎቹን ሰበሰበና (የፒንግ-ፖንግ ተጫዋቾቹ ሳይቀሩ) እንዲመገቡ ወደ ላይኛው አዳራሽ ወሰዳቸው። ከጐዳናው ጋር ኩታ - ገጠም የሆነው ምግብ ቤት ለዚህ ጉዳይ ተስማሚ የሚሆን መሰለው። እና አንድ አግድም ወምበር ላይ ተንሰራፍቶ የተቀመጠው ባልቴትዋ ሙዋከንና ትሩስካዮንን ፊት ለፊት ካለው ጠረጴዛጋ ከማየቱ በፊት ነበር። አይተውት መደሰታቸውን በምልክት ሲያሳዩት፣ የከት ልብስ ለብሶ ከወይዘሮዋ ጋር የሚሽኮረመመው ሰውዬ ፖሊስየው መሆኑን ለመለየት ተቸገረ። ጋብሪዬል

ደግ ልቡ ከሚነግረው ሌላ ሳያስብ ከጉሳው ጋር እንዲቀሳቀሱ በእጁ እንቅስቃሴ ጋበዛቸው፣ እነሱም ለእሺታ አላመነቱም!

ቱሪስቶቹ የጉሳው አባላት ይህን የመሰለውን አይተው የማያውቁትን ያካባቢ ልዩ ውበት ሲመለከቱ አድናቆቱ ፈነቀሳቸው። ይህ ሲሆን ሳለ ሸርጥ የለበሱ ቦዮች ማቅረብ የጀመሩት ልዩ ልዩ የፈረንሳይና የጀርመን የምግብ አይነት ላብ ባጠመቃቸው ጠርሙስ ቢራዎች የታጀበ ነበር፡-

ዛዚ ምግቡን ስትቀምሰው በቀጥታ ሜርድ መሆኑን አወጀች። ህንፃ ጠባቂ የሆኑት እናቱ በጨዋ ባህል የበሬ ስጋ mironton በሚባል የምግብ አበሳሰል ያሳደጉት ፖሊስ፣ እና በበኩላቸው የድንች ጥብስ ኤክስፐርት ባለሙያ የሆኑት ሴት ወይዘሮ፣ እና ጋብሪዬል ራሱ በናይት-ክለቦቹ የሚቀርቡትን መምጫቸው ያልታወቀ ምግቦች የለመደ ሆኖ፣ ይህ ሁሉ ሆኖ ሶስቱም ልጅቱ ዝም እንድትል ሊመክሩዋት ተጣደፉ። ይሄ ፈሪ ዝምታ እየፈቀደላቸው'ኮ ነው አቅራቢዎቹ በውስጣዊ ፖለቲካ ዘርፍ በአሸር-ባሸር ምግብ የህዝቡን የማጣጣም ህዋስ የሚያበላሹት፣ በውጭ ጉዳይ ፖለቲካው ዘርፍ ደሞ ለውጭ አገር እንግዶች ሆን ብለው ሲሰጡዋቸው፣ ከጥንታውያን ጎልዋ አያቶቻችን የተወረሰውን የፈረንሳይ የምግብ አበሳሰል ጥራት የሚበክሉት። ሌላ ሌላውን እንተውውና፣ ሁሉም እንደሚያውቀው፣ ከጎልዋ አያቶቻችን በተጨማሪ በርሜል መስራትን፣ እና ኢ-ስእላዊ አርትን ተቀብለናል።

"መናገር አትከለክሉኝም መቸስ" አለች ዛዚ "ይሄ (በእንቅስቃሴ ታሳያለች) ያቅለሸልሻል"

"እውነት ነው፣ እውነት ነው" አለ ጋብሪዬል "ላስገድድሽ አልፈልግም። ይገባኛል'ኮ እኔ፣ አይደለም 'ንዴ፣ ማዳም?"

"አንዳንድ ጊዜ" አሉ ባልቴትዋ ሙዋክ "አንዳንድ ጊዜ"

"ነገሩ እዚህ ላይ አይደለም" አለ ትሩስካዮን "ለጨዋነት ተብሎ ነው"

"ጨዋነት የቂጤን አበሳ ይስጠው!" አለች ዛዚ

"አንቱ" አለው ጋብሪዬል ፖሊስየውን "እቺን ልጅ እኔ እንደሚታየኝ አሳድጋት ዘንድ እንዲፈቅዱልኝ እጠይቃለሁ። እኔ ነኝ ሀላፊነቱ የተጣለብኝ። አይደለም'ንዴ፣ ዛዚ?"

"ይመስላል" አለች ዛዚ "ለማንኛውም፣ ምንም ቢመጣ ይህን ጭምልቅልቅ አልበላም"

"ማድሟዜል ምን ይፈልጉ ይሆን?" በግብዝነት ጠየቀ አንዱ ከይሲ ቦይ ረብሻ እየሸተተው

"ሌላ ነገር ነው 'ምንፈልገው" አለች ዛዚ

"የአልዛስ ጉመን ወጣችን ወጣትዋን ማድሚዜል አላስደሰታቸ ውም?" ጠየቀ ክይሲው ቦይ።

ምፀት መናገሩ ነበር፣ ይሄ ጆል

"የለም" አለ ጋብሪዬል በአስገዳጅ ስልጣን "አልወደደችውም"

በዩ ለጥቂት ቅፅበት የጋብሪዬልን ግዙፍነት መዘነ፣ ትሩስካዮንም ፖሊስ መሆኑን አውቋል። ይህን ይህል ሀይለኛ ጉልበት ባንዲት ልጅ እጅ መጠቃለሉን ሲገነዘብ ጊዜ ለከት-የለሽ አፉን ዘጋ። ይህን ጊዜ ከሱ የባሰ ጆላጆል አስተዳዳሪ ጣልቃ ለመግባት ሞከረ። ወድያው የማስመሰል ትያትሩን ሲጀምር፡-

"አይሆንም!" ብሎ ተንጣጣ "እኮ 'ንዴት ነው ባእድ ሰዎች ስለኛ ምግብ አዘገጃጀት አፋቸውን ሞልተው ለመናገር የሚደፍሩት? ሜርድ! የዚህ አመት ቱሪስቶችስ ሲበዛ ደፋር ሆኑ። ብለው ብለው'ኮ bectance አበሳሰልን እናውቃለን ይሉ ይሆናል"

ከቱሪስቶቹ አንዳንዶቹን ጠየቃቸው፡-

"ስሙኝ'ስቲ፣ አያሌ ጦርነቶችን በድል አድራጊነት የተዋጋነው እናንተ መጥታችሁ ማስቲካችሁን እያኘካችሁ አይስክሬማችን ላይ እንድትተፉበት ይመስላችኋል 'ንዴ? ትልልቁን ቀያይ እና የሚያነደውን አልኮል በግንባራችን ላብ የምናመርተው እናንተ ባመጣችሁት ቆሻሻ ኮካ-ኮላ ወይ ኪያንቲ ወይን እንዲጣበብ ይመስላችኋል? እናንተ ሰው በምትበሉበት ዘመን የጠበሳችሁትን የጠላቶቻችሁን አጥንት ቅልጥም ስትመጥጡ፣ ኢየሩሳሌምን ነፃ ለማውጣት የዘመቱት የመስቀል ጦረኛ አያቶቻችን ቢስቴካ ፓርማንትዬ በድንች ጥብስ ያበስሉ ነበር፣ ይህም ልታዘጋጁት ሞክራችሁ እንኳ ስለማታውቁት ስለ አሳማ ቋሊማ በፋሶልያ ሳንናገር ነው። አላስደሰታችሁም? የለም አላችሁ? ስለነገሩ የምታውቁ ይመስል!"

ትንፋሹን ሰበሰበና በጨዋ አባባል ቀጠለ

"እንደዚህ ያስኰረፋችሁ ምናልባት ዋጋው ይሆን? የኛ ዋጋ ግን ሀቀኛ ነው። አይገባችሁም? ቆንቋና ሁሉ! ያን ሁሉ የምታረጉበት የጠፋችሁን ዶላራችሁን ከግምት ባያስገቡ ኖሮ ግን ባለቤትየው ግብር በምን ይከፍሉ ነበር?"

"መገልፈጥህን ጨረስክ?" ጠየቀ ጋብሪዬል

አስተዳዳሪው በንዴት ናላው ዞርበት አንራ!

"ይሄ ደሞ ፈረንሳይኛ ተናገርኩ ብሎ ሞቷል" እያለ መጮህ ጀመረ ወደ ቅድሙ ከይሲ ቦይ ዞረና ቀጠለ

"ትሰማዋለህ አንተ ይሄ ባለጌ ሜርድ በቋንቋችን ሲያናግረኝ እንደ ደፈረ? ይሄስ በጣም ይቀፋል!"

"ግንኮ መናገሩን ይችልበታል" አለ ከይሲው ቦይ፣ እንዳይደበደብ በመፍራት

"ክሀዲ!" አለው አለቃው፣ ንዴቱ የባሰውን ገንፍሎ እየተንቀጠቀጠ

"ጥርሱን አታስለቅመውም'ንዴ? ምን እየጠበቅክ ነው?" አለችው ዛዚ ጋብሪዬልን

"እሽ!!" አለ ጋብሪዬል

"የወንድ መሳርያውን ይጨፍልቁለት!" አሉ ባላቸው የሞተባቸውን ሙዋከ "መኖር እንዲማር"

"እኔ ይህን ማየት አልፈልግም" አለ ትሩስካዮን ፊቱ እየተለወጠ "እናንተ ስራችሁን እስከታጠናቅቁ እኔ ከዚህ ልጥፋ። እንድያውም ወደ ትራፊክ ጣብያ እምደውለው ስልክ አለኝ"

ከይሲው ቦይ ወድያው አስተዳዳሪውን ለማስጠንቀቅ ሆዱን በክርን ነካ እያደረገው የጋብሪዬልን አስተያየት አጠናከረ። ወድያው ሁኔታዎች ተለወጡ።

"ይሄ ከተባለ ዘንዳ" ሲል ጀመረ አስተዳዳሪው "ይህ ከተባለ ዘንዳ፣ ማድሟዜል ምን ምን ይሻሉ?"

"ይሄ ያቀረባችሁልኝ እንትን" አለች ዛዚ "የለየለት ሜርድ ነው"

"ስህተት ተሰርቷል" አለ አስተዳዳሪው በጥሩ ፈገግታ "ስህተት ተሰርቷል። ይሄ ለዚያኛው ጠረጴዛ ነበር፣ ለተንገሮቹ"

"ከኛ ጋር ናቸው" አለ ጋብሪዬል

"ሀሳብ አይግባዎት" አለ አስተዳዳሪው በግብረ-አበር አስተያየት "ቀይ ጕመን ወጤን በቀላሉ እተካዋለሁ። በሱ ፈንታ ምን ይፈልጋሉ፣ ማድሟዜል?"

"ሌላ ቀይ-ጕመን ወጥ"

"ሌላ ቀይ ጕመን ወጥ?"

"አዎን" አለች ዛዚ "ሌላ ቀይ ጕመን ወጥ"

"ሌላኛው ከዚህኛው አይሻልም ብዩ ነው" አለ አስተዳዳሪው "ይህን አሁን የምነግሮት የቅድሙ ጥያቄዎ ከሚደገም ብዩ ነው"

"እንግዲህ ከዚህ ነገር ሌላ የሚበላ የላችሁም ማለት ነው?"

"ለርስዎ ለማቅረብ" አለ አስተዳዳሪው "አቤት ይሄ ግብር የሚሉት ነገር ባይኖር ኖሮ!" (በረዥሙ ይተነፍሳል)

"ኛም! ኛም!" አለ አንዱ ተጓዥ፣ ከጕመን ወጥ ሰሀኑ የመጨረሻውን ጉርሻ እያጣጣመ

በእጁ እንቅስቃሴ እንደገና መፈለጉን አሳየ

"ይኸዋ!" አለ አስተዳዳሪው በድል አድራጊነት

እና ከይሲው ቦይ ያነሳውን የዛዚን ሰሀን ወድያው ሰውየው ፊት ቁጭ አደረገለት።

"ሙያን አጣርታችሁ የምታውቁ መሆናችሁን ስለተገነዘብኩ" አለ አስተዳዳሪው ሲቀጥል "ከበቆሎ ጋር በቆርቆሮ የታሸገ የበሬ ስጋችንን ላምጣላችሁ። ቆርቆሮውን እዚሁ እያያችሁኝ እከፍተዋለሁ"

"እስኪገባው ብዙ ጊዜ ወሰደ" አለች ዛዚ

በእፍረት ርቆ ሲሄድ ጋብሪዬል ደጉ ሊያፅናናው ጠየቀው፡-

"ግረናዲናችሁንሳ? ጥሩ ነው የናንተ ግረናዲን... እ?"

# አስራ ሶስት

ማዶ ፐቲ-ፒዬ ስልኩ ሲደውል ለሶስት ሰከንድ አየችው፣ ከዚያ በአራተኛው፣ በመደወያው በኩል ምን እየተፈጠረ እንደሆነ ለማዳመጥ አሰበች። መሳሪያውን ከመስቀያው እንዳወረደችው ጋብሪዬል ለባልተቤቱ ሁለት ቃል መናገር መፈለጉን ነገራት

"ፈጠን!" ሲል ጨመረ

"አልችልም" አለች ማዶ ፐቲ-ፒዬ "ብቻዬን ነኝ። መስየ ቱራንዶ አሁን የሉም"

"ታወራለህ ታወራለህ" አለች ላቨርድዩር "ይህን ብቻ ነው ማድረግ 'ምታቀው"

"አንቺ ጅል" አለ የጋብሪዬል ድምፅ "ሰው ካለ አስወጪው። ገባሽ አንቺ ደደብ?"

"አዎን፣ መስየ ጋብሪዬል"

"ስልኩን ዘጋችው። እንዲህ ቀላል አልነበረም። እንደ እውነቱ፣ አንድ ደምበኛ ነበረ። ደሞ ትታው ልትሔድም ትችል ነበር፣ ሰውየው ሻርል ስለነበረ። ሻርል ደሞ ትንሽ ገንዘብ ለመውሰድ ብሎ ካዝና ውስጥ የሚያነፈንፍ አይነት አይደለም። ሀቀኛ ሰው ነው ሻርል። የዚህ ማረጋገጫም አሁን ማዶ ፐቲ-ፒዬን ጋብቻ መጠየቁ ነው።"

ማዶ ፐቲ-ፒዬ ስለዚህ ፐሮብሌም ማሰብ ገና ከመጀመርዋ ስልኩ እንደገና መጥራት ጀመረ

"ሜርድ!" አገሳ ሻርል "እዚህ ሸርሙጣ ቤት ሰላም ማግኘት አልተቻለም"

"ታወራለህ፣ ታወራለህ" አለች ላቬርድዩር፣ ሁኔታዎች እያስጨነቋት "ይህን ብቻ ነው ማድረግ 'ምታቀው"

ማዶ ፕቲ-ፒዬ ማዳመጫውን አነሳች፣ ከቅድሙ የባሰ ስድብ ሲወረውርባት ሰማች

"እንዳትዘጊ፣ አንቺ ቡዳ! የት መልሰሽ እንደምትደውይልኝ አታውቂም፡፡ እኮ ፈጠን! ብቻሽን ነሽ ወይስ ሰው አለ?"

"ሻርል አለ"

"ከሻርልማ ምንም 'ሚፈለግበት አይኖርም" አለ ሻርል በጨዋነት

"ታወራለህ፣ ታወራለህ" አለች ላቪድዩር "ይህን ብቻ ነው ማድረግ 'ምታውቀው"

"እሱ ነው እንዲህ አፉን 'ሚከፍተው?" ጠየቀ ቴሌፎኑ

"አይደለም፡፡ ላቪርዲዩር ናት፡፡ ሻርል ስለ ጋብቻ እያናገረኝ ነው"

"እረ! ቆጠረ" አለ ቴሌፎኑ፣ ስሜት ሳይሰጠው "ይሄ ታድያ ሄዶ ማርሰሊንን ከመጥራት አያግደው፣ አንቺ ደረጃዎቹን እየተደገፍሽ መውጣት ካልፈለግሽ፡፡ ይህን ላንቺ ሲል ያረግልሻል፣ ሻርልየው"

"አጠይቀዋለሁ" አለች ማዶ ፕቲ-ፒዬ

(ትንሽ ቆይታ ተመለሰች)

ማዶ ትእግስቷን ጨረሰች

"ታድያስ፣ እየመጣ ነው?" ጠየቀ ስልኩ

"እምን" አለች ማዶ ፕቲ-ፒዬ (በምልክት እየጠራችው)

ከዚህ ሁሉ በኋላ ሻርል ብርጭቆውን ጨልጦ በዝግታ ወደ ማዳመጫው ተጠጋ፡፡ ከዚያ መሳርያውን ከምናልባት-የወደፊት ባልተቤቱ እጅ እየመነጨቀ፣ ይህን ኮምፒዩተራዊ ቃል ሳከ፦

"አሎ"

"አንተ ነህ፣ ሻርል?"

"ነኝ"

"በል ቶሎ በልና ማርሰሊንን ፈልግልኝ ላናግራት፡፡ አስቸኳይ ነው"

"እኔ ከማንም ትእዛዝ አልቀበልም"

"ሽረ ባክህ ነገሩ ሌላ ነው። ቶሎ በል እያልኩህ?! አስቸኳይ ነው"

"እኔ ደሞ ከማንም ትእዛዝ አልቀበልም እያልኩህ?!" ብሎ ስልኩን ዘጋ

ሲያዩት ማዶ ፕቲ-ፒዬ ከባንኮኒው ጊላ ከሀሳቧ ጋር እየተጫወተች ይመስላል ወደ ባንኮኒ ተመለሰ።

"ታድያስ" አለ ሻርል "ምን አሰብሽ? እሺ ነው? እምቢ ነው?"

"ነገርኮት'ኮ" አንሾካሾከች ማዶ ፕቲ-ፒዬ "እንደዚሁ ዝም ብለው ነው የነገሩኝ፣ ሳያስጠነቅቁኝ። ደነገጥኩኝ። ይሆናል ብዬ አላሰብኩም ነበር። ማሰብ ይጠይቃል፣ መስየ ሻርል"

"እስካሁን ያላሰብሽበት ይመስል"

"እኔ መስዩ ሻርል፣ ሰው አያምኑም መቸስ፣ ኢ-አማኒ ኖት"

የእንትን-እቃው ደወል እንደገና ቴሌድምፆችን ማሰማት ጀመረ

"እንዴ! ደሞ ምን ሆነ፣ ምን ነካው?"

"ወደዛ ተይው ይቅር" አለ ሻርል

"ያን ያህልም ድርቅ ማለት አይገባም። ምንም ቢሆን ጓደኛ ነው"

"ነው። ግን ልጅቱ ስትጨመርበት ምንም ልክ አይመጣም"

"ስለልጅቱ ስታስቡ። በሷ እድሜ'ኮ ይሄ የአራዳ ቋንቋ መሆኑ ነው"

ነገርየው በማንኮራፋት ድምፅ ሲቀጥል ጊዜ፣ እንደገና ሻርል ከተነቀለው መሳሪያ ጫፍ ጋ ቆመ

"አሎ!" አጓራ ጋብሪዬል

"አቤት" አለ ሻርል

"በል'ንግዲህ ጅል አትሁን። ፈጥነህ ወደ ማርስሊን ሂድ። ደሞ ተወኝ ማበሳጨትህን አትጀምረኝ"

"ይገባሀል?" አለ ሻርል በትእቢት ድምፅ "እያስቸገርከኝ'ኮ ነው"

"አይደለም'ንጂ!" ጮኸ ቴሌፎኑ "ጆሮ አይሰማው የለ! አስቸገርኩህ አንተን? ምን የሚረባ ጉዳይ እየሰራህ ሊሆን ይችላል'ና ነው?"

ሻርል እጁን እመሳሪያው መደወያ አካል ላይ በሀይል አስቀመጠና፣ ወደ ማዶ ዞሮ ጠየቃት፡-

"እሺ አልሽ? እምቢ አልሽ?"

"እሺ አልኩ" አለች ማዶ ፐቲ-ፒዬ፣ ፊቷ በእፍረት እየቀላ

"የውነት?"

(በእጇ ምልክት የውነት! ትለዋለች)

ሻርል እጁን ከመደወያው አንስቶ፣ ከወድያኛው የስልኩ ጫፍ ሲጠብቅ ለቆየው ጋብሪዬል የሚከተለውን አሳወቀው፡-

"ይኸውና፣ እምነግርህ የምስራች አለኝ"

"ስሜት አይሰጠኝም። ሂድና... ማርሰሊንን..."

ሻርል በተቻለው ፍጥነት ቀጠለ፡-

"ማዶ ፐቲ-ፒዬና እኔ፣ አሁን ተጫጨን"

"እንኳን! በቁም ነገር ሳስብበት ጊዜ፣ ተወው አትድከም..."

"የነገርኩህ ነገር ገብቶሀል? ማዶ ፐቲ-ፒዬና እኔ፣ ልንጋባ ነው"

"አለኝቶህ ከሆነ። ማርሰሊን እንድትቸገር አያስፈልግም። ዝም ብለህ ንገራት ልጅቱን ሞን-ደ-ፒዬቴ ልወስዳት ነው ትርኢቱን እንድታይ። አብረውኝ የሚሄዱ የተከበሩ ተጓዦች አሉ፣ እና አንዳንድ ጓደኞች - ሙሉ ሰራዊት ነው፣ ምን አለፋህ። የኔ ሾው ደሞ ለዛሬ ማታ በተለየ ነው 'ምዘጋጅበት። ዛዚንም ጥሩ ይጠቅማታል፣ ለሷ ድንቅ እድል ይሉሀል ይሄ ነው።"

"እንዴ! እውነቴን'ኮ ነው፣ አንተም ያለብህ መምጣት ብቻ ነው፣ ከማዶ ፐቲ-ፒዬ ጋር ለፍጥምጥሚችሁ የደስ ደስ ይሆናችኋል፣ እውነቴን አደል? ይሄ'ኮ ሊጠጡለት ይገባል! እኔ ነኝ ምከፍለው — ለትርኢቱ ጭምር። ከዚያ ቁራንደ፣ እሱም ይምጣ ይሄ ጉመን ራስ፣ ላቤርድዩርም፣ እሚያስደስታት ከመሰላችሁ። እና ግሪዱ፣ ልንረሳው አይገባም ግሪዱን። sac're ግሪዱ።"

እዚህ ላይ ጋብሪዬል ስልኩን ዘጋ

ሻርል የስልክ መስሚያውን እንደተንጠለጠለ ተወው፣ እና ወደ ማዶ ፐቲ-ፒዬ እየዞረ፣ እንዳይረሳ ሊመዘገብ የሚገባው ቁምነገር ተናገረ

ታድያስ" አለ "ደኅና ነው? ጉዳያችን ተጠናቀቀ?"

ቱራንዶ ሲገባ "መጋባታችን ነው እኔና ማድሌን" አለው ሻርል

"አሪፍ ሀሳብ!" አለ ቱራንዶ "የደስ ደስ አንድ reconfortant ል.ጋብዛችሁ። ማዶን ማጣቴ ግን ያበሳጨኛል። ስትሰራ በሚገባ ነበር።"

"አዎን፣ ግን እዚሁ 'ምቀር ነኝኮ" አለች ማድሌን "እሱ ታክሲውን ሲነዳ እኔ ቤት ውስጥ መቀመጥ ይሰለቸኛል።"

"እውነት ነው" አለ ሻርል "በመሰረቱ ምንም ለውጥ አይኖርም፣ ልዩነቱ፣ ያን ነገር ስንሰራ በህጋዊነት ይሆናል"

"ዞሮ ዞሮ፣ ሁልጊዜ የሚመችንን ምክንያት እንፈጥራለን። ምን ትጋበዛላችሁ?"

"እኔ በበኩሌ ግድ የለኝም" አለ ሻርል

"ዛሬስ እኔ ነኝ የማቀራርብልሽ" አለ ቱራንዶ በጨዋነት፣ ቂጧን መታ እያደረገ። እንዲህ የማድረግ ልማድ አልነበረውም፣ በስራ ሰአታት ካልሆነ በስተቀር፣ ያውም የቤቱን ድባብ ሞቅ ለማድረግ ብቻ።

"ሻርል አንድ ፊርኒጥ-ብራንካ ለመውሰድ ይችላል" አለች ማድሌን

"እሱስ ሰው የሚፈልገው መጠጥ አይደለም" አለ ሻርል

"ቢሆንም በስድስት ሰአት አንዱን በሚገባ ጨልጠሀል" ቱራንዶ አስተያየቱን ሰነዘረ

"እውነት ነው ደሞ። እንግድያው ለኔ ቦዡሌ ወይን ይሁንልኝ"

ብርጭቆዋቸውን አጋጨ

ዛሬ ህጋዊ ስሆነው የጨለማ መደባዊ ትግላችሁ!" አለ ቱራንዶ

"እናመሰግናለን" መለሰ ሻርል፣ አፉን በኮፍያው እየጠረገ

"እሱ ብቻም አይደል" ሲል ቀጠለ፣ "ሄጄ ለማርሰሊን መንገር ይኖርብኛል"

"አትድከም ጋሽዬዋ" አለች ማድሌን "እኔ 'ሄዳለሁ"

"አገባህ አላገባህ ለማርሰሊን ምን ስሜት ይሰጣታል?" አለ ቱራንዶ "ሳትሰማው እስከ ነገ መቆየት ትችላለች"

"የማርሰሊን ጉዳይ ሌላ ነው" አለ ሻርል "ጋብሪዬል ዛዚዋን ከሱ ጋር አስቀርቷታል። እና ሁላችንን፣ አንተንም ጨምሮ፣ ሄደን የሱን ሸው አብረን እንድናይለት ጋብዞናል። በበኩሌ ደጋግመን እንደምናይለት ተስፋ አደርጋለሁ"

"አቤት!" አለ ቱራንዶ "አይቀፍህም? ፍጥምጥምህን ለማክበር ስትል ወደ ቡሽቲዎች ናይት-ክለብ ትሮጣለህ? ኧረ ልድገምልህ፣ አይዘገንንህም?"

"ታወራለህ፣ ታወራለህ" አለች ላቬርዲዩር "ይህን ብቻ ነው ማድረግ 'ምታቀው"

"አትጨቃጨቁ" አለች ማድሌን "እኔ ሄጄ ለማዳም ማርሰሊን እነግራቸውና፣ ለወዳጃችን ጋቢ ክብር ዘንጬ እለብሳለሁ"

ሄደች በረረች። ሁለተኛ ፎቅ ደረሱ፣ የበሩን መደወያ ተጫኑት ወይዘሪት እሙኚት። በንዲህ ያለ ደማምነት የተደወለ በር ላይከፈት አይችልም። ስለሆነም የተባለው በር ተከፈተ

"ደህና ዋልሽ፣ ማዶ ፕቲ-ፒዬ" አለች ማርሰሊን በልስላሴ

ይኸውሎት" አለች ማድሌን፣ ደረጃውን እየተጠማዘዘች ስትወጣ እንደ መተው ብላው የነበረ ትንፋሽዋ እየተመለሰ

"ይግቡና አንድ ብርጭቆ ግረናዲን ይጠጡ" አለች በልዝቡ፣

እያቋረጠቻት

"መልበስ አለብኛ"

"ሳይዎት ራቁትዎን አይደሉም" አለች ማርሰሊን በዝግታ

ማድሌን በእፍረት ፊቷ ቀላ። ማርሰሊን ለስለስ ብላ፡-

"እሱ'ኮ ያልነውን ብርጭቆ ግረናዲን አይከለክልም፣ አይደል? ሴቶች እንደመሆናችን..."

"ቢሆንም"

"ሀይለኛ ስሜት የወረረዎት ይመስላሉ"

"አሁን ታጭቼ መጣሁ። ይገባዎታል መቸም"

"አርግዘው እንዳይሆን?"

"አሁን'ንኳ አላረገዝኩም"

"እ'ንግድያው አንድ ብርጭቆ ግሬናዲን እምቢ አይሉኝማ"

"አቤት አነጋገርዎት ማማሩ!"

"እሱ'ንኳ ምንም አይደለም" አለች ማርሰሊን በእርጋታ ራሷን እያዘነበለች "ይግቡዋ"

ማድሌን ግር ብሏት ጫዋ ቃላት እያንሾካሾከች ገባች። ትቀመጥ ዘንድ ተጋበዘች፣ ቁጭ አለች። የቤት እመቤቷ ሁለት ብርጭቆ፣ አንድ ፋሽኮ ውሀ፣ እና አንድ ሊትሮ ግሬናዲን ሲያመጡ ሄዱ። ይህን የመጨረሻውን ፈሳሽ በጥንቃቄ ቀዱ፣ ለእንግዳቸው ጠቀም አድርገው፣ አንድ ጣት 'ምታክል ለራሳቸው

"መጠንቀቋ ነው" አለች በፈገግታ

ከዚያ መጠጡን በረዘችውና በወይዛዝርት ወግ ፉት አሉለት

"ታድያስ?" ጠየቀች ማርሰሊን በቀስታ

"ይኸውሉት" አለች ማድሌን "መስየ ጋብሪዬል ደውለው ሚጡን ወደሳቸው ናይት-ክለብ ይወስዷታል ትርኢታቸውን እንድትመለከት፣ ሻርልንና እኔንም፣ ለመተጫጨታችን የደስ ደስ"

"ሻርል ነው'ንዴ ለካ?"

"ክሌላ ይሻላል። ረጋ ያለ ሰው ነው፣ ከዚህም ጋር እንተዋወቃለን"

ሁለቱም ፈገግ ማለታቸውን ቀጠሉ

"ይንገሩኝ እስቲ፣ ማዳም ማርሰሊን" አለች ማድሌን "ምንድነው መልበስ ያለብኝ?"

"እሱማ" አለች ማርሰሊን ለዘብ ብላ "ለመታጨት ሲሆን መካከለኛ ነጭ ግድ ነው፣ ብርማ ብልጭልጭ ጣል ተደርጎበት"

"ብርማው ብልጭልጭ 'ንኳ ሲያምረኝ ይቅር" አለች ማድሌን

"እንደዚህ ነው 'ሚደረገው"

"ቡሽቲዎች ናይት-ክለብ ለመግባትም ቢሆን?"

"እሱ ለጉዳዩ ልዩነት አያመጣም"

"እሺ ግን፣ እኔ መካከለኛ ነጭ ቀሚስ፣ ብርማ... ጣል የተደረገበት ሳይኖረኝስ፣ ኧረ 'ንድያውም ኮትና ጉርድ ሙሉ ልብስ... ባይኖረኝስ፣ እ? ምን አረጋለሁ? ይበሉ ይንገሩኝ 'ንጂ ይንገሩኝ፣ ምን አረጋለሁ?"

ማርሰሊን ራሷን ደፋች፣ በሀሳብ የተዋጠች መሆንዋን እጅግ ግልፅ በሆኑ ምልክቶች እያሳየች

"እንዲህ ከሆነማ" አለች በዝግታ "አንድ ቀን ለአብዮት በአል የዳንስ ፓርቲ ላይ ለብሰውት ያየሁዎትን... ኮት ከአረንጓዴና ቢጫ ሽንሽን ጉርድ ጋር ለምን አይለብሱትም?"

"ይህን አስተውለውልኛል?"

"አዎና" አለች ማርሰሊን፣ ለስለስ ብላ

"ምክንያቱም እኔ" አለች ማድሌን "እኔ ሳዮት በጣም ቆንጅዬ ኖት"

"እውነት?" አለች ማርሰሊን በሚጥም አንደበት

"አዎና" መለሰች ማዶ፣ ሞቅ ባለ ስሜት "ይሄማ በጣም እውነት ነው።... ኖት'ኮ። እንደርሶ ብሆን አቤት እንዴት ደስ ይለኝ ነበር! የደም ገምቦ ኖት። በዛ ላይ ደሞ ሲያሸበርቁ!"

"ማጋነን ይቅርብን" አለች ማርሰሊን በእርጋታ

"ኖት ኖት ኖት! በጣም ... ኖት። ለምን አይታዩም ግን? ይበልጥ ብናዮት ደስ ይለን ነበር። እኔ ብዙ ባዮት እወዳለሁ" ፈገግ እያለች

ማርሰሊን ራሷን ደፋች ባይናፋርነት ፊቷ ላመሉ ቀላ አለ

"አዎን" ቀጠለች ማድሌን "ለምን ይበልጥ አናዮትም? እንደዚህ የሚያበራ ጤና ያሉት መሆኑን ልነግሮት ያስደፍረኛል፣ በዛ ላይ ደሞ መልኮት ሲያምር! ለምን አናገኞትም?"

"በተፈጥሮዬ ሁካታ ስለማያምረኝ ነው" አለች ማርሰሊን በሰላማዊ አንደበት

"እስከ ሁካታም ሳይደርሱ የሚቻለው..."

"ያን ያህልም አይገፋፉኝ፣ አንቱዬ" አለች ማርሰሊን

እዚህ ላይ ዝም ብለው ቆዩ፣ ሀሳቦቻቸውና ምኞቶቻቸው እየወሰዱዋቸው ጊዜው አልሮጠባቸውም። በርቀት፣ መንገዶቹ ውስጥ፣ ጉማሮች "እስ!" እያሉ በሌሊቱ በዝግታ ሲተነፍሱ ይሰማቸዋል። በተከፈተው መስኮት ሲመለከቱ ጨረቃዋ በአንድ የቲቪ አንቴና ላይ ታበራለች - የቲቪው ድምፅ በጣም ትንሽ ነው።

"እንግዲህ ሄደው መልበስ ሊኖርብዎት ነው" አለች ማርሰሊን በልዝብነት "የጋብሪዬል ሾው እንዳያመልጥዎት ከፈለጉ"

"አለብኝ" አለች ማድሌን "እንግድያው የአብዮት በአሉን አፕል አፈንጓጼ ኮቴን ከብርቱካንማው ሎሚ-ከለር ቀሚሴ ጋር ልለብስ ነው"

"እንደሱ"

(ትንሽ ፀጥ አሉ)

"ቢሆንም ግን፣ ብቻዎትን ትቼዎት ስሄድ ሀዘን ይሰማኛል" አለች ማድሌን

"በጭራሽ" አለች ማርሰሊን "ለምጄዋለሁ"

"ቢሆንም"

ሁለቱም እኩል ባንድነት ተነሱ

"እሺ" አለች ማድሌን "እንዲህ ከሆነ ሄጄ ልልበስ"

"አይን ይማርካሉ" አለች ማርሰሊን፣ ለስለስ ብላ እየተጠጋቻት

ማድሌን አይን አይኗን ስታያት

በሩ ተንኳኳ

"እየመጣሽ ነው?" ሙሽ ሻርል

# አስራ አራት

ታክሲዋ ሞላችና ሻርል አስነሳ። ቱራንዶ አጠገቡ ተቀመጠ። ማድሌን ከጊላ፣ በግሬዱና በላቬርድዩር መሀል

ማድሌን በቀቀንዋን አየቻት አየቻትና ሁሉንም ጠየቀቻቸው፡-

"ትርኢቱ የሚያስደስታት ይመስላችኋል?"

"አታስቢ" አለ ቱራንዶ - ከጊላ የሚያስያየውን መስተዋት ከፍቶት ቆይቷል - ከጊላው ምን እንደሚያወሩ ለመስማት "ታውቂያለሽኮ፣ ራሷ በመሰላት ትደሰታለች፣ በሚያሰኛት ጊዜ። ስለዚህ ጋብሪዬልን እያየች ለምን አትደሰትም?"

"እነዚህ አራዊት" አለ ግዱን "ምን ሀሳብ እንደሚያሰላስሉ በፍፁም አይታወቅም"

"ታወራለህ፣ ታወራለህ" አለች ላቬርድዩር "እሱን ብቻ ነው ማድረግ 'ምታውቀው"

"አያችሁ?" አለ ግሬዱ "እኛ ከሚመስለን በላይ ይገባቸዋል"

"እሱ እውነት ነው" ስትል ማድሌን በልበ ሙሉነት ተስማማች

"በጣሙን እውነት ነው። እኛስ ብንሆን፣ ስለምኑስ ቢሆን ምኑ ገብቶን?"

"ምን ስለምን?" ጠየቀ ቱራንዶ

"ስለህይወት። አንዳንዴ ህልም ይመስላል"

"ሰው ሲያገባ ሲል የሚናገረው ነው እሱ" አለና ቱራንዶ የሻርልን ጭን በጥፊ ጧ! አደረገው፣ ታክሲዋ ከመገልበጥ አደጋ ለትንሽ ተረፈች

"ተውን'ጂ አታስቀዝነኝ" አለ ሻርል

"አይ!" አለች ማድሌን "እንደሱ አይደለም፡፡ ስለ ጋብቻ ብቻ እያሰብኩ አልነበረም፡፡ እንደዚሁ እያሰብኩ ነበር"

"እሱ ብቻ ነው ዘዴው" አለ ግሪዱ በሊቅ ቅላጼ

"ዘዴው የምኑ?"

"አሁን ያልሽው"

(ዝምታ)

"ምን አይነቱ ቅዘን ነው ይሄ ኑሮ ግን?!" ብላ ደገመች ማድሌን "እህህ!" ብላ በረዥሙ እየተነፈሰች

"አረ ተይ" አለ ግሪዱ "አረ ተይ"

"ታወራለህ፣ ታወራለህ" አለች ላቬርድዩር "ይህን ብቻ ነው ማድረግ 'ምታቀው"

"እቺ ደሞ ዲስክዋን ብዙ ጊዜ አትለውጥም፣ አይደል?"

"ምናልባት ተሰጥኦ የላትም ብለህ ማሽሟጠጥህ ይሆን'ንዴ?!" ጮኸ ቱራንዶ እየዞረ

ላቬርድዩር ስሜት የማትሰጠው ሻርል ወደ ባለቤትዋ ጉምበስ ብሎ በግማሽ ድምፅ፡-

"ጋብቻው እንደፀና ነው ወይ ብለህ ጠይቃት'ማ"

"ማን ናት'ምጠይቃት? ላቬርድዩርን?"

"ክጅል የባስክ አትሁንብኝ እንግዲህ"

"ዛሬስ መቀለድም ላንችል ሆነ'ንዴ" አለ ቱራንዶ በተለሳለሰ ድምፅ፡፡ እና ወደኋላ ዞሮ

"ማዶ ፕቲ-ፒዩ" አለ

"አለሁኝ" አለች ማድሌን

"ሻርል አሁንም ታገቢው እንደሆነ ማወቅ ይፈልጋል"

"አዎን" አለች ማድሌን በአስተማማኝ ድምፅ

ቱራንዶ ወደ ሻርል ዞሮ ጠየቀው

"ዛሬም እንደሁልጊዜ ማዶ ፕቲ-ፒዩን ለሚስትነት ትፈልጋታለህ?"

"እዎን" አለ ሻርል በአስተማማኝ ድምፅ

"እንግዲያው" አለ ቱራንዶ፣ አስተማማኝነቱ ከነሱ በማይተናነስ ድምፅ "ከ'ንግዲህ በጋብቻ የተሳሰራችሁ መሆኑ በይፋ ይታወቅ ብያለሁ"

"አሜን" አለ ግሪዱ

"ፉራ!" አለች ማድሌን እሳት ለብሳ "የመጨረሻ የጅል ቀልድ ነው ይሄ!"

"ለምን?" ጠየቀ ቱራንዶ "ትፈልጊያለሽ ወይስ አትፈልጊም? እዚህ ላይ አስቀድሞ መግባባት ይገባል"

"ቀልድየው ነው የማያስቅ አጉል የነበረው"

"እኔ ቀልዴን አይደለም። ሁለታችሁ ሻርሎች አንድ እንድትሆኑ ስመኝላችሁ ነው"

"የእርጎ ዝምብ አትሁኑብኝ፣ መስየ ቱራንዶ"

"ነገረችህ፣ አለቀ" አለ ሻርል በእርጋታ "እዚህ ውረድ። መኪናዬን አቁሜ 'ደርስባችኋለሁ?"

"በፍፁም!" አለች ማድሌን "ከጅልነትዎ የተነሳ ሰው ሊቀየሞት አይችልም"

ለአይን የሚከብድ ዩኒፎርም የለበሱ አድሚራል መጥተው መስኮቱን ከፈቱ። እና በቀቀንዋን ሲያዩ በአድናቆት ጮሁ

"አቤት ስታምር!" "እሷም ከናንተ ጋር ናት?"

ላቬርድዩር አንጓራች፡-

"ታወራለህ፣ ታወራለህ፣ ይህን ብቻ ነው ማድረግ 'ምትችለው"

"አሀ!" አሉ አድሚራልየው "እሷም አብራችሁ መግባት የፈለገች ይመስላል"

አዲስ ለመጡት ደግሞ፡-

"የጋብሪዬላ እንግዶች እናንተ ናችሁ? ገና ሲያዩዋችሁ ታስታውቃላችሁ"

"ስማ አንት ውዳቂ" አለ ቱራንዶ "ሰው አትድፈር"

"ይሄስ፣ ይሄም ጋብሪዬላን ማየት ይፈልጋል?" አለ

ቱራንዶን ለመበቀል ፈልጎ በቀቀንዋን ሲያያት እንገሽግሾት ሊያስታውከው የደረሰ አስመሰለ

"አስቸገረችህ?" ጠየቀ ቱራንዶ

"በመጠኑ" መለሰ አድሚራልየው "እንዲህ አይነቱ አራዊት ኮምፕሌክስ ያሳድርብኛል"

"ፕሲታኮ-አናሊስት ቤት መሄድ ያስፈልጋል" አለ ግሪዱ

"ከዚህ ቀደም ህልሞቼን ለመተርጎም ሞክሬአለሁ" አለ አድሚራሉ "ግን አስቀያሚ ናቸው። የትም አያደርስ"

"ህልምዎ ስለምንድ'ነው?" ጠየቀ ግሪዱ

"ስለ ሞግዚቶች"

"ይሄስ እውነትም ብሽቅ ነው" አለ ቱራንዶ፣ ለቀልድ ያህል

ሻርል መኪናውን አቁሞ ተመልሷል

"እንዴት ነው?" አለ ሻርል "እስካሁን አልገባችሁም?"

"ይኸዋ! ደሞ አንዱ ለካፌ መጣ" አለ አድሚራልየው

"እኔ ሰው ሲቀልድብኝ አልወድም" አለ ባለታክሲው

"ለወደፊቱ አስታውሳለሁ" አለ አድሚራልየው

"ታወራለህ፣ ታወራለህ" አለች ላቬርድዩር

"ሁካታ ፈጠራችሁ" አለ ጋብሪዬል እንደተከለተ "ኑ ግቡ። አትፍሩ። ደምበኞች ገና አልመጡም። ቱሪስቶቹ ብቻ ናቸው ያሉት። እና ዛዚ። በሉ ግቡ። ግቡ። ትንሽ ቆይታችሁ በሀይል ትደሰታላችሁ"

"ለምንድ'ነው በተለይ ዛሬ ማታ ኑ ያልከን?" ጠየቀ ቱራንዶ

"እስከ ዛሬ'ኮ" ቀጠለ ግሪዱ "ስራዎችህን በአይናፋርነት ሸሽ ስትጋርድብን ኖረሀል"

"እና ደግሞ" ጨመረችበት ማድሌን "እስከ ዛሬ የሙያዎን ጥበብ ሲያሳዩ እናደንቅዎት ዘንድ ፈቅደውልን አያውቁም"

"አዎን" አለች ላቬርድዩር "አሁን እዚህ ይህ እንዲህ ይሆን ዘንድ ምክንያቱ አልገባንም"

የበቀቀኒቱን ጣልቃ መግባት ችላ እያለ፣ ጋብሪዬል ለቅድሞቹ ጥያቄዎች የሚከተለውን መልስ ሰጠ፦

"ለምን? ለምን ብላችሁ ትጠይቃላችሁ? እንግዳ ጥያቄ ነው፣ እኔው ራሴ ማን ምን ለምን እንደምመልሰው የማላውቅ ስለሆንኩ። ለምን? አዎን፣ ለምን? ለምን ብላችሁ ትጠይቁኛላችሁ? የደስ ደስ ባላት በዚች ደቂቃ፣ ይችን የመሆንንና የለትንሽ-ለምንን ውህደት፣ በማኖር ማሳ ውስጥ የሚካሄደውን ክህሎት ላውሳው ፍቀዱልኝ። ለምን ለምን ለምን፣ ለምን ብላችሁ ትጠይቁኛላችሁ? እንዴ! ወይን-ጠጅዋ የቆላ እፅ ቅጠሎችዋ በውዳሴ ወረብ ሲንቀጠቀጡ አይሰማችሁምን?"

"ለኛ ነው 'ምትነግረን?" ጠየቀ ሻርል፣ ብዙ ጊዜ ጋዜጣው ላይ የሚያገኛቸውን የቃላት እንቆቅልሽ ለንጠረዦች ማጥናት የለመደው

"ኧረ በፍፁም!" መለሰ ጋብሪዬል "ይልቅ እዩልኝማ!"

ቀይ ከፋይ መጋረጃ የምትሀት ይመስል ከመሀሉ ተከፈለ—የመጠጥ ባንኮኒ፣ ወምበር፣ ጠረጴዛዎች፣ መድረክ፣ እና የተስተናጋጆች መመላለሻ፣ ይሄ ሁሉ ለተገረሙት ጎብኚዎች ተከሰተ - ሞን-ዶ-ፒዬቴ፣ ከሁሉ ዝነኛው የዋና ከተማዋ የሶዶማውያን ናይት-ክለብ። ይሄ ብቻም አይደል - በዚች ገና በትንሹ ጭራጭል እያለች መሟሟቅ በጀመረችው ሰአት፣ እኚውና በመሀል የተደነቀሩ፣ ለቤቱ ልዩ አይነት የሆኑ የጋይድ ጋብሪዬል ደቀ-መዛሙርት እና መሀላቸው፣ ዙፋንዋ ላይ ተቀምጣ ዲስኩር የምታረግላቸው ህንፃዋ ዛዚ

"ቦታ ስጡን፣ የተከበራችሁ እንግዶች" አላቸው ጋብሪዬል

በሙሉ ልብ ስለማያምኑት፣ አዲስ መጪዎቹ በመሀላቸው እንዲቀመጡ ቦታ አመቻቹላቸው። መሰባጠራቸው አብቅቶ፣ ላቬርድዩርን አንዱ ጠረጴዛ ዳር አስቀመጧት። ከደቃቅ ጥራጥሬ ስንቋ ዙርያውን በመበታተን ደስታዋን ገለፀች

አንድ እስኮትላንድ ተወላጅ የሆነ የቤቱ ተራ ቦይ ፍጡራቱን አስተዋላትና ከፍ ባለ ድምፅ አስተያየቱን ተናገረ፦

"እሉላችሁ እብዶች መቸስ! እኔ 'ንደሆንኩ አረንጓዴዋ መሬት..."

"አንቺ ዱባ ቡሽቲ" አለ ቱራንዶ "አጭር ቀሚስሽን ለብሰሽ ጨዋ ሰው የሆንሽ እንዳይመስልሽ ብቻ"

"ትወው ይሁን" አለ ጋብሪዬል "የስራ ልብሱ ነው፡፡ ስለ ላቬርድዬር ከሆነ" ቀጠለለት ለስኮትላንዱ ሶዶማዊ "እኔ ነኝ በቀቀንዋን እንድትመጣ የጋበዝኳት፡፡ ስለዚህ አፍህን ዝጋና ሀሳቦችህን ለግልህ አስብ"

"እንዲህ ነው መናገር!" አለ ቱራንዶ፣ የስኮትላንድዋን ሰው በድል አድራጊነት አይን እየገረመማት "ከዚህ ጋር ደግሞ" ቀጠለ ለወዳጆቹ "ምንድ'ነው 'ሚያቀርቡልን? ሻምፓኝ ወይስ ምን?"

"እዚህ እሱን ማዘዝ ግዴታ ነው" አለች ስኮትላንዳዊትዋ "ውስኪ ካልጠጣችሁ በስተቀር፡፡ ምን እንደሆነ የምታውቁ ከሆነ"

"እኔን ይህን ይጠይቀኛል?" ጮኸ ቱራንዶ "እኔ ለራሴ የሱሚናት ሰው ነኝ"

"መናገር ነበራ" አለች የስኮትላንድዋ ሰው፣ ጉርድ ቀሚስዋን በመዳፍዋ ጀርባ እየዳሰሰች

"በል አሁን ሂድ" አለ ጋብሪዬል "የቤቱን ባለጋዝ ቅራሪ አምጣልን"

"ስንት ጠርሙስ?"

"ዋጋው ታይቶ" አለ ቱራንዶ

"እኔ ነኝ 'ምከፍለው እያልኩህ!" አለ ጋብሪዬል

"ጥቅምህን መጠበቄ ነበራ" አለ ቱራንዶ

"ቆንቋና ስለሆነች'ኮ ነው አለች ስኮትላንድዋ ሴትዮ"

የቡና ማፍያ ማሺኑን እጀታ ነካ አድርጋ፣ የሚወጣው እንፋሎት እንዳይፈጃት ፈጥና ዘወር እያለች "ወፈር ያለውን ላምጣ?"

"ወፍራም ምን?" ጠየቀች ዛዚ፣ ድንገት ጭውውቱ ውስጥ እየገባች

"አስራ ሁለት ደርዘን ጠርሙስ ማለቱ ነው" አስረዳት ጋብሪዬል አባ መስጠት

ከዚህ በኂላ ዛዚ አዲስ መጪዎቹ መኖራቸውን ለማወቅ መልካም ፈቃድዋ ሆነ

"እሺ፣ አንቱ ባለታክሲ ሰውዬ" አለችው ሻርልን "የተጋባችሁ ይመስላል?"

"ይመስላል" አለ ሻርል ባጭሩ

"በመጨረሻ፣ የሚስማማዎትን ሰው አገኙ"

ዛዚ ማድሌንን ለመመልከት ጋደል አለች

"እሳቸው ናቸው?"

"ቦንዡር፣ ማድሚዜል" አለች ማድሌን፣ በወዳጅነት

"ሰላም" አለች ዛዚ

ወደ ባልቴትዋ ሙዋክ ዞረች፣ ነፃ ልታወጣቸው

"እነዚህ ሁለቱ" አለቻቸው፣ ተጠቃሾቹን በጣቷ እያመለከተች "እየተጋቡ ነው"

"እቤት! እንዴት ልብ ይነካል!" ሙሁ ባላቸው የሞተባቸው ሙዋክ ዋኔ ምስኪን ትሩስካዮን ይኼኔ አደጋ ላይ እየወደቀ ይሆናል በዚህ ጨለማ ሌሊት። እንግዲህ (በረኸኞሙ ይተነፍሳሉ) ይህን ስራ መሬጠ (ዝምታ) ለሁለተኛ ጊዜ ባልዋ የሞተባት ሴት ብሆን ግን ኮሚክ ይሆናል። ያውም ደሞ ሰውየውን ሳላገባው በፊት"

ጆሮ የሚበሳ አጭር ሳቅ አለሙ

"ማናት እቺ ቀውስ?" ጠየቀው ቱራንዶ ጋብሪዬልን

"እንጃ። ዛሬ ከሰአት በኋላውን ከኋላ-ኋላችን ሉኩ-ሉኩ ስትል ዋለች፣ መንገድ ላይ ከቀለበችው ዛፓ ጋር"

"የትኛው ነው ዛፓው?"

"ዘወር ዘወር ብሎ ሊመጣ ነው ሄዷል"

"ከንዲህ አይነት ሰው ጋር መሆን ደስ አይልም" አለ ሻርል

"እም" አለ ቱራንዶ "ነገሩ የጤና አይመስልም"

"እታስቡ" አለ ጋብሪዬል "እንድያው ከመሬት ተነስታችሁ ነው 'ምትሰጉት። ይልቅስ ይኸውናላችሁ ቅራሪው መጣ። እሰየው! ጉሮሮዋችሁ ደስ ይበለው ወዳጆችና ተንገኞች፣ አንቺም ውዲቱ የእህቴ ልጅ፣ እናንተም ሆድ እምታባቡ እጮኛሞች። እውነት ነው'ኮ! ልንረሳቸው አይገባም እጮኛሞቹን። ፅዋዬን አነሳለሁ! ለእጮኛሞቹ ፅዋችንን እናንሳ"

ተንገኞቹ ልባቸው ተነክቶ በህብረት ‹ሆፒ በርዝ-ደይ ቱ ዩ› ዘመሩ፣ አንዳንድ ሶዶማዊ ቦዮችም ኩላቸውን ሊያበላሸባቸው የነበረውን እንባ አይናቸውን ጨምቀው አስቀሩት

ከዚህ በኋላ ጋብሪዬል የለስላሳ ጠርሙስ መክፈቻ አንስቶ ብርጭቆ ላይ አንቃጨለ፤ እና የሰዉ ሁሉ ትኩረት ወድያው እንደተሳበ (ለሱ ያላቸው ክበሬታ ያን ያህል በመሆኑ) ወንበሩን እንደ ኩርቻ እየተቀመጠበት ተናገረ፡-

"ኢሺ፤ እናንተ የበግ ግልገሎቼ፤ እናንተም ጠቦት እመቤቶቼ፤ ለማሳረግያ እነሆ፤ ተሰጥኦዬን በውልብታ ልታዩልኝ ሆነ፡፡ እርግጥ ነው፤ ለረዥም ጊዜ ስታዩት ቆይታችኋል፤ አንዳንዶቻችሁ ደሞ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የማታውቁት ነው፤ የዳንስን ጥበብ ወስጄ የገቢዬ ጥገት እንደኛ ጡት አድርጌዋለሁ፡፡ መኖር አለብንና፤ አይደለም?

"እና ልጠይቃችሁ'ስቲ፤ በምንድነው 'ምንኖረው? ቢያንስ በከፊል በጊዜው አየር ነው እላለሁ በበኩሌ፤ እና በዚህ አየር መሞትም አለ፡፡ በበለጠ ወሳኝነት የምንሞተው ግን በዚያ ስሙ እንደ መቅኒ በሚጥመን በገንዘብ ነው፡፡ ይህ ስመ-ወለላ ስራ-ብዙ አገልጋይ በጣም በቀላሉ ተንኖ ይጠፋል፤ የሚገኘው ግን በግምባር ላብ ወዝ ብቻ ነው፡፡ ሌላው ቢቀር ይሄ አለም በሚበዘብዛቸው ጭቁኖች ዘንድ ህቅ ነው፡፡ ከነሱ አንዱ እኔው ስሆን፤ የመጀመርያው ሰለባ የተፀውኦ ስሙ አዳም ይባላል፡፡ እሱንም ‹ኤሎሂም› 'ሚባሉት ይጨቁኑት ነበር፤ ሰው ሁሉ እንደሚያውቀው፡፡ በዛሬው እይታና ግመዛዘናችን በኤደን የነበረ ሰው መሸሻ የማያጣ ቢመስለንም፤ ኤሎሂም የሚሉዋቸው ጨቋኖች ግን ወደ ቅኝ-ግዛቶቻቸው ይልኩት ነበር፤ ግሬፕ-ፍሩት ለማብቀል መሬቱን እንዲጭርላቸው፡፡ በሌላ በኩል ደሞ hypnotist የሚባሉትን የስነ-አእምሮ ሳይንቲስቶች በሙያቸው ጥበብ የአገሬቱን ሴቶች በአዋላጅነት እንዳይረዷቸው ይከለክሉዋቸው ነበር፤ ወጣቶቹን ደግሞ እግራቸውን አንገታቸው ዙርያ እንዲሰቅሉ ያስገድዱዋቸው ነበር፡፡ እኔም በዚህ አስገዳጅነት ሰቅያቸው የነበረውን እግሮቼን እነሱ ከቁብ ሳይቆጥሩልኝ፤ የመፅሀፍ ቅዱስ ሰው መሆኔንም ሳይገነዘቡልኝ ቀርተዋል፡፡"

"ዋሆን ሆኖ፤ የጉልበቴን አንጓ በተጠቀሰው የግንባሬ ላብ ወዝ ቀብቻለሁ፤ እና እንደዚህ ነው ኤደናዊም አዳምም ሆኜ እንጀራዬን 'ማገኘው፡፡"

ከጥቂት ደቂቃ በኋላ በስራ ላይ ታዩኛላችሁ፡፡ ግን ልብ በሉ፤ እንዳትሳሳቱ፡፡ ·ተራ ስትሪፕ-ቲዝ አይደለም 'ማቀርብላችሁ፤ ጥበብ እንጂ፡፡ Art በካፒታል A፤ እና በጣም እየተጠነቀቃችሁ l'art በአራት ፊደል፡፡ ባለአራት ፊደል ቃላት ደሞ የላቁ መሆናቸው 'የታወቀ ነው በፈረንሳይ ቋንቋ ግርማዊ ፍስሰት ላይ ልክ የለሽ ብልግና እያንሳፈፉ ከሚያሰራጩት ባለሶስት ፊደል ቃላትም፤ ከዚያ ባላነሰ ሁኔታ ከሚያናፍሱት ባለአምስት ፊደል ቃላትም ይልቃሉ፡፡

"ወደ ንግግሬ ማብቅያ ደርሻለሁ፡፡ የሚቀረኝ አለ፣ ይኸውም፣ ለኔ አክብሮት አስባችሁና ገናናነቱ የበለጠ እንዲልቅ ብላችሁ እንደ ዝናብ ለምታወርዱልኝ የጭብጨባ ነጉድጓድ ከፍ ያለ ልባዊ ውለታና ወሮታ ያለብኝ መሆኑን ልገልፅላችሁ እወዳለሁ፡፡ አመሰግናለሁ!"

ቀጥሎ፣ የተለየና ያልተጠበቀ በሆነ ቅልጥፍና፣ ያ የገደል ቅራሬ የሚያህል ሰውዬ እጆቹን የኋሊት እያሳየ፣ ትከሻውን ለአመል ዝቅ አድርጎ እንደ ቢራቢሮ እያራገባቸው፣ በእግሮቹ እንደገና እንዝርት ሽክርክር አለና ቀጥ ብሎ ቆመ፡፡

ይህ የጥበብ ትእይንት ተጓዦቹን በአድናቆት ፈነቀላቸው

"እንዲያ ነው! ሴትዮ" እያሉ ጮሁ ሲያጋግሉት

"ሂደው!" ጮኸ ቱራንዶ፣ እንደዚህ አይነት ግሩም ቀጭን ቢራ ጠጥቶ የማያውቀው

"አይ ጬኸታሚቱ!" አለ አንዱ ሶደማዊ አስተናጋጅ

አዲስ እንግዳዎች የዚህ አካባቢ አውቶቡሶች በየተራ አራግፈዋቸው በዘለላ እየመጡ እያለ፣ ጋብሪዬል በድንገት ተመልሶ ተቀመጠ፣ ከፋት በሚታይበት ገፅታ

"ደህና አይደሉም'ንዴ፣ መስየ ጋብሪዬል?" በሀዘኔታ ጠየቀች ማድሌን

"ብርክ ይዞኝ ነው"

"ፈራ-ፍርፋሪ!" አለ ሻርል

"ወይ እድሌ!" አለች ዛዚ

"እንዲህ'ማ ጉድ አታረገንም" አለ ቱራንዶ

"ታወራለህ፣ ታወራለህ" አለች ላቬርድዩር "ይህን ብቻ ነው ማድረግ 'ምታቀው"

"እቺ አራዊት'ኮ እምትናገረውን ታውቃለች" አለ አንዱ ሶደማዊ አስተናጋጅ

"ከጉዳይ አትቁጠራቸው፣ ጋቢ" አለ ቱራንዶ

"እኛም እንደሌሎቹ ሰዎች ነን፣ ብለህ አስብ" አለች ዛዚ

"እኔን ደስ እንዲለኝ" አሉ ባልቴትዋ ሙዋክ እየተቅለሰለሱ

"እርሶንማ" አለ ጋብሪዬል "እደብሮታለሁ። አይደለም'ንዴ፣ ወዳጆቼ?" ቀጠለላቸው ለሌሎቹ "አይደለም፣ ይሄ ብቻ አይደለም (በረዥሙ እየተነፈሰ) ቢሆንልኝና ማርሰሊንም ልታደንቀኝ ብትችል እንዴት በወደድኩ ነበር!"

ትርኢቱ በጣም በሚከይፉ የማርቲኒክ አገር ዳንሰኞች የሚጀምር መሆኑ ተነገረ።

# አስራ አምስት

ማርሰሊን ፎቴ ላይ ተኝታ ነበር። የሆነ ነገር ቀሰቀሳት። አይኗ እየተጥበረበረ ሰአቱን አየች፣ ምንም የተለየ መረጃ አልሰጣትም፣ በኋላ ነበር በጣም በቀስታ በሩ እየተንኳኳ መሆኑ የታወቃት

ወድያው መብራቱን አጠፋችና ሳትንቀሳቀስ ቆየች። ጋብሪዬል ሊሆን አይችልም፣ ምክንያቱም እሱ ከሌሎቹ ጋር ሲገባ ሰፈሩን ሁሉ የሚቀሰቅስ ሁካታ ያሰማሉ የታወቀ ነው። ፖሊስም አይሆንም፣ ገና ፀሀይ'ንኳ አልወጣችም። ጋብሪዬል ያጠራቀመው ገንዘብ ያጓጓው ቤት ሰርሳሪ ቢሆንስ? የሚለው ሀሳብ ደሞ ድንቄም! ያስብላል።

ፀጥታ ሆኖ ቆየ፣ ከዚያ የበሩን እጀታ አዞረው። በዚህ ምንም ውጤት ባለማግኘቱ ቁልፉን መጎርጎር ጀመረ። የተወሰነ ጊዜ ወሰደ። አያውቅበትም፣ አለች ለራስዋ ማርሰሊን። በመጨረሻም በሩ ተከፈተ።

ሰውየው ወድያው አልገባም። ማርሰሊን የምትተነፍሰው በጣም ቀስ ብላ እና በብልሀት ከመሆኑ የተነሳ፣ ሊሰማት የማይችል ሳይሆን አልቀረም።

በመጨረሻ አንድ እርምጃ ወሰደ። በዳበሳ ማብሪያውን ፈለገ። አገኘውና በረንዳው በራ።

የፊቱን ጥላ ከጕን ስታየው ማርሰሊን ወድያው አወቀችው —ፔድሮ— ሳልቫጅ ተብዬው ነው። እሷ ያለችበትን ክፍል ሲያበራው ግን ማርሰሊን የተሳሳተች መሰላት፣ ምክንያቱም ይሄኛው ሰውዬ አንገት ልብስም ጥቁር መነፅርም አላደረገም

ጫማውን በእጁ እንደያዘ ፈገግ አለ

"አስደነገጥኩት አደል?" ጠየቀ በጨዋነት

"አይደለም" መለሰች ማርሰሊን በዝግታ

ከተቀመጠ በኋላ በዝምታ ጫማውን ሲያጠልቅ ማርሰሊን በመጀመሪያ እይታዋ አለመሳሳትዋን አስተዋለች፡፡ በእርግጥ ያ ጋብሪዬል ወደ በረንዳው ቁልቁል የወረወረው ሰውዬ ነው

ተጫምቶ ሲያበቃ እንደገና ማርሰሊንን በፈገግታ ተመለከታት

"አሁን ግን" አለ "አንድ ብርጭቆ ግረናዲን እሺ እላለሁ"

"ለምን ‹አሁን ግን›?" ጠየቀች ማርሰሊን

"አላወቁኝም?"

ማርሰሊን አመነታች፣ ከዚያ በአዎንታ ራስዋን ወዘወዘች

"በዚህ ሰአት ምን ሊያረግ መጣ ይሆን? ብለው እያሰቡ ነው?"

"ረቂቅ ሳይኮሎጂስት ነዎት፣ መስዬ ፔድሮ"

"መስየ ፔድሮ? ለምንድነው ይሄ ‹መስዬ ፔድሮ›?" ጠየቀ ሰውየው እየከነከነው

"ዛሬ ጧት ስምዎ ይሄ ነበራ" መለሰች ማርሰሊን በእርጋታ

"እውነት?" አለ ሰውየው በግድ-የለሽነት "ረስቼው ነበር"

(ዝምታ)

"ታድያስ?" አለ ሲቀጥል "በዚህ ሰአት እዚህ ምን ልሰራ 'ንደመጣሁ አይጠይቁኝም?"

"የለም፣ አልጠይቅዎትም"

"ያሳዝናል" አለ ሰውየው "ምክንያቱም የተጋበዝኩትን ግረናዲን እሺ ብዬ ለመቀበል ነው የመጣሁት ብዬ እመልስሎት ነበር"

ማርሰሊን በዝምታ ለራሷ ስታስብ

"‹ይሄ ሰበብ ንኳ የምኝነት ነው› እንድለው ይፈልጋል፣ እኔ ግን ይህን ደስታ አልሰጠውም፣ ኧረ በፍፁም" አለች

ሰውየው ዙርያውን ተመለካከተ

"እዚያ ውስጥ ነው ነገርየው 'ሚገኘው?"

በአይነቱ አስቀያሚ የሆነውን ቁም-ሳጥን አመለከተ

ማርሰሊን ሳትመልስለት ስትቀር ጊዜ፣ ትከሻውን ከፍ-ዝቅ አደረገ፣ ተነሳ፣ ቁም-ሳጥኑን ከፈተ፣ ጠርሙስና ሁለት ብርጭቆ አወጣ፡፡

"ትንሽ ይወስዳሉ?" ሲል ሀሳብ አቀረበ

"እንቅልፍ ይከለክለኛል" አለች ማርሰሊን በለዘብታ

ሰውየው ድጋሚ አልጋበዘም:: ጠጣ

"በእውነት ብሽቅ ነገር ነው" አለ ለመናገር ያህል

ማርሰሊን እንደሆነች አንድም ቃል አልተናገረች

"እስካሁን ከሄዱበት አልመጡም?" ጠየቀ ሰውየው፣ ዝም ከማለት

"ይኸው እንደሚያዩት ነው:: ያ'ማ ባይሆን ኖሮ፣ ይህን ጊዜ እርስዎ ተንከባልለው ታች ነበሩ"

"ጋብሪዬላ" አለ ሰውየው በስመመን "አስደናቂ! የወጣለት እንቁ!"

ብርጭቆውን ጨለጠ

"ኡፍ!" አጉተመተመ

እንደገና ቤቱ በፀጥታ ተዋጠ

በመጨረሻ ሰውየው ከውሳኔ ደረሰ

"ይኸው እንግዲህ" አለ "የማቀርብልዎት የተወሰኑ ጥያቄዎች አሉኝ"

"ይጠይቁ" አለች ማርሰሊን በልዝብ አንደበት "እኔ ግን መልስ አልሰጥም"

"ግድ ነው" አለ ሰውየው "እኔ ኢንስፔክተር ቤርተር ፑዋሬ ነኝ"

ነገሩ ማርሰሊንን አሳቃት

"ይኸውና የአድራሻ ካርዱ" አለ ሰውየው በሽቆ:: እና ከሩቅ ለማርሰሊን አሳያት

"ፎርጅ ነው" አለች ማርሰሊን "ገና ሲያዩት ያስታውቃል:: እና ደሞ፣ የእውነት ኢንስፔክተር ብትሆኑ ኖሮ፣ ምርመራ ሲካሄድ እንዲህ እንዳልሆነ ያውቁ ነበር:: የፖሊስ ልቦለድ ለማንበብ ያህል እንኳ ጥረት አላደረጉም (በፈረንሳይኛ ማለቴ ነው መቸስ) እንጂ ባወቁት ነበር:: የሚያሳስርዎት ጉዳይ ነው-ቁልፍ ሰብሮ ሰስርቆት መግባት፣ የሰው መኖሪያ ለመጣስ መድፈር..."

"እና ምናልባትም ሌላ ነገር ለመድፈር"

"ምን አሉኝ?" ጠየቀች ማርሰሊን በሰላማዊ ድምፅ

"እንግዲህ ይኸውሎት" አለ ሰውየው "ከፉኛ ወድቄሎታለሁ። ገና ሳይዎት ለራሴ እንዲህ አልኩ ‹እዚች መሬት ላይ መኖር አልችልም፣ ከአንድ ቀን ወይ ሌላ ቀን ካልተኛኋት በስተቀር። ከዛ ለራሴ እንዲህ ቀጠልኩ ‹ብጣም በቅርቡ ቢሆን ይመረጣል› እኔ መቆየት አልችልም። ችኩል ነኝ በተፈጥሮዬ። ከዛም እንዲህ አሰብኩ ‹ዛሬ ማታ እድል ይኖረኛል፣ ምክንያቱም ያቺ መለኮታዊት - ማለትም እርስዎ - ጐጆዋ ውስጥ ብቻዋን የምትገኝ በመሆንዋ፣ ቤተኛው በሙሉ (ያ ጅል ቱራንዶ ሳይቀር) የጋብሪዬላን ዝላዮች ለማድነቅ ወደ ሞን-ደ-ፒዬቴ ይሄዳልና። ጋብሪዬላ! (ዝምታ) ድንቅዬ ጋብሪዬላ!›"

"እርስዎ ይህን ሁሉ እንዴት አወቁ?"

"ኢንስፔክተር ቤርተን ፑዋሬ ስለሆንኩ"

"ጭልጥ አርገው እየዋሹ ነው" አለች ማርሰሊን፣ በፍጥነት የአነጋገርዋን ስልት እየለወጠች "ይልቅስ የውሸት ፖሊስ መሆንዎትን እመኑ"

"ፖሊስ - በርስዎ አጠራር - ፍቅር ሲይዘው አይችልም ብለው ያምናሉ?"

"ልንገሮት፣ እርስዎ ከመጠን በላይ ጅል ነዎት"

"ያን ያህል ነቂ ያልሆንን ፖሊሶች አለን'ኮ"

"እርስዎማ ከዛም ይብሳሉ"

"እንግዲህ የኔ ኑዛዜ ያሳደረብዎት ስሜት ይሄ ብቻ ነው? ፍቅሬን ስናዘዝልዎት?"

"ምንስ ቢሆን፣ ገና ለገና ጠይቀውኛልና ብዬ ምጋደምልዎት መሰሎት እንዴ?"

"እውነቴን ነው ምልዎት፣ የኔ የግሌ ለዛ በመጨረሻ ስሜት ሳይሰጥዎት አይቀርም?"

"የዛሬውስ ተሰምቶም አያውቅ!"

"ያያሉ። ጥቂት አብረን ብናወጋ ሴት-አዋይነቴ ስራውን ይሰራል"

"ያልሰራ 'ንደሆነስ?"

"ያኔማ ዘልዩ ጉብ እልብዎታለሁ - በቃ"

"ነው 'ንዴ!? ይበሉዋ ይሞክሩ"

"ጊዜ አለኝ፡፡ እውነት ለመናገር፣ ሀሲናዬ ያለቅሬታ የማይፈቅደው በመሆኑ፣ የመጨረሻ ምርጫ ከሆነብኝ ብቻ ነው ይህን ዘዴ 'ምጠቀመው"

"ፈጠን ቢሉ ይሻልዎታል፡፡ ጋብሪዬል መምጫው እየደረሰ ነው"

"አይደለም ኧረ! የዛሬው ትርኢት እስከ ጧቱ አስራ ሁለት ሰአት ነው"

"ምስኪን ዛዚ!" አለች ማርሰሊን ልስልስ ባለ ድምፅ "ድካሙ ድቅቅ ያረጋታል! ደሞ'ኮ በአስራ-ሁለት ሰአት ከስድሳ ደቂቃ ባቡር መሳፈር ይኖርባታል"

"ዛዚ ስሜት አትሰጠንም፡፡ ብላቴናዎች ያንገሸግሹኛል፣ ይኮመጥጡኛል እክ! እንደርስዎ ያሉ የተዋቡ ሴት ግን... በስመአብ!"

"እየተንገሸገሹም ቢሆን ግን ያቺን ምስኪን ልጅ ዛሬ ጧት ከኋላ ኋላዋ ሲከተሉዋት ነበር"

"እንዲህ ማለት አይቻልም፡፡ እኔ ነኝ ልጅቱን ያመጣሁላችሁ፡፡ እና ደሞ የስራ ውሎዬን ገና መጀመሬ ነበር፡፡ እርስዎን ባየሁት ሰአት ግን..."

የምሽቱ ጉብኚ ጥልቅ ሀዘን የተሰማው እየመሰለ ማርሰሊንን ተመለከታት፣ ከዚያም የግረናዲን ጠርሙሱን አጥብቆ ጨበጠ፣ ከዚህ መጠጥ አንድ ብርጭቆ ይቀዳ ዘንድ፡፡ የተቀዳውንም ባንድ ትንፋሽ ጨልጦ ሲያበቃ፣ ብርጭቆውን ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠ — የኮተሌት ጥብሱን አጥንት ወይም የአሳውን እሾህ እንደምናስቀምጥ

"እክ!!" አለ፣ በለመደው ፍጥነት ሌላ ብርጭቆ ከጨለጠ በኋላ በቮድካ የረጠበ ከንፈሩን በመዳፉ ጀርባ (በግራው) ጠረገ፣ እና ቀደም ሲል ያሳወቀውን የሴት-አዋይ ተወዳጅነት ቆይታ ጀመረ

"እኔ" አለ ከመሬት ተነስቶ "ተለዋዋጭ ነኝ፡፡ የገጠርዋ ሚጡ ስሜት አልሰጠችኝም፣ የነብስ ግድያ ጉዳዮች ብታወራም፡፡ ይህን 'ምነግርዎት ስለጥዋቱ ነው፡፡ በውሎዬ ታድያ አንዲት ደርባባ ሴት-ወይዘሮ አያጋጥሙኝም? ገና እንደተያየን የታላቅ ሰዎች ዘር የሆኑት ባላቸው የሞተባቸው ባለማእረግዋ "ባሮን ሙዋክ" ልብ ውስጥ ገባሁ፡፡ አምስት ደቂቃ

ሳያልፍ ህይወቷ ምስቅልቅሉ ወጣ፡፡ እውነት ለመናገር፣ በዚያች ሰአት በጣም በሚያምርብኝ የትራፊክ-ፖሊስ ዩኒፎርሜ ዘንጬ ነበር፡፡ አቤት ስወደው! በዚህ ዩኒፎርም ምን ያህል እንደምደሰት ልነግርዎት አልችልም፡፡ ከሁሉ የበለጠ የሚያስደስተኝ አንዱ ታክሲ ላይ ፊሽካዬን ነፍቼ አቁሜው ስገባበት ነው፡፡ መሪውን የጨበጠው ጆላጅል በድንጋጤ ሊሞት ምንም አይቀረው፡፡ የግዱን ቤቴ ያደርሰኛል ትንፋሽ እያጠረው (ዝምታ) ትእቢተኛ ሆንኩብዎት'ንዴ ምናልባት?

"ሁሉም እንደ ስሜቱ"

"ስዛዬ አሁንም አልሰራም?"

"አልሰራም"

ቤተር ፑዋሬ ሁለት ሶስት ጊዜ ጉሮሮውን ጠረገ፣ ከዚያም በሚከተለው አባባል ቀጠለ፡-

"ባልቴትዋን እንዴት እንዳገኘኋት መናገር አለብኝ"

"ስሜት አይሰጠኝም" አለች ማርሰሊን በለዘብታ

"ለማንኛውም፣ ሞን-ደ-ፒዬቴ ውስጥ ነው (ጋብሪዬላ!) እኔ'ኮ የጋብሪዬላ እንቅስቃሴዎች ያፈዝዙኛል፡፡ እርስዎ ግን... እንዳንፀባርቅ ያደርጉኛል"

"እውይ! መስየ ፔድሮ-ሳልቫጅ፣ ጭራሽም አያፍሩ?

"እፍረት... እፍረት... ሲናገሩት ቀላል ነው፡፡ ሰው ሲለፈልፍ በረቂቅነት ነውን? ደሞ ፔድሮ-ሳልቫጅ ብለው አይጥሩኝ፡፡ ያበሽቀኛል፡፡ ለጋብሪዬላ ብዬ ድንገት የፈጠርኩት ስም ነው፡፡ ግን አልለመድኩትም፣ ተጠርቼበት አላውቅም፡፡ አሉኝ'ንጂ ሌሎች መቶ በመቶ የሚስማሙኝ ስሞች"

"እንደ ቤርተን ፑዋሬ?"

"ለምሳሌ፡፡ ወይም ደሞ የፖሊስ ዩኒፎርሜን ስለብስ የምጠራበት ስም" (ዝምታ)

ስጋት የያዘው መሰለ

"ስለብስ" ብሎ ደገመ እየዞረበት "ይሄ ግን ፈረንሳይኛ ነው? እለብሳለሁ፣ እሄዳለሁ አዎ ግን ተማታብኝ አይደል? እርስዎስ ለምን ይመስልዎታል፣ የኔ ውብ እመቤት"

"እንዴ! ይሂዱዋ"

"እሱማ ጨርሶ በሀሳቤም አይመጣ። እንግዲህ ስለብስ..."

"ሌላ ሰው የሚያስመስልዎትን ሲለብሱ..."

"አይደለም በጭራሽ!! ሌላ ሰው ለመምሰል አይደለም። ደሞስ ማነው እሱ የእውነት ፖሊስ አይደለም ያሉ"

ማርስሊን ትከሻዋን ከፍ ዝቅ አደረገች

"እንዴ! ይልበሷ!"

"‹ይላበሱ› ይበሉኝ የኔ ውብ እመቤት። ‹ይላበሱ› ነው 'ሚባለው"

ማርስሊን በሳቅ ፈነዳች "ይላበሱ! ይላበሱ! በጭራሽ አልሆነል ዎትም። ‹ይልበሱ› ነው 'ሚባለው"

"ይህንንስ መቸም ቢሆን አያሳምኑኝም" የበሽቀ መሰለ

"መዝገበ ቃላት ውስጥ ይመልከቱ"

"መዝገበ ቃላት? መዝገበ ቃላት አልያዝኩማ። ኧረ በቤቴም የለኝ። ለንባብ ጊዜ ያለኝ ይመስሎታል? እነዚያ ሙያዎቼ ሁሉ እያሉ?"

"እዚያ ያውልዎት" (ትጠቁማለች)

"ወይ ጉድ!" አለ በአድናቆት "ከዚህም ጋር የተማሩ ሊቅ ነዎት" ግን አልተንቀሳቀሰም

"ልሂድና ላምጣልዎት ይፈልጋሉ?" ጠየቀች ማርስሊን በእርጋታ

"አይ፣ እኔው እሄዳለሁ"

እየተጠራጠረ፣ መፅሀፉን ከመደርደርያው ለማውረድ ሄደ፣ ማርስሊን እንዳትጠፋበት በአይነ-ቁራኛ እያያት። ከዚያ መፅሀፉን አምጥቶ በመከራ ሊመረምረው ጀመረ፣ እና ትኩረቱ በዚህ ስራ ውስጥ ተጠምዶ ቀረ

"ምን ነበር..." በV የሚጀምሩትን የተለያዩ የፈረንሳይኛ ቃላት እያየ "ይሄማ የታሪካዊ ሰው እናት ስም ነው። ያ ቃል ግን እዚህ የለም ነጃሳ!"

"ዲክሺነሪው'ኮ ትልቅ ስለሆነ ለተመልካች ቀላል እንዲሆን ታቅዶ፣ ወረቀቱ የተለያየ ቀለም አለው። "ሮዝ ቀለም ካላቸው ገፆች በፊት ያለው ውስጥ ነው መመልከት"

"ሮዝ ከለር ያላቸው ወረቀቶች ውስጥ'ሳ ምንድነው ያለው? ባለጌ ቃላት መሆን አለበት መቾስ... ይኸዋ!፣ በላቲን ቋንቋ ነው። ዶሚኑስ፣ ቮቢስኩም፣ ኤት ኩም ስፒሪቱ... እዚህ ውስጥም የለም"

"ነገርኩዎትኮ' - ሮዝ ከለር ካላቸው ወረቀቶች በፊት"

"ሜርድ! እንዲህ ያለ መወሳሰብ... ኦ! ገና አሁን አገኘሁ ሰው ሁሉ 'ሚያውቃቸውን ቃላት"

... ቬስታላ... ቬዙሊየን... ቬቲየ ... ቬቲየዝ....

በቪ የሚቀጥሉትን ቃላት "ይሄ ምን ማለት ነው? ይሄኛውስ? ኧረ ሊሆን አይችልም!" እያለ በራሱ ሲያነበንብ ቆይቶ ."ይኸውና 'ንግዲህ ‹ያውልቁ› ነው 'ሚባለው። እንዴ!" ብሎ በድንገት ጮኸ "የኔ ውቢት፣ ያውልቁ! እኮ ፈጠን! ፈጠን!" እያለ ቀና ሲል አይኖቹ ፈጠጡ። ይህንንም ያባሰበት ከጩኸቱ ድንገተኛነት እኩል የተገለፀለት የማርሰሊን እዚያ አለመኖር ነበር።

እሷ ለራሷ አንድ ትንሽ ሻንጣ አንጠልጥላ በመውረጃው ጉን ባሉት እጅ መደገፊያዎች እየታገዘች ግድግዳውን እየታከከች በቀላሉ እየተራመደች ነበር፣ ሶስት ሜትር ከምናምን ብቻ ቁልቁል ዘለለችና ሽሽትዋ አበቃ። መንገድ ዳር ባለው ማእዘን ተጠምዝዛ ጠፋች።

# አስራ ስድስት

ትሩስካዮን አሁንም እንደገና የዛፓ ዩኒፎርሙን ለብሷል። ከሞን-ዴ-ፒዬቴ መጠጥ ቤት አልፍ ብሎ በምትገኘው ትንሽ አደባባይ በትካዜ ቆሞ፣ የተጠቀሰው ቤት እስከሚዘጋ ይጠብቃል። በሀሳብ ተውጦ (ይመስላል) ሲመለከት በሜትሮ ወደታች መግቢያ የበር መዝጊያ ብረቶች ላይ የተገኙ አያሌ ክሎሻር-ሰዎች፣ ይህ ጉድጓድ ከስር የሚሰድላቸውን እና እቺ የስራ ማቆም አድማ ልታቀዘቅዘው ያልቻለችውን የሜዲትራኒያን ባህር ሙቀት ይኮመኩማሉ። ጥቂት ጊዜ በሀሳብ እንደዚህ ሲያወጣ ሲያወርድ ቆየ፡- የሰው ነገር ተሰባሪ ስለመሆኑ፣ እና የአይጦች እቅድ እንደማይሳካ ሁሉ፣ የሰዎችም ቢሆን የትም እንደማያደርስ። ከዚያም በነዚህ ክሎሻር - ሰዎች ይቀናባቸው ጀመር - ለጥቂት ቅፅበት ያህል ብቻ ነው፣ ማካበድ አይገባም መቸስ። የነዚህ ርጋፊ የሆኑ ሰዎች ኑሮ አስቀናው፣ ርጋፊ ቢሆኑም ምናልባት ከማህበራዊ ባርነቶች እና እተከበረ ከሚባለው አሰም ተፅእኖ ከብደት ነፃ የወጡ በመሆናቸው። ትሩስካዮን በረጅሙ ተነፈሰ።

ከሱ እህህ የባሰ ሳግ አስተጋባ፣ ይህም ትሩስካዮናዊውን የሀሳብ መንሳፈፍ ረበሸው። ‹ምን-ምን-ምን?› አለ ትሩስካዮናዊው ሀሳብ፣ በተራው እንደአሳቢው የዛፓ ዩኒፎርሙን እየለበሰ፣ እና ሳግ ያስተጋባውን ጥላ በጥንቁቅ አይን ቢቃኝ፣ የጥልቅ ባዩ ድምፅ ምንጭ ቤንች ላይ ፀጥ ብሎ የተቀመጠ ፍጡር ሆኖ አገኘው። ትሩስካዮን ተጠጋው (የተለመደውን ጥንቃቄ ሳይወስድ አልቀረም መቸስ) ክሎሻር ሰዎቹ እንቅልፋቸውን ቀጠሉ፣ ሰው ሲያልፍ ሳመሉ እየተሰማቸው።

ግለሰቡ የሚያንቀሳቀሩ አስመሰለ፣ ይህም ትሩስካዮንን አላረጋጋውም፣ ቢሆንም ግን በሚከተሉት ቃላት ከመናገር አላገደውም፡-

"እንዲህ በመሸበት ሰአት እዚህ አካባቢ ምን ያረጋሉ?"

"እርስዎን ይመለከትዎታል?" መለሰ ሰውየው፣ የማይታወቅ በመሆኑ እንበለውና

ትሩስካዮን በበኩሉ ጥያቄ በሚወረውርበት ጊዜ ራሱን ይህንኑ ጥያቄ ሲጠይቅ ቆይቷል። አዎና! ነገሩ እሱን በምን ይመለከተዋል? ሙያው ነው'ኮ እንዲህ እንዲሆን ያደረገው፣ በተጠርጣሪ ላይ ከበባ የማድረግ ልምድ። ግን ማርሰሊን ከጠፋችበት ወዲህ የሁኔታውን ጠፍር በቅንዝር ስፐርም የማለስለስ ድክመት አምጥቷል። ይህን ወደ ጥፋት የሚወስድ ዝንባሌ እየታገለ ጭውውቱን ቀጠለ፡-

"አዎን" አለ "ይመለከተኛል"

"እንዲህ ከሆነማ" አለ ሰውየው "ጉዳዩ ሌላ ነው"

"እንግድያው መጀመርያ ያቀረብኳትን ሀሳብ እንደገና ለማቅረብ ይፈቅዱልኛል?"

"ያቀረብኩትን" አለ ሰውየው ጭለማው ውስጥ

"ያቀረብኳትን" አለ ትሩስካዮን

"ያቀረብኩትን - ‹ኩ›" ደግሞ አረመው

"ያቀረብኳትን" አለ ትሩስካዮን በመጨረሻ "አይ! እኔ'ኮ ሰዋሰው አይሆንልኝም አይቀናኝም። እና እሱ ነው ደጋግሞ ጉድ የሰራኝ። እንለፈው። እና?"

"እና ምን?"

"ጥያቄዬ"

"እንዴ?" አለ ሌላኛው "ረሳሁት። ያን ጊዜውኑ"

"እንደገና መጀመር አለብኝ ማለት ነው?"

"ይመስላል"

"አይ ልፋት!"

ትሩስካዮን በረጅሙ ሲተነፍስ አለና ተወው፣ ሰውየው እንዳያስተጋባው በመፍራቱ

"ይበሉ'ንጂ" አለ ይሄኛው በመግባባት "ትንሽ ይሞክሩ"

ትሩስካዮን በረዥሙ ዘረዘረለት

"ስም ያባት ስም የተወለዱበት ቀን የተወለዱበት ቦታ ታርጋ ቁጥር የስራ ዋስትና የባንክ ሂሳብ ቁጥር የቁጠባ ማህደር ደብተር የቤት ኪራይ ደረሰኝ የውሀ ደረሰኝ የጋዝ ደረሰኝ የመብራት ደረሰኝ የሜትር ሳምንታዊ

ካርድ የኦቶቡስ ሳምንታዊ ደረሰኝ የሞዝቮልድ እቃ የተገዛበት ደረሰኝ የፍሪጅ ማስታወቅያ ወረቀት የቁልፎች ሰንሰለት የመመገብያ ካርድ የይለፍ ወረቀት የጳጳሱ መልእክት እና ወዘተርፈ ወረቀቶችዎን ያለንግግር ያቀብሉኝ። ለዚያውም ለኦቶሞቢልን ጉዳይ ሳላነሳ ነው፡- ግራጫ ካርድ መጠባበቅያ የዘይት መብራት ኢንተርናሽናል ፓስፖርት እና የመሳሰሉት፣ ምክንያቱም ይህን ሁሉ ለማሟላት አቅምዎ አይፈቅድም ይሆናል"

"አለቃዬ፣ ያንን ኦቶቡስ ያዩታል?" (በምልክት እየጠቆመ)

"አዎን"

"እኔ ነኝ 'ምነዳው"

"እ!"

"እንዴ! ይበሉ'ንጂ፣ ያን ያህል ንቃት ይጐድሎታል ማለት ነው? እስካሁን አላወቁኝም?"

ትሩስካዮን በመጠኑ ተረጋግቶ ሄደና ከጐኑ ተቀመጠ

"ይፈቀዳል?" ጠየቀ

"አዎን'ንጂ"

"መኪናዎ የቆመው በተገቢው ስርአት አይደለም"

(ዝምታ)

"እውነት ነው" ቀጠለ ትሩስካዮን "ስነ-ስርአትን በተመለከተ፣ ዛሬ አብዝቼዋለሁ"

"መጠጥ ይሆን?"

"የውስጥ አርበኝነት"

(ዝምታ)

ትሩስካዮን ጨመረ፡-

"በሴቶች ምክንያት"

(ዝምታ)

ትሩስካዮን ቀጠለ፡-

"... ንስሀ አለብኝ ጉሮሮዬን እንቅ የሚያረግ... ንስሀው... ማለቴ እንዲወጣልኝ ያህል፣ ... በርከት ያለ የማወራው ይኖረኛል..."

(ዝምታ)

"ነው'ንጂ" አለ ፌዶር ባላኖቪች

አንዲት ቢምቢ ወደ መንገድ መብራቱ ድምቀት በረረች። ሌላ የሰው ቆዳ ከመብላትዋ በፊት ሙቀት ለመውሰድ ፈልጋ ነበር። ተሳካላት። የከሰለው ገላዋ በዝግታ ብጫው አስፋልት ላይ ወደቀ

"ጌሺ፣ ይቀጥሉዋ" አለ ፌዶር ባላዉቪች "አለዛ እኔ ነኝ ማውራት 'ምጀምረው"

"ዋለም አይሆንም" አለ ትሩስካዮን "ትንሽ እንቀጥል ስለኔ ማውራት"

ፀጉራም ቆዳውን በዘራፊና አጫጆ ጥፍሩ ካከከ በኋላ፣ ሚዛናዊነት ያልተሳናቸው፣ እንድያውም ጨዋ የሆኑ ቃላት ተናገረ። ቃላቱም እኚውና፦

"ስለልጅነቴም ሆነ ስለወጣትነቴ ምንም አልነግርትም። ትምህርቴ፣ ስለሱ አናውራ፣ ምንም የለኝ። ስለሙያዬ ስለጤናዬም ምንም ይህል አልናገርም፣ ትንሽ በመሆኑ፣ ይኸው ነው በቃ። አሁን እንግዲህ ወደ ወታደራዊ አገልግሎቴ መጣሁ፣ ስለሱ አበክሬ አልናገርም። ገና በጮርቃ እድሜዬ ወንደላጤ ሆንኩ፣ ኑሮ ነው እንዲህ እንድሆን ያደረገኝ"

አቋረጠ፣ ለቅንጣት ጊዜ በሰመመን ተዋጠ

"እንዴ! ይቀጥሉ'ንጂ" አለ ፌዶር ባላኖቪች "አለዛ እኔ መጀመሬ ነው"

"እውነትም" አለ ትሩስካዮን "ነገሮች ልክ አልመጡም... እና ይሄ ሁሉ ዛሬ ጧት በታወቅኩዋቸው ሴትዮ ምክንያት"

"ተዋወቅኩዋቸው"

"በታዋወቁሁዋቸው"

"በተዋወቅኩዋቸው--ተዋወ"

"በተዋወቅኩዋቸው"

"ያቺ ጋብሪዬል አስከትሏት የሚዞረው እርጊት?"

"አይ እሷ አይደለችም። በነገራችን ላይ፣ እሷ ሴትዮ ቅር አሰኝታኛለች። ለቀቀችኝ ወደ ስራዎቼ እንድሯሯጥ (አቤት ስራዎቼ ደሞ!) ለይስሙላ ያህል እንኳ ልታስቀረኝ አልሞከረችም። እሷ የፈለገችው አንድ

ነገር ብቻ ነበር - ጋብሪዬላ ስትደንስ ማየት፡፡ ጋብሪዬላ... ድንቅ... ከድንቅም ድንቅ"

"ትክክለኛው ቃል ነው" አለ ፌዶር ባላኖቪች "የጋብሪዬልን ትርኢት የሚወዳደር በፓሪስ ምድር የለም፣ ደሞ እመኑኝ፣ ስለዚህ ከተማ ናይት-ክለብ አማውቀው ብዙ ነው"

"እርስዎስ ታድለዋል" አለ ትሩስካዮን በግማሽ ልቦና

"ግን ይህን የጋብሪዬልን ትርኢት በጣም ብዙ ጊዜ ስላየሁት ስልችት ብሎኛል፣ እውነት ለመናገር፡፡ ከዚህም ጋር ትርኢቱ አይለዋወጥም፡፡ ምን ይደረግ፣ አርቲስቶች ሲባሉ ብዙ ጊዜ እንደዚህ ናቸው፡፡ ብልሀተኛ ዘዴ አንዴ ካገኙ፣ እስከመጨረሻ ይጠቀሙበታል፡፡ ሁላችንም በየፈርጃችን በመጠኑ እንደሱ መሆናችንን መገንዘብ ይገባል"

"እኔ እንደዚያ አይደለሁም" አለ ትሩስካዮን በቀጥታ "ዘዴዎቼን ሁልጊዜ እንደለዋወጥኩዋቸው ነው"

"የሚያረካዎትን ገና ስላላገኙት ነው፡፡ ይኸውሎት፣ ራስዎትን እየፈለጉ ነው፡፡ አንዴ አጥጋቢ ውጤት ካገኙ ግን በዚያው ይረጋሉ፡፡ ምክንያቱም እስከ ዛሬ ያገኙት ውጤት ያን ያህልም አልነበረም፡፡ እንደ እርስዎ ማለት ነው — ምስኪን ሰው ይመስላሉ"

"ዩኒፎርሜን ለብሼም?"

"እሱ ምንም ልዩነት አያመጣም" ትሩስካዮን ቅስሙ ተሰብሮ ዝም አለ

"ደግሞስ" ቀጠለ ፌዶር ባላኖቪች "ነገሩ ምን ትርጉም አለው?"

"እረ እኔ አላውቅም፡፡ ማዳም ሙዋክን እየጠበቅኩ ነው"

"እኔ ደሞ ዝም ብዬ ፋራዎቼን እየጠበቅኩ ነው ወደ ሆቴላቸው ለመውሰድ፣ ምክንያቱም በማለዳ ወደ ጂብራልታር ባለጥንታዊ ሰገነቶች መገስገስ አለባቸው፡፡ የጉዞዋቸው ቅደም ተከተል እንደሱ ነው፡፡"

"ምንኛ ታድለዋል!" አለ ትሩስካዮን በግማሽ ልቦና

ፌዶር ባላኖቪች ትከሻውን ከፍ-ዝቅ አደረገ፣ ስለዚህ ጉዳይ አስተያየት ለመስጠት ፈቃደኛ ሳይሆን ቀረ፡፡

ይህን ጊዜ ጫጫታዎች ተሰሙ፣ ሞን-ደ-ፒዩቴ እየተዘጋ ነው፡፡

"ልክ በጊዜ" አለ ፌዶር ባላኖቪች

ተነሳና ወደ ኦቶቡስ አመራ። ዝም ብሎ ሄደ፣ ያለስንብት ቃላት።

ትሩስካዮን ተራውን ተነሳ። አመነታ። ክሎሽር-ሰዎቹ ተኝተዋል። ቢምቢዋ ሞታለች

ፌዶር ባላኖቪች በንቹ ለመሰብሰብ ጥሩምባውን አንድ ሁለት ጊዜ ነፋ። እነሱ በበኩላቸው ስላሳለፉት አሪፍ፣ እንድያውም ድንቅ ምሽት እንኳን ደስ አለን እየተባባሉ፣ ይህንኑ መልእክት ባገርኛ ቋንቋቸው ለማስተላለፍ እየተሻሙ ይዘበራርቃሉ። ሰዉ ተሰነባበተ፣ ሴቱ ወገን ጋብሪዬልን ለመሳም ከጀለ፣ ወንዱ ወገን አልደፈረም።

"ጫጫታውን እንቀንስ" አለ ባላኖቪች

ተጓዦቹ ቀስ በቀስ ኦቶቡሱ ላይ ወጡ። ፌዶር ባላኖቪች አዛጋ።

የሸቦ ቤትዋ ውስጥ፣ ላቨርድዩር ተኝታለች። ዛዚ እንቅልፏን በአልበገር ባይነት ተጋፈጠችው፣ እንደ ላቨርዲዩር አልሆነችም። ሻርል ታክሲውን ሊያመጣ ሄዷል።

"ታድያስ፣ የኔ ቀጣፊ" አሉ ባልቴትዋ ሙዋክ፣ ትሩስካዮን ሲመጣ አይተውት "እንዳሰባችሁት ተደሰታችሁ?"

"ያን ያህልም አይደለም፣ ያን ያህልም አይደለም" አለ ትሩስካዮን

"አቤት እኛ የተዝናናነው መዝናናት! መስየ እንዴት ኮሚክ መሰሉህ"

"አመሰግናለሁ" አለ ጋብሪዬል "ሆኖም ግን ጥበቡን አይርሱብኝ። ቀልድና ሳቅ ብቻ አይደለም፣ ጥበብም አለበት"

"ታክሲውን ይዞ ቶሎ አይመጣም'ንዴ?" አለ ቱራንዶ

"ጥሩ ተዝናናች?" ጠየቀ አድሚራሉ፣ እንስሳዋ ራሷን በክንፏ ስር ስታኖር እየተመለከታት

"ትውስታዎች ይተውላታል" አለ ቱራንዶ

የመጨረሻዎቹ ተጓዦች ቦታቸውን ይዘዋል። ፖስት-ካርዶች ይልካሉ

"ሆሆ!" ጮኸ ጋብሪዬል "አድዮስ አሚጎስ፣ ቺንቺን! እስክምንገናኝ..."

ኦቶቡሱ ርቆ ሄደ፣ እነዚህን እጅግ የተደሰቱ የውጭ ሰዎች ወሰዳቸው። በዚያው ቀን፣ ጠዋት ባለጥንት ሰገነቶች ወደሆነችው ጂብራልታር ይጓዛሉ። የጉዞዋቸው ቅደም ተከተል እንደዚህ ነው።

የሻርል ታክሲ መጥታ እግረኛ-መንገዱ ጐን ቆመች

"ሰዎች በዝተናል" አለች ዛዚ

"እሱ ምንም ማለት አይደለም" አለ ጋብሪዬል "አሁን ሄደን አንድ የሽንኩርት ሾርባ እንከታለን"

"አመሰግናለሁ" አለ ሻርል "እኔ ወደ ቤቴ ነኝ"

ወድያው

"ታድያስ ማዳ፣ እየመጣሽ ነው?"

ማድሌን ገባችና ከወደ ፊት ባለቤትዋ ጐን ተቀመጠች

"ሁላችሁም ደህና ሁኑ" ጮኸች በመስኮቱ "አመሰግናለሁ ለቆንጆው እና የደ..."

የተቀረው አልተሰማቸውም፣ ታክሲው ርቆ ሄዷል።

"አሜሪካን አገር ብንሆን ኖሮ" አለ ጋብሪዬል "ሙሽሮቹ ላይ ሩዝ እንበትንባቸው ነበር"

"እሱ በድሮ ፊልሞች ውስጥ ያየኸው ነው" አለች ዛዚ "ዛሬ ፊልሙ መጨረሻ ላይ የሚጋቡት ከድሮ ቀንሷል። እኔ ይበልጥ 'ምወደው ሁሉም ሲሞቱ ነው"

"እኔ የሩዙ ይበልጥ ደስ ይለኛል" አሉ ባልቴትዋ ሙዋክ

"አልጠራኖትም" አለች ዛዚ

"ማድሟዜል" አለ ትሩስካዮን "ከአዛውንት ጋር ሲሆኑ ከዚህ የበለጠ ጨዋ መሆን ይገባዎታል"

"አቤት ሲከላከልልኝ ሲያምርበት!" አሉ ባልቴትዋ ሙዋክ

"ወደፊት!" አለ ጋብሪዬል "Les Nyctalopes ወደሚባለው መጠጥ ቤት ነው 'ምወስዳችሁ። እዚያ ነው በጣም 'ሚያውቁኝ"

ባልቴትዋ ሙዋክና ትሩስካዮን ተከተሉዋቸው

"አይተሀል?" አለችው ዛዚ ጋብሪዬልን "አሮጊቷና ዛፓው እየተከተሉን ናቸው"

"ልንከለክላቸው አንችልም፡፡ ነፃ ናቸው"

"አንተ ልታስፈራራቸው አትችልም? ላያቸው አልፈልግም"

"በህይወታችን ውስጥ ለሰዎች ከዚህ የበለጠ ሰብአዊነት ማሳየት ይገባናል"

"ዛፓ ቢሆንም'ኮ" አሉ ባልቴትዋ ሙዋክ፣ ሁሉንም ሰምተው ስለነበረ "ዞሮ ዞሮ ሰው ነው"

"አንድ ዙር መጠጥ በኔ ይሁን" አለ ትሩስካዮን፣ እንደማፈር እያለ

"በጭራሽ አይሆንም" አለ ጋብሪዬል "ዛሬ ማታ እኔ ነኝ 'ማምበሸብሻችሁ"

"አንዲት ትንሽ ዙር ብቻ" አለ ትሩስካዮን፣ በሚማፀን ድምፅ "ሙስካዴ ወይን ለምሳሌ፡፡ አቅሜ የሚፈቅደውን ያህል"

"ጥሎሽህን አታባክን" አለ ጋብሪዬል "የኔ ጉዳይ ሌላ ነው"

"ከዚህም ጋር" አለ ቱራንዶ "አንተ ምንም አትጋብዘንም፡፡ ዛፓ መሆንህን ረስተህ ነው፡፡ እኔ ሎሚናት እምጠጣ ሰው፣ አንድ ዛፓ፣ ሰዎች ይዞ ሊያጠጣቸው ቢመጣ፣ ምንም ቢመጣ አልቀዳላቸውም፡፡"

"እናንተስ አትረቡም" አለ ግሪዱ "አላወቃችሁትም 'ንዴ? የዛሬ ጧቱ ሴት አሳዳጅ ወጠጤ ነው'ኮ"

ጋብሪዬል በይበልጥ አትኩሮ ሊመለከተው ዘምበል አለ፡፡ ሁሉም (ዛዚ እንኳን ሳትቀር በጣም ስለገረማት እና ከዚህም ጋር ስላበሸቃት) የምርመራውን ውጤት ይጠብቃሉ፡፡ ትሩስካዮን ደንግጦ ዝምታ ውስጥ በተጠንቀቅ ቆየ

"ሙስታሽህን ምን አረግከው?" ጠየቀው ጋብሪዬል፣ ሰላማዊም አስፈሪም በሆነ ድምፅ

"ሊጉዱብኝ እንዳይሆን ብቻ!" አሉ ባልቴትዋ ሙዋክ

ጋብሪዬል ባንድ እጁ ትሩስካዮንን በጃኬቱ አንገት አነሳውና ጥናቱን ለማካሄድ ወደ መንገድ መብራት ወሰደው

"እ" አለ "ሙስታሽህሳ?"

"ቤቴ ተውኩት" አለ ትሩስካዮን

"ከዚህም ጋር ደሞ ፖሊስ ነህ፣ እውነት ነው?"

"የለም! የለም" ጮኸ ትሩስካዮን "የማስመሰል መልኬ ነው... እንድያው ራሴን ለማዝናናት ያህል... እናንተን ለማዝናናት... እንደ እርሶ ጥብቆ የሴት ጉርድ ቀሚስ... የሚፈረጅ ነው..."

"አብሮ የሚፈረጅ፣ እንዳንተ የሰው ጉዳይ ማነፍነፍ" አለ ግሪዱ፣ ብልጭ ብሎበት

"እንድያም ሆኖ፣ ሊጉዱት እንዳይሆን" አሉ ባልቴትዋ ሙዋክ

"ጉዳዩ ምክንያት ይጠይቃል" አለ ቱራንዶ፣ ጭንቀቱን እያሽነፈ

"ታወራለህ፣ ታወራለህ..." አለች ላቬርድዩር በድካም፣ እና ተመልሳ ተኛች

ዛዚ ፀጥ ብላለች፡፡ ተከታታይ ልብ ሰቃይ ሁኔታዎች በዝተውባት፣ ከባድ እንቅልፍ ተጫጭኗት፣ ሳሁኑ ሁኔታ እና ለሰብአዊ ክብሯ መጣኝ በሆነ ኩሩ አተያይ ለመከሰት ሞከረች፣ አልሆነላትም እንጂ፡፡

ጋብሪዬል ትሩስካዮንን በመንገድ መብራቱ ግንድ ወደ ላይ አንሸራተተው፣ እንደገና በዝምታ ተመለከተው፣ በቀስታ መልሶ በእግሩ አቆመው፣ እና እንደሚከተለው ተናገረው፡-

"ምን ፈልገህ ነው እንደዚህ 'ምትከተለን?"

"እናንተን አይደለም 'ሚከተለው" አሉ ባልቴትዋ ሙዋክ "እኔን ነው"

"እውነት ነው" አለ ትሩስካዮን "ምናልባት አያውቁም ይሆናል... ግን ለአንዲት እንስት ከወደቁላት..."

"ስለኔ (እውይ ይሄ ተወዳጅ ሰውዬ!) ምን አሽሙር (አንዲት እንስት አለኝኮ!) እየተናገርክ ነው?" ጋብሪዬል (እና ባልቴትዋ ሙዋክ) እኩል ተናገሩ - (አንደኛዋ በፍቅር ትኩሳት) ሌላኛው በሀይለኛ ቁጣ፡፡

"አንቱ ምስኪን የዋህ!" ቀጠለ ጋብሪዬል፣ ወደ ወይዘሮዋ እየዞረ "የሚሰራውን ሁሉ አይነግሮትም'ኮ"

"ገና ጊዜ አላገኘሁም'ና ነው"

"ቀፋፊ የሆነ ሴት - አዳኝ ወጠጤ ነው" አለ ጋብሪዬል "ዛሬ ጧት እቺን ሚጡ ሲያሳድዳት ሸሽታ ቤቷ ደረሰች፡፡ ወራዳ!"

"እንዲህ አርገሀል?" ጠየቁ ባልቴትዋ ሙዋክ፣ ስሜታቸው እየተናወጠ

"ያን ጊዜ ገና አላውቆትም ነበር" አለ ትሩስካዮን

"ሀጢአቱን አመነ!" አምባረቁ ባልቴትዋ ሙዋክ

"አምኗል!" ጮሁ ቱራንዶና ግሪዱ

"አሀ! አመንካ?!" አለ ጋብሪዬል በሀይለኛ ድምፅ

"ይቅርታ!" ጮኸ ትሩስካዮን "ይቅርታ!"

"ይሄ ወራዳ!" አናፉ ባልቴትዋ ሙዋክ

ይሄ የቃለ-አጋኖዎች ጫጫታ በጨለማው ውስጥ ሁለት ባለዶቅዶቂዎችን አስወጣቸው

"ጩኸት በውድቅቱ!" ጮሁ ሁለቱ ባለዶቅዶቂዎች "ሁካታ በጨረቃ፣ የስጋና-አትክልት-በሊታዎች አምባጓሮ፣ በእኩለ-ሌት አፍ መካፈት፣ አሀ! ይሄ'ማ'ኮ..." ጮሁ ሁለቱ ባለዶቅዶቂዎች

ጋብሪዬል የያዘውን የትሩስካዮንን የጃኬት አንገት ረጋ ብሎ ለቀቀ

"አንድ ጊዜ!" ጮኸ ትሩስካዮን፣ ሀይለኛ ወኔ ያለው መሆኑን እያስመሰከረ "አንድ ጊዜ፡፡ አላያችሁኝም'ንዴ? ዩኒፎርሜን ተመልከቱ፡፡ ፖሊስ ነኝ፣ ክንፎቼን እዩ" ብሎ የፖሊስ ካባውን አውለበለበ

"ከየት ብቅ አልክ?" አለ ለመነጋገር ብቃት ያለው ባለዶቅዶቂ "በሰፈሩ ታይተህ አታውቅም"

"ሊሆን ይችላል" መለሰ ቱራንዶ፣ ጥሩ ደራሲ "እብደት" ከማለት በሌላ ቃላት ሊገልፀው የማይችል ድፍረት ነብስ እየዘራበት "ሊሆን ይችላል፣ ግን ያ ሊያግደኝ አይችልም፡፡ ፖሊስ ነኝ፣ እና በፖሊስነቴ እቀጥልበታለሁ"

"እነዚህሳ" አለ ባለዶቅዶቂው፣ ተንኮል እየታየበት

"እነዚህ ሌሎች ሁሉም ፖሊስ ናቸው?" ሰውነቱን እያንቀሳቀሰ መለሰ

"አታምኑኝ ይሆናል'ንጂ፣ እንደ ፀበል ውሀ ንፁሀን ናቸው"

"ይሄ ሁሉ ያን ያህልም ክርስትያንነት መስሎ አይታየኝም" አለ ተናጋሪው ባለዶቅዶቁ

ሌላው ጭራቅ መሳይ ገፅታውን በመለዋወጥ በምርመራው ተሳተፈ

"ግን እኔ'ኮ በልጅነቴ በካቶሊክ ስርአት ቆርቤአለሁ" መለሰ ትሩስካዮን

"እቺ አስተሳሰብ'ንኳ ምኗም የፖሊስ ሽታ የላትም" ጮኸ ተናጋሪው ባለዶቅዶቁ "ከጠረንህ ስር ሲሸተኝ ደሞ የነዚህ የቤተ-ክህነትንና የፖሊስ ሰራዊትን ህብረት ለማሳመን የሚፈልጉ አመፀኛ እትሞች አንባቢ ነህ፣ እንድያም ሆኖ ግን፣ ትሰማላችሁ? (ዙርያውን ለቆሙት ይናገራል) ቄሶቹን ፖሊስ መዳፉ ውስጥ አርጓቸዋል"

ይህ የትወና እንቅስቃሴ በዝምታ ተስተዋለ፣ ቁራንዶ ብቻ በታዛዥነት ፈገግ አለ። ጋብሪዬል በግልፅ ትከሻውን ከፍ-ዝቅ አደረገ

"አንተ" አለው ተናጋሪው ባለዶቅዶቁ "ትሸታለህ ማርዣለይን ወይን ጠጅ"

"ማርዣለይን?" አለ ጋብሪዬል በርህራሄ "ባርቡዝ ነው፣ የታላቁ ፊዮር ሽቶ"

"እእ!" አለ ባለዶቅዶቂው ሳያምነው "አሳየን እንየው"

የጋብሪዬልን ኮት ለማሽተት ቀረብ አለ

"ኧረ በስማም!" አለ በማስከተል፣ ለማመን ምንም ያህል ሳይቀረው "እዩና ተመልከቱ" ብሎ ጨመረለት ለአጋሩ

ሌላው በተራው የጋብሪዬልን ኮት አሸተተ። ራሱን ነቀነቀ

"ቢሆንም" አለ መናገር የሚያውቀው "ይሄ የሚያሳምነኝ አይደለሁም። ማርዣለይን ወይን-ጠጅ ይሸታል"

"እነዚህ ፋራዎች ስለዚህ ጉዳይ ምን ሊያውቁ ይችሉ ይሆን? ብዬ ለራሴ እያሰብኩ ነው" አለች ዛዚ እያዛጋች

"እኔው ነኝና! እቺ ውርጋጥ!" አለ ማውራቱን የሚችልበት ባለዶቅዶቂ "ለምታችሁልኛል ንቀቷን? እየተሳደበች'ኮ ነው!"

"እየተሳደብኩ አይደለም" አለች ዛዚ በመለሳለስ እየተናገረች "ገለፃ ማድረጌ ነው"

ጋብሪዬልና ግሪዬ በሳቅ ሲንከተከቱ ጊዜ፣ ለነሱ ጠቃሚታና መዝናናት በማሰብ ጨመረችላቸው፡-

"ይሄም የጄኔራል ቤርሞትን ማስታወሻ ሳነብ ያገኘሁት ነው"

"አ! ይሄማ" አለ ባለዶቅዶቂው "እቺ ሚጢጢ'ኮ እየተጫወተችብን ነው፣ ሰውየው በማርገርለይን ወይን እንደቀለደብን"

"አይደለም" አለ ጋብሪዬል "ልድገምላችሁ - ‹ባርበ·ገዘ ነው፣ የታላቁ ፊዮር ሽቶ›"

ባልቴትዋ ሙዋከ በተራቸው ለማሽተት ተጠጉ

"የፌዮር ሽቶ ነው" አሉዋቸው ሁለቱን ባለዶቅዶቁዎች

"አልጠራኖትም" አለ መናገር የማያውቀው

"እሱስ እውነት ነው" አጉረመረመች ዛዚ "እኔም ቅድም ይህንኑ ነግሬያቸዋለሁ"

"እያዩ ማየት ተገቢ ነው፣ ለወይዘሮዋ ጨዋነትን ማሳየት" አለ ትሩስካዮን

"አንተ" አለ መናገር 'ሚያውቀው ባለዶቅዶቂ "ብዙ ትኩረት ወደ ራስህ ባትስብ ይሻልሃል"

"እያዩ ማየት ተገቢ ነው" ደገመ ትሩስካዮን፣ የባልቴትዋን ስሜት በሚነካ ወኔ

"በዚህ ሰአት ብትተኚ አይሻልሽም ነበር?"

"አ!አ!" አለች ዛዚ

መናገር የማያውቀው ባለዶቅዶቂ "በል 'ንጂ ወረቀቶችህን አሳየን" አለ ትሩስካዮንን፣

"እንዲህ አይነቱስ ታይቶም አያውቅ!" አሉ ባልቴትዋ ሙዋክ

"ዝም በይ አንቺ አሮጊት!" አለ መናገር የማያውቀው ባለዶቅዶቂ

"አ!አ!" አለች ዛዚ

"ለመቤቴ ጨዋነትን አሳዩዋቸው አልኳችሁ!" አለ ትሩስካዮን፣ የመጣው ይምጣ በሚል ድፍረት

"አሁንም የፖሊስ ያልሆነ አመለካከት" አለ መናገር የማያውቀው ባለዶቅዶቂ "ወረቀቶችህን!" እንራብት "እኮ ፈጠን!"

"አቤት ማስደሰቱ!" አለች ዛዚ.

"አሁንስ በዛ!" አለ ትሩስካዮን "እኔ ሆንኩ ወረቀት እምጠየቀው፣ እነዚህ ሰዎች ግን (እየጠቆመ) ምንም አይጠየቁም"

"ይሄማ ደግ አይደለም" አለ ጋብሪዬል

"የማን ነው ወራዳ?!" አለ ግሪዱ

ባለዶቅዶቂዎቹ ግን እንዲህ በቀላሉ ሀሳባቸውን የሚለውጡ አልሆኑም

"ወረቀቶችህን!" ጮኸ መናገር የማያውቀው

ይህን ጊዜ "ጩኸት በውድቅት!" ብለው ከጩኸቱ በላይ ጮሁ ሌሎች ዛፓዎች፣ በፖሊስ መኪና የታጀቡ "ሁካታ በጨረቃ፣ የስጋና-አትክልት-በሲታዎች አምባጓሮ፣ በእኩለ-ሌት አፍ መካፈት፣ አሀ ይሄማ'ኮ..."

ፍፁም በሆነ ሙያዊ ዘዴ ጥፋተኞቹ የትኞቹ እንደሆኑ በማወቃቸው፣ ሳያመነቱ ትሩስካዮንንና ሁለቱን ባለዶቅዶቂዎች ጫኑዋቸው። ሁሉም በፍጥነት ከአይን ጠፉ

"እውነትም ለካ ፍትህ አለ" አለ ጋብሪዬል

ባላቸው የሞተባቸው ወይዘሮ ሙዋክ በእድላቸው አዝነው አላዘኑ

"ማልቀስ አያስፈልጎትም" አለ ጋብሪዬል "ፍቅረኛዎ በሆነ ነገር የጨነገፈ ነበር። ከዚህም ጋር እየተከታተለን አስልችቶን ነበር። ይበሉ፣ ከኛ ጋር ይምጡና አብረውን የሽንኩርት ሾርባ ይቋደሱ። እሹሩሩ የሚለንና የሚፅናናን የሽንኩርት ሾርባ"

# አስራ ሰባት

አንዲት እንባ ትኩስ ዳቦ ላይ ጠብ አለችና እዚያው ተነነች

"አይዞት አይዞት!" አላቸው ጋብሪዬል ባልቴትዋን ሙዋክ "ይበርቱ! አንዱ ቢሄድ አስሩ ይመጣል፡፡ ፉንጋ ቢሆኑም አንዱን ሌላ ቀጣሬ መጥለፍ ምንም አያቅቶትም"

በረኛው ተነፈሱ፣ የሚተማመኑበት በማጣት፡፡ ቁራሽ ዳቦው ወደ ማንኪያው ውስጥ ተንሸራተተ፣ እየተነነ እያለ ባልቴትዋ ወደ ጉሮሮዋቸው ሸኙት፡፡ አቃጠላቸው

"እሳት አደጋ ይጥሩ" አላቸው ጋብሪዬል

እና ብርጭቆዋቸውን እንደገና ሞላላቸው፡፡ በዚህ አይነት እያንዳንዷ ሙዋካዊት ጉርሻ በበሳል ሙስካዴ ወይን-ጠጅ ተሸኘች፡፡

ዛዚ ወደ ላቬርድየር እንቅልፍ ገብታለች፡፡ ግሪዱ እና ቱራንደ በዝምታ ከፍቅፋቂው ከሮች ጋር በጥርስ ይታገላሉ

"ግሩም አይደለችም እቺ የሽንኩርት ሾርባ?" አላቸው ጋብሪዬል ሁኔታችሁ ሲታይ፣ አንተ ውስጡ የቦት ጫማ ገበር የጨመርክባት ይመስላል፣ አንተ ደሞ የመመገብያ እቃዎች እጣቢ ያፈሰስክባት ትመስላለህ፡፡ እኔ ግን 'ምወደው ያህንኑ ነው፣ ቤት ያፈራውን፣ ከተፈጥሮ የተገኘውን፣ ባንድ ቃል—ፅዳት!

ሌሎቹ ተስማሙ፣ ግን ምንም አልተናገሩም

"እንዴት ነው ዛዚ? ሾርባሽን አትጠጪም?"

"ይተዉዋት ትተኛ" አሉ ባልቴትዋ ሙዋክ፣ እንጀታቸውን ስለበላችው "የተዉዋት ህልሟን ታልም"

ዛዚ አንድ አይኗን ከፈተች

"እንዴ!" አለች "አሁንም አለች እቺ አሮጊት ፊልፊላ?!"

"ለሚያዝኑ ልናዝንላቸው ይገባል" አለ ጋብሪዬል

"እርስዎ ጥሩ ሰው ነዎት" አሉ ባልቴትዋ ሙዋክ "እንደዚች (ወደ ዛዚ እየጠቆሙ) አይደሉም። ልጆች ሀዘኔታ የላቸውም፣ የታወቀ ነው"

ብርጭቆዋቸውን ጨለጡና፣ እንደገና እንዲሞላላቸው ከልብ መመኘታቸውን ለጋብሪዬል በምልክት አሳዩት።

"ምን ሆና ነው እንዲህ 'ምትጃጃለው?" አለች ዛዚ፣ ድክም ብሏት

"ኤድያ!" አለ ጋብሪዬል "ምን ልዩነት ያመጣል? አይደለም'ንዴ የኔ አሮጊቴዋ?" ብሎ ጨመረ ለዋናው ተጠቃሽ

"እርስዎማ ጥሩ ሰው ነዎት" አሉት "እንደዚች አይደሉም። የታወቀ ነው፣ ልጆች ሀዘኔታ የላቸውም"

"እንደዚህ እያደነቆረችን መቀጠልዋ ነው?" ጠየቀው ጋብሪዬልን ቱራንዶ፣ የጉረሰውን ውጦ ሲያበቃ

"ኧረ 'ናንተስ ደነዝ ናችሁ!" አለ ጋብሪዬል "ምንም ቢሆን'ኮ ሀዘን በዝቶባቸዋል፣ እኚህ እና ሆነው የቀሩ ወይዘሮ"

"አመሰግናለሁ!" አሉ ባልቴትዋ ሙዋክ፣ ልባቸው ተነክቶ

"ምንም አይደል" አለ ጋብሪዬል "ወደዚች የሽንኩርት ሾርባ እንመለስና፣ በእውነት 'ምታስደንቅ ግኝት መሆኗን ልናጤነው ይገባል"

"እቺኛዋ?" ጠየቀ ግሪዱ - ምግቡን ጨርሶ ስሁኑ ላይ የተጣበቀውን ግሩዬር ፎርማጆ ለማጣጣም በትጋት እየፋቀው - "እቺኛዋ በተለይ፣ ወይስ የሽንኩርት ሾርባ በጠቅላላ?"

"በጠቅላላ" አለ ጋብሪዬል በቆራጥነት "እኔ ባጠቃላይ ካለሆነ በጭራሽ አልናገርም። ግማሽ-ግማሽ ብሎ ነገር አይሆንልኝም"

"ልክ ነህ" አለ ቱራንዶ፣ በበኩሉ ጉበት ጥብሱን ጨርሶ "ሰኞን ማክሰኞ ውስጥ መፈለግ አይሆንም። ለምሳሌ፣ ሙስካዴ ወይን ጠጁ ይኸው እያሰቀ ሄደ፣ አሮጊቷ ናት ሁሉን 'ምትገለብጠው"

"ቅራሪ ባለመሆኑ ነው'ኮ" አሉ ባልቴትዋ ሙዋክ፣ በያስተፌስህ ፈገግታ "እኔም ስፈልግ ባጠቃላይ እናገራለሁ"

"ታወራለህ፣ ታወራለህ" አለች ላቬርድዩር፣ እሷም ሌሎቹም በማያውቁት ምክንያት ነጥራ እየነቃች "ይህን ብቻ ነው ማድረግ 'ምታውቀው"

"ጠገብኩ በቃኝ" አለች ዛዚ፣ ሰሀኑን ወደዛ እየገፋች

"ቆዩኝ" አለ ጋብሪዬል፣ ሰሀኑን በፍጥነት ወደሱ እየሳበ "እኔ እጨርስልሻለሁ። እና ሁለት የሙስካዴ ወይን ጠርሙስ ይምጣልን እና አንድ ግረናዲን ወይን" ብሎ ጨመረ እዚያ ለሚዘዋወረው ቦይ "እና ለሷስ? (ወደ በቀቀንዋ እያመለከተ ረሳናት'ኮ። ምናልባት የሆነ ጥሬ ትቆረጥም ይሆን?)"

"ሆ! ላቬርድዩር" አለ ቱራንዶ "ርቦሻል?"

"ታወራለህ፣ ታወራለህ" አለች ላቬርድዩር "ይህን ብቻ ነው ማድረግ 'ምታውቀው"

"ይሄ" አለ ግሪዱ "አዎን ማለት ነው"

"እሷ 'ምትናገረውን ለማወቅ 'ምታስተምረኝ አንተ አይደለህም" አለ ቱራንዶ በኩራት

"ያን ያህልስ አልንጠራራም" አለ ግሪዱ

"መንጠራራቱ አልቀረም" አሉ ባልቴትዋ ሙዋክ

"ነገሩን አታባብሱት'ንጂ" አለ ጋብሪዬል

"ይገባሀል?" አለው ቱራንዶ ግሪዱን "ላንተ የሚገባህ ለኔም ካንተ እኩል ይገባኛል። ከሌላ ሰው የባሰ ፋራ አይደለሁም"

"ከኔ እኩል የሚገባህ ከሆነ" አለ ግሪዱ "እኛ የምትመስለንን ያህል ጅል አይደለህም ማለት ነው"

"ለመምሰል ከሆነማ" ባልቴትዋ ሙዋክ "ኮርቶ ይመስላል"

"ደፋር ናት እቺስ!" አለ ቱራንዶ "አሁንማ ይኸው አበሳዬን እያሳየችኝ'ኮ ነው"

"የተከበረ ሰው አለመሆን ይህን ያመጣል ይኸውልህ" አለ ግሪዱ "የመጨረሻው ወራዳ ሳይቀር በንቀት ይተፋብሀል። እኔን ቢሆን ግን እቺ ሴት አትደፍረኝም"

"ሰዎች ሲባሉ ሁሉም ጅል ናቸው" አሉ ባልቴትዋ ሙዋክ፣ እና ድንገት "እርስዎም ጭምር" ብለው ጨመሩለት ለግሪዱ

ወድያውኑ አንድ ጥሩ ጥፊ ቀመሱ

ባላነሰ ፍጥነት አፀፋውን መለሱ

ግሪዱ ታድያ አንድ መጠባበቅያ ጥፊ ነበረውና፣ ሙዋካዊው ፊት ተሙለ

"ኧረ የበስማም ያለህ!" ጮኸ ቱራንዶ

እና ተነስቶ በጠረጴዛዎቹ መሀል ዱብ-ዱብ ይል ጀመር:: ሲታይ ጋብሪዬላ ‹የነጩ ዳክዬ ሞት› ትርኢቱን ሲጫወት ለማስመሰል መሞከሩ ነው::

ዛዚ ወደ እንቅልፏ ተመልሳለች:: ላቬርድዩር፣ በበቀል መንፈስ ሳይሆን አይቀርም፣ ከጎጆዋ ትኩስ ኩስ ለመተኮስ ትሞክራለች

ይሄ ሁሉ ሲሆን ሳለ፣ በግሪዱና በባልቴትዋ ሙዋክ መሀል የጥፊ ልውውጡ እንደቀጠለ ነው፣ ጋብሪዬል ደሞ ቱራንዶ አንድ እግሩን ተክሎ ለመዞር ሲሞክር እያየ በሳቅ ይንከተከታል

ይሄ ሁሉ ግን የ‹አ ኒክታሎፕ›ን አስተናጋጆች የሚያስደስታቸው አልሆነም:: እነሱ መሀል በንዲህ አይነት ጀብዱ ልዩ እውቀት ያላቸው ሁለቱ ቱራንዶን በፍጥነት ያዙትና በሁለት ክንዱ አንጠልጥለው፣ እንደ ቀልድ በቶሎ ውጭ ወስደው እግረኛ መንገዱ አስፋልት ላይ ቢወረውሩት፣ አንዳንድ አስቀያሚ ታክሲ ማሳፈር በተከለከለበት ቦታ እንዳይዘዋወር አቋረጡ፣ በማለዳው ጭጋግና ብርዳማ አየር

"ይሄማ አይሆንም!" አለ ጋብሪዬል "አይሆንም!"

ብድግ አለና፣ ሁለቱ አስተናጋጆች ደስ እያላቸው ሲመለሱ፣ አፈፍ አድርጎ ጭንቅላታቸውን ቢያጋጫቸው፣ ከጉልበቱና ከፍጥነቱ የተነሳ ሁለቱም ጉልቤዎች ተከክተው ወደቁ

"ብራቮ!" ጮሁ ባንድ ድምፅ ግሪዱና ባልቴትዋ ሙዋክ፣ የጥፊ ቅብብላቸውን በስምምነት አቋርጠው::

ስለረብሻ ልዩ እውቀት ያለው ከቦዮቹ አንዱ፣ በቅፅበት ድል ሊቀዳጅ ፈለገ:: አንዱን ጠርሙስ አንስቶ የጋብሪዬልን ጭንቅላት ሊደውለው ነበር:: ነገር ግን ግሪዱ መልሶ የማጥቃት ዘዴውን ቀድሞት አስቦ ነበር:: እንደዚያኛው የሚካበድ ሌላ ጠርሙስ በጥንቃቄ አስተካክሎ ቢወረዉርበት፣ የጮካውን ትንሽዬ ጭንቅላት እንዳይሆን አደረገው::

"ሽሪ የበስማም ያሰህ!" አጓራ ቱራንዶ፣ ጭለማ ለብሰው በሚዘዋወሩ አንዳንድ ሰዎች ድጋፍ መንገዱ ላይ ተስተካክሎ ከቆመ በኋላ፣ ቅብርር እያለ የአምባጓሮ ጉጉት እያሳየ ተመልሶ ወደ መጠጥ ቤቱ ገባ

አሁን እንግዲህ የቦይ መንጋ ከያለበት ብቅ ብቅ አለ፡፡ ይህን ያህል ይበዛሉ ብሎ ማመን በፍፁም የሚቻል አልነበረም፡፡ ከወጥ-ቤቶቹ፣ ከምድር በታች (የወይን-ጠጅ ማቀዝቀዣ) ዋሻዎቹ፣ ከቢሮዎቹ፣ ከእቃ-ቤቶቹ ወጡ፡፡ ግሪዱን፣ ሳይታሰብ የመጣባቸውን ቱራንዶን ዋጡዋቸው፡፡ ጋብሪዬልን ግን እንዲህ በቀላሉ ሊያደክሙት አልቻሉም፡፡

እነሆ፣ የጉንዳን ሰልፍ ያሳደደው ጢንዚዛ ይመስል፣ እንዲሁም እፍኝ አልቅት የተጎነጨ በሬ ይመስል፣ ጋብሪዬል ሰውነቱን አራገፈ፣ የከበቡትን ገነደሰ፣ እንደ እቃ በየአቅጣጫው የወረወራቸው ሰዎች ሲወድቁ ጠረጴዛና ወምበር ሰባበሩ፣ የተቀሩት በተስተናጋጆቹ ደምበኞች እግር መሀል ተንከባለሉ

የዚህ መተራመስ ጩኸት ሲቀጥል ዛዚን ከእንቅልፍዋ ቀሰቀሳት፡፡ አጎትዋ በሎሚናት ጠጪው መንጋ ተከቦ ስታይ ጊዜ "አይዞህ አጎቴ!" ብላ ጮኸችና አንድን የውሀ ማቅረብያ ጆግ አንስታ ወደ ትርምሱ እንደ መጣላት ወረወረችው፡፡ የፍራንስ ሴት ልጆች ወታደራዊ ወኔ ይህን ያህል የላቀ ነውና፡፡ ይህን አርአያ ተከትለው ባልቴትዋ ሙዋክ የሲጃራ መኰስተርያዎች ወደያሉበት ወረወሩ፡፡ ያዩትን የመከተል መንፈስ ከመሪ·ቸው፣ አነስተኛ ችሎታ ያላቸውን ሰዎችም ቢሆን መጠነኛ ጀብዱ እንዲፈፅሙ ያስችላቸዋልና፡፡

ይህን ጊዜ ከፍተኛ ኳኳታ ተሰማ፣ ጋብሪዬል ሰህኖች መሀል ተዘረገፈ - ወደ ስብርባሪው መሀል ሰባት ጉልቤ ቦዮች፣ አምስት አምባጓሮው ውስጥ የተሳተፉ ደምበኞች እና አንድ የሚጥል በሽታ ያለበት ሰው እያግበሰበሰ፡፡

እኩል ብድግ እያሉ ዛዚና ባልቴትዋ ሙዋክ በአናጢ እንጨት ፍቅፋቂና በቅብ ሽክላ ስብርባሪ ላይ የሚተራመሰውን ህዝብ ተጠጉት፡፡ አንዳንድ የተወረወረ ጠርሙስ በትክክል ተነጣጥሮ ከተወዳዳሪዎቹ ተሰባሪ የራስ ቅል ያላቸውን ደፋቸው፡፡ በዚህም የተነሳ ጋብሪዬል ማንሰራራት ቻለ፣ የባለጋራዎቹ ከበባ ከልክሎበት የነበረው የሰው መጋረጃ ተቀደደ፣ በዚያውም እንዳይሆን ሆኖ የተዘረረው የግሪዱና የቱራንዶ ቁመና ወለሉ ላይ ተከሰተ፡፡ የቃሬዛ አገልግሎት አቅራቢ የሆነው እንስት አካል ጋዝ ያለው ውሀ አነጣጥሮ ፊታቸው ላይ ሲረጭባቸው ቀልባቸው ተመለሰ፡፡ ከዚህ በኋላ የፍልሚያው ውጤት የሚያጠራጥር አልሆነም፡፡

ያን ያህልም ያልተጨነቁበት ወይም ምንም ስሜት ያልሰጣቸው ደምበኞች ሹልክ እያሉ ሲጠፉ፣ ችኮዎቹ ደምበኞችና ቦዮቹ ቁና ቁና እየተነፈሱ፣ በጋብሪዬል ክባድ ቡጢ፣ በግሪዱ አስደንጋጭ ክንድ፣ እና በቱራንዶ የከረረ ጫማ-ጥፊ ተዘረሩ።

ካለቀላቸው በኋላ ዛዚና ሙዋክ ከኦ-ኒክታሎፕ ምድር አጠፉዋቸው እስከ መንገዱ ድረስ እየጐተቱ። እዚያም ሰው አፍቃሪ የሆኑ የነብስ ርህራሄ ያለባቸው በጎ-አድራጊዎች ባንድ ቦታ ከመሩዋቸው።

ላቬርድዩር ብቻ ነበረች በዚህ አልቂት ውስጥ ያልተሳተፈች - ገና ሲጀመር የሾርባ ሰሀን ስባሪ ስለመታች፣ ጎጆዋ ጥግ ተኝታ እያቃሰተች "ድንቅ ምሽት! ድንቅ ምሽት!" እያለች ታጉረመርማለች ስኑ-ልቦናዋ በመቃወሱ የሙዚቃ ዲስክ ለውጣለች።

እሷ ባታግዛቸውም ድሉ በቶሎ ተጠናቀቀ

የመጨረሻውን ባላጋራ ከወደቀ በኋላ ጋብሪዬል በደስታ መዳፉን እያሻሸ "አሁን አንድ ቡና በወተት ብጠጣ በጣም አሪፍ ነው!" አለ

"ጥሩ ሀሳብ" አለ ቱራንዶ፣ ወደ ቡና ማፍያው አልፎ እየገባ። ሌሎቹ አራቱም ባንኮኒውን ተደገፉ

"ላቬርድዩርሳ?"

ቱራንዶ ፍለጋ ቢሄድ ወደፊቱ አሁንም ስታጉረመርም አገኛት። ከጎጆዋ አወጣትና ደባበሳት "የኔ አረንጓዴ ዶሮዬ" እያለ። ላቬርድዩር እንደገና ሰላም እየተሰማት መለስችለት፡-

"ታወራለህ፣ ታወራለህ፣ ይህን ብቻ ነው ማድረግ 'ምታውቀው"

"ይሄ እውነት ነው" አለ ጋብሪዬል "ቡና በወተቱስ?"

ቱራንዶ ተረጋግቶ ወደ ማሺኖቹ ቀረበ። ሊለኩሳቸው ሞከረ፣ ግን ያልለመደው አይነት ሞዴል ስለሆኑ፣ ገና ሲጀምር እጁን የፈላ ውሀ ፈጀው

"ውይ! ውይ! ውይ!" አለ በጣም ባጭሩ

"የተረገምክ ገልቱ!" አለ ግሪዱ

"ምስኪን ዘንካታ!" አሉ ባልቴትዋ ሙዋክ

"ሜርድ!" አለ ቱራንዶ

"የኔ ቡና በወተት" አለ ጋብሪዬል "በጣም ነጣ ያለ ይሁን"

"የኔ ደም" አለች ዛዚ "ላዩ ስልባቦት ይኑርበት"

"አ-ይ!" መለሰ ቱራንዶ፣ ፊቱን የእንፋሎት ጀት ቢያቃጥለው

"የቤቱን ሰው ስራልን ብንል ይሻላል" አለ ጋብሪዔል ረጋ ብሎ

"እውነትም!" አለ ግሪዱ "ልሂድና አንዱን ልፈልግ"

ከክምሩ መሀል አንዱ በጣም ያልተበላሸውን መረጠ - እየጐተተ አመጣው::

"የመጨረሻ ወንዳታ ሆንክ፣ ታቃለህ?" አለችው ዛዚ ጋብሪዔልን "እንዳንተ ያሉ ሶዶማውያን ብዙ አይኖሩም"

"ማድሚዜል ቡና በወተታቸው እንዴት ይሰራላቸው?" አለ ወደቀልቡ የተመለሰው ተስተናጋጅ

"ከልጣጭ ጋር" አለች ዛዚ

"ለምን ሶዶማዊ ነህ ማለቱን አትተይኝም?" ጠየቀ ጋብሪዔል በእርጋታ "አሁን ሞን-ደ-ፒዬቲ ውስጥ አይተሽኛል፣ እርግጠኛ መሆን አለብሽ"

"ሶዶማዊ ብትሆንም ባትሆንም" አለች ዛዚ "የመጨረሻ ጀግና ነው የሆንከው"

"ምን ላርግ ብለሽ ነው?" አለ ጋብሪዔል "አቀራረባቸውን አልወደድኩላቸውም"

"አይ ጌታዬ!" አለ የተጠቀሰው አስተናጋጅ "በጣም እናዝናለን አባኮትን"

"ስለሰደቡኝ ነውኮ" አለ ጋብሪዔል

"ኧረ ይተዉ ጌታዬ" አለ አስተናጋጅ "እዚህ ላይስ ተሳስተዋል"

"ሰድባችሁኛል'ንጂ" አለ ጋብሪዔል

"ግድ የለህም!" አለው ግሪዱ "ሁልጊዜ በሆነ ሰው እንደተሰደብን ነው"

"እንዲህ ነው ማሰብ ይሉሀል" አለ ቱራንዶ

"እና አሁን" ግሪዱ ጋብሪዔልን ጠየቀው "ምን ለማድረግ እያሰብክ ነው?"

"እንዴ! ይህን ቡና-በወተት ለመጠጣት ነዋ"

"ከዚያስ?"

"በቤቱ በኩል አልፌ ልጆቹን ወደ ሜትሮ ጣብያ መውሰድ"

"ውጪውን ተመልክተሀል?"

"አይ!"

"እንግድያውስ ሂድና እይ"

ጋብሪዬል ሄደ

"እውነትም" አለ ሲመለስ

ሁለት ፈጥኖ ደራሽ ብረት ለበስ ክፍለ ጦር፣ እና አንድ የተረሩ ቡድን ፒጋል አደባባዩን ከበውታል።

# እስራ ስምንት

"ለማርሰሲን ልደውልላት መሰለኝ" አለ ጋብሪዬል

ሌሎቹ ቡና በወተታቸውን በዝምታ መጠጣት ቀጠሉ

"ጉድ ፈላ" አለ አስተናጋጁ በግማሽ ድምፅ

"አልጠራንዎትም" መለሱ ባልቴትዋ ሙዋክ

"ወዳመጣሁህ ቦታ እንዳልመልስህ" አለ ግሪዱ

"ኧረ ይቅር!" አለ ቦዩ "እኔስ መቀለዴ ነበር"

ጋብሪዬል ተመለሰ

"ይገርማል" አላቸው "ስልኩ አይሰራልስም"

ቡና በወተቱን መጠጣት ፈለገ

"ሜርድ!" አለ በብስጭት "ቀዝቃዛ!ል"

ተፀይፎ ባንኮኒው ላይ አስቀመጠው

ግሪዱ ለማየት ሄደ

"እየቀረቡ ነው" አለ

ሌሎቹ ባንኮኒውን ለቀው ከበቡት፣ አስተናጋጁ ብቻ ካዝናው ስር ተደበቀ

"ደስ ያላቸው አይመስሉም" አለ ጋብሪዬል

"ምኑም ደስ አይል" አጉረመረመች ዛዚ

"ላቬርድዩር ችግር እንደማይደርስባት ተስፋ አረጋለሁ" አለ ቱራንዶ "እሷ ምንም ያጠፋችው የለም"

"እኔስ ብሆን ታድያ?" አሉ ባልቴትዋ ሙዋክ "ምን አድርጌያለሁ?"

"ሄደው ትሩስካዮንምትን ያገኙታል" አለ ግሪዱ፣ ትከሻውን ከፍ-ዝቅ እያደረገ

"እንዴ! እሱ ነው'ና!" ብለው ጮሁ

ባልቴትዋ ሙዋክ ከኦ-ኒክታሎፕ መግቢያ ፊት እንደ አጥር ሆነው የተከመሩትን ድንጉጦች እየተሻገሩ፣ በዝግታና በቀጥታ ይመጡ ወደነበሩት አጥቂዎች ለመፍጠን ተጣደፉ።

እፍኝ የማይሞላ የመትረየስ እሩምታ ይህን ሙከራቸውን ባጭሩ ቀጨው። ባልቴትዋ ሙዋክ አንጀታቸውን በሁለት እጃቸው እየጨበጡ ተዘረገፉ።

"አይ ጅልነት!" ብለው እያጉረመረሙ "ያውም ገቢ የነበረኝ ሰው እየሆንኩ!" አሉና ሩጫቸውን ፈፀሙ።

"ነገሩ ሁሉ ተበላሸ" አለ ቱራንዶ "ላቤርድዩርን እንዳይጉዱብኝ ብቻ"

ዛዚ አእምሮዋን ስታ/ለች

"በጥንቃቄ ማድረግ ነበረባቸው!" አለ ጋብሪዬል በንዴት እየጦፈ "ልጆች አሉ'ኮ"

"የጀብዱዋቸውን ዘገባ ልታቀርብላቸው ትችላለህ" አለ ግሪዱ "እኚውና መጡልህ"

እነዚህ በሚያስፈራ ሁኔታ የታጠቁ ሰዎች አሁን የሚገኙት ከበሩና ከመስተዋት መስኮቶቹ በወዲያ በኩል በቅርበት ነው - ያውም አብዛኞቹ መስተዋቶች ባለፈው ረብሻ ስለተፈረካከሱ፣ ለመከላከያነት ቢፈለጉ እንኳ የሉም። እነዚህ የሚያስፈሩ የታጠቁ ሰዎች በእግረኛ መንገዱ በሰልፍ ቆመዋል። አንድ ሰውዬ ቦርሳ በክንዱ እንዳንጠለጠለ ከቆሙበት ተነጠለና፣ የባልቴትዋ ሙዋክን ሬሳ ተሻግሮ መጠጥ ቤት ውስጥ ገባ።

"እረግ!" አሉ ጋብሪዬል፣ ቱራንዶ፣ ግሪዱ፣ እና ላቤርድዩር ባንድ ድምፅ

"አዎን" አለ (ባለአዲስ) ቦርሳው ሰውዬ "እኔ ሀሩን አልራሺድ ነኝ። እኔ እኔ ነኝ - ካሁን በፊት የምታውቁኝ፣ አንዳንዴም በመጥፎ ያወቃችሁኝ። የዚህ አለም፣ እና የአያሌ አጉራባች ክልሎች ንጉስ እንደ መሆኔ፣ በግዛቴ መዘዋወር ያስደስተኛል፣ የተለያዩ ገፅታዎችን እየተላበስኩ - ጥርጣሬና ስህተት በተለይ የግሌ ናቸውና። አስቀድሞ ፖሊስ፣ ከዚያ የሰከረ በሌሊት ተዘዋዋሪ ወምበዴ፣ መምረጥ ያልተቻለው የባልቴቶችም የወላጅ

አልባ ልጃገረዶችም አሳዳጅ - እነዚህ አፍታዊ ገፅታዎቼ መሳቅያም የመሆንን፣ ይሉኝታዊ እና ስሜታዊ እንባ የመርጨትን (ወደ ሚች ባልቴት ሙዋከ አቅጣጫ የጨዋ ሰው እንቅስቃሴ ያሳያል) እና ሌሎች አነስተኛ አደጋዎችን ያለፍራቻ ለመቻል ያስችሉኛል። ወረተኛ ህሊናችሁ ‹የለም ጠፍቷል› ገና ከማለቱ፣ ተመልሼ በድል-አድራጊነት እከሰታለሁ - ያውም ያለእንዳች ትህትና። ተመልከቱ!" (በጨዋነት ከቅድሙ ያነሰ፣ አሁን ግን አጠቃላዩን ሁኔታ የሚጨምር እንቅስቃሴ ያሳያል)

"ታወራለህ፣ ታወራለህ" አለች ሳቬርድዩር "ይህን..."

"እቻትና አንዲት፣ ለድስት ጥሩ 'ምትሆን" አለ ትሩስካዮን ይቅርታ! ሀሩን አልራሺድ

"በጭራሽ!" ጮኸ ቱራንዶ፣ ጉጆዋን እያቀፈ "አንገቴ ይቆረጥ!"

እንዲህ እያለ ወደ መሬት ተደፋ፣ እንዲሁም ጋብሪዬል፣ ዛዚ እና ግሪዱ፡-

ቀድመው የደረሱት የአጥቂው ጓድ አባላት ሁሉም ወደ ኦ-ኒክታሎፕ መጠጥ ቤት ከመንገዱ ወርደው በደረጃዎቹ ገቡ። አለቅየው ከጨለማው ውስጥ በለሆሳስ (ግን የሚያስፈራራ ትዕዛዝ በታመቀበት ድምፅ).

"ተከተሉኝ" አላቸው "እኮ ፈጠን!" የያዘውን የኤሌክትሪክ ፋኖስ ያወዛውዛል — ‹እንሰባሰብ› የማለት መልዕክት እያስተላለፈ፣ በዚያውም በፋኖሱ ባትሪ ሀይለኛነት እየተኩራራ!

ይህ ሲሆን ሳለ፣ በሚያስፈራ ሁኔታ የታጠቁ ወታደሮች ምድር ቤቱ ውስጥ ስሜት ፈንቅሏቸው በእግሮቻቸው መሀል ወደ መሬት የመትረየስ እሩምታ ሲተኩሱ፣ የትንሹ ቡድን አባላት ከላይ የተጠቀሰውን ትእዛዝና መብራቱን ተከትለው በጣም እየፈጠኑ፣ በሙስካዲንና በግረናዲን ወይን-ጠጅ በታጨቁት ቁም-ሳጥኖች መሀል እየተሽሎከለኩ ጠፉ - ጋብሪዬል ዛዚን አሁንም አእምሮዋን እንደሳተች ተሸከሟት፣ ቱራንዶ ሳቬርድዩርን አሁንም እንዳኰረፈች ይዟት፣ እና ግሪዱ ምንም አይሸከም

አንድ ደረጃ ወረዱ፣ ከዚያ የአንድ ትንሽ በር ደጃፍ ተሻገሩ፣ እና አንድ የፈሳሽ ቦይ ጋ ደረሱ። ትንሽ እልፍ ብለው የአንድ ሌላ ትንሽ በር ደጃፍ ተሻገሩና፣ አንድ ቫርኒሽ በተቀባ ሸክላ የተገነባ ኮሪዶር ሲደርሱ፣ አሁንም ጭለማና ባዶ ነው።

"እንግዲህ" አለ ብርሀን ለጋሹ በዝግታ "እንዳንያዝ የፈለግን እንደሆነ፣ እያንዳንዳችን በየፊናችን መሄድ ይኖርብናል። አንተ" አለው ቱራንዶን "ወፍህ ችግር ታመጣብሀለች"

"ጥቁር ቀለም እቀባታለሁ" አለ ጋብሪዬል "በጭራሽ ደስ አይልም"

"እግዜር ይይልህ፣ አንተ ጋብሪዬል!" አለ ግሪዱ "ሁልጊዜ የሚያስቅ ንግግር እንደወረወርክ"

"እኔ" አለ ብርሀን ለጋሹ "ልጅቱን እወስዳለሁ። ጋብሪዬል፣ አንተ እሰው አይን ትገባለህ። እኔ ትንሽ ቦርሳዋን ይዤላታለሁ። ግን የረሳሁዋቸው ነገሮች ሳይኖሩ አይቀሩም። ተጣድፌ ነበር"

"እንዴት እንደነበር ንገረኝ"

"አሁን ጊዜ የለም"

መብራቶች በሩ

"ጎሽ!" አለ ሌላው በቀስታ "ሜትሮው ሊሰራ ጀምሯል። ግሪዱ፣ አንተ ወደ ኤትዋል አቅጣጫ ተሳፈር። ቱራንዶ፣ አንተ ደሞ ወደ ባስቲይ አቅጣጫ"

"እና እንደተቻለን ራሳችንን እናወጣለን?" አለ ቱራንዶ

"እንዴት እንደምትሄድ ግራ ሳይገባህ" አለ ጋብሪዬል "በምናብህ መጠቀም ሊኖርብህ ነው"

"እኔ ራሴ የወፍ ጎጆዋ ውስጥ ብገባስ?" አለ ቱራንዶ "እና ላቬርድዩር ብትሸከመኝስ?"

"የሚያስኬድ ሀሳብ ነው"

"እኔ ቤቴ መሄዴ ነው" አለ ግሪዱ "ደግነቱ፣ የጫማ ስራ ከማህበረሰቡ መሰረታዊ ጉዳዮች አንዱ ነው። ደሞስ አንዱ ጫማ ሰፊ ከሌላው በምን ይለያል?"

"በምንም"

"በሉ ደህና ሁኑ፣ ጉበዝ!" አለ ግሪዱ

እና ወደ ኤትዋል ጣብያ አቅጣጫ መረሸ

"እሺ ደህና ሁኑ፣ ጉበዝ" አለች ላቬርድዩር

"ታወሪያለሽ፣ ታወሪያለሽ" አለ ቱራንዶ "ይህን ብቻ ነው ማድረግ 'ምታውቂው"

እና ወደ ባስቲይ ጣቢያ አቅጣጫ በረሩ።

# አስራ ዘጠኝ

ዣን ላሎሼር ድንገት ከእንቅልፏ ነቃች፡፡ የራስጌ ኮሞዲኖው ላይ የነበረው የእጅ ሰአትዋን አየች፣ አስራ ሁለት ሰአት አልፏል

"መንተት የለብኝም"

እንድያም ሆኖ ትንሽ ጊዜ አሳለፈች — ፍቅረኛዋን ለማስተዋል፣ ራቁቱን ሲያንኮራፋ፡፡ በጅምላ አየችው፣ ከዚያም በችርቻሮ፣ በተለይም አንድ ቀንና ሁለት ሴሲት ያን ያህል ቀልቧን ማርኮት የቆየውን ንብረትዋን በድካምና በእርጋታ እያስተዋለች

"ከዚህ ጋር ደሞ፣ ምንኛ ጅል ነው!"

በፍጥነት ለባበሰች፣ የተለያዩ እቃዎች ወደ ጉዞ-ቦርሳዋ ወረወረች፣ ፊቷን ደባበሰች

"ልጅቱን ለመውሰድ ከፈለግኩ መዘግየት የለብኝም፡፡ ጋብሪዬል እንደማውቀው ነው፡፡ በጊዜ ይደርሳሉ እርግጠኛ ነኝ፡፡ አንድ ነገር ካልደረሰባት በስተቀር"

የከንፈር ቀለሟን ወደ ልቧ አቀፈች

"አንድ ነገር ደርሶባት ባልሆነ ብቻ!"

አሁን ዝግጅቷን ጨረሰች፡፡ ፍቅረኛዋን እንደገና አየችው

"ሲፈልገኝ ከመጣ፡፡ አበክሮ ከጠየቀኝ፡፡ ምናልባት እምቢ አልልም፡፡ ግን ከንግዲህ እኔ አይደለሁም እሱን ፍለጋ 'ምሄደው"

ስትወጣ በሩን በቀስታ ዘጋች፡፡ የሆቴል ሰራተኛው ታክሲ ጠራላትና በተኩል ጣቢያው ደረሰች፡፡ ሁለት መሳፈርያ ገዝታ ተመልሳ ወረደች፡፡ ትንሽ ቆይታ ዛዚ አንድ ሰውዬ ሻንጣዋን ተሸክሞላት መጣች

"ታድያስ፣ ማርሴል" አለች ዣን ላሎሼር

"እንደሚያዩት ነው"

"እንዴ! በቁሚ ተኝታ የለም'ንዴ?"

"ስንጨፍር ነበር። ይቅርታ ያርጉላት። ለእኔም ይቅርታ ያርጉልኝ፣ መሄድ አለብኝ"

"ይገባኛል። ጋብሪዬልሳ?"

"የሱ ነገር የሚያሳስብ አይደለም። ለማንኛውም እኛ እየተሰወርን ነው። ቻው ሚጡ" አለ ሰውየው።

"ቻው መስየ" አለች ዛዚ፣ እዚያ የሌለች ያህል

ዣን ላሎሼር ወደ ፉርጎው ይዛት ገባች

"ታድያስ፣ ጥሩ ጊዜ አሳለፍሽ?"

"ምንም አይደል"

"ሜትሮውን አየሽው?"

"አላየሁትም"

"ታድያ ምን አረግሽ?"

"እድሜ ጨመርኩ"

**Raymond Queneau**

# ZAZIE

ለኔ ዛዚ ናሙና የስነ-ጽሁፍ ፈጠራ ገጸ-ባህሪ ናት። መፃሐፉን ሳነብ ገና ምዕራፍ አንድ ውስጥ እያለሁ ከሷ ጋር ፍቅር ያዘኝ (የገዛ ራሴ ተንኮለኛ ልጅ መሰለችኝ - አቤት ተንኮሉቿ ሲከይፉኝ!)

ዛዚ እንደ ፈጣሪዋ ረይሞን ከኖ በተለያየ አጋጣሚና ሁኔታ የተለያየ ሰው ትሆናለች። "Zazie dans le me'tro" ውስጥ ያሉት ገጸ-ባህሪያት ሁሉ አዋቂዎች ናቸው። እሷ ብቻ ናት ልጅ። እና ይህን የእኛን የአዋቂዎች አለም፣ አራዳ - ነቄ - ቆቅ ዛዚ እያየችው ስትኖርበት፣ ስትጫወትበት፣ ስትማርበት እንዴት ነው?!

እሷን ሆኜ ባየሁትና በኖርኩት ያለኛል፡- የራሴን ኑሮ ጉድለትና ጭንቀት እሷን ሆኜ ተጋፍጬው፣ በድል አድራጊነት አልፈዋለሁ። አልፌው ወድያው እረሳዋለሁ። ወደሚቀጥለው "የቂጤን አበሳ ይስጠው" ፍጥጫ ወይም መመዛዘን ወይም....

እንዲህ የሚያስጋልብ የሚያንሳፍፍ፣ የሚያበር ልቦለድ የጻፈልን ምርጥ ባለቅኔ እና እንቁ የልጆች ነብስ አዋቂ ለረይሞን ከኖ የሳቅ ብርሀን ሆነን መንፈሳዊ ሻማ እንለኩስለታለን።

እኔ ሳነባትም ስተረጉማትም የሳቅኩትን ያህል፣ እናንተም ስታነቡዋት እንድትስቁ እመኝላችኋለሁ።

ስብሐት ለአብ

ብር - 23.00

[illegible]